አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ

ለፎክሎር የፒኤች ዲ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

አንዱዓለም አባተ

አዲስ አበባ

2014 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ

ለፎክሎር የፒኤች ዲ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

አንዱዓለም አባተ GSR /0170/06

አማካሪዎች

ዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

አየለ ፍቅሬ (ዶ/ር)

አዲስ አበባ

2014 ዓ.ም.

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ


በ

አንዱ ዓለም አባተ ሞገስ


2014 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| ------------------------------------------ | ------------------------------------------ |
| ------------------------------------------ | ------------------------------------------ |
| አማካሪዎች | ፊርማ |
| ------------------------------------------ | ------------------------------------------ |
| ------------------------------------------ | ------------------------------------------ |
| ፈታኞች | ፊርማ |

# ምስጋና

ይህ ጥናት ከውጥኑ አንስቶ እስከ መጨረሻው ድረስ ልዩ ልዩ አካላት የበኩላቸውን ድርሻ ያበረከቱበት ነው፡፡ አንዳንዶቻችሁ በሀሳብ፣ ጥቂቶቻችሁ በምክር ስላገዛችሁኝ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

በተለይም አማካሪዎቼ ዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ፕሮፌሰር) እና ዶ/ር አየለ ፍቅሬ ሥራው የተቃና እንዲሆን በሥራው ውስጥ ለነበራቸው ትልቅ ድርሻ፣ ድካምም በተሰማኝ ጊዜ እንድበረታ ላደረጉት ጥረት ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ሰፊ ጥናት በራስ ጥረት እና በግል ገንዘብ መማር እጅግ ከባድ እንደሆነ ይታወቃል፤ በተለይም ሀገራችን ካሏት ብሔር ብሔረሰቦች መርጦ ብዙም ወዳልታወቁ እና ማንነታቸው በሰፊው ጎልቶ ወዳልወጣ ሕዝቦች ተሄዶ ጥናት ሲካሄድ ሁኔታዎች እጅግ ፈታኝ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ በዚህ ረጅምና ድካምን በሚጠይቅ ሥራ ውስጥ የትምህርት ክፍሉ አመራሮችና መምህራን ያደረጉት የማበረታት እና የአይዞህ ባይነት ምክር ሥራውን በማሳካት ረገድ ትልቅ አቅም የፈጠረ ነውና ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ በተለይ ዶ/ር ግርማ ገብሬ እና ደረጀ ገብሬ (ረ/ፕሮፌሰር) በብዙ አመሰግናችኋለሁ፡፡ በየጊዜው ጥናቱ የደረሰበትን በመጠየቅ በማንበብና ሀሳብ በመስጠት ዶ/ር ነጻነት ጆቴ፣ እና ዶ/ር እንዳለጌታ ከበደ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

ለጥናቱ መሳካት ሰፊነ ዋነኛ ድርሻ የነበራችሁ የመኤኒት ብሔረሰብ የጎሳ መሪዎች (ኬኒ ቀኛዝማች ጋሊ፣ አቶ ቻሪ)፣ የብሔረሰቡ የሃይማኖት መሪዎች (ኘራይ አወቀ ፎሮሾዋ)፣ የዝናብ ንግሥቷ ወ/ሮ ሌማው ጃና፣ የዝንጀሮ ንጉሡ አቶ ሴላ እንዲሁም ኮሞሮቶችና የሀገር ሽማግሌዎች ምስጋና ይድረሳችሁ፡፡ መረጃ የሚሰጡ አካላትን በማገናኘት እና በመኤኒትኛ ቋንቋ የተደረጉ ቃለ መጠይቆችን ወደ አማርኛ ቋንቋ በመተርጎም ያገዛችሁኝ፤ አቶ ብርሃኑ ወርቁ፣ አቶ በድሉ ካሳ እና አቶ ቦኒ ሀየች ብዙ ደክማችኋልና ምስጋናዬ ትልቅ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መረጃ በመስጠትና በልዩ ልዩ መንገድ ለተባበራችሁና በዚህ ጥናት ውስጥ ለተሳተፋችሁ በሙሉ ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡


# አጠቃሎ

የመኤኒት ብሔረሰብ በደቡብ ክልል፣ በቤንች ማጂ ዞን ውስጥ የሚገኝ ብሔረሰብ ነው፡፡ የብሔረሰቡ አባላት በዋናነት በመኤኒት ጎልዲያ እና በመኤኒት ሻሻ ወረዳዎች ሲገኙ፣ በጥቂቱም ቢሆን በጉራ ፈርዳ እና በአንዳንድ አጎራባች ወረዳዎች ውስጥ ይኖራሉ፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብን ታሪክ፣ ባሕልና እሴቶችን ለመረዳት ይህ ጥናት የብሔረሰቡ ሚትና ፋይዳ ያተኩራል፡፡ ሚትን አስመልክቶ በብሔረሰቡ ላይ የተጠኑ ጥቶች አለመኖራቸው ይሄንን ጥናት ለማድረግ ዐቢይ ምክንያት ሲሆን፣ ጥናቱን የተሳካ እንዲሆንም መረጃዎች በቀዳማይ እና በካልአይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች በተረካዊ እና በመዋቅራዊ ንድፈ ሀሳቦች ተተንትነዋል፡፡

ይህ ጥናት ዋና ዋና የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶችን ለይቷል፡፡ እነሱም የአፈጣጠር ሚት፣ የመንፈሳዊ ሚት፣ የመስተጋድላውያን ሚትና የዳግም ውልደት ሚት ናቸው፡፡ በጥናቱ በየሚቶቹ ውስጥ የሚገኙ ትዕምርቶች በትንተናው ወቅት ተፈክረዋል፡፡ የብሔረሰቡ አባላት ለሚቶቹ ያላቸው አመለካከትም ተብራርቷል፡፡ እነዚህ ሚቶችም ለብሔረሰቡ የሚሰጧቸው ልዩ ልዩ ፋይዳዎችም እንዲሁ በጥናቱ ግኝት ውስጥ ቀርበዋል፡፡ የብሔረሰቡ አባላት ለሚያነሷቸው ዘለዓለማዊ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት የብሔረሰቡ ሚቶች የብሔረሰቡን ልዩ ልዩ ባሕሎች፣ ታሪኮች፣ ሃይማኖትን እና ዕሴቶች የመግለጥ፣ የማስተማር፣ የመግታትና የመቆጣጠር፣ ማኅበረሰባዊ መዋቅርን የመገንባት፣ የሥልጣን ክፍፍል እንዲኖር የማድረግ፣ የተለያዩ የኅብተረሰብ ክፍሎችን አንድ የማድረግ ፋይዳዎች እንዳላቸው በጥናቱ ተመልክቷል፡፡

ይህ በመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ፋይዳ ላይ ያተኮረው ጥናት ብሔረሰቡ ፀንቶ የቆመባቸውን እና የቡድን ሕላዌውን ያስጠበቀባቸው መሠረቶች አሳይቷል፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶች እንዲጠበቁ፣ እንዲዳብሩ በልማትና ዕድገት ላይ የላቀ ሚና እንዲኖራቸው የሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ እንዲያደርጉ የይሁንታ ሀሳብ በማቅረብ ጥናቱ ተጠናቋል፡፡

**የቤንች ማጂ ዞን ካርታ**




ምንጭ፡- የመኤኒት ጎልድያ ወረዳ ባሕል ቱሪዝምና የመንግሥት ኮምኒኬሽን ጽ/ቤት፡፡

# ማውጫ

**ምስጋና** ........ I

**አጠቃሎ** ........ II

**ማውጫ** ........ IV

**የቁልፍ ቃላት ብያኔ** ........ VII

**ምዕራፍ አንድ** ........ 1

**1. መግቢያ** ........ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 2
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ........ 3
1.3 ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ........ 4
1.4 የጥናቱ ዓላማ ........ 4
*1.4.1 የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ* ........ *4*
*1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች* ........ *4*
1.5 የጥናቱ ፋይዳ ........ 5
1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 5
1.7 የአጠናን ዘዴ ........ 6
*1.7.1 የጥናቱ ዓይነት* ........ *6*
*1.7.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ምንጮች* ........ *6*
*1.7.3 የናሙና አመራረጥ* ........ *9*
*1.7.4 መረጃ መሰብሰቢያ የመስክ መቼቶች* ........ *10*
*1.7.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች* ........ *10*
1.8 የጥናቱ አደረጃጀት ........ 10
1.9 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች ........ 11
1.10 ጥናቱ የተከተላቸው የሙያ ሥነ ምግባራት ........ 13

**ምዕራፍ ሁለት** ........ 14

**2.ክለሳ ድርሳናት** ........ 14

2.1 ጽንሰ ሐሳባዊ ዳራ ........ 14
*2.1.1 ሚት* ........ *14*
*2.1.2 የሚት ዓይነቶች* ........ *18*
*2.1.3 የሚት ባህሪያት* ........ *31*
*2.1.4 የሚት ሚና* ........ *32*
2.2 ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ........ 35

*2.2.1 ተረካዊ ንድፈ ሐሳብ፣* ... *35*
*2.2.2 መዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሐሳብ፣* ... *36*
2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ... 38
**ምዕራፍ ሦስት ... 44**
**3. የመኤኒት ብሔረሰብ ማኅበረ ባሕላዊ ዳራ ... 44**
3.1 መልክአ ምድራዊ ገጽታ ... 44
*3.1.1 መኤኒት ጎልዲያ* ... *45*
*3.1.2 መኤኒት ሻሻ* ... *45*
3.2 የመኤኒት ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥና አሰፋፈር ... 45
3.3 ቋንቋ ... 48
3.4 እምነት ... 49
3.5 የኢኮኖሚ መሠረት ... 49
3.6 ማኅበረሰባዊ ሕይወት ... 50
*3.6.1 ጋብቻ* ... *51*
*3.6.2 ለቅሶ* ... *52*
*3.6.3 ጥርስ ነቀላ* ... *53*
*3.6.4 ስም አወጣጥ* ... *54*
*3.6.5 አለባበስ* ... *55*
*3.6.6 አመጋገብ* ... *57*
*3.6.7 ጥበበ ዕድ* ... *58*
*3.6.8 የሚጥል በሽታ* ... *59*
3.7 ማኅበረሰባዊ ተቋም ... 62
3.8 ባሕላዊ የፍትሕ ሥርዓት ... 63
*3.8.1 ኮሞሮት* ... *63*
*3.8.2 ኙራይ* ... *64*
*3.8.3 የሀገር ሽማግሌዎች* ... *65*
**ምዕራፍ አራት ... 66**
**4. የመኤኒት ብሔረሰብ የአፈጣጠር ሚት ... 66**
**ምዕራፍ አምስት ... 87**
**5. የመኤኒት ብሔረሰብ መንፈሳዊ ሚት ... 87**
**ምዕራፍ ስድስት ... 114**
**6. የመኤኒት ብሔረሰብ የባሕል መስተጋድላን ሚት ... 114**
6.1 የወባ ንጉሥ ... 114
6.2 የዝንጀሮ ንጉሥ ... 121
6.3 የባሕል መስተጋድል አቶ ጥጋቡ ... 129
6.4 የባሕል መስተጋድልት ወ/ሮ ኮራይ ... 136
6.5 የባሕል መስተጋድልት ሞናይ ... 141
**ምዕራፍ ሰባት ... 148**
**7. የመኤኒት ብሔረሰብ የዳግም ውልደት ሚት ... 148**

ምዕራፍ ስምንት ........ 165

8. የመኤኒት ሚቶች ማኅበረሰባዊ ፋይዳ ........ 165

8.1 የመግለጥ ፋይዳ ........ 165
8.2 የማጠናከር እና የመትከል ፋይዳ ........ 170
8.3 የማምለጥ ፋይዳ ........ 183
8.4 የማስተማር ሚና ........ 187
8.5 የመግታትና የመቆጣጠር ሚና ........ 189

ምዕራፍ ዘጠኝ ........ 191

ማጠቃለያ ........ 191

ማረጋገጫ ........ 196

የተጠቀሱ ምንጮች ........ 197

አባሪዎች ........ 203

# የቁልፍ ቃላት ብያኔ

**ኮሞሮት** - በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ የሚገኙ የጎሳ መሪዎች መጠሪያ ሲሆኑ፣ አንዳንድ ጊዜ የሃይማኖት መሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**ኀራይ** - የባሕል ሃይማኖት መሪ

**መስተጋድላውያን** - በሃይማኖት ወይም በባሕል ጉዳይ ይዘው በተነሱት አንድ ዓላማ ምክንያት ተጋድሎ የሚያደርጉ፣

**አሻ** - ሰባት ከብቶች እና አንዲትን ልጃገረድ በካሳነት በመስጠት የሚፈጸም ሀገረሰባዊ የግድያ የዕርቅ ሥርዓት

**የደ/ብ/ብ/ህ/ ፕሮፋይል** - የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፕሮፋይል

**ቱማ/የሪ** - የመኤኒቶች አምላክና ፈጣሪ

**ጋመን** - በቤተሰብ ስምምነት የሚፈጸም ጋብቻ

**ቀረን ጎራቤት** - የጠለፋ ጋብቻ

**ቀነሰኤ** - የውርስ ጋብቻ

**ቴአ** - የመጀመሪያ ወንድ ልጅ

**ዶቢት** - እንጨት በማለስለስ የሚሠራ ባሕላዊ ልብስ

**ውሽኪት** - ከልጥ የሚሠራ ባሕላዊ ልብስ

**ካቲላ** - ከጤፍ የሚሠራ ባሕላዊ ምግብ

ኮልፌ/ ኳይዛ - የጎመን ዓይነት፣ በጥሬው የሚበላ

-

**ዛምጣ** - እንጉዳይ ዓይነት በብሔረሰቡ የሚዘወተር ምግብ

**ቡንጥላ/ጨሞ** - ቡና

**ጳሩ** - የበቆሎ እና የማሽላ ገንፎ

**ቃምጹት** - ቡዳ

**ጫልኩት** - የሀገር ሽማግሌዎች ግድያን ለማስቆም የሚይዙት ዘንግ

**ሞሲት** - እሳት በሰበቃ ማቀጣጠል

**ቢደበራን** - በሰው እጅ ተገድሎ የሞተ ሰው የመቀበሪያ ከብት /የገዳይ ቤተሰቦች ለሟች ቤተሰቦች የሚሰጡት በሬ/

**ቢዴጀኑን** - የጦር መመለሻ ከብት /የገዳይ ቤተሰቦች ለሟች ቤተሰቦች የሚሰጡት በሬ/

**ሞኡ** - ከሞት በኋላ ሕይወት እንደሚቀጥል የሚታመንበትና መኤኒቶች ከሞቱ በኋላ እንደሚኖሩበት  የሚታመንበት በጉራ ፈርዳ ወረዳ የሚገኝ በጥቅጥቅ ደብ የተሸፈነ ተራራ

**ከሜሲቬ** - ከጎሽ ቆዳ የተሠራ እንደ ጠፍር ያለ ጫማ

**ሚቲዮሎጂ** - ሚትን የሚያጠና የጥናት መስክ

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

እያንዳንዱ ማኅበረሰብ የራሱ የሆኑ ሀገረሰባዊ ልማዶች፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ ሥነ ቃሎች እና ቁሳዊ ባሕሎች አሉት፡፡ እነዚህን ዋና ዋና የማንነት መሠረቶች በፎክሎር ሥር የታቀፉ እና የሚመረመሩም ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብም የራሱ ፎክሎሮች፣ የራሱ ስነ ቃሎች እና የራሱ ሚቶችም አሉት፡፡

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሀገር እንደመሆኗ መጠን፤ እንደ ብሔር፣ ብሔረሰቦቿ እና ሕዝቦቿ ብዛትና ዓይነትም የተለያዩ ሀገረሰባዊ የአኗኗር ሥርዓታት፣ ደንቦች፣ እምነቶች፣ እሴቶችና ሚቶች መኖራቸው እርግጥ ነው፡፡ ነገር ግን ሚትንና ፋይዳውን በጥልቀትና በስፋት የመረመረ ጥናት አላጋጠመኝም፡፡ እንዲሁ የመኤኒት ብሔረሰብ የተለያዩ ሚቶች ቢኖሩትም በሚቶቹ እና በፋይዳቸው ላይ የተጠና ጥናትም አላገኘሁም፡፡ ስለዚህ ይህ በመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ላይ የቀረበው ጥናት ዐቢይ ትኩረት የመኤኒት ብሔረሰብ የሚት ዓይነቶችን መለየትና ማኅበረሰባዊ ፋይዳቸውን ማሳየት ነው፡፡

መረጃዎች በቀዳማይ እና ባካልአይ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ ከቤተ ማጻሕፍት ፍተሻ በተጨማሪ የተለያዩ ድረገጾችን ለመመርመር የተሞከረ ሲሆን መረጃው በቃለ መጠይቅ በምልከታ እና በቡድን ውይይት ተሰብስቧል፡፡

ይህ ጥናት የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶች ምን ምን ናቸው፣ ማኅበራዊ ፋይዳቸውስ ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ሲሆን፡ የጥናቱ በዘጠኝ ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ስለ ሚት በርካታ ብያኔዎች ተሰጥተዋል፡፡ የተለያዩ የእውቀት መስኮችም እንደየዘውጋቸው እሳቤ ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ የአንትሮፖሎጂስቶች፣ ፎክሎሪስቶች፣ የስነ ልቡና አጥኝዎች እና የስነጽሑፍ ተመራማሪዎች ብያኔ እንደሰጡ እና ሚት የሚለው ቃል ከግሪክ ቋንቋ ለመመዘዙ Philip ሲገልጹ word myth derives from the Greek *mythos*, signifying "word" or "story." A myth has different meanings for the believer, the anthropologist, the folklorist, the psychologist, the literary critic. ብለዋል (Philip, 2007, 6)[1]፡፡

እንደ Leeming ብያኔ ደግሞ ሚት ቃላዊ በሆነ ትረካ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተሸጋገረ የሚጓዝ፣ በአማኙ ዘንድ ቅዱስ እንደሆነ የሚታመን እና መሠረቱም ከአማልዕክት እንደሚነሳ ይገልጻል(Leeming 2010)፡፡ ሚቶች የሰው ልጅን ለሚያባትሉት ሰርካዊ የሕይወት ጥያቄዎች፣ የሕይወት መነሻ እና መድረሻ፣ የዓለም አፈጣጠር እና ፍጻሜ መልስ ለማግኘት የተጠቀመበት መንገድ ነው፡፡ Brient "አብዛኞቹ ሚቶች ስለ አማልዕክት እንዲሁም ከተራው ሰው የተለየ ትልቅ ጉልበት እና ኃይል ስላላቸው ሰዎች ይተርካሉ" (Brient 2009) ሲሉ፣ Cambel "ሚቶች የኅብረተሰቡን ችግሮች ለመፍታት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው ግለሰቦች ወይም መንፈሳዊ አካላት በሕይወት ዘመናቸው የፈጸሟቸውን መስዋዕት፣ ገድላትና ተአምራት የሚገልጹ ናቸው" በማለት ይገልጻሉ (Cambel 2004)፡፡

ማንኛውም ማኅበረሰብ የራሱ የሆኑ ሚቶች እንዳሉት ሁሉ የመኤኒት ብሔረሰብም ከትውልድ ወደ ትውልድ ያሸጋገራቸው የራሱ ሚቶች አሉት፡፡ ብሔረሰቡ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል፣ በቤንች ማጂ ዞን ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ የብሔረሰቡ አባላት በዋናነት በሁለት ወረዳዎች ውስጥ፣ ማለትም በመኤኒት ጎልዲያ እና በመኤኒት ሻሻ ወረዳ ውስጥ፣ በጥቂቱም በጉራ ፈርዳ ወረዳ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ብሔረሰቡ የራሱ የሆኑ ሚቶች አሉት፡፡ ይህ

---

1 *በዚህ ጥናት ውስጥ የተጠቀሱ የዘመን አቆጣጠሮች፣ የላቲን ፊደላትን ተከትለው የመጡትን በአውሮፓውያኑን ዘመን አቆጣጠር የተጠቀምኩ ሲሆን፣ የግዕዝ ፊደላትን ተከትለው የመጡትን ደግሞ የኢትዮጵያውያንን የዘመን አቆጣጠር መጠቀሜን መግለጽ እወዳለሁ፡፡*

ጥናትም የሚያተኩረው በመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ ላይ ነው፡፡ አንድ ማኅበረሰብ ጸንቶ ከቆመባቸው እሴቶቹ ውስጥ ሚት አንዱ ቢሆንም በተለይ በኢትዮጵያ በሚት ላይ የተጠና ጥናት ብዙ አይገኝም፡፡ ይሄም በዘርፉ ከፍተኛ የሆነ ክፍተት እንዳለ ያመላክታል፡፡ በመሆኑም የመኤኒት ብሔረሰብ ሚትን በማጥናት ላይ የሚታየውን ክፍተት ለመሙላት አንድ ጅምር እንደሚሆን በማመን ይህ ጥናት ተጠንቷል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ይሄንን ጥናት እንዳከናውን ገፊ የሆኑ ሦስት ምክንያቶች አሉ፡፡ አንደኛው ምክንያት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ የሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ውስጥ ሚቲዎሎጂን አስመልክተው የተሠሩ ጥናቶች ብዙም አይታዩም፡፡ እንዲያውም ከወጥነት አንጻር ከቃኘነው የሉም በሚያስብል ደረጃ የሚታይ ነው፡፡ ይሄንን ዘርፍ ከሌሎች የፎክሎር ዘሮች አንጻርም ለማነጻጸር ቢሞከር ንጽጽሩ ፈጽሞ የማይመጣጠን ሆኖ ይገኛል፡፡ በትምህርት ክፍሉ በስነ ቃል ዘሮች ውስጥ እንኳን ከሥነ ቃል፣ ከሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት፣ ከቁሳዊ ባህል እና መሰል ዘሮች አንጻር ብናወዳድረው ሚቶሎጂ ያልተደፈረ ርዕስ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይሄም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ሀገር ሲታይ በዘርፉ የሚካሄደው ጥናት እጅግ ክፍተት ያለበት መስክ ሆኖ ይታያል፡፡ በመሆኑም ይህ ሰፊ አካዳሚያዊ ክፍተት ይሄንን ጥናት ለማጥናት እንደ ሁነኛ ምክንያት ነው፡፡

ሁለተኛው ምክንያት፤ የኤም.ኤ.ዲግሪ የመመረቂያ ጥናቴን በብሔረሰቡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ ሠርቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ የማስትሬት ዲግሪ ጥናት በዐውዱ ጠባብ በመሆኑና እኔም ከዚያ ወዲህም ስለ ብሔረሰቡ በንባብ ያገኘሁት እውቀት ስላለ፣ ስለብሔረሰቡ ሰፊ እና የተስፋፋ ጥናት ለማድግ ያደረብኝ ውስጣዊ ግፊት አንድ ምክንያቴ ሆኗል፡፡

ሦስተኛው ምክንያት፤ በሥራ አጋጣሚ የብሔረሰቡ አባላት ባሉበት የጉራ ፈርዳ አካባቢ ስሄድ፣ የብሔረሰቡ አባላት ከሞት በኋላ በዳግም ሕይወት ይኖሩበታል ተብሎ የሚታመንበትን ተራራ ማየቴ ነው፡፡ ከሚት ዓይነቶች አንዱ

ደግሞ ይሄው ከሞት በኋላ ያለው የዳግም ሕይወት አስተሳሰብ በመሆኑ፣ ስለሚትና ስለቦታው የበለጠ ጥናት እንዳደርግ እንደ ሦስተኛ መነሻ ምክንያት ሆኗል፡፡

## 1.3 ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡ በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ ያሉ የሚት ዓይነቶችና ትንታኔያቸው ምን ምን ገጽታዎች አሏቸው? በመኤኒት ብሔረሰብ ዋና ዋና የሚቶች ውስጥ ያሉ ትዕምርቶች ፍካሬ ምን ዓይነት ነው? የመኤኒት ብሔረሰብ አባላት ለሚቶቹ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል? እና የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶች ለማኅበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት የራሱ የሆነ ዐቢይ ዓላማ ያለው ሲሆን ከዐቢይ ዓላማው ሥር የሚመጡ ንዑሳን ዓላማዎችም ይኖሩታል፡፡ እነሱም ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

### 1.4.1 የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ የመኤኒት ብሔረሰብን የሚት ዓይነቶችን ለይቶ መግለጽ እና የሚቶቹን ፋይዳ መርምሮ ውጤቱን ማሳየት ነው፡፡

### 1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች አሉት፡፡

- በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና የሚት ዓይነቶች ለይቶ መተንተን፣
- በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና የሚት ዓይነቶች ትዕምርቶች መፈከር፣
- የመኤኒት ብሔረሰብ አባላት ለሚቶቹ ያላቸውን አመለካከት ማሳየት፣
- የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶችን ማኅበረሰባዊ ፋይዳ ማሳየት

## 1.5 የጥናቱ ፋይዳ

ይህ ጥናት ከዚህ በታች ያሉት ፋይዳዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- የሀገራችን የተለያዩ ሕዝቦች ሚት በበቂ ሁኔታ አለመጠናቱ በተለይም ከፎክሎር አንጻር እንዳልተጠና በተለያዩ ቤተመጻህፍት እና ድረ ገጾች ባደረኩት ፍለጋ ለማወቅ ችያለሁ፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት በዘርፉ ያለውን የጥናት ክፍተት የመሙላት ፋይዳ አለው፡፡
- የብሔረሰቡን ሚት ማወቅ ባሕሉን ማወቅ ነው፡፡ ባሕሉን ማወቅ ደግሞ የልማትን፣ የትምህርትን፣ የጤናን ወዘተ...፣ አስተሳሰቦች ለማስረጽ ስለሚጠቅም ብሔረሰቡን በተመለከተ ለሚወጡና ለሚነደፉ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ግብአት በመሆን ፋይዳ ይኖረዋል፡፡
- የጥናት ርዕስ ከሚገኝባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ የቀደሙ ጥናቶች መኖራቸው ነው፡፡ ይሄንን ጥናት ለሚመረምሩ አጥኝዎች የጥናት ርዕስ የማስገኘት ፋይዳም ይኖረዋል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቦታ አንጻር የተገደበ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው የብሔረሰቡ አባላት ከሚኖርባቸው ሦስት ወረዳዎች ውስጥ በነባሩ የአኗኗር ዘዬ ከሚኖሩ አርባ አምስት ቀበሌዎች ውስጥ በሃያ አምስት ቀበሌዎች ላይ ሲሆን እነሱም ባቹማ፣ ጀሙ፣ ጉራፈርዳ፣ ኮላይ፣ ያርጣ፣ ጨበራ፣ ጎማ፣ ዱማ፣ ቢያጌሊች፣ ግርሻ ጤና፣ ዲልቂባ ጣያ፣ ሽርሽር፣ ካንቲ፣ ኤራ፣ ሻሪያ፣ ኩዱም፣ ባሮ፣ ኤራ፣ ወጅናሌሙ፣ ሀዱባ፣ ዳርጃ፣ ቂራ፣ ቡክቱ፣ ጢይጉይ፣ ጥቅምትሸት ናቸው፡፡

ይህ ጥናት በየመኤኒት ብሔረሰብ አራት ሚቶች ላይ ብቻ ያተኩራል ነው፡፡ እነሱም የአፈጣጠር ሚት፣ የእምነት ሚት፣ የመስተጋድላውያን ሚት እና የዳግም ውልደት ሚት ላይ የተገደበ ነው፡፡

## 1.7 የአጠናን ዘዴ

በዚህ ርዕስ ስር የጥናቱ ዓይነት፣ የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ምንጮች፣ የመረጃ ሰጭዎች የናሙና አመራረጥ፣ መረጃ መሰብሰቢያ የመስክ መቼቶች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች እና የጥናቱ መተንተኛ ዘዴ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 1.7.1 የጥናቱ ዓይነት

የፎክሎር ምንነት ብያኔ የተለያየ እንደሆነ ሁሉ ፎክሎርንም ለማጥናት አንድ ወጥ የሆነ የማጥኛ ዘዴ እንደሌለ Goldstein ይገልጻሉ (Goldstein 1964፣ 2)፡፡ በመሆኑም ፎክሎርን የተለያዩ እና ተስማሚ የሆኑ ዘዴዎችን በመጠቀም ማጥናት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንጻር ይህ ጥናት ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ይከተላል፡፡ ይህም ዘዴ ቀመራዊ ወይም በቁጥር እና በአሀዝ ተገላጭ ያልሆኑ ምርምሮች የሚካሄዱበት ስለሆነ ነው፡፡

### 1.7.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ምንጮች

ይህንን ጥናት የተሳካ ለማድረግ መረጃዎች በተለያዩ መንገዶች ተሰብስበዋል፡፡ ጥናቱ  የመኤኒት ብሔረሰብ የሚት ዓይነቶች እና ማኅበረሰባዊ ፋይዳቸው ላይ በመሆኑ ተገቢው መረጃ በቀዳማይ የመረጃ ምንጮች እና በካልዓይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስቧል፡፡

#### 1.7.2.1 ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች

ይህ የመረጃ ምንጭ አጥኝው መረጃውን ከዋና የክዋኔ ዐውዱ ላይ የሚያገኝበት መንገድ ነው፡፡ በመሆኑም የመስክ አጥኚ በተለያዩ ቴክኒኮች እና መንገዶች መረጃዎችን ይሰበስባል፡፡ በዚህ  ረገድ፣ የዚህ ጥናት መረጃዎችም በሁለት መንገዶች ማለትም በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት ተሰብስበዋል፡፡

ቃለ መጠይቆቹና የቡድን ውይይቶቹ በአማርኛ እና በመኤኒትኛ ቋንቋዎች የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ በመኤኒትኛ የተደረጉ ቃለ መጠይቆችንና ውይይቶችን አቶ ብርሃኑ ወርቁ፣ አቶ በድሉ ካሳ እና አቶ ቦኒ ሀየች ቃል በቃል

በመተርጎም መረጃዎቹ በተገቢው መልኩ እንዲቀመጡ አስችለዋል፡፡ እነዚህ ሦስት ሰዎች የማስትሬት ዲግሪ ምርምሬን በብሔረሰቡ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ ሥሠራ ጀምሮ የማውቃቸው ናቸው፡፡ አቶ ብርሃኑ እና አቶ በድሉ ያኔም በማስተርጎም ሥራ ጥናቴ ውስጥ ተሳታፊ ነበሩ፡፡ ሦስቱም ሰዎች ሁለቱንም ቋንቋ በሚገባ የሚናገሩ እና በማስተርጎም ሥራም ልምዱ ያላቸው እና የብሔረሰቡን ባህል፣ ቋንቋ፣ ወግና ልማድ በሚገባ የሚያውቁ ናቸው፡፡

አቶ ብርሃኑ እና አቶ በድሉ ካሳ በመኤኒት ጎዲያ እና በመኤት ሻሻ ወረዳዎች የተደረጉ ቃለ መጠይቆች እና ውይይቶችን በኮላይ እና በያርጣ ቀበሌዎች የተደረጉ የቡድን ውይይቶች ላይ በመኤኒትኛ ቋንቋ የሚደረጉ ንግግሮችን በመተጋገዝ በመተርጎምና የተናጋሪዎቹ ሀሳብ የተሟላ ትርጉም እንዲኖረው አድርገዋል፡፡ አቶ ቦኒ ሀየችም በጉራ ፈርዳ ወረዳ የተደረገውን ቃለ መጠይቅ በመተርጎም ጥናቱን የተሟላ ለማድረግ ጥረዋል፡፡

## 1.7.2. 2 ካልዓይ የመረጃ ምንጮች

አንድ የመስክ ጥናት የሚያደርግ የመስክ ተመራማሪ ወደ ተጠኚው ማኅበረሰብ ከመሄዱ በፊት የሚያጠናውን ማኅበረሰብ በደንብ ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ማኅበረሰቡ ሲቀላቀልም ምን ማድረግ እንዳለበት እና የሚያደርጋቸውም ነገሮች በወጉ የተጠኑ እንዲሁም የታቀደባቸው መሆን ይገባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አጥኚው የማኅበረሰቡን አጠቃላይ ባሕላዊ፣ ፓለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ሃይማኖታዊ እና መልክአምድራዊ ገጽታውን ጠንቅቆ ማወቅ እንደሚገባው ለዚህም እንዲረዳው የተለያዩ መዛግብቶችን መመርመር እንዳለበት ፈቃደ (1991፡124-125)፣ Goldstein (1964፡38)፣ MacDonald (1972፡408) ይመክራሉ፡፡

ለዚህ ጥናት መሳካት መረጃዎች ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ከሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ባሕልና ቱሪዝም፣ ከቤንች ማጂ ዞን ባህልና ቱሪዝም፣ ከመኤኒት ጎልዲያ፣ ከመኤኒት ሻሻ እና ከጉራፈርዳ ወረዳዎች ባሕልና ቱሪዝም ጽ/ቤቶች፣ ከማጂ ወረዳ ቤት መዛግብት ማዕከል፣ በብሔረሰቡ ላይ የተሠሩ ጥናቶች፣ መጻሕፍት እና ሌሎች መረጃዎች

ታይተዋል፡፡ በተጨማሪም ከርዕሱ ጋር የተዛመዱ መረጃዎችን ለማግኘት የተለያዩ ድረ-ገጾች ተቃኝተዋል፡፡

### 1.7.2.3 ቃለ መጠይቅ

የዚህን ጥናት መረጃዎች በተገቢው ደረጃ እና መንገድ ለማሰባሰብ አስቀድመው የተዘጋጁ ጥያቄዎችን በማቅረብ፣ በምልከታ ወቅት ከታዩትና መብራራት ከሚገባቸው ሀሳቦችን እና ትርጓሜዎች የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት እንዲሁም መረጃ ከሚሰጡ ሰዎች መልስም በመነሳት የተለያዩ ጥያቄዎችን በማቅረብ መረጃው ተሰብስቧል፡፡ መረጃው በዋናነት ከሁለቱም ወረዳዎች እና ከጉራ ፈርዳ ስለ ሚት እና ስለ ፋይዳው መረጃ እንዲሰጡ ለተመረጡ፤ ለ"ኮሞሩቶች" /የጎሳ መሪዎች/፣ ለ"ኤሪዮች" /የባሕል ሃይማኖት መሪዎች/፣ ባሕሉን ጠንቅቀው ለሚያውቁ የሀገር ሽማግሌዎችና የዕድሜ ባለጸጋዎች፣ በፆታ፣ በሥራ፣ በእድሜ ለሚለያዩ ልዩ ልዩ የብሔረሰቡ አባላት፣ ለወረዳ የባሕል ጽ/ቤት ባለሙያዎች አመቺ በሚሆኑ ቦታዎችና ጊዜዎች ላይ በማቅረብ ተሰብስቧል፡፡

በመኤኒት ብሔረሰብ ከሚነገሩ ቋንቋዎች አንዱ አማርኛ ሲሆን በወረዳዎቹ በሥራ ቋንቋነትም ያገለግላል፡፡ በመሆኑም ቃለመጠይቆቹ በአማርኛ እና በመኤኒተኛ በሁለቱም ቋንቋዎች ተካሂደዋል፡፡ ቃለ መጠይቆቹ የተዘጋጁት በአማርኛ ቋንቋ ሲሆን ቋንቋውን ለማይናገሩ የመረጃ ሰጪዎቹ እኔ በአማርኛ ቋንቋ የምጠይቃቸውን ጥያቄዎች አስተርጓሚዎቹ ወደ መኤኒትኛ በመተርጎም ለተጠያቂዎቹ በማቅረብ፣ ተጠያቂዎቹ የሚሰጡትን መልስም ወደ አማርኛ ቋንቋ በመለወጥ ተከናውኗል፡፡ በዚህም መንገድ በአጠቃላይ ከሦስቱም ወረዳዎች 16 ቁልፍ እና 32 አጋዥ የመረጃ አቀባዮች በቃለ መጠይቁ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

### 1.7.2.4 ተተኳሪ የቡድን ውይይት

ይህ ዓይነቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በምልከታ እና በቃለመጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎችን የበለጠ ለማጠናከር፣ አጥኝው ሊያይ ያልቻላቸውን እና በቃለመጠይቅ ያገኛቸውን መረጃዎች ለማጣራት፣ እርስ በርስ የሚቃረኑ መረጃዎች ከመጡም ለማስታረቅ እና ወደተጨባጭ እውነት ለመምጣት የሚያስችል የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ዓይነቱ የመረጃ ማሰባሰቢያ

ስልት፣ ከያርጣ፣ ከጉራ ፈርዳ እና ከኮላይ ቀበሌበ  የተውጣጡ፣ በሃይማኖት፣ በእድሜ፣ በጾታ፣ በሥራ፣ በማኅበራዊ ኃላፊነትና ደረጃ የተለያዩ የብሔረሰቡ አባላት ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ በሁለቱ ወረዳዎች አንድ አንድ ጊዜ የቡድን ውይይት ተደርጓል፡፡  በያርጣ ቀበሌ የካቲት 8 ቀን 2011 ዓ.ም ከጧቱ 4፡00 - 5፡00 ውይትት ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይም በኮላይ ቀበሌ ግንቦት 12 ቀን  2011 ዓ.ም፣ ከሰዓት ከ10፡00 - 12፡00 የቡድን ውይይቱ ተደርጓል፡፡ ከሁለቱም ቀሌዎች ሰባት ሰባት የተመረጡ ሰዎች የውይይቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

### 1.7.3 የናሙና አመራረጥ

መረጃውን ለመሰብሰብ የመረጃ ሰጭዎች ባሕሉን ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ ማኅበረሰቡ እምነት የሚጥልባቸው፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በክብር እና በሙያ አገልግሎታቸው የተለያዩ ሰዎች እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ ያሉ "ኮሞሩቶች" /የጎሳ መሪዎች/፣ ኤሪዎች /የባሕላዊ ሃይማኖት መሪዎች/፣ ዝናብ በማዝነብ፣ ንብን፣ አንበሳን፣ ወባን እና ሌሎችን የማዘዝ ስልጣን እንዳላቸው በብሔረሰቡ የሚታመኑ "ኮሞሩርት ኘራዮዎች"፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና የብሔረሰቡ ተወላጆች ከተለያየ የሥራ መደብ የተውጣጡ (ነጋዴዎች፣ የፖሊስ ሠራዊት አባላት፣ የከተማ ኗሪዎች፣ በግብርና እና በእንስሳት ርባታ የሚተዳደሩ ሰዎች፣ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ "ኮኮዎች" ወይም የባሕል መስተጋድላውያን ረዳቶች መረጃ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

እነዚህን ቁልፍ እና አጋዥ የመረጃ ሰጪዎች በመምረጥ ከፍተኛውን ድርሻ የተወጡት በመኤኒት ሻሻ እና በመኤኒት ጎልዲያ አቶ ብርሃኑ ወርቁ እና አቶ በድሉ ካሳ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ሰዎች በወረዳው የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ውስጥ በተለያዩ ጊዚያት የጽ/ቤቱ ሐላፊ በመሆን  ያገለገሉ ሲሆን የብሔረሰቡን ባሕልና ታሪክ ያውቃሉ፡፡ ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችም ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ የናሙና አመራረጡ ላይ ጥንቃቄ ወስደው ምርጫውን በማድረግ ጥናቱን አግዘዋል፡፡ በተመሳሳይም አቶ ቦኒ ሀየች በጉራ ፈርዳ ወረዳ በተለያዩ ሐላፊነቶች የሠሩ በመሆናቸው መረጃ ቢሰጡ ትክክለኛ መረጃ ይሰበሰባል ያሏቸውን ሰዎች በመምረጥ ከፍተኛ እገዛ አድርገዋል፡፡

### 1.7.4 መረጃ መሰብሰቢያ የመስክ መቼቶች

መረጃን ከመስክ ለመሰብሰብ ሦስት ዓይነት መቼቶች እንዳሉ እና አጥኚው ለጥናቱ ተስማሚውን መጠቀም እንደሚገባው ፈቃደ (1991፡11-13) ይገልጻሉ፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ የሚት ዓይነቶች እና ፋይዳ ለማጥናት ተፈጥሯዊ መቼቶች በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

### 1.7.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለጥናቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ወደተጠኚው ብሔረሰብ ከ2008 ዓ.ም. እስከ 2011 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በተለያዩ እና አመቺ በሆኑ ጊዜያት በመመላለስ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከህዳር 2 ቀን እስከ ህዳር 14 ቀን 2008 ዓ.ም፣ ከሰኔ 6 ቀን እስከ ሰኔ 21 ቀን 2008 ዓ.ም፣ ከህዳር 10 ቀን 2010 እስከ ህዳር 24 ቀን 2010 ዓ.ም፣ ከታኅሣሥ 7 ቀን እስከ ታኅሣሥ 15 ቀን 2010 ዓ.ም፣ ከየካቲት 4 ቀን እስከ የካቲት 14 ቀን 2011 ዓ.ም፣ ከግንቦት 2 ቀን 2011 ዓ.ም እስከ ግንቦት 17 ቀን 2011 ዓ.ም እና ከግንቦት 22 ቀን 2011 ዓ.ም እስከ ከግንቦት 27 ቀን 2011 ዓ.ም  ድረስ በመኤኒት ጎልዲያ፣ በመኤኒት ሻሻ እና በጉራፈርዳ ወረዳዎች በመጓዝ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ወደ ተጠኚው ብሔረሰብ በተለያዩ ጊዜያት አንዳንዴም በወር ሁለት የተለያዩ ጊዜያት ተመላልሻሻሁ፡፡ ይኸውም የመረጃ አቀባዮች በተለይም የጎሳ እና የሃይማኖት መሪዎች የሚመቻቸውን ጊዜ በመጠበቅ እና የሚሰጡትን ቀጠሮ በመቀበል ሲሆን አንዳንዴም የአካባቢው ወቅታዊ የጸጥታ ሁኔታን ማዕከል ያደረገ ስለነበረ ነው፡፡

በአጠቃላይ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እና እንዲሰነዱ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሁሉ አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ የድምጽና ምስል፣ እንዲሁም የፎቶግራፍ ካሜራዎች፣ መቅረጸ-ድምጾች፣ የማስታወሻ ደብተሮችን በመጠም መረጃዎቹ ተሰብስበዋል፡፡

## 1.8 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በአጠቃላይ ዘጠኝ ምዕራፎች አሉት፡፡ ምዕራፍ አንድ የጥናቱን መግቢያ፣ የጥናቱን ዳራ፣ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱን ዓላማ፣ ጥናቱን

የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱን ፋይዳ፣ የጥናቱን ወሰን፣ የጥናቱን ዘዴ፣ የጥናቱን አደረጃጀት፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን እና የተወሰዱ የመፍትሔ መፍትሔዎችን ይዟል፡፡ ምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳናት ሥር፣ የጥናቱ ጽንሰ ሐሳብ፣ የጥናቱ ንድፈ ሐሳብ እና የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ቀርቦበታል፡፡ ምዕራፍ ሦስት የመኤኒት ብሔረሰብን ያስተዋውቃል፡፡ ምዕራፍ አራት የመኤኒት ብሔረሰብ የአፈጣጠር ሚት፣ በምዕራፍ አምስት የመኤኒት ብሔረሰብ መንፈሳዊ ሚት፣ በምዕራፍ ስድስት የመኤኒት ብሔረሰብ የባሕል መስተጋድላውያን ሚት፣ በምዕራፍ ሰባት የመኤኒት ብሔረሰብ የጳግም ውልደት ሚት፣ በምዕራፍ ስምንት የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶቹ ፋይዳ ተካትተዋል፡፡ ምዕራፍ ዘጠኝ ማጠቃለያና ይሁንታን ይዟል፡፡

## 1.9 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች

የሀገሪቱ አጠቃላይ ሰላም ከአራት ዓመታት በላይ አደጋ ውስጥ የወደቀ መሆኑ እንደዚሁ ዓይነቱን ወደ ዳር ሀገር ያለ ጥናት ለማጥናት አስቸጋሪ መሆኑ፣ ከአንዴም ሁለቴ ወደ ሥፍራው ባደረኳቸው ጉዞዎች የመንገድ መዘጋት እና የተቃውሞ ሰልፎች አጋጥመውኛል፡፡ በአንደኛው ወቅት መረጃ ሰብስቤ በመጣሁበት ጊዜ በመሆኑ መንገዶቹ እስኪከፈቱ እና የፀጥታው ችግር እስኪያልፍ ድረስ በሚዛን ከተማ አምስት ቀናት በማሳለፍ ችግሩ ተቃልሏል፡፡ የሁለተኛው ጊዜ መንገድ ቦንጋ ከተማ ላይ በመዘጋቱ ከጅማ ከተማ እንደገና በመመለስ በሐዋሳ በኩል በማድረግ ጉዞውን ለማሳካት ችያለሁ፡፡

ጥናት ካደረኩባቸው ቀበሌዎች ውስጥ አንዱ ያርጣ የተሰኘው ቀበሌ አዲስ እና በ2003ዓ.ም ከቀረው የመኤኒት ብሔረሰብ ጋር የተቀላቀለ በመሆኑ እና በዘር ላይ ከመሠረተው የሀገሪቱ የፖለቲካ ዐውድ ጋር ተቀላቅሎ በሚፈጥረው የገለልተኝነት ስሜት በተለያዩ ቀበሌዎች ላይ ረዘም ያለ ጊዜ ለመቆየት አያስችልም፡፡ ይሁን እንጅ አካባቢውን ጠንቅቀው የሚያውቁ እና ተሰሚነት ያላቸው ሰዎች የአካባቢውን ሰዎች ቀድመው በማነጋገር፣ የጎሳ እና የባሕል ኃይማኖት መሪዎችን በማስፈቀድ መረጃዎችን በአጭር ጊዜ ሰብስቦ ለመመለስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በአንዳንድ የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ያገኘኋቸው የብሔረሰቡ አባላት መረጃ ከሰጡ በኋላ የተለየ እርዳታ (የገንዘብ፣ የምግብ፣ የልብስ፣ የጫማ) ለራሳቸውና ለልጆቻቸው እንዳደርግላቸው ጠይቀውኛል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ በራሱ ልብን የሚነካ እና የሚያሳዝን ሲሆን ከወረዳው አብረውኝ የተጓዙት አስተርጓሚዎችና የባሕልና ቱሪዝም ሠራተኞች እንዲሁም የየቀበሌው ተወካዮች የእኔን ዓላማ በማስረዳት እና ችግራቸው በእነሱ በኩል እንደሚቃለል በመንገራቸው ችግሩ ሊታለፍ ችሏል፡፡

የቋንቋ ችግር እንዲህ ዓይነቱን ጥናት እንደ ልብ እንዳያጠኑ ዋና ችግር ነው፡፡ መረጃ ሰጪዎች በሚናገሩበት ቋንቋ የተናገሩትን አጥኘው የሚያዳምጠው በአስተርጓሚው በኩል መሆኑ አንድ ተግዳሮት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የኤም ኤ ዲግሪ ጥናቴን በማጠናበት ወቅት በዚሁ ሥራ የተባበሩኝ ወረዳው ላይ ከአስተዳዳሪነት ጀምሮ፣ የባሕልና ቱሪዝም ኃላፊ እና በብዙ የሥራ ኃላፊነት ላይ የነበሩት አቶ ብርሃኑ ወርቁ እዲሁም በኤም ኤ ዲግሪ ጥናቴ ወቅት የባሕልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ፣ በኋላም የገጠር መንገድ ኃላፊ የሆኑት አቶ በድሉ ካሳ እንዲሁም፣ መረጃዎችን በሰበሰብኩ ሰዓት ሁለት የባሕልና ቱሪዝም ኃላፊዎች በሁሉም ቀበሌዎች አብረው የተንቀሳቀሱ በመሆኑ፣ በትርጉም ሥራው በመተጋገዝ፣ አንዱ ያጎደለውን ሌላው በመሙላት፣ ሊፈጠር የሚችለውን ክፍተት እንዳይኖር ለማድረግ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ጊዜውና የሀገሪቱ የፖለቲካ ዐውድ የፈጠረው አለመረጋጋት፣ የአካባቢው መራቅ እና የትራንስፖርት አለመኖር፣ በአንዳንዱም ቀበሌ ለትራንስፖርት አስቸጋሪ መሆንና ጥናት በተደረገበት አካባቢም የፀጥታ ችግሮች ቢስተዋሉም፤ በተለይም የመኤኒት ጎልዲያ ወረዳ አመራሮች፣ የባሕልና ቱሪዝም ባለሙያዎች፣ የወረዳው የሰላምና የፀጥታ ኃላፊዎች፣ የወረዳው የፖሊስ ኮሚሽንና የሥራ ኃላፊዎች እና አባላት፣ የጎሣ መሪዎች እና የኃይማኖት አባቶች፣ የጉራ ፈርዳ የሰላምና የፀጥታ ኃላፊዎች የየራሳቸውን ድርሻ በመወጣት፣ አስቸጋሪም ቢሆን መኪና በሚገባባቸው ቀበሌዎች መኪና በመመደብ፣ በስውር እና በግልጽ የፀጥታ ኃይላትን በአጃቢነት እና በጠባቂነት በመላክ ለተፈጠሩ ችግሮች መልስ በመስጠትና ስነ ልቡናዊ ዝግጅትን በማድረግ የተፈጠሩ ችግሮችን ለማለፍ ተችሏል፡፡

## 1.10 ጥናቱ የተከተላቸው የሙያ ሥነ ምግባራት

በጥናቱ 48 ሰዎች ዋና እና አጋዥ የመረጃ ምንጭ በመሆን ተሳትፈዋል፡፡ እነዚህ የመረጃ ምንጭ በመሆን የተሳተፉ ሰዎች በሙሉ በየወረዳዎቹ የአስተዳደር አካላት፣ የባህልና ቱሪዝም ሐላፊዎች፣ የጎሳ እና የሃይማኖት መሪዎች እንዲሁም የአካባቢ ሽማግሌዎች የተመረጡ ናቸው፡፡ ለሁሉም መረጃ የሚሰጡበት ምክንያትና ለማኅበረሰቡም የሚሰጠው የጥቅም በመረጧቸው አካላት ገለጻ ተደርጎላቸዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃ የሰጡት በሙሉ ድምጻቸው እንዲቀረጽ፣ ምስላቸው በፎቶ እና በቪዲዮ እንዲቀረጽ የተስማሙ ናቸው፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ሃይማኖታዊ እና የግል የሆኑ ምስጢሮች አስቀድመው እንዳይቀረጹ በተነገርኩበት አካባቢ መረጃ አቀባዮቹን ቃል አክብሬያለሁ፡፡ ድርቶቹን ሳይ በድምጽም ሆነ በምስል ያልያዝኳቸው መረጃዎች አሉ፡፡

በሃይማኖት መሪው ኘራይ አወቀ ፎሮሾዋ ቤትና ግቢ የተከናወኑ የሾርቃ ውሃ መድፋት እና የግቢ ጠረጋ የመሐላ ክንውኖች በፎቶም ሆነ በቪዲዮ መቀረጽ እንደሌለባቸው ስለተነገረኝ ክንውኖቹን በፎቶም ሆነ በቪዲዮ አልቀረጽኩም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2.ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ርዕስ ሥር የጥናቱ ጽንሰ ሐሳብዊ ዳራ፣ የጥናቱ ንድፈ ሐሳብ እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ቀርበዋል፡፡

### 2.1 ጽንሰ ሐሳባዊ ዳራ

በዚህ ጽንሰ ሐሳባዊ ዳራ በተሰኘ ንዑስ ርዕስ ሥር ሚት፣ የሚት ባህሪያት፣ የሚት ዓይነቶች እና የሚት ፋይዳ በቅደም ተከተል ቀርበውበታል፡፡

#### 2.1.1 ሚት

ስለሚት በርካታ ብያኔዎች ተሰጥተዋል፡፡ ይሁን እንጅ ራሱን የቻለ፣ አንድና ወጥ ብያኔ የለውም፡፡ Leeming ሚት በቃል እየተነገረ ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ ተጠብቆ የቆየ ቅዱስ መሆኑን፣ መነሻውም ከአምላክ ወይም ከአማልዕክት እንደሆነ ሲገልጹ "Myths are retold orally from generation to generation and/ or preserved in sacred collections or scripture, often believed to have emanated from a deity or deities." (Leeming, 2010: xvii) ይላሉ፡፡

ሚት ረጅም እድሜ ያለው፣ ቃላዊ ትረካ፣ ሰዎች ሁለንተናዊና የማያቋርጡ ጥያቄዎቻቸውን በተለይም የማንነትና የምንነትን፣ የየትመጣንነትን መሰል ጥያቄዎችን የጠየቁበትና መልስም የሰጡበት የእምነት፣ የአስተሳሰብና የፍልስፍና ማራመጃቸውም ነው፡፡ ሚቶች "ዓለም እና መላው ሕዋ ከየት ነው የመጡት? ፍጥረታት እንዴት ወደዚች ምድር መጡ? እኛ ማን ነን? በዚህ ዓለም ላይ ሚናችን ምንድነው? የእኛ እሴቶች ምን ምን ናቸው? እንዴት ነው መኖር ያለብን?" ለሚሉ የሰዎችን መሠረታዊ ጥያቄዎች የመመለስ ኃይል ያላቸው እና ረጅም ዕድሜ ያሳለፉ አፈ ታሪኮች እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡

> *Myths are ancient narratives that attempt to answer the enduring and fundamental human questions: How did the universe and the world come to be? How did we come to be here? Who are we? What are our proper, necessary, or inescapable roles as we relate to one another and to the world at large? What should our*

*values be? How should we behave? How should we NOT behave? What are the consequences of behaving and not behaving in such ways? (Leonard and McClure, 2004).*

*ሚቶች ዘላቂ እና መሠረታዊ የሆኑትን የሰዎች ጥያቄዎች ለመመለስ የሚሞክሩ ጥንታዊ ትረካዎች ናቸው፡፡ አጽናፈ ሰማይ እና ዓለም እንዴት ተገኘ? ወደዚህ እንዴት መጣን? እኛ ማን ነን? እርስ በእርሳችን እና በአጠቃላይ ከዓለም ጋር ስለምንገናኝ ተገቢ፣ አስፈላጊ፣ ወይም የማይሸሽ ሚናዎች ምንድናቸው? እሴቶቻችን ምን መሆን አለባቸው? ምን ዓይነት ጠባይ ማሳየት አለብን? ምን ዓይነት ጠባይ ማሳየት የለብንም? በእንደዚህ ዓይነት መንገዶች ጠባይ ማሳየት እና አለማድረግ የሚያስከትላቸው ውጤቶች ምንድናቸው? (Leonard and McClure, 2004)፡፡*

ምንም እንኳን ሚት ረጅም እድሜን ያሳለፈ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገር፣ ቅዱስ የሆነ እና ሃይማኖታዊነት የሚጫነው እንደሆነ የሚያምኑ ቢኖሩም፤ ይህን አስተሳብ የሚቃረኑ እና ተጠራጣሪዎችም አሉት፡፡ የሚትን ቅዱሳዊነት እና ሃይማኖታዊነት አጽንተው የሚከራከሩት፣ ይሄንን ብያኔ እና አስተሳሰባቸውን ለማስረጽ ሚት ለተጠራጠሩት መልስ የመስጠት ጉልበትና ኃይል እንዳለው ያብራራሉ፡፡

*Myths are prose narratives which, in the society in which they, are told, are considered to be truthful accounts of what happened in the ' remote past. They are accepted on faith, they are taught do be believed, and they can be cite as authority in answer to ignorance, doubt or disbelief. Myths are the embodiment of dogma; they are usually sacred, and they are often associated with theology and ritual. (Bascom 1965, 4)*

*ሚቶች በድሮ ጊዜ የተከናወኑ፣ በቃል የሚነገሩ እና በማኅበረሰቡ ዘንድ እውነት እንደሆኑ የሚታመኑ ትረካዎች ናቸው፡፡ ሚትን ለተጠራጠረ፣ ቸል ላለ ወይም ላላመነ መልስ የመስጠት ኃይል እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ ሚቶች የዶግማ መገለጫ ናቸው፣ ብዙውን ጊዜ ቅዱስ፣ በአብዛኛውም ከሥነ-መለኮት እና ከአምልኮ ሥርዓቶች ጋር የተቆራኙ ናቸው።" በማለት ሀሳቡን ይጋራል (Bascom፣ 1965, 4) ፡፡*

Bascom እንደሚሉት ሚቶች በአንድ ማኅበረሰብ ያለፈ ታሪክ ውስጥ ተደርገዋል ተብለው የሚነገሩ እና የሚታመኑ ታሪኮችም ናቸው፡፡ እነዚህ

ተደርገዋል ወይም ተፈጽመዋል ተብለው የሚታመኑ ታሪኮች ዓለምን ልክ እንደ ግጥም በተምሣሌታዊ አነጋገር ለመገንዘብና ለመረዳት የሚያገለግሉ መንገዶች መሆናቸውን ደግሞ Muller, 1907) (Philip, 2007, 6) ይገልጻሉ፡፡

ሚት የአንድ ማኅበረሰብ የባሕል እሴቶችን መሠረት አድርጎ የሚገኝ ሲሆን በዚያ ማኅበረሰብ ውስጥ ያለን የአንድ ግለሰብን ምንነት በመቅረጽ ከፍተኛ ኃይል አለው፡፡ ከግለሰብ ባሻገር የአንድን ብሔረሰብ እና ከዚያም አልፎ ሀገራዊ ማንነትን በመቅረጽ እና እርስበርስ ቁርኝትና መስተጋብር የሚፈጥሩበት መንገድ ነው፡፡

ሚቶች የተመሠረቱት በባሕል ውስጥ ባሉ ግለሰቦች እምነት እና ባህሪ ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ ባሕላዊ እሴቶች ላይ ነው፡፡ ይህ ማለት ሚቶች ግላዊ እና ግለሰባዊ፤ ብሔረሰባዊ እና ብሔራዊ ሊሆኑ ይችላሉ። ሚቶች በተናጥል እና በብሔራዊ ደረጃ ትርጉም ስለሚገነቡ ሰዎችን ከባሕላቸው ጋር ለማገናኘት እንደ አንድ መንገድ ያገለግላሉ *(Brown, 2004, 276 )*፡፡

የሚት ከዋኞች፣ የመከወኛ ቦታውና ሰበቡ እጅግ በርካታና ገደብ የለሽ ነው፡፡ የባለታሪኮቹ ማንነትም ይሁን ታሪኩ ሊከወንበት የሚችለው ቦታ ፈጽሞ ገደብ የሚበጅለትና የሚቀነበብ እንዳልሆነ Segal ያብራራሉ፡፡

> *There is no uniform definition of myth. For some theories of myth, myth need not even take the form of a story, as might be assumed, but can instead be a belief or a conviction. For other theories, mythological stories need not take place in the past but can take place in the present or the future. Myths can take place on earth, in heaven, or in space. The characters in myth need not be gods but can alternatively be humans or even animals. What happens in myth is open ended. (Segal, 2015)*
>
> *ሚቶች ባለፉት ጊዜ ብቻ መከናወን አያስፈልጋቸውም፤ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ወይም ለወደፊቱ ሊከናወኑ ይችላሉ፡፡ መሬት ላይ፣ በገነት ወይም በሕዋ ላይ ሊከወኑ ይችላሉ፡፡ የሚት ገጸ-ባሕሪያት አማልዕክት ብቻ ሳይሆኑ፣ ሰዎችም እንስሳትም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በሚት ላይ የሚፈጸሙ ጉዳዮችን ገደብ ልናበጅላቸው አንችልም ( Segal, 2015) ይላል፡፡*

ከላይ ስለሚት ምንነትና ብያኔ እንደ ተጠቀሰው፣ የብያኔ ሰጪዎቹ የትርጓሜ ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ባነሷቸው ባህሪያት መሠረት የሚጋሯቸው ሀሳቦች እንዳሉ መረዳት ይቻላል፡፡ Fryeም ይሄንኑ ሀሳብ ያጠናክሩልናል፡፡ "በአብዛኛው ብያኔዎች ላይ የሚታዩ ተመሳሳይ ባህሪያት አሉ፡፡ በአብዛኛው ሚት እንደ ታሪክ /story/ እና ትረካ /narration/ ተደርጎ ይወሰዳል" (Frye, 1984፣ 465-476)፡፡ በአብዛኛው ለሚት የተሰጡት ብያኔዎች ከዚህ በታች ባሉት ሊጠቃለሉ ይችላሉ፡፡

1. ሚቶች የነገረ ፍጥረታት ትረካዎች ናቸው፡፡ ከሕዋ አፈጣጠር ጋር ግንኙነት እንዳላቸው ይታመናል፡፡
2. ሚቶች የቅዱሳን ተፈጥሮ አፈ ታሪኮች ናቸው፡፡ ከሥርዓትና ከበራ ጋርም ተያያዥነት አላቸው፡፡ ሚቶች ከሃይማኖት ጋር ተያያዥነት ያላቸው አፈ ታሪኮች መሠረት ነው፡፡ እነዚህ አፈ ታሪኮች በአማኞቹ ዘንድ ተአማኒነት አላቸው፡፡
3. የሚቶች ትረካዎች የአንድን ማኅበረሰብ የባሕል እሴቶች ማሳያ ናቸው፡፡
4. የሚቶች ትረካዎች በአብዛኛው የመስተጋድላን ታሪክ የያዙ ናቸው፡፡
5. የሚት ትረካዎች የሰዎችን እውቀት፣ ተፈጥሮንና የተደራጀበትን አስተሳሰብ ለመረዳት መንገዶች ይከፍታሉ፡፡
6. ሚቶች ልክ እንደ ግጥም ዓለምን በዘይቤያዊ አነጋገር የምንረዳባቸው መንገዱ ናቸው፡፡
7. ሚቶች ረጅም እድሜ ያላቸው አፈ- ታሪኮች ሲሆኑ፣ የሰዎችን መሠረታዊ ጥያቄዎች የመመለስ ኃይል አላቸው፡፡

ሚትን ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች በመነሳት እንደሚከተለው መበየን ይቻላል፡፡ ሚት የሰው ልጅ ለዘመናት የማንነት እና ከየት መጣሁነቱን ቅኝት ያካሄደበት፣ የመሰለውን እና ሊሆን የፈለገውን ነገር የበየነበት፣ በእሱ እና በአጠቃላይ የሕይወት መስተጋብር መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ያነጻረበት እምነቱ ነው፡፡ ከአፈጣጠሩ እና ከአመጣጡ አስተካክሎ የሚገነዘባቸውን እና የሚገምታቸውን የዘላለም ጥያቄዎች በራሱ እሳቤ የተረዳበት፣ የተረዳውንና ያመነበትን የተረጎመበት፣ እንዲሁም እውቀትና እምነቱን፣ መላምቱንና ምኞቱን

አስጠብቆ ለትውልድ ያቆየበት ታላቅ ሁለንተናዊ ውርሱ፣ አሁንም የሚኀዝበትና የሚመራበት የሕይወት መንገዱ ነው፡፡

## 2.1.2 የሚት ዓይነቶች

ሚት የተለያዩ ክፍሎች እንዳሉት ምዳቤ የሰጡት የዘርፉ ምሁራን የየራሳቸውን አስተሳሰብ ዋቢ አድርገው ከፋፍለዋል፡፡ Leeming (2010፣1)፣ Vitalino (1968) የየራሳቸውን የሚት ምዳቤዎችን ሰጥተዋል፡፡ የሚት ዓይነቶችን ምደባ በራሱ ችግር እንዳለበትና በዘርፉ አጥኝዎችም ዓለም አቀፋዊ መግባባት ላይ የራሱ ተጽዕኖ እንዳለው ቢታወቅም ዐውዳዊ ትረካው ላይ ትኩረት ማድረግ የዓይነቶቹን እና ምዳቤውን መልክ ለማስያዝ መሞከር እንደሚሻል ፊኔጋን ትገልጻለች (Finniegan 1970፣ 126)፡፡ እንደ Finniegan እምነት እያንዳንዱ ሚት ሲተረክ፣ የራሱ የትረካ ጊዜ፣ የትረካ ቦታ፣ የትረካ ቅደም ተከተል ከአጠቃላይ ዐውዱ ጋር ተናብቦ መታየት እንደሚያስፈልገው መገንዘብ ይቻላል፡ ፡ ሚቶቹ አንዳንዴም በቀጭን የጋራ መሥመር የሚገናኙ እና አንዱ በአንዱ ክሱት የሚሆኑበት አጋጣሚም ሊኖር የመቻሉን ዕድል መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ Kittelstad (2013) በበኩላቸው የሚት ዓይነቶችን ሲመድቡ በአራት አንኳር ምዳቤዎች ሥር ደልድለዋቸዋል፡፡ እነዚህ አራት የሚት ምዳቤዎች የእንስሳት ሚት፣ የአፈጣጠር ሚት፣ የሞት ወይም የምድር በታች ሚት እና የመስተጋድላውያን ሚት በማለት መድበዋቸዋል፡፡ Leeming ደግሞ በርከት እና ዘርዘር አድርገው የሚትን ምዳቤዎችን ገልጸዋል፡፡ “ሐተታ ተፈጥሮዊ ሚት፣ የዳግም ውልደት ሚት፣ የመስተጋድላውያን ሚት፣ መንፈሳዊ ሚት፣ የትንሳኤ ሚት፣ የለውጥ ሚት፣ የዘመናዊ የምድር ሚት፣ የነገሥታትና የሰማዕተት ሚት፣ የመሲሕነት ሚት፣ የማስታወስና መዘንጋት ሚት፣ የዘመናዊ ማኅበረሰብ ሚት፣ የጥበቃ እና የእጣ ፋንታ ሚት፣ የጊዜ እና የዘለዓለማዊነት ሚትና ጂኦሜቶሎጂ” ብለዋቸዋል (Leeming, 2010)፡፡ ከዚህ በታች ጥቂት የሚት ዓነቶችን በዝርዝር ማየት እንዲቻል የአፈጣጠር ሚት፣ የእምነት ሚት፣ የመስተጋድላውያን ሚት እና የዳግም ውልደት ሚትን በአጭሩ ቀርበዋል፡፡

### 2.1.2.1 የአፈጣጠር ሚት

የአፈጣጠር ሚት የሰው ልጅ ስለራሱ፣ እሱ ስለሚኖርባት ምድር እና ምድርን ስለከበባት ዓለም፣ ስለሚታየው እና ስለማይታየው፣ ከቅርቡ ስላለውና

በጣም ርቆ ስለሚገኘው፣ ስለረቂቁ እና ስለግዙፋን ፍጥረታት መስተጋብር፣ በየአንዳንዱ ደቂቃ አእምሮውን ሲያስጨንቁት ለሚኖሩት ከየት መጣን? መቼ መጣን? እንደምን መጣን? ማን አመጣን? እንዲሁም ለምን መጣን? የሚሉትን እረፍት የለሽ ጥያቄዎች፤ እንደገባው፣ እንዳመነው እና ነው እንዳለው መልስ የሰጠበት እውቀቱ እና እምነቱ ነው፡፡ Leeming “Creation myths tell us where we came from, how things began. They are our “primary myths, the first stage in what might be called the psychic life of the species. Creation is almost always linked to the concept of Deity.” (Leeming, 2010፣ 12)

ይህ የሚት ዘርፍ የራሱ በርካታ ንዑሳን ክፍሎች አሉት፡፡ የተለያዩ ምሁራንም እንደየ ዘርፋቸው ምዳቤውንም የተለያየ አድርገውታል፡፡ (Bascom፣ 1965)፣ Muller, max (1889)፣ (Philip, 2007)፣ (Timothy J . Brown, 2004)፣ (Robert Segal, 2015)፡፡ Leeming ደግሞ የአፈጣጠር ሚትን በአምስት ምድቦች ከፍለዋቸል፡፡ እነሱም “Ex Nihilo Creation” /እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ /ካለመኖር ወደ መኖር/ መፈጠር፣ “Creation from Chaos” ግብር እምግብር/ከተፈጠረው የተፈጠረ /ከአለ ነገር መፈጠር፣ “World Parent Creation” ከቤተሰብ መፈጠር፣ “Emergence Creation” በድንገት መፈጠር፣ “Earth-Diver Creation” በርድኾት (ወደ መሬት በመስጠም) መፈጠር ናቸው፡፡ (Leeming, 2010፣ 1)፡፡

በLeeming አተረጓጎም ውስጥ ከምንም ነገር መፈጠር አንደኛው እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ /ካለመኖር ወደ መኖር/ መፈጠር ሲሆን፣ ግብር እምግብር /ከተፈጠረው የተፈጠረ /ከአለ ነገር መፈጠር ደግሞ ሁለተኛው ነው፡፡ በዚሁ የአፈጣጠር ሚት ውስጥ ከቤተሰብ መፈጠርን ሦስተኛው የአፈጣጠር ሚት አድርገው ሲያመጡ፣ በአራተኛነት በድንገት መፈጠርን፣ በአምስተኛነት ደግሞ በርድኾት (ወደ መሬት በመስጠም) መፈጠርን አስቀምጠዋል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት እያንዳንዳቸው በተለያዩ ሕዝቦች፣ ባህሎች እና ሃይማኖቶች ግንዛቤ የተለያዩ የአፈጣጠር ሚት ትረካዎች አሏቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ሦስቱ እና ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ተያያዥኙነት ያላቸውን እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ /ካለመኖር ወደ መኖር/ መፈጠር፣

ግብር እምግብር/ከተፈጠረው የተፈጠረ /ከአለ ነገር መፈጠር እና ከቤተሰብ መፈጠር ቀርበዋል፡፡

- **እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ /ካለመኖር ወደ መኖር/ መፈጠር**

ከምንም ነገር መፈጠር፣ አስቀድሞ ወይም ከዚያ በፊት የተፈጠረ ምንም ነገር አልነበረም ብሎ ማመን ሲሆን፣ በዚህ የሚት ትረካ ውስጥ ግን አንድ ሁሉን ማስገኘት የሚችል ኃይል፣ አስቀድሞም ራሱን በራሱ ያስገኘ ወይም ያኖረ ኃይል መኖሩን የሚቀበል ነው፡፡ በመሆኑም ያ ቀድሞ ራሱን በራሱ ያስገኘ ኃይል "ፈጣሪ" በቃሉ ወይም ከራሱ ማንነት ብቻ በሚወጣ ልዩ ኃይል የማይታየውን ይሄንን ዓለም እና የሚታየውን ጭምር እንዳስገኘ እና እንደፈጠረ የሚገልጽ ነው፡፡ ለምሳሌ በአይሁድና በክርስትና ሃይማኖቶች የአፈጣጠር ሚት ትረካ ውስጥ ይሄንን ዓለም ያስገኘው፣ የሚታየውንም ሆነ የማይታየውን ነገር የፈጠረው እግዚአብሔር እንደሆነ ሲታመን፣ በእስልምና ደግሞ አላህ ነው፡፡ ከምንም መነገር የመፈጠር ሚቱ እንደሚያስረዳው እግዚአብሔር አስቀድሞ በራሱ ሕላዌና ኑባሬ የኖረ ሲሆን በኋላ ይሄንን ዓለም እና የሰው ልጆችን ጭምር በቃሉ ብቻ መፍጠሩን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የአፈጣጠር ሚትን ሲተርክ ከዚህ በታች ባለው መልክ ያትታል፡፡

> *በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ፡፡ ምድርም ባዶ ነበረች፣ አንዳችም አልነበረባትም፣ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፡፡ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ሰፍፎ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም፤ ብርሃን ይሁን አለ፣ ብርሃንም ሆነ፡፡ እግዚአብሔርም ብርሃኑ መልካም እንደሆነ አየ፣ እግዚአብሔርም ብርሃንና ጨለማን ለየ፡፡ እግዚአብሔርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው፣ ጨለማውንም ሌሊት አለው፡፡ ማታም ሆነ፣ ጠዋትም ሆነ አንድ ቀን፡፡ እግዚአብሔርም በውኃዎች መካከል ጠፈር ይሁን፣ በውኃ እና በውኃ መካከል ይከፈል አለ፡፡ እግዚአብሔርም ጠፈርን ሰማይ ብሎ ጠራው፣ ማታም ሆነ፣ ጠዋትም ሆነ፣ ሁለተኛ ቀን፡፡ እግዚአብሔርም ከሰማይ በታች ያለው ውኃ በአንድ ስፍራ ይሰብሰብ፣ የብሱም ይገለጥ አለ፣ እንዲሁም ሆነ፡፡ እግዚአብሔርም የብሱን ምድር ብሎ ጠራው፣ የውኃ መከማቻውንም ባሕር አለው፣ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ፡፡ እግዚአብሔርም፡፡ ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬ የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ፣ እንዲሁም ሆነ፡፡ ማታም ሆነ ጠዋትም ሆነ ሦስተኛ ቀን፡፡ እግዚአብሔርም አለ ቀንና ሌሊቱን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ፣*

*ለምልክቶች፣ ለዘመኖች፣ ለዕለታት፣ ለዓመታትም ይሁኑ፡፡ እግዚአብሔርም ሁለት ታላላቆች ብርሃናትን አደረገ፣ ትልቁ ብርሃን በቀን እንዲሰለጥን፣ ትንሹም ብርሃን በሌሊት እንዲሰለጥን ከዋክብትንም ደግሞ አደረገ፡፡ እግዚአብሔርም በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር አኖራቸው፣ በቀንም በሌሊትም እንዲሰለጥኑ፣ ብርሃንና ጨለማን እንዲለዩ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ፣ ማታም ሆነ ጠዋትም ሆነ አራተኛ ቀን፡፡ . . . እግዚአብሔርም አለ፡፡ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር፣ የባሕር ዓሶችንና የሰማይ ወፎችን፣ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ይግዙ፡፡ እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፣ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፡፡ (ኦሪት ዘፍጥረት፣ 1፣ 1- 27)፡፡*

በሀገራችን ውስጥ ካሉ በርካታ ብሔረሰቦች ውስጥ አንዱ የሆነውና በጋምቤላ ክልል የሚገኘው የአኝዋክ/ አኝዋ ብሔረሰብ ሰማይና ምድርን የፈጠረ፣ በምድር ላይ የሚኖሩትን ሁሉ ፍጡራን የፈጠረ አንድ አምላክ "ጆክ" እንደሆነ ባይለየኝ ጣሰው እንደሚከተለው አስፍሮታል፡፡ "በጥንታዊ እምነቱ መሠረት ህብረተሰቡ ሰማይና ምድርን የፈጠረ፣ እንዲሁም በምድር ላይ ፍጡራንን ሁሉ የሠራ አንድ አምላክ አለ ብሎ ያምናል፡፡ ይህን አምላክም "ጆክ" ብሎ ይጠራዋል፡፡ "ጆክ" ማለት እግዚአብሔር እንደማለት ነው፡፡" (ባይለየኝ፣ 1995፣ 6 )፡፡

- **ግብር እምግብር /ከተፈጠረው የተፈጠረ /ከአለ ነገር መፈጠር**

ይህ ዓይነቱ የሐተታ ተፈጥሯዊ ሚት የሚያስረዳው ከአንድ ቀድሞ ካለ ነገር መፈጠርን ነው፡፡ ይህ ቀድሞ ያለው ነገር፣ አዲስ ፍጥረትን የሚያስገኘው ከራሱ በሚመነጭ ኃይል ሳይሆን እንደ እሱ ቀድመው ካሉ ሌሎች ነገሮች ጋር እርስ በርስ በመዋሐድ፣ በመጋጨት ወይም በተመሳሳይ መልኩ ነው፡፡ እነዚህ ቀድመው የነበሩ ግብአቶች አየር፣ መሬት፣ ውኃ፣ እሳት እና መሰል ፍጥረታት ወይም ቁሶች ሊሆኑ ሲችሉ፣ እርስ በርሳቸው በመዋሐድ አዲስ ፍጥረትን ሊያስገኙ ይችላሉ፡፡ ወይም የአንዱ ባህሪ በአንዱ ውስጥ ሕልው ሲሆን የሚፈጠረው አዲስ ነገር የነበረውን በሙሉ ወይም በከፊል ሊቀይረው ከቻለ አዲሱ ፍጥረት ከአለ ነገር የተፈጠረ መሆኑን ያትታል፡፡ ይህ የአፈጣጠር ሚት፤ ምድር፣ አየር፣ ውኃ . . .፡፡ በሰማይ፣ በምድር ወይም በባሕር ውስጥ በሚኖረው

መስተጋብር ውሕደት ወይም ግጭት ወይም ለውጥ በሚገኝ አዲስ መፈጠር የሚገኝ ነው፡፡

> *እነዚህ ደግሞ ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ ከተባሉት ከመሬት፣ ከውኃ፣ ከነፋስ እና ከእሳት የተገኙ ናቸው፡፡ . . . "ምድር (መሬት) ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል" ብሎ ባዘዘበት ሰዓት መሬት በእጅ የሚለቀሙ፣ በማጭድ የሚታጨዱ፣ በመጥረቢያ የሚቆረጡ አዝርዕት፣ አትክልትና ዕፅዋትን አስገኘች፡፡ በዚሁ መሠረት ከባሕር ውኃ አደር ፍጥረታት፣ ከመሬት የብስ አደር እንስሳትና የሰው ልጅ ፈጥረዋል፡፡ አስገኘች፡፡ (ስንታየሁና ብርሃኑ፣ 1996 ዓ.ም.)*

ይኽ ግብር እምግብር/ከተፈጠረው የተፈጠረ /ከአለ ነገር መፈጠር በተለይም በክርስትና ሃይማኖት ዕይታ የሰው ልጅ የተሠራበትን ልዩ ልዩ ባሕሪያትም የሚያጠይቅ ነው፡፡ የሰው ልጅ ከእሱ ቀድመው በተፈጠሩ የራሳቸው ልዩ ልዩ ባህሪያት ባላቸው ፍጥረታት እንደተፈጠረ ያስረዳሉ፡፡ " . . . በዚህም መሠረት ሰውን ከምድር አፈር አበጀው ሠራው፡፡ በገቢር (በሥራ) ሰው የሚባለው ፍጥረት ከምድር አፈር ፈጠረው *(ዝኒ ከማሁ፣ 1996 ዓ.ም.)*፡፡

- **ከቤተሰብ መፈጠር**

ይህ ዓይነቱ ሐተታ ተፈጥሯዊ ሚት አንድ ነገር ሲከፈል ወይም ራሱን ሲያበዛ የሚኖረውን የአዲስ ፍጥረት ማንነት የሚያስረዳ ነው፡፡ አዳም ሔዋንን ከአጥንቱ እንዳስገኘ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል፡፡ የሔዋን አመጣጥ አዳም ከወሰደው ከባድ እንቅልፍ ውስጥ፣ ከግራ ጎኑ በተወሰደ አንድ አጥንት እንደሆነም ያስረዳል፡፡ አስቀድሞ ከነበረው የአዳም አጥንት በተወሰደ አንድ ቅንጣት የሔዋን ሕልውና የተረጋገጠው የአዳም የሥጋ ሁነት ከሁለት ተከፍሎ መሆኑን ያስረግጣል፡፡ በመሆኑም አንዱ አካል አዳም ተከፍሎ ሔዋን እንደተፈጠረች መረዳት ቀላል ነው፡፡ ሥነ ፍጥረት በተሰኘው መጽሐፍ ላይ የሔዋንን የአዳም መገኘት፣ አፈጣጠርን እንዲህ ይገልጸዋል፡፡

> *. . . በዚህም ውሳኔ መሠረት ረዳት ይፈጥርለት ዘንድ በአዳም ላይ እንቅልፍ ጣለበት፡፡ እጅግም ሳያንቀላፋ፣ እጅግም ሳይነቃ በመንቃትና በማንቀላፋት መካከል ሳለ ከጎኑ አንዲት አጥንት ወስዶ ያቺን የወሰዳትን አጥንት ሙሉ አካል አድርጎ፣ በነፍስም በሥጋም መገኛዋ አዳምን አሳክሎ፣ አስመስሎ፣ በተፈጥሮ ጠባይ ከአዳም ሳያሳንሳት በአስራ አምስት ዓመት ቆንጆ መጠን ፈጠራት፡ ፡ ፈጠራት ሲባልም እንግዳ ፍጥረት ማስገኘት ሳይሆን በአዳም*

አካል የነበረችው ሔዋን በሕልውና እንድትገለጥ አደረጋት ማለት ነው፡፡ (ስንታየሁና ብርሃኑ፣ 199 6ዓ.ም.)፡፡

በተመሳሳይም በባቢሎናውያን ሚት የጀግንነት አምላክ የሆነው ማርዱክ፣ ቲያማት የተሰኘችውን የመጀመሪያዋን እናት ጭራቅ አሸንፎ የነበረውን ምስቅልቅል መልክ እዳስያዘው ይተርካል፡፡ ማርዱክ የመጀመሪያ የሆነችውን ጭራቅ ካሸነፈ በኋላ ሰውነቷን ከሁለት ሰንጥቆ አንደኛውን ክፍል ገነት አንደኛው ክፍል ደግሞ መሬት እንዳደረገው ያትታል፡፡ (Lemming፣ 2010፣ 17) የቤተሰብ የመፈጠር ሚት ከአንድን አካል ስለመከፈል ማንንትና አፈጣጠር ሲያስረዳ አንዱ አካል ከሁለት እንዲከፈል የሚያደርግ ወይም የሚፈጥር አንድ ኃይል ወይም ፈጣሪ እንዳለ ያትታል፡፡

### 2.1.2.2 መንፈሳዊ ሚት

መንፈሳዊ ሚት ከሚት ዓይነቶች አንዱ ሲሆን፤ እንደ Lemming ገለጻ መንፈሳዊ ሚት፣ መንፈሳዊ ኃይላት በአንድ ማኅበረሰብ ዘር ቅጥልጥሎሽ ወይም የአንድ ቤተሰብ ታሪካዊ አመጣጥ ላይ መንፈሳዊ ኃይላት ያላቸውን ሚና የሚያሳይ ነው፡፡ (Lemming 2002፣ 76)፡፡ ሚቶቹ መደበኛ በሆኑ እና ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት አግኝተው፣ በዘመን እና በጊዜ ሂደት ሊቀየር፣ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ በማይችለው ዶግማና እና እንደየ ጊዜው፣ እንደየ ሃይማኖቱ መሪዎች ፈቃድ ሊለወጥ፣ ሊሻሻል እና ሊስተካከል በሚችለው ቀኖና በተሳሰሩ ሃይማኖቶችም ይሁን፣ ቋሚ ዶግማና ቀኖና በሌላቸው ሀገረሰባዊ እምነቶች አስተምህሮቶች ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ ዋና ትረካቸው መንፈሳዊ ኃይላት በእምነቱ እና በአማኙ ዙሪያ ያላቸውን ሚና እና ስለ እነሱም የሚታመነውን ነገረ እምነት የሚያስረዳ ነው፡፡

በክርስትና እና በእስልምና እምነት አስተምህሮ ውስጥ የእግዚአብሔር እና የአላህ ማንነት እና ሚና ባሕሪያቸው የሚገለጥበት ትረካዎች የሚጠቃለሉት በዚህ የሚት ምድብ ውስጥ ነው፡፡ የእግዚአብሔር አንድነት እና ሦስትነት፣ የሚገለጸው በዚህ ዘርፍ ነው፡፡ እግዚአብሔር በአካል፣ በስም፣ በግብር … አንድ ነው፤ በመለኮት፣ በአገዛዝ፣ በስልጣን፣ ይህንን ዓለም በመፍጠር፣ በማሳለፍ፣ በምልአት፣ በምጥቀት፣ በርቅቀት፣… አንድ ነው የሚለው አንድምታ የክርስትና ዶግማ ውስጥ

የእግዚአብሔር ባሕሪይ መገለጫ ነው፡፡ አላህ አንድ ነው፡፡ አይወልድም፣ አይወለድም፣... ደግሞ የእስልምና ሃይማኖት ዶግማ የአላህን ባሕሪይ የሚገልጽበት ነው፡፡

በሲዳማ ነባር እምነት ሲዳማዎችን የፈጠረው ማጋኖ ነው፡፡ ማጋኖ የሰውን ልጅ ከአፈር መፍጠሩን፣ ሰውም በምድርም ላይ ሲኖር ሁሉ ተሟልቶለት፣ ያለድካምና ልፋት፣ እንዲኖር መደረጉን እና በራሱ በሰው ያልተገባ ሥራ ተረግሞ በልፋቱ እና በድካሙ እንዲኖር መደረጉን የሚቀጥለው ትረካ ያስረዳል፡ ፡

> *ማጋኖ ሰውን ከአፈር/ቡሻ/ ፈጥሯል፡፡ በዚህ አንጻር ባቶ/ምድር አፈር በመስጠቷ በሰው ፍጥረት ላይ ድርሻ አላት፡፡ ስለዚህም አንድ ተአምራዊ ነገር የተፈጠመ እንደሆነ ማጋኖ ጉኡ ባቶ ዲሚቶ/እግዚኦ አምላክ ምድርም ትርጋ/ ይላሉ፡፡ ማጋኖ ሰውን ከፈጠረ በኋላ በምቾት እንዲኖር አዝዞት ነበር፡፡ ነገር ግን ሰው የማጋኖን ትዕዛዝ በመጣስ፣ ወደ ችግር እና ልፋት ውስጥ ገብቷል፡ ፡ የጥንት ሰዎች ገንዘብ ሳያዋጡ፣ ጉልበት ሳያፈሱ የፈለጉትን ሁሉ ያገኙ ነበር፡፡ ለሚያገኙት ሁሉ "አቶቴ"/በረከት ነበረው፡፡ እንደዛሬ ልፋት አልነበረም፡፡ ስለዚህ ውኃ ወይም የማገዶ እንጨት ሲያስፈልግ፣ የሰው እጅ ሳይነካው እስከቤት ድረስ ይመጣ ነበር፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ከእለታት አንድ ቀን አንዲት ሴት ባሪያ ወደጫካ ሂዳ ደረቅ አንጨት ሰብስባ ስላመጣች ማጋኖ ተቆጥቶ፤ ሰው ከምቾት ይልቅ ድካም መርጧልና ከእንግዲህ ከልፋቱ ይብላ ብሎ በማዘዙ ለሰው ልጅ ምቾትና መንደላቀቅ ቀርቶበታል፡፡ (ቤታና ሆጤሶ፣ 1983፣ 115)*

የክርስትና እምነት እንደሚያስረዳው እግዚአብሔር አምላክ ከሙሴ ጋር ቃል በቃል ተነጋግሯል፡፡ እንዲሆን የሚፈልገውን እየነገረው፣ ሕዝቡ በሥርዓትና በሕግ እንዲመራ፣ የአምልኮ ሥርዓቱንም በመቃኘት አሥርቱን ትዕዛዛት ጭምር ሰጥቶታል፡፡ አብሯቸው እንደሆነው ሁሉ ሲያጠፉ ተለይቷቸዋል፡፡ በዚህም ኃይላቸው ደክሟል፣ ለስደት፣ ለሞትና ለባርነት ተዳርገዋል፡፡ ጭራሽ ከሃይማኖታዊው መንገድ እና ከአምልኮ ርቀው ክፉ ሥራቸው ባየለ ጊዜ ፈጽመው ለጠላቶቻቸው ተላልፈው ተሰጥተው አጥር ቅጥራቸው ፈርሶ፣ ከሀገራቸው ተሰድደው ለባርነት ተዳርገዋል፡፡ እስራኤላውያን ከፈጣሪያቸው መንገድ ብዙ ጊዜ ርቀው ብዙ ጊዜ ለጠላቶቻቸው ተላልፈው እንደተሰጡ መጽሐፍ ቅዱስ በሚከተለው መልክ ይገልጻል፡፡

> *የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ፣ በፍልስጤማውያ እና በአሞን ልጆች እጅ አሳልፎ ሰጣቸው (መሳ፣ 10፣7) . . . የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ ሥራን ሠሩ፣ እግዚአብሔርም በፍልስጤማውያን አርባ ዓመት አሳልፎ ሰጣቸው፡ ፡ (ማሳ፣ 13፣ 1) . . . አምላካቸው እግዚአብሔርን ረሱ፤ ለአሶር ሠራዊትም አለቃ ለሲሣራ እጅ፣ ለፍልስጤማውያንም እጅ፣ ለሞአብም ንጉሥ እጅ አሳልፎ ሰጣቸው (ሣሙ.ቀ፣ 12 ፣ 9)፡፡*

እንደ እስራኤላውያን ሁሉ የሀገራችን የሲዳማ ብሔረሰብ አባላት እላካቸው “ማጋኖ”ን በማስቀየማቸው እንደተረገሙ ሁሉ፣ ለሰው የምታገለግለው በቅሎ በሠራችው ጥፋት አምላካቸው ተለይቷቸው ቃል በቃል ያገኙት ያወሩት የነበረው አምላክ ርቋቸዋል፡፡ ቤታና ሆጤሶ ሚታዊ ትረካውን ከዚህ በታች ባለው መልኩ አስፍሮታል፡፡

> *ከዚህ ሌላ ያን ጊዜ ማጋኖ ቅርብ ስለነበር በየቀኑ ከሰዎች ጋር ይነጋገር ነበር፡፡ ሆኖም ከእለታት አንድ ቀን በቅሎ አንጣጥ ብላ “ማጋኖ”ን ስለረገጠችው ተቆጣና ከሰው ተለይቶ ሄደ፣ ሲሄድም እንዳትውልድ ርጉት ስለሄደ በቅሎ እስከዛሬ አትወልድም ይላሉ፡ ፡ በእነዚህ እና በመሳሰሉት ምክንያች ማጋኖ ርቆ ስለሄደ፣ የሰው ልጅ ብዙ ችግር ደርሶበታል፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳን ማጋኖ ከሁሉ በላይ ፈጣሪ ቢሆንም ከሰው ርቆ ስለሄደ ሰው ሌሎችን ማለትም የሚቀርቡትንና ያማልዱኛል ብሎ የሚያምናቸውን ማምለክ ግድ ሆኖበታል፡፡ (ቤታና ሆጤሶ፣ 1983፣ 115)*

እንደ እስራኤላውያን እና እንደሲዳማ ሕዝብ ሁሉ የመኤኒት ብሔረሰብም አምላኩን “ቱማ” በሰላምና በተድላ ሲያኖረው ቆይቶ በሠራው ክፉ ሥራ አምላክ ቱማም ተቆጥቶ ስለተለያቸው ከመልካሙና ከለምለሙ ምድራቸው ላይ ርሀብ ገብቶ የብሔረሰቡ አባላት ለስደት ተዳርገዋል፡፡ በአጠቃላይ በተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችም የተለያዩ የመንፈሳዊ ሚት ትረካዎች ይቀርባሉ፡፡

### 2.1.2.3 የመስተጋድላውያን ሚት

የቃሉን ፍቺ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ “መስተጋድል፤ (ልት፣ ላን፣ ላት)፣ የሚጋደል.፣ የሚታገል፣ ተጋዳሊ” (ኪዳነወልድ፣ 1948፣ 597 ዓ.ም.) በማለት ይፈቱታል፡፡ የመስተጋድላውያን ሚት ሲባልም የእነዚህኑ መስተጋድላውያን ታሪክና ተጋድሎ የሚተርክ ነው፡፡ ይህ የመስተጋድላውያን ሚት በሁለት ዓይነት

ሊከፈሉ የሚችሉ ሲሆን አንደኛው መንፈሳዊ መስተጋድላውያን ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ የባሕል መስተጋድላውያን ናቸው፡፡

መንፈሳዊ መስተጋድላውያን ሚት በአንድ ሃይማኖታዊ፣ ወይም እምነታዊ ሥርዓት መፈጠር፣ አስተምህሮ፣ ስርጭት፣ ሂደትና ተጋድሎ ዙሪያ የሚያጠነጥን ሲሆን፤ ለዚሁ አፈጣጠር፣ አስተምህሮ፣ ስርጭትና ተጋድሎ ድርሻ ስላላቸው አካላት የሚያትት ነው፡፡ እነዚህ አካላት በአንድም ይሁን በሌላ መልክ ለሃይማኖቱ ወይም እምነቱ ልዩ ልዩ አስደናቂ እና ታላላቅ ገድላትና ተአምራትን የሚፈጽሙ ሲሆን፣ የተአምራታቸውና የገድላቸውን ታላቅነት የሚፈጽሙት አንድም ሰው ከመሆን በሚያገኙት ታላላቅ ጥንካሬ እና ተሞክሮ፣ አንድም ልዩ ኃይላት በሚያቀዳጇቸውና በሚያጎናጽፏቸው ኃይል ደጋፊነት፣ አንድም ደግሞ ባህሪያቸው ከልዕለ ኃያላን ጋር የተካፋይነት ድርሻ ስላላቸው እና ከፊል ሰው ከፊል የታላቅ ኃይል ባለቤትና መናፍስት ስለሆኑ ጭምር ነው፡፡

Bryant "አብዛኞቹ ሚቶች ስለ አማልዕክት እንዲሁም ከተራው ሰው የተለየ ትልቅ ጉልበት እና ኃይል ስላላቸው ሰዎች ይተርካሉ፡፡" Bryant /2009 / ሲሉ Campbell ሚቶች "የኅብረተሰቡን ችግሮች ለመፍታት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው ግለሰቦች ወይም መንፈሳዊ አካላት በሕይወት ዘመናቸው የፈጸሟቸውን መስዋዕት፣ ገድላትና ተአምራት የሚገልጹ ናቸው" Campbell (2004) በማለት ይገልጻሉ፡፡ Bryantም ይሁን Campbell እንደሚገልጹት ከተራው ሰው የተለየ ጉልበትና ኃይል ያላቸው የኅብረተሰብን ችግር ለመፍታት ገድላትና ተአምራትን የሚያከናውኑት መስተጋድላውያን ተብለው የተሰየሙት፣ ጀግና ሆነው የሚታወሱትን ነው፡፡

Lemming የታላላቅ ሃይማኖት መሥራቾችን ለምሳሌም ኢየሱስ ክርስቶስን፣ ነቢዩ ሙሐመድን እና ሌሎችንም በመስተጋድላውያ ሚት ሥር ይመድቧቸዋል፡፡ በመስተጋድላውያን ሚት ምዳቤ ውስጥ ገድላቸው ወይም ተጋድሏቸው፣ ተአምራታቸው ወይም ድንቃቸው የሚነገርላቸው ሰዎች ወይም መንፈሳዊ አካላት ላሉበት ሃይማኖት መታነጽ፣ መጽናት እና ማደግ አበርክቷቸው ሰፊና ጥልቅ እንደሆነም ይገልጻሉ (Lemming 1998)፡፡

ሁለተኛው እና በመስተጋድላውያን ሚት ሥር የሚታቀፈው የሚት ዓይነት የባሕል መስተጋድላውያን ሚት ነው፡፡ ይህ የሚት ዓይነት ትኩረቱን የሚያደርገው ባሕል ነክ ጉዳዮች ላይ የሚነገሩ የተጋድሎ ታሪኮችን ላይ ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ ሚት በአንድ ባሕል ወይም የተለየ አካባቢ ባሉ የማኅበረሰብ አባላት ውስጥ የሚገኙ መስተጋድላውያን የሠሩትን ሥራ ይተርካል፡፡ የመስተጋድላውያኑ ሥራና የሥራቸውም ውጤት ላሉበት ማኅበረሰብ ባሕል መመሥረት፣ መጽናት፣ ማደግ እና መስፋትም ልዩ አበርክቶ ያላቸው ግለሰቦች ታሪክ የሚተርክ ነው፡፡ (ዝኒ ከማሁ)

በዚህ የሚት ዓይነት ሥር ተጠቃሽ ከሆኑት ውስጥ በታዋቂው የጥቁሮች መብት ተሟጋቹ በማርቲን ሉተር ኪንግ ላይ የሚነገሩ ታሪኮች፣ በምዕራብያኑ ዘንድ በሽብርተኝነት የተፈረጀው እና በዐረቡ ዓለም ደግሞ የፍትሕ መስተጋድል ተደርጎ በሚታየው በኦሳማ ቢንላደን ዙሪያ የሚነገሩ የተጋድሎ ታሪኮች የዚህ ሚት ምሳሌዎች ተደርገው ይጠቀሳሉ፡፡ Lemming ውሸት ተናግሮ አያውቅም የሚባለውን የአሜርካ መሪ ጆርጅ ዋሽንግተንን በዚሁ ምዳቤ ውስጥ ይጠቅሰዋል፡ (Lemming 2002፣ 8)፡፡ በሌላም መልኩ በፖለቲካው ባሕልም ዘርፍም ተጠቃሽ ታሪክ ያበረከቱትን የቻይናውን መሪ ማኦ ዜዱንግ፣ የጀርመኑን አዶልፍ ሒትለር በዚሁ ምዳቤ ሥር ያጠቃልላቸዋል (ዝኒ ከማሁ፣ 22)

ከዚህ አንጻር ይህ የሚት ዓይነት ሰፊ ማዕቀፍ ያለው ባሕል በሚያቅፋቸው ባሕላዊና ፖለቲካዊ ዐውዶች ሥር በሚጠቃለሉ ሁነቶች ላይ የየራሳቸው ተጋድሏዊ ታሪክ ስላላቸው ሰዎች የሚነገሩ ታሪኮች ላይ ያተኩራል፡፡

መስተጋድላውያን ማኅበረሰብ ውስጥ ሲኖሩ የማይታወቁና ከማኅበረሰቡ እንደ አንዱ ሆነው ሊቆዩ ይችላሉ፡፡ እነሱ ወደፊት ለመውጣትና ለመገለጥ አንዳች ጠንካራ ሰብና ምክንያት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በዚያ ምክንያትነት መስተጋድላውያን ወደፊት ይመጣሉ፣ ይታወቃሉ፡፡ ቴዎድሮስ ገብሬ የመታወቂያና የመከሰቻ ምክንያታቸውን እንዲሁም ከተግባራቸው በመነሳትም ያላቸውን ሚና ሲገልጹ "የትኞቹም ዘመናት ተጋዳልያን ወገኖቻቸው በተጨነቁ፣ መከራ በተጫናቸው፣ ታላቅ ቀውስ በነገሰበት ወቅት የሚደርሱ መልዕክተኞች ወይም የሚወለዱ ዳኞች ናቸው" (ቴዎድሮስ፣ 2001፣ 44) በማለት አስፍረዋል፡፡

በዓለማችን ውስጥ የሚኖሩ የተለያዩ ሃይማኖቶች፣ በሕሎችና ዕሴቶች ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዳላቸው የንቃተ ኅሊና ዕድገትና ከፍታ፣ እንደየዘመናቸው ግንዛቤ የየራሳቸው መስተጋድላውያን አላቸው፡፡ ቴዎድሮስ "ሁሉም ዘመን እንደየ ንቃተኅሊናው ደረጃ የሚፈጥረውና እሴቶቹን የሚያኖርበት - ነገሮችን የሚዘልቅበት ወይም/እና የሚቀብርበት አዳዲሶቹን የሚያጸድቅበት የሚያለመልምበት የራሱ ተጋዳሊ አለው፡፡ የየዘመኑ፣ የየትውልዱ ንቃተኅሊና ደረጃ በተጋዳልያኑ ማንነትና በተጋድሏቸው፣ በግባቸው፣ በግባቸው ምንነት መካከል ልዩነት ይፈጥራል" (ዝኒ ከማሁ፣ 44)፡፡

መስተጋድላውያን በሕይወት ዘመናቸው በተለያዩ የሕይወት ምዕራፎች ውስጥ እንደሚያልፉ Campbell በሰፊው የተነተኑ ሲሆን ዋና ዋና የሕይወት ምዕራፎቹ ግን ሦስት መሆናቸውን እና እነሱም አንድ መስተጋድል በደረሰው ጥሪ ሰበብ ከነበረበት ሕይወት እና ዐውድ ውስጥ መነጠል፣ የተመረጠበትን እና የተጠራበትን ዓላማ ለማሳካት መነሳት እና የመጣበትን ዓላማ አሳክቶ መመለስ መሆናቸውን ገልጸዋል Campbell (2004)፡፡

### 2.1.2.4 የዳግም ውልደት ሚት

ይህ ዓይነቱ ሚት ከአፈጣጠር ሚት ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት ያለው የሚት ምድብ ነው፡፡ የአፈጣጠር ሚት ስለሁሉም ነገር አመጣጥ እና ምንጭ የሚተርክ በመሆኑ የአጠቃላይ ኑባሬን ጅማሬን ያጠይቃል፡፡ ጅማሬ ካለ ደግሞ አንድም የሚደረስበት አንድም የማይደረስበት መጨረሻ ይኖረዋል፡፡ የሚደረስበት ከሆነ የታወቀ መነሻ እንዳለው ሁሉ የታወቀ መድረሻ ይኖረዋል፡፡ የማይደረስበት ከሆነ ዘለዓለማዊ ጉዞ ሆኖ የጊዜን ሂደት ያለተጠየቅ ይቀበላል፡፡ የክርስትና እና የእስልምና የአፈጣጠር ሚቶች በአንድ አምላክ ምንጭነት ይሕ ሕዋ እንደመጣ፣ የሰው ልጆችም ከአንድ ምንጭ መቀዳታቸውን ይተርካሉ፡፡ መነሻቸውን እንደሚያሳውቁት ሁሉ መድረሻቸውንምን ያስረግጣሉ፡፡ ዓለም እና ኗሪዎቿ፣ አጠቃላይ የሕዋው መስተጋብር በመጨረሻ ወደ የታወቀ መዳረሻ ይጠቃለላሉ፡፡ አንድም ገሀነመ እሳት፣ አንድም መንግሥተ ሰማይ መዳረሻ ይሆናል፡፡ ይሂም ቀጥተኛን የጊዜ አስተሳሰብ የሚከተል፣ የሰው ልጆችን የምድር አኗኗራቸውን ፈጽመው ወደ ቀጣዩ ዓለም እና አዲስ ወደሆነው ቦታ እንደሚሻገሩ የሚገልጥ ነው፡፡

በሲዳማ ብሔረሰብ እምነት ሞት የመጣው በራሱ በሰው ልጅ ስህተት እንደሆነ የሚከተለው ትረካ ያስረዳል፡፡

> *. . . ከዚያ በፊት ሞት አልነበረም፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ማጋኖ መንገድ ሲሄድ ደከመውና በሰው ተመስሎ አንድ ቤት ገብቶ የሚጠጣ ውኃ ለመነ፡፡ የቤቱ እመቤት ሴትዮ እንግዳውን በማክበር በውኃ ፋንታ ወተት ሰጠችው፡፡ ማጋኖ የጠማኝ ውኃ ነው እንጅ ወተት አይደለም ብሎ ተቆጣና ሳይጠጣ ሄደ፡፡ ቀጥሎ ሲጓዝ ሐማሾ/ የእባብ ቤት ገባና ውኃ ስጡኝ ብሎ ለመነ፡፡ የሐማሾ ባለቤት ብልጥ ነበረችና ይህ ወደቤቷ የገባው እንግዳ ሰው መሆኑ ቀርቶ ማጋኖ ይሆን ይሆናል ብላ ተጠራጠረች፡፡ ማጋኖ ደግሞ ያለውን እንጅ ሌላ ነገር እንደማያደርግ ታውቅ ነበርና ውኃ የለመነው ወተት እንደማይጠጣ ስላወቀች የለመነውን ውኃ ሰጠችው፡፡ ማጋኖ ውኃ ከጠጣ በኋላ የሰው ልጅ ስላልታዘዘው ሞት እንዲሞት ሆኖ የእባብ ልጅ ስለታዘዘው ሞት እንዳይሞት ባማለት ትዕዛዝ ሰጥቶ ሄደ ይባላል፡፡ ትዕዛዙም የሚለው "ማንቿአሬ ሬይቶ ሐማሹ አሬ ሙቶ" ይኸውም የሰው ሚስት ትሙት፣ የእባብ ሚስት ለዘለዓለም ትኑር ማለት ነው፡፡ የሲዳማ ብሔረሰብ ከዚህ የተነሳ ሰው ካልገደለው በስተቀር እባብ አይሞትም ብለው ያምናሉ፡፡ ከረጅም ቅርፊቱ ሲሞላቀቅ እንደገና ወጣት ሆኖ ይወጣል፡፡ እንዲህ እየሆነ ለዘለዓለም ይኖራል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ "ሐማሾ ሙጣኖ" ቢባል፣ እባብ ተመልሶ ወጣት እየሆነ ለዘለዓለም ይኖራል ማለት ነው፡፡ (ቤታና ሆጤሶ፣ 1983 ዓ.ም፣ 15)*

ከዚህ ቃል ትረካ በመነሳት እና ሰው ካልገደለው በቀር የእባብን ዘላለማዊ ኗሪነት ትረካ በመረዳት፣ በሲዳማ ብሔረሰብ እምነት የጊዜ እሳቤ ቀጥተኛ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ትረካው ከሞት በኋላ ያለውም ሕይወት የሚቀጥለው በምድር ላይ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ የሰው ልጅ መወለድ እና መሞት ሁለት የማይነጣጠሉ ክስተቶች ሆነው ዘመናትን ኖረዋል፡፡ ሞት የሰው ልጅ ሁሉ እጣፋንታ እንደሆነም ይታመናል፡፡ የዚያኑ ያህል ከሞት በኋላ ዳግም ሕይወት መቀጠሉን የሚያምኑና ተስፋ የሚያደርጉ ብዙዎች ናቸው፡፡ "For most of humanity, the moment when linear time stops is at death. All mythologies hold out the hope that was so dear to the initiates of Eleusis, that there may be a new life beyond this one." (Philip፣ 2007, 10)፡፡ የዚያኑ ያህል የሰው ልጆች እንዳላቸው እሳቤ እና ትርጓሜ ለድግመ ውልደት እና ለድግም ሕይወት ጅማሬም የተለያየ እሳቤ አላቸው፡፡ መሞት እንዳለ ሁሉ አዲስ ሕይወት እንደሚኖር ይታመናል፡፡ የጥንት ግብጻውያን ስለ

ዳግም ውልደት ያላቸውን እሳቤ Neil Philip እንዲህ አስፍረውታል፡፡ "The Egyptians hoped to be reborn to live a new life in the Field of Reeds, which was a perfected version of the Egypt they knew." (Neil Philip፣ 2007, 10)፡፡

የዳግም ሕይወት መቀጠልን ከአንድ የተወሰነ ቦታ ጋር አያይዘው የሚያምኑ ሕዝቦችም አሉ፡፡ የግህዱን ዓለም ሕይወት በሞት ተሰናብተው ከሄዱ በኋላ ወደዚያ ስፍራ ለመድረስ ብዙ ጥረት አድርገው አዲስ ሕይወት የሚጀምሩበትን እድል እንደሚያገኙ ይታመናል፡፡ የጓራዩ ሕንዳውያን ከሞት በኋላ ስላለው የነፍስ ጉዞ ይናገራሉ፡፡ ከሞት በኋላ ነፍስ በምዕራብ በኩል ወደሚገኘው የቀዳሚ ሟች ዘሮቻቸው መኖሪያ ወደ ታሞይ ለመድረስ የሁለት መንገዶች ምርጫ እንደሚገጥማቸው ያምናሉ፡፡ አንደኛው ሰፊ እና ቀላል፣ ሌላኛው ጠባብ እና አደገኛ ነው፡፡ ነፍስ በቅድመ አያቶቿ መኖሪያ ከደረሰች በኋላ ስለሚያጋጥማት ሁኔታ Philip ሲገልጹ "ነፍስ ከመድረሷ በፊት ከባዱን መንገድ መምረጥ እና ብዙ ፈተናዎችን ማሸነፍ አለባት፡፡ አንዴ በአያቶቻቸው መኖሪያ ከደረሰች በኋላ በዚያ በሚገኘው መታጠቢያ ውስጥ ትታጠባለች፡፡ ከዚህ በኋላ ነፍስ እንደገና ወጣት ትሆናለች፡፡ እናም በምዕራብ ምድር እንደገና መሳቅ፣ ማደን፣ መኖር እና መውደድ ይችላል" (Neil Philip፣ 2007, 11)፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ አባላትም የሟች ነፍስ ምድር ላይ ወዳለው፣ የቀድሞ አያት ቅድመ አያቶች መኖሪያ መንደር ሞኡ እንደምትጓዝ በዚህ ጥናት ውስጥ ተገልጽዋል፡፡

በሁለተኛው ምድብ ውስጥ የሚገኘው ከታወቀው እና ከታመነው ዓለም ውጭ የሚቀጥል ሌላ ዓለም አለመኖሩ እና የሰው ልጆችም በዚሁ ዓለም ውስጥ ከመላው ሕዋ ጋር ባላቸው መስተጋብር ውስጥ ተፈጥሯዊ የሰውነት ባህሪያቸውን በመቀየር፣ የሌላ ፍጥረት ባሕሪን ተላብሰው የመከሰታቸው አስተሳሰብ ነው፡፡ ይህኛው የዳግም ሕይወት አስተሳሰብ የጊዜ እሳቤን ሉላዊ ወይም ዞሮ ገጣሚ ያደርገዋል፡፡ መነሻውም ይሁን መድረሻው አንድ ቦታ እንደሆነ እና እንደጀመረ ይጨርሳል፣ ሲጨርስ መልሶ ይጀምራል፡፡

በሩቅ ምሥራቅ መሠረቱን የጣለው የሒንዱይዝም አስተምህሮ የጊዜን እሳቤ የሚረዳበት መንገድ እንደ ክርስትና እና እስልምና እምነት ዓይነት ቀጥተኛ ጉዞን አይደለም፡፡ የሒንዱይዝም የእምነት አስተምህሮ የጊዜ እሳቤን የሚረዳው በሉላዊነት ወይም ክባዊነት ነው፡፡ ከሞት በኋላ ሕይወት የሚቀጥለው ሰው እንደ ሥራው በሚሰጠው ፍርድ ቢሆንም፣ የሚፈጠመው ከዚህ ዓለም ውጪ በተዘጋጀለት የመጽደቂያ እና የመቃጠያ ቦታ ሳይሆን እዚሁ ነው፡፡ አንድ ሰው መልካም ከሰራ መልካም ናቸው ተብሎ ወደሚታሰቡት እንስሳትነት ይለወጣል፡፡ የሟች ነፍስ ላም ወይም በሬ በመሆን ነፍስ አዲስ ኑረቷን ትቀጥላለች፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የዘለዓለማዊነት የጊዜ እሳቤ ሉላዊ ወይም ክባዊ ነው፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያም የዚህን ዓይነት የጊዜ እሳቤ ያላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች አሉ፡፡ ባይለየኝ ጣሰው ከእነዚህ የሀገራችን ክፍሎች ውስጥ በጋምቤላ ክልል የሚኖሩት የአኝዋ/አኝዋክ ብሔረሰቦች ጊዜን የሚረዱበትን እና ከሞት በኋላ ያለውን ሕይወት ሲገልጽ በአኝዋክ አንድ ሰው ሲሞት ነፍሱ በአካባቢው ወዳለው ወንዝ ሄዳ ትሰፍፋለች፡፡ ይህች የሟች ነፍስ ከዚያ በኋላ ዳግም የሕይወት ዑደቷን ለመቀጠል ላም፣ ወይም በሬ፣ ወይም ሌላ እንስሳ በመሆን ድጋሚ ትመጣለች (ባይለየኝ፣ 1999)፡፡

### 2.1.3 የሚት ባህሪያት

ባህሪ የአንድ ነገር ተፈጥሯዊ መሠረት ነው፡፡ የአንድ ተገላጭ ሁነኛ መልክ የሚመነጨው ከዚሁ ከባህሪው ነው፡፡ የአንድን ጽንሰ ሐሳብ ትርጓሜ ለመስጠት ከሚጠቀሙት መንገዶች ዋንኛው ስለ ጽንሰ-ሐሳቡ ተፈጥሯዊ ባህሪያት በቅጡ መገንዘብና መረዳት ነው፡፡ ሚትንም ለመረዳት ያሉትን ልዩ ልዩ ባህሪያት ማወቅም እንዲሁ ዋና ጉዳይ ነው፡፡ Bryant, ሚቶች፣ ስለ አማልዕክት፣ ስለ ልዕለ- ተፈጥሯዊ ኃይላት፣ ስለዓለም አፈጣጠርና ስለ ሰዎች አመጣጥ የማብራራት እና የቅዱሳዊነት ባሕሪይ እንዳላቸው እና ይሄው ባህሪም በተናጠል ወይም በመደራረብ ሊታይ እንደሚችል ያብራራሉ፡፡ (Bryant, 2009)፡፡

የእምነት ሚት ዋና ባህሪያት ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር መደበኛም ሆነ መደበኛ ያልሆነ እምነት በዚህ ስር የሚጠቃለል በመሆኑና ሚት ከሃይማኖት ጋር ባለው ቀጥተኛ መስተጋብር ሃይማኖታዊነት የሚት አንዱ

ባህሪው ነው፡፡ ሃይማኖቶች ለሚያምኑባቸው ማኅበረሰብ ካላቸው ክብር እና መታመን አንጻር፣ በአማኙ ዘንድ ቅዱስ ተደርገው ይታመናሉ፡፡ በዚህም መነሻነት ቅዱሳዊነት የሚት ሌላው ባህሪ ነው፡፡ ይሁን እንጅ እንደየ ማኅበረሰቡ የእውቀት ደረጃ እና ንቃተ ኅሊና የሚለያዩ አስተሳሰቦች በቦታ፣ በዘመን እንዲሁም በሌሎች ጉዳዮች በመኖራቸው አንዱ የተቀበለው እና በቅዱስነት የሚያምነው ሚት ለሌላው ፍሬ ፈርስኪ ወይም የማይታመን ሊሆን ይችላል፡፡ የሚቱ ቅድስና መለኪያው የኔ ነው ብሎ የተቀበለው ማኅበረሰብ እምነት በመሆኑ የሌላው አስተያየት እና አረዳድ ምንም የሚፈጥረው ነገር አይኖርም፡፡

እያንዳንዱ ሚት ለባለታሪኩ ቅድስና ያለው በመሆኑና በዚህ የቅድስና ባህሪውም መሠረትነት ለባለታሪኩ ማኅበረሰብ እውነትትን ስለሚያጎናጽፈው እያንዳንዱ ሚት እውነት እንደሆነም ይታመናል፡፡ ባለታሪኩ ማኅበረሰብ ሚቱን ሳይጠራጠርና ማስረጃ ሳያስፈልገው እውነት እንደሆነ በእምነት ይቀበለዋል፡፡ በዚህም ምክንያትነት የሚት ሌላው ባህሪ እውነት ነው ተብሎ ተቀባይነት ማግኘቱ ስለሆነ፣ እውነት የሚት ሌላው ባህሪ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሚቶች ስለ ዓለም አፈጣጠር እና ስለሰው ልጅ አመጣጥ የሚተርኩ፤ ስለ ፈጣሪ፣ ስለ ፍጥረት፣ ስለማንነትና ስለ ዕጣ ፈንታም የሚታተትባቸው በመሆናቸው እንዲሁም የሰውን ልጅ ዘለዓለማዊ ጥያቄዎች በመመለሳቸው በቃል ትረካ ሲተላለፉ የመጡ መሆናቸው ቃላዊነት ሌላው ባህሪቸው ነው፡፡ Bryant, "አብዛኞቹ ሚቶች ስለ አማልዕክት እንዲሁም ከተራው ሰው የተለየ ትልቅ ጉልበት እና ኃይል ስላላቸው ሰዎች ይተርካሉ፡፡ ሚቶች ስለዓለም አፈጣጠር እና ስለ ሰዎች አመጣጥ ያብራራሉ፡፡ አብዛኛው ሚቶች ምንም እንኳን ሌላው የማይታመኑ እና የፈጠራ ቢመስሉም ለሚናገረው ማኅበረሰብ ግን እውነትነት አላቸው" (Bryant, 2009) በማለት ሀሳቡን ያጸናሉ፡፡ ሚቶች ስለአማልዕክት እና ከፊል ሰው ከፊል አማልዕክት ስለሆኑም ስለሚገልጹ፣ በትረካቸው ውስጥ ምንም ዓይነት የጊዜ እና የቦታ ገደብ የሌላቸው ናቸው፡፡ በሚት እሳቤ ውስጥ የማይሆነው ይሆናል፣ የማይቻለው ይቻላል፣ ከዚህም አንጻር ገደብ የለሽነት ሌላው የሚት ባህሪ ነው፡፡

### 2.1.4 የሚት ሚና

ስለሚት ተግባርና ፋይዳ ሲነሳ ተያይዞ የሚነሳ አጠቃላይ እውነታ አለ፡፡ እሱም ሚት የስነ ቃል አንዱ ክፍል መሆኑ እና ስነ ቃል ደግሞ በፎክሎር ሥር

ከሚታቀፉ ዘርፎች ውስጥ አንዱ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በማኅበረሰቡ ውስጥ በሚጫወቱት ሚና አንዱ በአንዱ ውስጥ ተገልጠው ይታያሉ፡፡ ፈቃደ አዘዘ Allen Dundesን ጠቅሰው ፎክሎር የሚያጠቃልላቸውን እና በስሩ የሚይዛቸውን ክፍሎች እንደሚከተለው ዘርዝረዋል፡፡ “ፎክሎር የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡ “ሚቶች፣ ሌጀንዶች፣ ተረቶች፣ ቀልዶች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ እንጉርጉሮዎች፣ ድግምቶች፣ ምርቃቶች . . . ዓመት በዓሎች (ገናአረፋ፣ ጥምቀት፣ ፋሲካ፣ መውሊድ)፣ ድግሶች፣ የዕረፍት ቀኖች፣ የድል በዓል፣ የልደት በዓል” (ፈቃደ፣ 1991፣ 4)፡፡

ስለሚት ፋይዳ ሲነሳ አንዳንዴ የስነ ቃል ዘሮች በሆኑ በተለያዩ ዘውጎች ውስጥ ተመሳሳይ ሚናዎች ሊገኙ ይችላሉ፡፡ ይህ ከፎክሎር ባህሪያት አንዱ መገለጫ ነው፡፡ በገድል ውስጥ ያለው ሚና በሚት ውስጥ ሊታይ ይችላል፣ በተረት ውስጥ የታየው ተግባር በቃል ግጥም ውስጥ ሊከሰት ይችላል፡፡ ፈቃደ የስነ ቃል ተግባራትን በአምስት ዐበይት ክፍሎች ከፍሎ ማየት እንደሚቻል ገልጸውና እነሱም “የመግለጥ ተግባር፣ የማጠናከርና የመትከል ተግባር፣ የማምለጭ[2] ተግባር፣ የማስተማር ተግባር እና የመግታት- የመቆጣጠር ተግባር እንደሆኑ አስፍረው ስለእያንንዳንዳቸውም ተግባር በዝርዝር የሚከተለውን አስፍረዋል፡፡

> *የመግለጥ ተግባር፣ ገላጭ ትረካዎች በአካባቢው ለሚኖሩ ሰዎች መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሚሞክሩ ናቸው፡፡ አካባቢያቸውን፣ ሰውን፣ እንስሳትን፣ ዕፅዋትን ማን ፈጠራቸው እያሉ ለሚጠይቋቸው ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሞክራሉ፡፡ . . . ባጠቃላይ አነጋገር ፍቺ አልሰጥ ብሎ እንቆቅልሻዊ እና አስፈሪ ሆኖ ላስቸገራቸው ዩኒቨርሱ የሰው ልጅ መልክና ፍቺ ይሰጠዋል፡፡ በዚህም ለአካባቢው መጠነኛ ሥርዓት ያበጃል፣ ኀሊናውም አንጻራዊ መረጋጋትን ያገኛል፡፡*
>
> *የማጠናከር፣ የመትከል ተግባር፣ . . . ማኅበራዊ ድርጅቶቻቸውን እና ልዩ ልዩ ባህሎቻቸውን በስነቃል አማካይነት ያጠናክራሉ፡፡ ከልደት እስከ ሞት የሚያከናውኗቸውን ድርጊቶች አስፈላጊነትና ተገቢነት እያሳመኑ ክዋኔዎቹ እንዳይከስሙ፣ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ፡፡ . . . የጀግንነት፣ የቆራጥነት፣ የፅኑ እምነት፣ የታጋይነት ወዘተ ... ትዕምርት (symbol) አድርገው በመሳል አርአያነታቸውን ዘላለማዊ ለማድረግ ይሞከራል፡፡*

---

[2] *በፈቃደ አዘዘ አገላለጽ ሲሆን፣ ማምለጥ የሚለው አቻ ትርጉሙ ይሆናል፡፡*

*የማምለጥ ተግባር፤ የሰው ልጅ ከወትሮአዊው የዕለት ተዕለት ህይወት ውጣ ውረድ ማምለጥ ይፈልጋል፡፡ . . . እንግዳ ዓለም ውስጥ ገብቶ የጀግኔውን (የheroውን) ሳቅና ፈንጠዝያ እየተጋራ በምናቡ አዲስ ገጠመኝ ውስጥ ይኖራል ማለት ነው፡፡*

*የማስተማር ተግባር፤ በተለይ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ፋቡላዎች፣ . . . የአኗኗር ሥርዓትን፣ ምግባርና ብልሃት ያስተምራሉ፡፡ . . . በህይወት ውስጥ የትጋትን፣ የለጋስነትን፣ የኅብረትን ጥቅም አጥብቀው ይሰብካሉ፡፡ የልጆችንና የወጣቶችን ባህርይ ከና ከለጋነታቸው ለመቅረጽ ያገለግላሉ፡፡*

*የመግታት፣ የመቆጣጠር ትግባር፤ ... እሴቶች በልዩ ልዩ የስነ ቃል ቅርፆች የሚቀረጹት እና የሚነገሩትም እንደተግባራዊ የህይወት መመሪያ እንዲያገለግሉ ነው፡፡ በአንዳንድ ቦታም እንደ እውነተኛ ታሪክ ሲቆጠሩ ይታያል፡፡ ዓለማቸው አንደ ጎሳ ወይም ማኅበረሰብ በተለምዶ የሚከተላቸውን የአኗኗር ልምዶችና ይትበሀሎች ግለሰቡ እንዲከተል ማድረግ ላይ ቢሆኑም በተለይ የሚያነጣጥሩት ዒላማ (target) ግን አላቸው፡፡ ያም ማኅበሩ ምስጉን እና ድንቅ ከሚላቸው እሴቶች የሚያፈነግጡትን ወይም ለማፈንገጥ ገና ዳር ዳር የሚሉትን በ"አርፌህ ተቀመጥ" ግሳፄ ወደ ብዙኀኑ አስተሳሰብ መመለስ ነው (ፈ.ቃደ፣ 1991፣ 16 - 21)፡፡*

ሚት በአንድ ግለሰብ ወይም በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ የተለያዩ ሚናዎችን ይጫወታል፡፡ ከግለሰብ እና ከማኅበረሰብ ባሻገርም እንደሀገርም የሚጫወታቸው ሚናዎች የጎሉ ናቸው፡፡ Brown, ቀደምት የተሠሩ ጥናቶችን መሠረት በማድረግ የሚትን ጠቀሜታ በአራት መንገድ ከፍለው አስፍረዋል፡፡ እነሱም ውስጥ አንደኛ፣ ሚቶች እምነቶችን፣ አመለካከቶችን፣ እሴቶችን፤ ለማረጋገጥ፣ ለማሳደግ እና ለማጠንከር ይጠቅማሉ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ሚቶች እውነታን ለመሸሽ መጠቀማቸው ሲሆን፣ ሁለተኛው ሀሳባዊ የሆኑ ነገሮችን አዕምሯችን ውስጥ በመፍጠር እውነታውን እንድንሸሽ መጥቀሙ በዚህም አንድን የሕይወት ክፍል በማጉላት ሌላውን እንዲረሳ መንገድ መፍጠራቸው ነው፡፡ (Brown, 2004, 277)፡፡

የአንድ ማኅበረሰብ መነሻው ግለሰብ ነው፡፡ ግለሰቦች በሚመሠርቱት የጋራ ተቋም ቤተሰብ እና ማኅበረሰብ እንደ ደረጃቸው ይመሠረታሉ፡፡ ሁለቱም ጸንተው እንዲቆዩ ሰዎች የጋራ በሆኑ ፍላጎቶቻቸው ላይ በጋራ እንዲኖሩ ለማስቻል የሚቶች ሚና ዋንኛ ነው፡፡ ሚት አንድነት ለማምጣት፣ የሕይወት መስተጋብር ተሳልጦ እንዲጓዝ፣ የጋራና ተቀባይነት ያለው መዋቅርን በመፍጠር

የተለያዩ ማኅበረሰቦችን አንድ በማድረግ፣ ማኅበረሰባዊ መዋቅርን በመገንባትም ሚናው ሰፊ መሆኑን Brown እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡

> *ሦስተኛው የሚቶች ፋይዳ ሚቶች የተለያዩ የኀብተረሰብ ክፍሎችን አንድ የማድረግ ፋይዳቸው ነው፡፡ ምክንያቱም የሚቶቹ ትረካዎች፣ ነጻነትን፣ አለመገዛትን እና የሀገር ፍቅርን ያስተላልፋሉ፡፡ የማኀበረሰቡ ሚቶች በእያንዳንዱ ውስጥ የታተሙ በመሆኑ፣ የማኀበረሰቡን ስሜት ለመንካት ወይም አፋጣኝ ምላሽ ለማግኘት ስለሚታቸው ማውራት ብቻ በቂ የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡ አራተኛው ፋይዳ ሚቶች ማኀበረሰባዊ መዋቅር ለመገንባት ይጠቅማሉ፡፡ በዚህ በየቀኑ እየተለወጠ እና በቴክኖሎጂ እያደገ በሚሄድ ኀብረተሰብ ውስጥ፣ ሚቶች ለእያንዳንዳችን ማንነት እና ምንነት ትርጉም እንድንሰጥ ይረዱናል፡፡ (Brown, 2004, 277)፡፡*

በአጠቃላይ የመንፈሳዊ ሚት የአንድ ማኅበረሰብ እንደማኅበረሰቡ እምነት፣ ባሕል፣ እሴቶች እና መሰል ጉዳዮች መሠረት አድርጎ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደቡድን የሚጫወታቸው ሚናዎች አጠቃላይ ሕላዌን የማስቀጠል እና የማጠንከር ጭምር ናቸው፡፡ ሚቶቹ ማኅበረሰቡ እንደማኅበረሰብ እንዲጸና ግለሰብም ከማኅበረሰቡ እና ከአጠቃላይ መስተጋብሩ ጋር ተስማምቶ እንዲኖር የማድረግ ሚናቸው የጎላ ነው፡፡ ለዚህም ነው Jaja ሚቶች በአፍሪካ ውስጥ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱና የአፍሪካ ፍልስፍናን ለመረዳትም አስፈላጊውን ትንታኔ እና ትክክለኛውን የፅንሰ ሀሳብ ማሕቀፍ እንደሚያሲዙ የሚገልጡት (Jaja 2001, 13)፡፡

## 2.2 ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር ሁለት ንድፈ ሐሳቦች ቀርበዋል፡፡ አንደኛው ተረካዊ ንድፈ ሐሳብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መዋቅራዊ ተግባራዊነት ነው፡፡

### 2.2.1 ተረካዊ ንድፈ ሐሳብ፣

ተረካዊ ንድፈ ሀሳብ ዘለግ ያለ እድሜ ያስቆጠረ ሲሆን መሠረቱ ከጥንታዊቷ ግሪክ ይነገራል፡፡ Cobley የተረካዊ ንድፈ ሐሳብን ቅርጽ ያስያዘው አርስቶትል እንደሆነ ይገልጻል (Cobley, 2005)፡፡ ይሁን አንጅ  ንድፈ ሐሳቡ እስከ ሃያኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የነበረው ጉዞ የጎላ የእሳቤ ለውጥ አልታየበትም ነበር፡፡ የሩስያ የፎክሎር ተመራማሪዎች በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ላይ የተሻለ

መሠረት ጥለዋል፡፡ በተለይም የሩስያ ፎክሎሪስቶች በመዋቅራዊ ተግባራዊነት ሥራዎቻቸው ሚናቸው ጎልቶ ታይቷል፡፡ በተለይም Lévi-Strauss’s በሚት ላይ የተገነባውን የሶፎክሊስ ድርሰት የሆነውን ንጉሥ ኤዲፐስ ታሪክ በተረካዊ ንድፈ ሐሳብ በመጠቀም ከቅርጽ እና ከመዋቅር አንጻር ትንታኔ እንደሰጡበት Cobley ጠቅሰዋል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዘርፉ ተመራማሪዎች የሚጠቀሙባቸው አራት ዋና ዋና የትረካ ባህሪያት መኖራቸውን እና እነሱም ጊዜያዊነት፣ ምክንያታዊነት፣ ነጠላነት እና ተያያዥነት መሆናቸውን የሚገልጹት Richardson, የአራቱንም ባህሪያት እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡

> *ጊዜያዊነት ክስተቶቹ ወይም ሁነቶች ጊዚያቸውን ጠብቀው በቅደም ተከተል መተረካቸውን የሚገልጽ ሲሆን ምክንያታዊነት ደግሞ የሚገልፀው የሀሳቦችን ቅደም ተከተል እና የምክንያትና ውጤት መስተጋብርን ነው፡፡ በአንጻሩ ነጠላነት የእያንዳንዱን ሀሳብ ነጠላ ትረካ ራሱን ችሎ እና ከቀጣዩ ሀሳብ ጋር ሰንሰለቱን ጠብቆ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ መጓዝ መቻል መሆኑን ሲያስረዳ የተያያዥነት ባህሪ የሚገልጠው አንድ ሙሉ ትረካ ወይም ጽሑፍ በወጥነት የሚተረክበት መንገድ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ከአራቱ የትረካ ባህሪያት በአብዛኛው የምንጠቀመው ጊዜያዊነት እና ምክያታዊነትን ነው፡፡ (Richardson, 2000)*

ከዚህ አንጻር ይህ ንድፈ ሐሳብ ለዚህ ጥናት ተስማሚ ነው፡፡ ምክንያቱም ሚቶች በባሕሪያቸው መተረክ የተስተላልፎት ዋና መንገዳቸው በመሆኑ፣ እያንዳንዱም ሚት የራሱ ጊዜ፣ ምክንያት፣ ነጠላነት እና ተያያዥነት ያላው ስለሆነ ይሄንን ንድፈ ሐሳብ በመጠቀም ጥናቱ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

### 2.2.2 መዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሐሳብ፣

የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሐሳብም በአካዳሚው መስክ በስፋት ለመዳረስ የበቃው በ19ኛው መቶ ክ/ዘመን ሰፊ ተቀባይነት የነበረውን የአዝግሞተ ለውጥ እና የተስተላልፎት ንድፈ ሐሳብን በመተቸት እንደሆነ ric. Porth, Kimberlay NeutZling, Jessica Edwards (2009, Web 12) ጠቅሰው፣ በዚህ ንድፈ ሀሳቡ ሰፊ ተቀባይነት ከነበራቸው ውስጥ ከBronislaw Malinowski (2012, 170-181) እና Radcliffe-Brown (2012,154-170) እንደነበሩም

ያብራራሉ፡፡ በተጨማሪም መዋቅራዊ ተግባራዊነት በ20ኛው መቶ ክ/ዘመን መጀመሪያ ተከስቶ ሰፊ ተቀባይነትን እያገኘ የመጣ እንዲሁም ከBronislaw Malinowski እና Radcliffe-Brown በተጨማሪ Email Durkheim፣ Marcel Mass እና William R. Bascom የዚህ ንድፈ ሐሳብ አራማጆች ነበሩ፡፡ (Porth, Eric, Kimberley Neutzling, and Jessica Edwards. (2009, Web 12)፡፡ የዚህ ፈለግ አራማጆች ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በዚህ መልኩ ሲተነትኑ እና ሲያስተነትኑ ቢቆይም ሀሳባቸውን የሚሞግቱ በርካታ ትችቶች ሲቀርብባቸው ቆይቷል፡፡

ከንድፈ ሐሳቡ ተቺዎች ውስጥ Mullen፣ ሦስት አንኳር የሆኑ ጥያቄዎችን በማንሳት፣ ጥያቄዎች በወጉ አልታዩም፣ ፋይዳቸውም አልተመረመረም ሲሉ ነጥቦቹን በማስቀመጥ ይሞግታሉ፡፡ ጥያቄዎቹ ቦታ፣ ባህል እና ጊዜ መሆናቸውን የሚጠቅሱት Mullen፣ አንድ ፎክሎር መተንተን ያለበት በሚገኝበት ቦታ፣ የፎክ ቡድኑ ባለው ሁለንተናዊ ባሕል፣ እንዲሁም ባለው ውስን እና አጠቃላይ ጊዜ መሆን አለበት ይላሉ (Mullen፣ 2003፣ 177)፡፡ ይሄንኑ ሐሳብም Bonnie Blair O'connor (1995), ይደግፉታል፡፡

Malinowski እና Radcliffe-Brown በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ያለው ባሕል ያለምንም ተጨማሪ ጉዳይ በራሱ፣ በተፈጥሮው ሙሉ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ይሁን እንጅ ይሄንን ሀሳብ የማይቀበሉትና የሚሞግቱት Oring ደግሞ የፎክሎር ተለዋዋጭነት፣ ዘውግ እና ተግባረ ብዙነትን አልተረዱም ብለው ቀዳሚዎቹን ተችተዋል፡፡ (Oring፣ 1976፣ 74) በተጨማሪም Finnegan የፎክሎር ተግባር ብዙ የሆነበት ምክንያት ፎክሎር በያዘው በርካታ ክፍል እንደሆነ እና አንዱ የፎክሎር ጉዳይ በተለያየ ቦታ፣ በተለያዩ አካላት፣ በተለያየ ዐውድ ቢከወን ውጤቱም እጅግ የተለያየ መሆኑን በማብራራት የሐሳቡ ተጋሪነታቸውን አሳይተዋል፡፡ (Finnegan 1992፣ 126)::

ነባር ወይም ጥንታዊ የፎክሎር ተንታኞች የፎክሎርን ሚና በሚቃኙበት ጊዜ ፎክሎራዊ ጉዳዩ የሚከወንበትን ዐውድ፣ የማኅበረሰቡን ታሪካዊ አመጣጥ እንዲሁም የፎክሎሩን ተናጠላዊ ተግባር ምርኩዝ ያደረጉ ባለመሆናቸው በቅርብ ጊዜ የተነሱት የፎክሎር አጥኝዎች አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይን ለመመርመር ጉዳዩ የሚከወንበት ዐውድ፣ የከዋኙ ማኅበረሰብ ታሪካዊ ገጽታ፣ የማኅበረሰቡን ባሕል፣ እንዲሁም የፎክሎሩን ቅንጣት በተናጠል ማጥናትን ዋና ምርኩዝ አድርገዋል፡፡

ንድፈ ሐሳቡ ሚት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ የአንድን ሚት ሙሉ ተፈጥሯዊ መገለጫዎች በመተንተን ባሕሪውን ለማወቅ ይጥራል፡፡ እያንዳንዱን ሚት ሲያጠና በሚቱ ምዳቤ ወይም ዘርፍ መሠረት ስለሚጣና የሚቶቹን ዓይነት እንደ ባሕሪያቸው ለያይቶ ይመለከታል፡፡

የሚት ባሕሪው እንደየሚቱ ዓይነት የተለያየ ነው፡፡ አንድን ተናጠላዊ ሚት ለመረዳት ሚቱ የተከወነበትን ጊዜ፣ ቦታ፣ የመከወኛ ሰበብ መረዳት ያስፈልጋል፡ ፡ የሚቱን ዋና መልዕክት ለመረዳት ሚቱ ያለውን የትረካ መዋቅር አያይዞ መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ Jaja የአፍሪካ ሚቶችን በተመለከተ የየማኅበረሰቡን ማንነትና እውቀት ለመረዳት ሚቶች ጠቃሚ መሆናቸውን “Myth also play an important role the African understanding of reality” በማለት ይገልጻሉ (Jaja, 2011፣ 13 ) ፡፡ የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሐሳብ የሚትን ሚና በሚፈትሽበት ጊዜ የማኅበረሰቡን ታሪካዊ አመጣጥ፣ የማኅበረሰቡን ባሕል፣ ሚቱ የተከናወነበትን ዐውድ፣ የአንድን ሚት ተናጠላዊ ሚና ይመረምራል፡፡ በመሆኑም ይህ መዋቅራዊ ተግባራዊነት የንድፈ ሀሳብ ይሄንን ጥናት ለማካሄድ እንደ አንድ ንድፈ ሐሳብ ቀርቧል፡፡

በአጠቃላይ የመኤኒት ብሔረሰብ ሚትና ማኅበረሰባዊ ፋይዳ የተሰኘው ይህ ጥናት ከላይ የቀረቡትን ሁለቱን ንድፈ ሐሳቦች በማዋሐድና ምርኩዝ በማድረግ የመኤኒት ብሔረሰብን የሚት ዓይነቶች፣ ምዳቤያቸውን፣ ማኅበረሰቡ ለሚቶቹ ያለውን አመለካከት እና የሚቶቹን ማኅበረሰባዊ ሚና ይተነትናል፡፡፡

## 2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶች ላይ የተጠና ቀጥተኛ ጥናት አላገኘሁም፡፡ የሚቶቹን ዓይነት፣ ምደባቸውን፣ ባህሪያቱን እና ፋይዳቸውን የተነተነ ጥናትም አላገኘሁም፡፡ ይሁን እንጅ ከዚህ ጥናት ጋር በጥቂቱም ቢሆን ተቀራራቢነት ያላቸው (በመኤኒት ብሔረሰብ ልዩ ልዩ ባሕሎችና ታሪኮች ላይ ትኩረት አድርገው የተጠኑ) ጥናቶች ይገኛሉ፡፡ በመኤኒት ብሔረሰብ ልዩ ልዩ ባሕሎችና ታሪኮች ላይ ትኩረት አድርገው የተጠኑ 15 ልዩ ልዩ ጥናቶችን ለማግኘት ችያለሁ፡፡ 8ቱ በአንድ የውጭ ሀገር አጥኝ የተጠኑ ሲሆን፣ ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመደው እና በዚህ ርዕስ ስር የቀረበው ግን አንድ ብቻ ነው፡፡

ብሔረሰቡ ልዩ ልዩ ባሕሎችና ታሪኮች ላይ ትኩረት አድርገው የተጠኑ ሌሎቹ 7ቱ ደግሞ በሀገር ውስጥ አጥኝዎች የተጠኑ ናቸው፡፡ በፒኤች ዲ ደረጃ በብሔረሰቡ ሚት ላይ የተደረገ ጥናት አልተገኘም፡፡ በኤም ኤ ዲግሪ ደረጃ በፎክሎር የትምህርት መስክ የተጠኑ ሁለት ጥናቶች፣ እንዲሁም በታሪክ የትምህርት ክፍል የተጠና አንድ ጥናት ቀርበዋል፡፡ በተለያዩ ዐውደ ጥናቶች ላይ የቀረቡ አምስት የጥናት ወረቀቶች ከታተሙበት ዘመን ርቀት አንጻር በማስቀደም ከዚህ በታች ተቃኝተዋል፡፡

የሕይወት አበሩ ጥናት "የመኤኒት ብሔረሰብ ባሕላዊ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ" የሚል ሲሆን፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ሚሚያነት በ2004 ዓ.ም. የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የሕይወት ጥናት ዋና ትኩረት፣ በመኤኒት ብሔረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ ላይ ሲሆን፣ በብሔረሰቡ ዘንድ ሰው ሲሞት የሚካሄደውን የአቀባበር ሥርዓት ይገልጻል፡፡ በአምስት ምዕራፎች የተካተተው ይህ ጥናት በዋናነት በብሔረሰቡ የለቅሶ ሥርዓት ላይ ያለውን የዕድሜ እና የደረጃ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ከህጻናት እስከ አቅመ አዳም/ሔዋን ለደረሱ፣ ለእድሜ ባለጸጋዎች፣ ለባሕላዊ ባለስልጣናት፣ ለጎሳ መሪዎች/ኮሞሩት የሚደረገውን የቀብር ሥርዓት አሳይቷል፡፡ ጥናቱ ቅድመ ቀብር ክንውኖች፣ ወቅተ ቀብር ክንውኖች፣ ድህረ ቀብር ክንውኖችን አካትቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቀብር ያለውን ገጽታ እና የብሔረሰቡን የለቅሶ ክዋኔ ማኅበራዊ ተግባራት ተንትኗል፡፡ ይህ ጥናት በብሔረሰቡ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ ላይ የተደረገ ጥናት በመሆኑ እና የቀብር እና የሞትን ጉዳዮች አያይዞ ስለሚያነሳ፤ በተለይም ከሞት፣ ከአቀባበር ሥርዓትና እሳቤ፣ ከሞት በኋላ ካለ እሳቤ ጋር ባለው የዳግም ውልደት እና የዳግም ጅማሬ ሚት ሀሳብ ጋር ለሚቱ መባያ ሰበብ ስለሆነ ከእኔ ጥናት ጋር ይዛመዳል፤ ይሁን እንጂ፣ የሕይወት ሥራ በቀጥታ ሚታዊ ዐውዳዊ ትርጓሜው ላይ አያተኩርም፡፡ ከሞትና ከቀብር ጋር ያሉትን ክዋኔዎች ምንነት ይገልጻል እንጂ ያላቸውን ሚታዊ እሳቤና ፍካሬያቸውን እንዲሁም ማኅበራዊ ፋይዳቸውን በዝርዝር እና በጥልቀት አያሳይምና ከእኔ ጥናት ጋር ይለያል፡፡ የእኔ ጥናት ሰዎች ከሞቱ በኋላ ምን ይሆናሉ? እንዴት ተብሎ ይታሰባል? የዳግም ውልደት ሚት እሳቤው እና ዐውዳዊ ትርጓሜው እንዴት ያለ ነው? የሚቶቹስ ፋይዳ ምንድነው የሚለውን በስፋት እና በጥልቀት የሚያሳይ እና የሚተነትን በመሆኑ ልዩነት አላቸው፡፡

“ባሕላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በመኤኒት ብሔረሰብ” በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ሟሟያነት በ2004 ዓ.ም. ያቀረብኩት ጥናት ሌላው በብሔረሰቡ ላይ የተደረገ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የመኤኒት ብሔረሰብ ባሕላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓትን ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ በብሔረሰቡ ውስጥ ጎልተው የሚታዩ የግጭት ዓይነቶችን፣ የብሔረሰቡን ባሕላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትን፣ የግድያ ዕርቅ ሥርዓት ሂደትን እንዲሁም የድርጊቶቹን ትርጓሜ እና እሳቤ አሳይቷል፡፡ ጥናቱ በብሔረሰቡ ከሞትና ከቀብር ጋር የሚያነሳቸው አንዳንድ እሳቤዎችና ትርጓሜዎች ስላሉ ከዚህኛው ጥናት ጋር በጥቂቱም ቢሆን ይዛመዳል፡፡ ይሁን እንጅ የሚነሱት የሞት እና የቀብር እሳቤዎች ዋንኛ ትኩረት ተደርገው የተነሱ አይደሉም፡፡ ዋና ትኩረቱ የግጭት አፈታት ሥርዓቱ ሂደት ላይ ነው፡፡ ከሞት ጋራ የተያያዙ ሀሳቦችም ሰፊና ጥልቅ የሆነ ትንታኔ የተሰጠባቸው ባለመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋራ ሰፊ ልዩነት አላቸው፡፡

Jon Abbink መኤኒትን በስፋት አጥንተዋል፡፡ ብሔረሰቡን ከቁሳዊ ባሕል (1992)፣ ከባህላዊ ሃይማኖት (1993)፣ “ሞሲት” ከተሰኘው የብሔረሰቡ ክብረ-በዓል (1995) ጋር አያይዘው አጥንተዋል፡፡ Abbink በ“The Final Rite: Burial Among the Me’en of South-West Ethiopia.” በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ባቀረቡት ጥናት የአረጋውያንን ሞት ዋና ዓላማው ያደርጋል፡፡ ጥናቱ ሙሉ በሙሉ ትኩረት ያደረገው በብሔረሰቡ ውስጥ ለአረጋውያን በሚደረገው የቀብር ሥርዓት ላይ ነው፡፡ ይህ ሥራ ከቀብርና ከሞት ጋር የተገናኘ በመሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር የሚዛመድ ሲሆን በብሔረሰቡ ውስጥ ካሉት የቀብር ሥርዓቶች ውስጥ አንዱን ብቻ ነጥሎ ያተኩራል፡፡ አረጋዊ ሰው ሲሞት የሚደረግለትን የቀብር ሥነ ሥርዓት ያሳያል፡፡ ይሁን እንጅ እያንዳንዱን ክንውን የሚደረግበትን ዝርዝር ፋይዳ፣ ከቀብርና ከሞት ባሻገር ስላለው እሳቤና ዐውዳዊ ትርጓሜ ስለማያብራራ እና ስለማይተነትን ከእኔ ጥናት ጋር ልዩነት አለው፡፡

በብሔረሰቡ ላይ የተጠናው ሌላው ጥናት የAweke Hamzaye፣ “Mosaic Culture and Peoples of South Nation’s Nationalities and Peoples, Regional State.” የተሰኘው እና በ2007 የቀረበው ነው፡፡ ይህ ጥናት በብሔረሰቡ ላይ

በመጠናቱ ከዚህ ጥናት ጋር ሲገናኝ፣ ዋነኛ ትኩረቱ ጥበበ ዕድ ላይ በመሆኑ ደግሞ ልዩነት አለው፡፡ በብሔረሰቡ ውስጥ ጥበበ ዕድን በመሥራት ስለሚተዳደሩት ሰዎች፣ ሙያተኞቹ በሌላው ማኅበረሰብ ዘንድ ዝቅ ተደርገው የሚታዩ ስለመሆናቸው ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህ ሙያተኞች በምን ምክንያትና እሳቤ ከሌላው ማኅበረሰብ ተለይተው ዝቅ ተደርገው እንደሚታዩ፣ ማኅበረሰቡ እነሱን የሚረዳበት መንገድ ብቻ ሳይሆን፤ እነሱም ማኅበረሰቡን የሚያዩበትን መንገድ አያሳይም፡፡ በአብዛኛው ምርቶቹ ላይ ያተኩራል እንጂ የምርቶቹን፣ ቁሶችን ትዕምርታዊ ፍቺ አይተነትንም፡፡ በገለጻ ላይ ከማተኮር በቀር ሰፊና ጥልቅ ትንታኔ አይሰጥም፡፡ ነገር ግን የኔ ጥናት እነዚህ በማኅበረሰቡ ውስጥ ዝቅ ተደርገው የሚታዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከእነሱ ውጭ በሆነው የማኅበረሰብ ክፍል ዝቅ ተደርገው የሚታዩበትን ሚታዊ ትረካ ያሳያል፡፡ ሰፊ ትንታኔም ይሰጣል፡፡

በመኤኒት ብሔረሰብ ላይ ከተደረጉት ጥናቶች ሌላው Zerihun Doda, "The Ethno-history Me'enit Ethinic Group, South Nation's Nationalities and Peoples, Regional Government," (2008) የሚለው ነው፡፡ ዘሪሁን በዚህ ጥናታቸው ፖለቲካዊ፣ ባሕላዊ፣ ማኅበረሰባዊ፣ ታሪካዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን በገለጻና በማስተዋወቅ መልክ አንስተዋል፡፡ ከብሔረሰቡ ጥንታዊ አመጣጥ እስከ ዘመነ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ድረስ ያሉ ሁሉን አቀፍ ጉዳዮች ተዳስሰዋል፡፡ ይህ በዘጠኝ ምዕራፎች የተከፋፈለው ጥናት በተለይም በምዕራፍ አራት፣ አምስት እና ስምንት ላይ ባነሳቸው ጉዳዮች ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ ይገናኛል፡፡ በአራተኛው ምዕራፍ ስለሞትና ቀብር ሥርዓት ያነሳቸው ርዕሶች፣ በምዕራፍ አምስት ውስጥ ስለ ነባሩ ሃይማኖት እና ስለአዳዲስ ሃይማኖቶች መምጣት፣ በምዕራፍ ዘጠኝ ደግሞ ስለ ባሕላዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርሶችና ቦታዎች ያነሳያቸው ገለጻዎች ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው፡፡ ይሁን እንጅ ጥናቱ አጠቃላዩን የብሔረሰቡን ፖለቲካዊ፣ ባሕላዊ፣ ማኅበረሰባዊ፣ ታሪካዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን ከብሔረሰቡ ጥንታዊ አመጣጥ እስከ ዘመነ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አጠቃልሎ የሚገልጽ በመሆኑ ገለጻው ምጥን ነው፡፡ ድርጊቶች ወይም ሁነቶቹ እንደሚካሄዱ ይተርካል እንጂ፣ ለምን ተብለው ይካሄዳሉ? ፋይዳቸው ምንድነው? የሚለው ጉዳይ በሰፊው ተፍታቶ እና ተብራርቶ የቀረበ አይደለም፡፡ በአብዛኛው አንኳር መረጃዎችን በመስጠት ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ በመሆኑም በብሔረሰቡ የሚት ፋይዳ ላይ

ከተቀነበበውና የብሔረሰቡን ሚት ዓይነት እና ክፍሎች መድቦ ከሚተነትነው ከእኔ ጥናት ጋር ያለው ልዩነት የጎላ ነው፡፡

በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ፣ በታሪክ የትምህርት መስክ ለሁለተኛ ዲግሪ ሟሟያነት የቀረበው የHailu Megersa. "A History of Me'en People 1898-1991 G.C" ሌላው በመኤኒት ብሔረሰብ ላይ በ2004 ዓ.ም. የተደረገ ጥናት ነው፡፡ Hailu የጥናታቸውን ዓላማ ከታሪክ ክስተቶች እና ለውጦች ጋር አስተሳስረው ነው ያጠኑት፡፡ በተጠቀሰው ዘመን የተከሰቱ ማኀበረሰባዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች የነበራቸውን ለውጥ እና ተከታታይነት አሳይተዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በዘመኑ ስለተከሰተው የባሪያ ንግድ፣ ስለገባር ሥርዓት እና በወታደራዊው የደርግ ዘመን ስለታወጀው የመሬት ዐዋጅ እና ተያይዘው ስለተከሰቱት ፖለቲካዊና ማኀበራዊ እንዲሁም በዘመኑ ወደ አካባቢው ስለመጡት አሜሪካዊ ሚሲዮኖች እና ሃይማኖታዊ ለውጦች ገልጸዋል፡፡

የHailu ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር በብሔረሰቡ ላይ በመደረጉ እና ሃይማኖት ላይ ባነሳው ለውጥ ላይ በጥቂቱ ይገናኛል፡፡ መኤኒቶች መጀመሪያ በቱማ ስለማመናቸው አንስቶ ወደኋላ ከተለያዩ አጎራባቾቻቸው የወረሷቸው የእምነት ሥርዓቶች መኖራቸውን ይጠቁማል፡፡ ጥናቱ በጥቂቱ ከመጠቆም በቀር ርዕሰ ጉዳዩን በሰፊው እና በዝርዝር አያነሳም፡፡ የእኔ ጥናት ሃይማኖትን ማንሳት ሳይሆን ሃይማኖታዊ ሚት ምን እንደሚመስል፣ የብሔረሰቡ አባላት ስለሚቱ ያላቸውን አስተሳሰብ፣ ሚቱ ለብሔረሰቡ አባላት በቡድንም በተናጠልም ስለሰጣቸው ፋይዳ ስለሚያትትና ስለሚተነትን ልዩነቱ የጎላ ነው፡፡

ሌላው ጥናት የNiguse, Belay "Socio- cultural History of Me'nenit,1898-1991," የሚለው ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ በተዘጋጀ ዓመታዊ የኮንፈረንስ ላይ ቀርቦ በ2005 ዓ.ም የታተመ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ የመኤኒት ብሔረሰብ ማህበረ-ባህላዊ ገጽታ ከዳግማዊ አጼ ምኒልክ ወረራ 1898 እስከ ወታደራዊው የደርግ መንግሥት ውድቀት እ.ኤ.አ. 1991 ድረስ የነበረውን የብሔረሰቡ ማሕበረ-ባሕላዊ ጉዞ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጥናቱ ብሔረሰቡን ካስተዋወቀ በኋላ፤ ብሔረሰቡ በዋናነት ከእንስሳት ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳለው እና ይሄውም ከብቶችን ለደም ካሳነት፣ ለጋብቻ ክፍያዎች እና ለሎች ማኀበራዊ ጉዳዮች በዋናነት እንደሚጠቀሙባቸው ይገልጻል፡፡

በዘጠና ሦስት ዓመታት ውስጥ ያለውን ለውጥ ያነሳው ይህ ጥናት የብሔረሰቡን ሃይማኖት፣ የባህል መድሃኒት እውቀት፣ የጋብቻ፣ የጥርስ ነቀላ፣ የቀብር ሥርዓት፣ እና የአሻ ሥርዓት ምንነቶችን ይገልጻል፡፡ በመሆኑም ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታ ስለብሔረሰቡ ማኅበራዊ እና ባሕላዊ ጉዳዮች በማንሳቱ ይገናኛል፤ ይሁን እንጂ ጥናቱ የተጠቀሱትን ማሕበረ- ባሕላዊ ገጽታዎችን በወፍ በረር ከማስተዋወቅ እና ገለጻ ከመስጠት ውጪ በጥልቀት አይቷል ለማለት አይቻልም፡፡ በተለይም የሃይማኖት እና ሚታዊ እሳቤዎችን እና ትርጓሜዎችን ትኩረት ሰጥቶ አያብራራም፡፡ ማኅበረሰቡም የሚረዳበትን መንገድ አያሳይም፡፡ የእኔ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር በስፋትም በዝርዝር ዓላማዎችም ሚቱን ከፋፍሎ በማየትና በመተንተን፣ የሚቶቹንም ፋይዳ በስፋት በማሳየት ይለያል፡፡

በአጠቃላይ የተደረጉ ቀደምት ጥናቶችን ስናይ አብዛኞቹ በብሔረሰቡ ልዩ ልዩ ባሕሎች ላይ የተለያዩ ዓላማዎችን ይዘው የተጠኑ ናቸው፡፡ ይበልጡንም ከታሪክ አንጻር የታዩት በርከት ይላሉ፡፡ ጥናቶቹ ከብሔረሰቡ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ጋብቻ፣ ቀብርና ሌሎች ማሕበራዊ ጉዳዮች ጋር ተያይዘው የተጠኑም ናቸው፡፡ ጥቂቶቹ ስለሞትና ቀብር፤ ጥቂቶቹ ደግሞ ስለሃይማኖትና የብሔረሰቡ ታሪክ፣ እንዲሁም ጥቂቶቹ ስለግድያና ባሕላዊ የፍትሕ ሥርዓት በማንሳታቸው ከእኔ ጥናት ጋር በጥቂቱም ቢሆን ይዛመዳሉ፡፡ የእኔ ጥናት የመኤኒትን ሚት ዓይነቶች እና ማኅበረሰባዊ ፋይዳቸውን በጥልቀት እና በስፋት የሚመለከት በመሆኑ የተለየም ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የመኤኒት ብሔረሰብ ማኅበረ ባሕላዊ ዳራ

በዚህ ርዕስ ስር የመኤኒት ብሔረሰብ፣ ማኅበረ ባሕላዊ ዳራ የተዳሰሰ ሲሆን፣ የመኤኒት ብሔረሰብ መልክአ ምድራዊ ገጽታ፣ ታሪካዊ አመጣጥና አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ እምነት፣ የኢኮኖሚ መሠረት፣ ማኅበረሰባዊ ሕይወት እና ማህበረሰባዊ ተቋም ቀርበዋል፡፡

### 3.1 መልክአ ምድራዊ ገጽታ

የመኤኒት ብሔረሰብ ከ1980ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ እስከ 2012 ዓ.ም. ድረስ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል፤ በቤንች ማጂ ዞን ሥር ከነበሩት ስድስት ብሔር ብሔረሰቦች አንዱ ነበር፡፡ ነገር ግን የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የክልሉ መቀመጫ እና ከነበሩት ዞኖች ወስጥ አንዱ የነበረው የሲዳማ ዞን ባነሳው ራሱን የቻለ ክልል የመሆን ጥያቄ መሠረት ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ራሱን የቻለ ክልል ሆኗል፡፡ በዚህም ምክንያት የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል የራሱን አዲስ ክልላዊ አወቃቀር አደራጅቷል፡፡ በተነጻጻሪም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ሥር ከነበሩት ዞኖች ውስጥ አንዱ የነበረው እና ስድስት ብሔረሰቦችን አካትቶ የቆየው የቤንች ማጂ ዞንም የራሱን አዲስ አደረጃጀት መሥርቷል፡፡ በመሆኑም በቤንች ማጂ ሥር ለረጅም ጊዜ ከቆዩት ውስጥ ሦስቱ ብሔረሰቦች፣ ማለትም መኤኒት፣ ዲዚ እና ሱርማ ብሔረሰቦች ራሳቸውን በአዲስ ዞን በማዋቀር የምዕራብ ኦሞ ዞን በመባል አዲስ ዞናዊ አደረጃጀትን መሥርተዋል፡፡ እነዚህን ሦስቱን ያካተተው አዲሱ የምዕራብ ኦሞ ዞን ዋና ከተማውን የመኤኒቶች አንድ ወረዳ በሆነችው ጀሙ ከተማ አድርጓል፡፡

የመኤኒት ብሔረሰብም በአዲሱ አደረጃጀት ሥር በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በምዕራብ ኦሞ ዞን ወስጥ፣ በዋናነት በሁለቱ ወረዳዎች ማለትም በመኤኒት ጎልዲያ እና በመኤኒት ሻሻ ወረዳዎች ውስጥ ይገኛል፡፡ የመኤኒት ጎልዲያ ወረዳ ዋና ከተማ ባቹማ ስትሰኝ፣ የመኤኒት ሻሻ ወረዳ ዋና ከተማ ደግሞ ጀሙ ትባላለች፡፡ በሁሉም ወረዳዎች ውስጥ ያሉት የብሔረሰቡ አባላት

በባህል፣ በቋንቋ፣ በእምነት እና በሌሎች እሴቶቹ አንድ ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የብሔረሰቡ አባላት የሚኖሩባቸውን ሁለቱን ወረዳዎች በተናጠል እንመለከታለን፡፡

### 3.1.1 መኤኒት ጎልዲያ

የመኤኒት ጎልዲያ ወረዳው ዋና ከተማ ባቹማ፣ ከአዲስ አበባ በ645 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ወረዳው ሦስት ዓይነት የዓየር ጸባያት የሚታይበት ነው፡፡ ቆላ፣ ደጋ እና ወይናደጋ የአየር ንብረት የሚታይበት ወረዳ ነው፡፡ ካለው 16.881 ሔክታር የቆዳ ስፋት ውስጥ 43% ቆላ፣ 52% ደጋ እና 5% ወይናደጋ የአየር ንብረት እንዳለው (የደ/ብ/ብ/ህ/ ፕሮፋይል፣ 2001) ይገልጻል፡፡

መኤኒት ጎልድያ ወረዳ ስያሜውን ያገኘችው በከተማዋ እንብርት ላይ ከነበረ ድንጋይ ነው “መሐል ባቹማ ከተማ ውስጥ አንድ ጠፍጣፋ ድንጋይ ነበረ፡፡ ድንጋዩ በብሔረሰቡ ስም “ጎሎ” ይባላል፡፡ “ጎሎ” ማለት መፍጫ (ወፍጮ) ማለት ነው፡፡ ድንጋዩ ወፍጮ ስለሚመስል ከድንጋዩ መነሻነት ነው መኤኒት ጎልድያ የተባለው” (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ብርሃኑ ወርቁ፣ ሰኔ 2008ዓ.ም ባቹማ)፡፡

### 3.1.2 መኤኒት ሻሻ

የመኤኒት ሻሻ ወረዳ ዋና ከተማ ጀሙ ከአዲስ አበባ 675፣ ከመኤኒት ጎልዲያ ዋና ከተማ ከባቹማ 30 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ሁለት ዓይነት የአየር ጸባይ ያለው መኤኒት ሻሻ ወረዳ የቆዳ ስፋቱ 277.100 ሄክታር ነው፡፡ ወይናደጋው 15% እንዲሁም ቆላው 85% መሆኑን ሕይወት ገልጻለች (ሕይወት፣ 2003) ፡፡ የወረዳው ዓመታዊ አማካኝ የሙቀት መጠን 17.6- 27.50c ሲሆን የሚገኘው እንደ መኤኒት ጎልዲያ ሁሉ 501- 2500 ሜ. ከባህር ጠለል በላይ ነው፡፡

## 3.2 የመኤኒት ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥና አሰፋፈር

የመኤኒት ብሔረሰብን አመጣጥና አሰፋፈርን በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎች ዘግበዋል፡፡ ከቤንች ማጂ ዞን የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ያገኘሁት ያልታተመ ጽሑፍ የብሔረሰቡን አመጣጥ በተመለከተ የተሰጡትን አራት አፈ-ታሪኮች በቅደም ተከተል አስፍሯል፡፡

የመጀመሪያው ብሔረሰቡ ከነገደ ኩሽ ከመሐል አገር ፈልሰው ወደ ደቡብ ምዕራብ የመጡ ናቸው የሚል ሲሆን ሁለተኛው አፈ-ታሪክ የብሔረሰቡ አመጣጥ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት የብሔረሰቦች ፍልሰት ጋር የተያያዘ እንደሆነና ከ3000ዓ.ዓ. በፊት ከደቡብ ሱዳን ፈልሰው ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከገቡት ጎሳዎች እንደ ቤጃ እና ከመሳሰሉት አንዱ ነው የሚል ነው፡፡ ሦስተኛው ደግሞ በጋሞ ጎፋ ክ/ሀገር በኦሞ ሸለቆ አካባቢ ከብት እያረቡ ሲኖሩና ከብቶቻቸው በበሽታ ሲያልቁባቸው አካባቢውን ጥለው እንደመጡና አሁን ባሉበት ጸንተው እንደ ቆዩ የሚያትት ሲሆን አራተኛው በብዙ የብሔረሰቡ አባላት የሚነገረው የኦሞን ወንዝ ተሻግረው መምጣታቸውን የሚተርክ ነው፡፡ እኔም የብሔረሰቡን የት መጣነት በስፍራው ተገኝቼ ባደረኩት ቃለ- መጠይቅ ከአውራ የመረጃ አቀባዮቼ የሰማሁት ብሔረሰቡ ከደቡብ ኦሞ መምጣቱን ነው፡፡ አቶ ብርሃኑ ወርቁ የሚከተለውን ይገልጻሉ፡፡

> *እኛ የምናውቀው፣ አባት አያቶቻችንም በቃል ከአንዱ ወደ አንዱ ሲያሸጋግሩልን የቆዩት የመኤኒት ብሔረሰብን አመጣጥ ታሪክ፣ ከደቡብ ኦሞ አካባቢ መምጣታችንን ነው፡፡ በድሮ ጊዜ እዚያው አካባቢ የነበረው ሕዝብ ከፍተኛ ድርቅ ስላጋጠመው አካባቢውን ለቅቆ ተሰደደ፡፡ ያኔ የጥንት አባቶዎች ቻችን አካባቢውን ለቅቀው ሲፈልሱ ጥቂት ጎሳ ግን አካባቢውን አንለቅቅም ብለው ቀርተዋል፡፡ ያኔ በዚያ አካባቢ ተቆርጦ የቀረው ጎሳ ቺሪም[3] በመባል ይታወቃል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር 2010ዓ.ም ባቹማ)፡፡*

ብሔረሰቡ የኦሞን ሸለቆ አቋርጦ እንደመጣ የሚተርከው ይህ የብሔረሰቡ የአሰፋፈር ታሪክ መኤኒቶች ዛሬ ከሠፈሩባቸው ዋና ዋና ወረዳዎች መኤኒት ሻሻ እና መኤኒት ጎልዲያ ከመድረሳቸው በፊት እንደ ቺሪም ጎሳ ሁሉ በየአካባቢው የተቆረጡ ጎሳዎች እንዳሉ ሁሉ በሰፊው ይነገራል፡፡ በድሉ የብሔረሰቡ አባላት የኦሞን ሸለቆ አቋርጦ አሁን በስፋት ወዳለበት ምድር እስኪደርስ በመንገድ ከቀሩት ጎሳዎች ውስጥ አንዱ "ሜላ" በመባል የሚታወቀው ጎሳ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ "በስደቱ ጊዜ በመንገድ ከቀሩት ጎሳዎች አንዱ፣ ሜላ የሚባለው ጎሳ

---

*[3] ቺሪም የሚለው ጎሳ መጠሪያ የወሰደው ከከብቶች አቀማመጥ እንደሆነ በአፍ ታሪክ ይነገራል፡፡ በስደቱ ጊዜ አካባቢውን ሳይለቅ እዚያው የቀረው ጎሳ ከብቶች ብርክክ ብለው እንደተኙ፣ ቀንዳቸው ቀጥ ብሎ እንደቆመ ሲታዩ ቺሪም ተባሉ፡፡ ቺሪም ማለት ብዙ ከብቶች አንድ ላይ ተኝተው ሲታዩ ማለት ነው፡፡ (ቃለ መጠይቅ አቶ በድሉ ካሳ፣ ህዳር 2010፣ ባቹማ)*

ነው፡፡ ሚላዎች አሁን የሚገኙት የመኤኒት አጎራባች በሆነው በካፋ ዞን፣ በዴቻ ወረዳ ውስጥ ነው፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ በድሉ ካሳ፣ ህዳር 2010ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡

በእርግጥም የመኤኒት ብሔረሰብ በዋናነት በሁለቱ ወረዳዎች፣ በመኤኒት ሻሻ እና በመኤኒት ጎልዲያ ውስጥ ይገኝ እንጂ አጎራባች በሆነው የካፋ ዞን፣ በዴቻ ወረዳ ውስጥ እና በሸኮ ዞን ውስጥ ባለው ጉራፈርዳ ወረዳ ውስጥም በጥቂቱ ይኖራል፡፡ እንደ ብርሃኑ ወርቁ አገላለጽ ቦዲ ተብሎ የሚታወቀው ብሔረሰብም የመኤኒት አንድ አካል እንደሆነ ይታመናል፡፡

> *ቦዲዎች በቋንቋ ይቀራረቡናል፣ በባህል እንዛመዳለን፡፡ መኤኒቶች ናቸው፡፡ በጊዜ ሂደት ተነጥለው የቀሩ ናቸው፡፡ ስማቸውን ያገኙት ከአንድ ፈረንጅ ነው፡፡ ሃይማኖት ለማስፋፋት ወደ ሥፍራው ከገቡት ፈረንጆች ውስጥ የሰዎችን አካላዊ ቁመና በማየትና በተስተካከለ እና በፈረጠመ ሰውነታቸው በመደነቅ ቦዲ የሚል ስም ሰጧቸው ይሄ አጠራርም በሌሎች እየተዘወተረ ከጊዜ በኋላ የብሔረሰብ ስም ሆነ፡፡ ቦዲ በብዙ ነገሩ መኤኒት ነው[4] (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር 2010ዓ.ም ባቹማ)፡፡*

የመኤኒት ብሔረሰብ ባደረገው የፍልሰት እና የአሠፋፈር ታሪክ ውስጥ በየሥፍራው ተቆርጠው የቀሩ ጎሳዎች መኖራቸው እርግጥ ነው፡፡ የብሔረሰቡ አባላት በተለያዩ መልክአምድር ውስጥ መገኘታቸው አንድ ማስረጃ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የብሔረሰቡ አባላት ሆነው ፈጽሞ መኖራቸውም ሳይታወቅ ለዘመናት ኖረው በቅርቡ ወደ ብሔረሰባቸው የተቀላቀሉ መኖራቸው ዋና ምስክር ነው፡፡

> *ያርጣ የተሰኘው ቀበሌ የተገኘው በ2003 ዓ.ም ነው፡፡ ከዚያ በፊት በዚያ አካባቢ የተደራጀ እና ብዙ ሕዝብ ይኖራል ተብሎ አይታወቅም ነበር፡፡ ያርጣ አካባቢ በጥቅጥቅ ደን የተሸፈነ፣ ምንም ዓይነት የመገናኛ መንገድ ያልነበረው እና በእግርም ሄዶ አንድ*

---

[4] *ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ሀገር መሆኗ እሙን ነው፡፡ ስለ ሀገሪቱ ብሔር ብረሔሰቦች እና ሕዝቦች ቁጥር በተለያዩ ሚዲያዎችም ሲጠራ ከሰማኒያ በላይ የሚለው ጥቅል መጠሪያ ተደጋሞ ይደመጣል፡፡ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መንግሥት በውስጡ ያሉትን ብሔር ብሔረሰቦች ሃምሳ ስድስት መሆናቸውን የክልሉ ሕገ መንግሥት ጭምር ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ አንጻር የመኤኒት ብሔረሰብ እና የቦዲ ብሔረሰቦች ጉዳይ አንድ ጥያቄን ማጫሩ አይቀርም፡፡ ብሔረሰቦቹ አንድነታቸውን የሚያጎሉ የተለያዩ ማስረጃዎች ካሉ፣ የብሔር ክፍፍሉንና ድልድሉን እንደገና እንዲታይ የሚያደርግ አንድ መነሻ ይሆናል፡፡ የዚህ ጥናት ዓላማ ይሄንን መነሻ መመርመር ባለመሆኑ ጥያቄውን ብቻ አጭሮ ማለፍ የግድ ይላል፡፡*

*ሰዓት የሚያስጉዝ አካባቢ ነበር፡፡ በዚህ አካባቢ ሰዎች መኖራቸው ተረጋግጦ፣ ቋንቋቸው፣ ሃይማኖታቸው እና ባሕላቸው የመኤኒት መሆኑ ተረጋግጦ የመኤኒት ጎልዲያ አንድ ቀበሌ በመሆን በ2003 ዓ.ም ተመዝግበዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ በድሉ ካሳ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡*

ያርጣ አካባቢ ከወረዳው ከተማ በጣም የራቀ እና ሰው ይኖርበታል ተብሎ የማይገኝበት በመሆኑ ትኩረት ሳይሰጠው ኖሯል፡፡ ይሁን እንጅ ከብሔረሰቡ የፍልሰት ታሪክ ጋር ተያይዞ ሕዝቡ የየጎሳ መሪውን ተከትሎ ለከብቶቹ የግጦሽ መሬት ባገኘበት አካባቢ ለመኖር ችሏል፡፡ እኔም የኤም ኤ ዲግሪ ጥናቴን በብሔረሰቡ ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ በምሠራበት ወቅት የያርጣ ቀበሌ መገኘት ለሕዝብ ተበስሮ፣ በወረዳው ጽ/ቤት የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ተለጥፎ ነበር፡፡ አሁን፣ የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶች እና ማኅበረሰባዊ ፋይዳቸው የሚለውን ጥናት ሳካሂድ፣ ቀበሌው መረጃ ለመሠብሰብ ፣ አንድ የጥናት አካባቢ ተደርጓል፡፡

## 3.3 ቋንቋ

የመኤኒት ብሔረሰብ ተለይቶ ከሚታወቅባቸው ማንነቱ አንዱ ቋንቋው ነው፡፡ ብሔረሰቡ የሚናገረው፣ ቋንቋው በአጎራባች ወረዳዎች ውስጥ ካሉት ሕዝቦች ቋንቋዎች ጋር ተቀራራቢነት ያለው ቢሆንም በራሱ ተነጥሎ የቆመ ቋንቋ ነው፡፡ የብሔረሰብ አባላት የሚናገሩት ቋንቋ "መኤኒትኛ" ነው፡፡ ቋንቋውም ከሱርሚክ ቋንቋዎች አንዱ እንደሆነና በዓባይ ሰሀራዊ የቋንቋ ቤተሰብ እንደሚመደብ፣ ከሙርሲ፣ ከሱርማና ከሌሎች ብሔረሰብ ቋንቋዎች ጋር ተቀራራቢነት እንዳለው *"The language of m'einit belongs to east Sudanic nailo Saharan language, specifically to the south east Surmic language sub family with Surma Zilimamo or Balu Mursi, Muguji and Kawegu" (Aweke፣ 2007፣110) ሲሉ ገልጸዋል፡፡*

Abbink የተሰኙት አጥኚም በተመሳሳይ ቋንቋው ከሱርሚክ ቋንቋዎች አንዱ መሆኑንና ከቲርማ፣ ከቻይ፣ ከባሌሲ /የዚልማሙ ቋንቋ/ ከቦዲና ከሙርሲ ብሔረሰብ ቋንቋዎች ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው ገልጸዋል (Abbink,1995፣ 163) ፡፡

## 3.4 እምነት

በመኤኒት ብሔረሰብ ሰማይና ምድርን እንዲሁም መኤኒቶችን እንደፈጠራቸው የሚታመነው አምላክ ቱማ ይባላል፡፡

የመኤኒቶች አምላክ ቱማ፣ ተለዋጭ ስም አለው፡፡ የብሔረሰቡ አባላት ሁለቱን ስሞች በማፈራረቅ ይጠቀማሉ፡፡ "ቱማ"፣ "የሪ" የተሰኘ ተለዋጭ ስምም አለው፡፡ ብሔረሰቡ ሁለቱን ስሞች በማፈራረቅ ይጠቀማል" Zerihun፣ 2008፣ የደ/ብ/ብ/ህ/ ፕሮፋይል 2001፣ አንዱዓለም (2004)፡፡

አምላክ ቱማ /Tumma/ ወይም የሪ /Yerry/ ከሰዎች በላይ የሆነ ነው፡፡ አምላካቸው የሁሉ ነገር ፈጣሪ የሆነና በሰማይ የሚኖር ነው፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ የሃይማኖት ታሪክ በሦስት የተለያዩ ዘመኖች ሊታይ እንደሚችል እና እሱም በቱማ/Tumma/ ወይም በየሪ/Yerry/፣ እና በጠንቋይና በቃልቻ ማመን የጀመሩበት፣ እንዲሁም ዘመናዊ ሃይማኖቶች መምጣትና ማመን የጀመሩበት እንደሆነ Zerihun (2008) ይገልጻሉ፡፡

የመኤኒት ብሔረሰብ በአምላክ ቱማ የሚያምን ቢሆንም በጊዜ ሂደት ደርቦ የተቀበላቸው እምነቶች አሉ፡፡ አብዛኛው ሕዝብ በባሕል ሃይማኖት ወይም በቃልቻ የሚያምን ሲሆን፣ የኦርቶዶክስ፣ እስልምና እና የፕሮቴስታንት እምነትም ይገኛል፡፡ ይሁን እንጅ አብዛኛው ሰው በቃልቻ ማመንን ከሌሎች እምነቶች ጋር ደርቦ እንደሚይዝ አወቀ ይገልጻሉ፡፡ "አብዛኛው ሰው የባሕል ሃይማኖትን ያምናል፡፡ የሌላ እምነት ተከታይ ቢሆን እንኳን፣ በተደራቢነት ያምናል፡፡" (አወቀ ፎሮሽዋ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 2008 ዓ.ም፣ ጨበራ)

## 3.5 የኢኮኖሚ መሠረት

የመኤኒት ብሔረሰብ ጥንት የኢኮኖሚ መሠረቱ በእንስሳት ርቢ ላይ እንደነበረ የብሔረሰቡ አባላት ይገልጻሉ፡፡ አቶ ብርሃኑ የብሔረሰቡን የጥንት እና የአሁን ዘመን ኢኮኖሚያዊ መሠረት እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> *የጥንት አባቶቻችን አኗኗር እና የኢኮኖሚው መሠረት ከብት እርቢ ነበር፡፡ ቅድም አያቶቻችን የሚኖሩበት አካባቢ በአብዛኛው ቆላ በመሆኑ ማኅበረሰቡም የሚተዳደረው ከብቶችን በብዛት*

በማርባት ነበር፡፡ ነገር ግን በጊዜ ሂደት እና በብሔረሰቡ ላይ በደረሰ ፍልሰት ምክንያት የጥንቱን አካባቢ በመልቀቅ አሁን ወዳለንበት አካባቢ ስንመጣ፣ የአኗኗር ሥርዓታችንም ላይ ወደ እርሻ ሥራ በማዘንበል ዋናው የኢኮኖሚ መሠረት ወደመሆን መጥቷል (ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 2008ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡

ምንም እንኳን የብሔረሰቡ አባላት አሁን የእርሻን ሁኔታ የኢኮኖሚያቸው አንዱ ዋልታ ቢያደርጉትም ከከብት እርባታ ጋር የተያያዘው አጠቃላይ የሕይወት መስተጋብራቸው እንደቀጠለ ነው፡፡ የከብት እርባታው አሁንም ለብሔረሰቡ ሕይወት ዑደት ዋንኛ ማጠንጠኛ ነው፡፡ ከብቶች ለጋብቻ የሚሰጡ የጥሎሽ ዋና መደራደሪያ፣ የሀዘን መግለጫ እና ከሞት በኋላ አለ ብለው ለሚያምኑት ሕይወት ስንቅ፣ ለአምልኮታዊ ሥርዓቶች የሚቀርቡ መስዋዕቶች፣ እንደ ግድያ እና ከሰው ዝሙት ለመሳሰሉት የማኅበረሰብ አኗኗር እንቅፋቶች መፍቻ የካሳ ክፍያዎች እንዲሁም ከኃጢአት የመንጻት መንገዶች በመሆንም ያገለግላሉ፡፡ አቶ በድሉ የብሔረሰቡን እና የከብቶችን ጥብቅ ቁርኝት ሲገልፁ "በመኤኒት ብሔረሰብ የከብት እርባታ የኑሮ ዋና መሠረት ነው፡፡ የሀብት መገለጫውም ይሁን ለልዩ ልዩ አገልግሎት ማከናወኛ የሚያስፈልጉ ናቸው፡፡ ከብት እርባታ ዋንኛ የኢኮኖሚ መሠረት ነው" (ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 2008 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡ በብሔረሰቡ ከብት ማርባት እና እርሻ ዋና የገቢ ምንጮች ቢሆኑም በተለይ በእርሻ ሥራ ላይ ያለው ልምድ አድካሚ እና ያልዘመነ ነው፡፡

ባሉባቸው የብሔረሰቡ አባላት በሠፈሩባቸው አካባቢዎች፣ ደጋ፣ ወይና ደጋ እና ቆላ የሆነ የዓየር ንብረቶች አሏቸው፡፡ በእነዚህ የተለያዩ አካባቢ ባሉ የዓየር ንብረት ጠባዮች በቆሎ፣ ቡና፣ ገብስ፣ ባቄላ፣ ሸንኩርት፣ ጎመን፣ ማር እና ሌሎች ይበቅላሉ፡፡ ብሔረሰቡም እነዚህን የግብርና ውጤቶች ከራሱ ፍጆታ ባሻገር ኢኮኖሚያዊ አቅሙን ለማጠናከር እንደሚጠቀምበት ዋየች ጃሻ ገልጸዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 2008ዓ.ም፣ ጨበራ)፡፡

## 3.6 ማኅበረሰባዊ ሕይወት

በዚህ ርዕስ ሥር የመኤኒት ብሔረሰብ ማኅበራዊ ገጽታዎች ከሆኑት ውስጥ ለዚህ ጥናት ቀረቤታ ያላቸው ጋብቻ፣ ለቅሶ፣ ጥርስ ነቀላ እና ስም አወጣጥ፣ አለባበስ፣ አመጋገብ፣ ጥበበ ዕድና የሚጥል በሽታ ተቃኝተዋል፡፡

### 3.6.1 ጋብቻ

በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ ጋብቻ የራሱ ልዩ ልዩ ገጽታዎች አሉት፣ ጋብቻ ከፍተኛው የሕይወት እርከን በመሆኑ አንድ መኤኒት እዚህ ደረጃ ላይ ከመድረሱ በፊት ሊያልፍባቸው የሚገቡ የሕይወት ገጽታዎች እና ወግና ማዕረጎች አሉ፡፡ ወንድም ይሁን ሴት እነዚህን እርከኖች አልፎ ለጋብቻ ይደርሳል፡፡ በብሔረሰቡ ከህጻንነት እስከ ሙሉ ሰውነት ያለው ሽግግርም የራሱ የሆነ መጠሪያ አለው፡፡ "ህጻን ልጅ 'ዎት' ይባላል፡፡ ወደ ወጣትነት ከፍ ሲልም 'ቦሊያ' ይባላል፡፡ ሴት ልጅ ደግሞ 'ውንጃይ' ተብላ ትጠራለች" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ብርሃኑ ወርቁ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም ባቹማ)፡፡ ወንድም ይሁን ሴት ለጋብቻ መድረሳቸው የሚታወቀው በአካላቸው ላይ በሚታየው ለውጥ ነው፡፡ በድሉ ለውጡን ሲገልጹ "ወንዱ ድምጽ መጎርነን፣ አካሎቹ መፈርጠም፣ ሴቷ ዳሌዋ መስፋት፣ ጡቶቿ መጉላት ሲጀምሩ ለጋብቻ መድረሳቸው ይታወቃል፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ በድሉ ካሳ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡ ለአንድ የመኤኒት ወንድ ጋብቻ መመሥረት፣ ቀላል ተግባር አይሆንለትም፡፡ ምክንያቱም ጋብቻ ዋና የክብር ማሳያ እና መገለጫ ሥርዓት በመሆኑ ነው፡፡ ሴት ልጆች የበዙለት ቤተሰብ በሴቶቹ ምክንያት የሀብት ደረጃው ከፍ ይላል፡፡ በብሔረሰቡ አንድ ወንድ ሲያገባ ለሴቷ ከሰባት ያላነሰ ከብቶችን በጥሎሽ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ "አንድ ሰው ከስምንት በላይ እስከ አስራ አምስት ድረስ ከብት ሰጥቶ ሊያገባ ይችላል፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ሻልታ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም ባቹማ)፡፡ በብሔረሰቡ ጋብቻ ሥርዓት ውስጥ እንድ ወንድ ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት መቻሉ ደግሞ ወንዱ በተደጋጋሚ ጥሎሽ ማበርከት እንዲያገባ ያስገድደዋል፡፡ "እኔ አራት ሚስቶች አሉኝ፡፡ ለመጀመሪያዋ አስር ከብት፣ ለሁለተኛዋ ስምንት ከብት፣ ለሦስተኛዋ ሰባት ከብት፣ ለአራተኛዋ ስምንት ከብት ሰጥቼ ነው ያገባኋቸው፡፡ ልጆቼ ወደ ሃያ ስምንት ደርሰው ነበር፡፡ የሞቱም አሉ" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ዳንኬር ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ያርጣ)፡፡ ከአንድ በላይ ሚስት ላሏቸው ሰው፣ በአሥራ ሁለት ከብቶች ጥሎሽ ሦስተኛ ሚስት ሆነው እንደተገቡ ወ/ሮ ኮላሽ ገልጸዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም ያርጣ)፡፡

ስለ መኤኒት ብሔረሰብ ጋብቻ ሲወሳ የሚነሳው ሌላው ገጽታው ጋብቻው ወጥ የሆነ ሥርዓት የሌለው መሆኑ ነው፡፡ የተጋቢዎቹ የቅርብ ዘመዶችን

ሊያስተናግድ የሚችል መጠነኛ የመብልና የመጠጥ ዝግጅት ተደርጎ የጥሎሽ ሥርዓቱ ይካሄዳል፡፡ "ከጥሎሹ በኋላ ሲመሽ ሙሽራው ሚስቱን ይዞ ወደተዘጋጀለት ቤት ይሄዳል፡፡ በዚህ ጊዜ የሙሽሪት የቅርብ ጓደኞች ተከትለዋት በመሄድ ለሦስት ቀናት ያህል አብረዋት ቆይተው ይመለሳሉ፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ሻልታ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም ባቹማ)፡፡ በመኤኒት ብሔረሰብ ነባር ልማድ ውስጥ ሦስት ዓይነት ጋብቻዎች ይፈጸማሉ፡፡ እነዚህ የጋብቻ መንገዶች የየራሳቸውን የባህል ዐውድ ተከትለው ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡ በብሔረሰቡ ቋንቋም "ጋመን"፣ "ቀረን ጉራቤት" እና "ቀነሰኤ" ናቸው፡፡ "በመኤኒት ብሔረሰብ የተለመዱ ሦስት ዋና ዋና የጋብቻ ሥርዓቶች አሉ ፡፡ እነሱም "ጋመን" በቤተሰብ ስምምነት የሚፈጸም ጋብቻ ፣ "ቀረን ጉራቤት" የጠለፋ ጋብቻ እና "ቀነሰኤ" የውርስ ጋብቻ ናቸው" (የደ/ብ/ብ/ህ/ ፕሮፋይል፣2001)፡፡

ብሔረሰቡ ለጋብቻ ከሚሰጠው ክብር አንጻር የሴት ልጅ ክብረ ንጽሕናም ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ነው፡፡ ወንድ ደግሞ ሀብታም ከሆነ እና የሚጠየቀውን ጥሎሽ መጣል እስከቻለ ድረስ ከአንድ በላይ ሚስቶች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ እነዚህም ሚስቶች ባሕሉን አክብረው እና እርስ በእርስ ተከባብረው በመተጋገዝ የሚኖሩ ናቸው፡፡ "በሚስቶቹ መካከል የመናናቅና የመቀናናት መንፈስ ቢኖርም በባሕሉ የተገራ ስለሆነ ክሱት አይደለም፡፡ ይልቁንስ ሴቶች አንድ ሰው በባለቤትነት እንዳገባቸው በግልጽ እያወቁ በእርሻ ቦታቸው በአንድ ላይ ሆነው በመቆፈር፣ በማረምና ሌላም ሥራ በመስራትና በመተጋገዝ ተከባብረው በአንድነት ይኖራሉ" (ሕይወት፣ 2003 ዓ.ም.)፡፡

### 3.6.2 ለቅሶ

በመኤኒት ብሔረሰብ ካሉት ማኅበራዊ ግንኙነቶች አንዱ ለቅሶ ነው፡፡ በብሔረሰቡ ነባር ልማድ ሰውጥ ለቅሶ እና ሀዘን በእድሜ፣ በጾታ እና ሟች በሚኖረው ማኅበራዊ ከበሬታ በተለያየ የአፈጻጸም ሥርዓት ይከወናሉ፡፡

"ለቅሶ ሥርዓቱም ሆነ የቀብሩ ሁኔታ እንደ ሟቹ ማንነት ይለያያል፡፡ ህጻን ሲሞት የሚደረገው አዋቂ ሲሞት ከሚደረገው ይለያል፡፡ ገና ወጣት የሆነ ሰው እና በእድሜ ብዙ ቆይቶ፣ ወልዶና ከብሮ የኖረ ሰው ሲሞት የቀብሩም ሆነ የሀዘኑ ሥርዓት ይለያያል፡፡" (በድሉ ካሳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 2008 ዓ.ም፣ ባቹማ)

መኤኒቶች በለቅሶ ጊዜ ከያሉበት ተጠራርተው ለሟች ክብር ከብት በድንጋይ ግንባሩን መትተው በመግደል፣ ከሞተም በኋላ በማረድ ምግቡን ለለቀስተኛው ምግብነት ያውሉታል፡፡

አዋቂ ሰው ሲሞት የሚከወነው የለቅሶ ሥርዓት በሕጻናት ወይም በወጣቶች ሞት ጊዜ እንደማይከወንና ለአዋቂውም ሞት የቀብር ሥርዓት በርካታ ከብቶች (በሬ፣ ኮርማና ጥጃ) በድንጋይ እየተቀጠቀጡ እንደሚገደሉ ስጋውም በለቀስተኛው እንደሚበላ ሕይወት ገልጸዋል፡፡ (ሕይወት፣ 2003 ዓ.ም) ከዚህ በተጨማሪ በቀብር ጊዜ በርካታ ከብት የሚቀጠቀጥለት ሰውም ሊኖር ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚወሰነው በሟቹ ሴት ልጆች በኩል ባለ ጋብቻ ነው፡፡ "ሟች በርካታ ሴት ልጆች ካሉት በሞተ ጊዜ የሚቀጠቀጥለትም የከብት ብዛት ብዙ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ከብት በማምጣት የሚቀጠቅጡት የሟቹ ሴት ልጆች ባሎች ናቸው፡፡ " (አወቀ ፎሮሽዋ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 2008 ዓ.ም፣ ጨበራ)

### 3.6.3 ጥርስ ነቀላ

ይህ ሥርዓት በመኤኒቶች የሕይወት ጉዞ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ የሚሰጠው ማኅበራዊ ክንውን ነው፡፡ ጥርስ የማውለቅ ወይም የመንቀል ሥርዓት ለሁለቱም ጾታዎች የሚከናውን ሥርዓት ሲሆን መኤኒቶች ከልጅነት ወደ አቅመ አዳም እና አቅመ ሔዋንነት መሻገራቸውን የሚያረጋግጡበት ሥርዓት ነው፡፡ አቶ በድሉ ካሳ ስለ ጥርስ ነቀላው እና የተነቃዮቹን ለሥርዓቱ መድረስ እንዲህ ይገልጻሉ፡፡

> *በመኤኒት አንድ ሴት ወይም አንድ ወንድ ለትዳር ደርሷል፣ ልጅነቱን ወይም ልጅነቷን ጨርሳለች ለወግ ማዕረጉ መብቃት ትችላለች የሚለው ይፋ የሚሆንበት ሥርዓት ነው፡፡ አንዲት ሴት ለጥርስ ነቀላው ደርሳለች ብሎ የሚወስነው ቤተሰቧ ነው፡፡ ቤተሰቧ አካላዊ ሁኔታዋን በመረዳት፣ የጡጦቿን ማደግ፣ የሰውነቷን መጨመር ወንድም ሲሆን የድምጹን መጎርናት እና የአካሉን መፈርጠም በማየት ለሥርዓቱ ይዘጋጃል (ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 2008 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡*

ጥርስ ነቀላው የሚከናወነው በሰፈር ውስጥ የአካባቢው ሰው በተሰበሰበበት እና ድግስ ተዘጋጅቶ ነው፡፡ ከበቆሎ የሚዘጋጅ መጠጥም ይዘጋጃል፡፡ እግር የጣለው ሁሉ በሥርዓቱ ላይ መገኘት እና መካፈል ይችላል፡፡ ይህ የጥርስ መንቀል ሥርዓት በባሕላዊ መንገድ የሚከናወን በመሆኑ በተነቃዮቹ ላይ

ከፍተኛ ሕመም ያስከትላል፡፡ ተነቃዮች ግን ከአንድ የሕይወት ክፍል ወደ ሌላኛው እንደሚሸጋገሩ ስለሚያውቁ ወደ ደስታ ይቀይሩታል፡፡ አቶ ብርሃኑ እና አቶ መልኬ ኬላጊ ይሄንን እንደሚከተለው ገልታጹታል፡፡

> *ጥርስ የሚነቀለው የታችኛው ሲሆን የሚነቀሉትም ሁለት የፊት ጥርሶች ናቸው፡፡ መንቀያው ባሕላዊ መንቀያ በመሆኑ በተነቃዮች ላይ ከፍተኛ ሕመም እና የደም ማፍሰስ ያስከትላል፡፡ ነገር ግን ነቃዮቹ ይሄ እንዳይካሄድ ጨርቅ ነገር በማቃጠል እና ቁስሉ ላይ በመተምተም ደሙ እንዳይፈስስ ያደርጋሉ፡፡ የተነቃይ የሠፈር ጓደኞች ደግሞ ተሰብስበው በደስታ ለተነቃዩ ይጨፍሩለታል፣ እንኳን ደስ ያለህ አድገሃል፣ ተለውጠሃል ትልቅ ሆነሃል የሚል ይዘት ያቸው ዘፈኖችን ይዘፍኑለታል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 2008 ዓ.ም፣ ባቱማ)*

የጥርስ ነቀላ ሥርዓት አንድ ሰውን ለሙሉ ሰውነት ከማብቃት ሌላ ተጨማሪ ጠቃሚ ጎን እንዳለው የሚገልጹት አቶ በድሉ “ጥርሱ የተነቀለ ሰው በጾና ታምሞ ምግብ አልበላ በሚልበት ሰዓት ወተት በቀሰም በማድረግ ወደ ውስጡ እንዲንቆረቆር ለማድረግም እንጠቀምበታለን” ይላሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 2008 ዓ.ም፣ ባቱማ)፡፡

### 3.6.4 ስም አወጣጥ

ስም አወጣጥ ለመኤኒት ብሔረሰብ ከተለያዩ ታሪኮች፣ አጋጣሚዎች፣ ክስተቶች፣ ከሚወዷቸው እንስሶች እና ከሌሎች ማኅበራዊ ዐውዶች ጋር ይገናኛል፡፡ የበኩር ልጅም ትልቅ ክብር አለው፡፡ በብሔረሰቡ የመጀመሪያ ልጅ ቴአ በመባል ይታወቃል፡፡ ቴአ የመጀመሪያ ቀዳሚ ማለት መሆኑን የሚያብራሩት አቶ ብርሃኑ ቴአው በተለየ መልኩ ስለሚፈጽማቸው አንዳንድ ተግባራት የሚከተለውን ይገልጻሉ፡፡ “የመጀመሪያ ልጅ ቴአ፣ እንደግድያ ዓይነት ችግሮች አጋጥመው በባሕላዊ ሥርጫቱ እሻ እርቅ ሲፈጸም ቤተሰቡንና ዘመዶቹን ወክሎ የሚቀርብ ነው፡፡ ከገዳዩ ጋራ የሚተያየው፣ አንጀት የሚበላው[5] ይሄው ቴአው ነው፡፡” (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ብርሃኑ ወርቁ፣ ህዳር 2010ዓ.ም፣ ባቱማ)፡፡

---

[5] *አንጀት መብላት/መባጠስ በእርቅ ሥርዓቱ ላይ ገዳይ እና የሟች ወንድም ቴአው ለእርቅ ሥርዓቱ ከታረደው ከብት አንጀት ታልቦ ከአንድ ሜትር ባልበለጠ ርቀት እጆቻቸው ታስሮ፣ ዓይን ለዓይን ተፋጥጠው የቀረበላቸውን አንጀት ከሁለቱም አቅጣጫ እየበሉ እንዲቀራረቡ ተደርጎ ሲቀራረቡ አስታራዊ ሽማግሌዎች በጦር በጥሰው የሚጥሉበት ሥርዓት ነው፡፡ ትርጉሙም ለበቀል ስንፈላለግ፣ ስንተያይ የነበርነው ሰዎች፣ አካላት፣*

በመኤኒት ብሔረሰብ ስም አወጣጥ የራሱ የሆነ ልማድ አለው፡፡ መኤኒቶች ድንገት ደራሽ እንግዳ በአካባቢያቸው መጥቶ እያለ እናትየዋ ብትወልድ ልጁ በእንግዳው ሰው ስም ይሰየማል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ማኅበራዊ አጋጣሚዎችም ላይ ብትወልድ የሚወለደው ልጅ ከአጋጣሚዎቹ ጋር ተሳስረው የተሰየሙ ቋሚ ስሞችን ይወርሳል፡፡ "Child naming in Me'init depends on different occurrences. For example, if a child is born when a guest is visiting his/her families' house the newborn child gates the name of the guest." (Aweke, 2007፣114)

አንዲት እናት ከትልቅ ሰው የቀብር ስነ-ስርአት ስትመለስ ወይም የቀብር ስነ-ስርአት ላይ ልጅ ከወለደች 'ሞይና' ብላ ህፃኑን ትሰይማዋለች፡፡ የመኤኒት እናት ከጉዞ ስትመለስ ወይም ከቦርዴ ቤት ስትወጣ ልጅ ከወለደች 'ኑርጌ' ወይም 'ሹሉዋ' ብላ ትጠራዋለች፡፡

### 3.6.5 አለባበስ

የመኤኒት ብሔረሰብ አባላት በአለባበስ ረገድ በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ አልባሳትን ተጠቅሟል፡፡ በጥንት ጊዜ በደጋው አካባቢ የሚኖረው የብሔረሰቡ አባላት "ዶቢት" ከተሰኘ እንጨት ተፈትጎና ለስልሶ የሚሠራ እንዲሁም "ወሽኪት" ከተሰኘ ልጥ የሚሠራ ልብስን ይለብስ ነበር፡፡ በተነጻጻሪ በቆላው አካባቢ የሚኖረው ሕዝብ የጥጃ እና የፍየል ቆዳን አለስልሶ ይለብስ ነበር፡፡ በሁለቱም አካባቢዎች የሚኖረው የብሔረሰቡ አባላት ከእንጨትና ልጥም ይሁን ከቆዳ የሚሠራቸውን ልብሶች ከሰውነቱ የግራና የቀኝ ክፍል ክፍት አድርጎ ከአፍረተ ሥጋና ከኋላ በኩል ሰውነትን እንዲሸፍን በማድረግ ነው፡፡ ልዩ ልዩ ጌጣጌጦችንም ያደርጋሉ፡፡

---

*ቡድኖች በመካከላችን የነበረውን ውጥረት ቆረጥነው፣ ከአንድ ከብት የወጣን አንጀት በየሆዳችን በማስገባት እርቅ አወረድን ማለት ነው፡፡*

የመኤኒት ብሔረሰብ የማጌጪያ ቁሳቁሶች፣ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡

ብዙውን ጊዜ ሴቶች በባዶ እግራቸው ሲሆኑ፣ ወንዶች ከሜሲቬ ወይም ጎሽ ቆዳ የተሠራ እንደ ጠፍር ያለ ጫማን ይጫማሉ፡፡

የመኤኒት ልጃገረድ ከፊት ለፊት ድቡልቡል ሆኖ ከኋላው ቅርጽ ያለው መላጣ በማድረግ ጸጉራቸውን ያስውባሉ፡፡ ያገቡና እና ሙሉ ሴቶች  ከኋላቸው በኩል በትንሹ በመላጨት ቀሪውን ጸጉር ዙሪያውን ይገምዳሉ፡፡ አብዛኛቅ ወንድ ጸጉሩን በአጭር የሚቆረጥ ወይም የሚያሳጥር ነው፡፡

ከግራ ወደ ቀኝ የያርጣ ቀበሌ ልጃገረድ እና ወጣቶች አጥኚው በመሀላቸው ሆኖ ፣ (ፎቶ በአቶ በድሉ ካሳ)፡፡

### 3.6.6 አመጋገብ

የመኤኒት ብሔረሰብ በአመጋገብ ረገድ መደበኛ የሆኑ እና የዘወትር የምግብ ዓይነቶች አሉት፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በቆላውም ይሁን በደጋው ሕዝብ ተወዳጁ እና መደበኛው ምግብ ከሆኑት ውስጥ “ካቲላ” ቀዳሚው ነው፡፡ “ካቲላ” እንደ ጤፍ ዓይነት የሆነ በአብዛኛው በገንፎ እና በጭብጦ መልክ የሚቀርብ ምግብ ነው፡፡ “ካቲላ” ብዙ ጊዜ የሚበላው ለበርካታ ምግቦች ማባያ ከሆነው “ኮልፌ” ወይም “ኳይዛ” ከተሰኘ የጎመን ዓይነት ጋር ነው፡፡ በጥቂት ቦታዎች ደግሞ “ካቲላ” ከጎመን ይልቅ “ዛምጣ” ከተሰኘ እንደ እንጉዳይ ዓይነት ከሆነ የምግብ ዓይነት ጋር ነው፡፡

በመኤኒት ሌላው መደበኛው ምግብ “ጳሩ” ነው፡፡ ጳሩ ገንፎ ሲሆን የበቆሎ እና የማሽላ ገንፎ ለምግብነት በስፋት ይውላሉ፡፡ ሁለቱ የገንፎ ዓይነቶች ከለቅሶ እና ከግድያ እርቅ ሥርዓት ጋር ተያይዞ የተለያየ ዓይነት ትርጉም እና ሥርዓት አላቸው፡፡  ሁለቱም የገንፎ ዓይነቶች ከ“ኮልፌ” ወይም “ኳይዛ” ጋር ሆነው ይቀርባሉ፡፡ እነዚህ ዓይነት የጎመን ዘሮች ብዙዎን ጊዜ ከደጅና ከጓሮ የማይጠፉ ሲሆን አንዳንዴ በበቀሉበት ቦታ ላይ ቀጥታ እየተቆረጡ ይላሉ፡፡





ከግራ ወደ ቀኝ፣ የመኤኒት ብሔረሰብ ባሕላዊ ምግብ ጳሩ/ገንፎ እና ቡንጡላ ወይም ጨሞ የተሰኘው ቡና (ፎቶ በአጥኝው)፡፡

የመኤኒት ብሔረሰብ እንደ የምግብ ዓይነቶች ሁሉ ከቤት የማይጠፉ “ቡንጡላ” ወይም “ጨሞ” የተሰኙት የመጠጥ ዓይነቶችን ይጠቀማል፡፡ እነዚህ መጠጦች የቡና ዓይነቶች ሲሆኑ ቡናው የሚዘጋጀው ከቡናው ፍሬ ሳይሆን ከቅጠሉ ወይም በተለምዶ ጀንፈል ከሚባለው ነው፡፡ በብሔረሰቡ ለመጠጥነት ከሚውሉት ውስጥ ቦርዴና ጠጅ ዋንኞቹ ናቸው፡፡

### 3.6.7 ጥበበ ዕድ

በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ የጥበበ ዕድ ሙያ ያላቸው የብሔረሰቡ አባላት በተለያየ ሥፍራ ይገኛሉ፡፡ እኒህ ሙያተኞች በብረታ ብረት ሥራ፣ በቆዳ ሥራ እና በሸክላ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሲሆን መተዳደሪያቸውም ነው፡፡

> *እነዚህ የተለያየ ሙያ ላይ የተሠማሩ ሰዎች የመኤኒት ብሔረሰብ አባላት ናቸው፡፡ በአብዛኛው የሚኖሩት ቢጋቺት ወረዳ በቤሩ ቀበሌ እንዲሁም በዜማ ቀበሌ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች በዋናነት አፈር ያነጥራሉ፡፡ የሚኖሩበት አካባቢ ካለ አፈር በማቅለጥ እና በማንጠር "ወሌ"፣ "ጎና" እና የመሳሰሉትን ዓይነት ለግብርና ሥራ የሚውሉ የመቆፈሪያ መሣሪያዎችን ያመርታሉ፡፡ ከብረት ከሚሠሩት ሥራ ውስጥም ለጦር እንቅስቃሴና ለጦር መሣሪያነት የሚውሉ ቁሶችንም ይሠራሉ፡፡ ( አቶ ብርሃኑ ወርቁ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡*

በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ ያሉ እነዚህ የሚገለሉ የኅብረተሰብ አባላት ለተለያዩ ተግባራት የሚያውሉት የአፈር ዓይነት የተለየ ነው፡፡ ከሚነጥሩት አፈር ከብረታ ብረት እስከ ልዩ ልዩ የሸክላ ውጤቶችን በመሥራት ለቤት ቁሳቁስ እና ለሌሎች አስፈላጊ ድርጊቶች ያውላሉ፡፡ ይሁን እንጅ ይሄንን ዓይነት ችሎታና ጥበባቸው ሲያስንቃቸው፣ በልዩ የጥርጣሬ ዓይን እንዲታዩ ሲያደርጋቸው ኖረ እንጅ ሲያስከብራቸው አልኖረም፡፡

> *የሚጠቀሙት አፈር "ሌሊት" የሚባል ነው፡፡ እነሱም የሚኖሩት ይኸ አፈር ባለበት አካባቢ ነው፡፡ ከአፈሩ ብረት ማቅለጥ ብቻ ሳይሆን ልዩ ልዩ የሸክላ ሥራዎችን ይሠራሉ፡፡ እነዚህ የሸክላ ሥራ ውጤቶች ለተለያዩ የቤት ዕቃዎች የሚሆኑ ናቸው፡፡ በተመሳሳይም ከጠፍር የሚሠሯቸው ልዩ ልዩ መገልገያ ዕቃዎች እና የጠፍር ውጤቶች አሏቸው፡፡*
>
> *የብሔረሰቡ አባላት እነዚህን የማኅበረሰብ ክፍሎች በተለየ ዓይን ሲያዩቸው ኖረዋል፡፡ ከእነሱ ጋርም አይቀላቀልም፡፡ የተገለሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ ከእነሱ ጋር ጋብቻ የሚፈጽም የመኤኒት ጎሳ የለም፡፡ ጋብቻ የሚፈጽሙት እርስ በእርሳቸው ነው፡፡ በማንኛውም ማኅበራዊ አገልግሎት ውስጥ ተሳታፊ አይደሉም፡፡ እነሱም ይሄንን ስለሚያውቁ ብዙ አይቀርቡም፡፡ ማኅበረሰቡ እንደተረገሙ እና እንደተለዩ ፍጡራን ሲያያቸው ነው የኖረው፡፡ (አቶ ሻልታ ታዬ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡*

በዚህ በጥበበ ዕድ ላይ የተራቀቁ እና ለሰው ልጅ የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ ሥራዎችን የሚያመርቱ የኅብረተሰብ አባላት ከመገለላቸው በተጨማሪም ከሰውነት ተራ ወጥተው የሰው ያልሆነ ባሕርይ ሲሰጣቸው ኖሯል፡፡ ይሄ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክልሎች ባሉ እና በዚህ ሙያ ላይ በተሠማሩ ሰዎች ላይ የሚደርሰውን ዓይነት የማግለል እና የማነወር ሂደት በመኤኒትም ወስጥ ይታያል፡፡

> *የመኢኒት ብሔረሰብ አባላት ከእነዚህ ማኅበረሰብ አካላት ጋር ጋብቻና መሰል ማኅበረሰባዊ ግንኙነቶችን አያደርግም፡፡ የተለየ እርግማን ያለባቸው እና የተጠሉ አድርጎ ያያቸዋል፡፡ በማኅበረሰቡ ውስጥ እነሱን ቡዳ ናቸው ብሎ፣ ዓይናቸው መጥፎ ነው፣ ሰው ይበላሉ ብሎ ያምናል፡፡ የሚርቃቸውም በዚሁ አስተሳሰብ ነው፡፡ ቃምጹት ናቸው ብሎ ያምናል፡፡ ቃምጹት ደግሞ ቡዳ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ትኩስ የተቀበረ አስከሬን አውጥተው ይበላሉ ብሎ ማኅበረሰቡ ያምናል፡፡ ይሄንን የማድረግ የተለየ ጥበብ እና ኀይል እንዳላቸው ይታመናል፡፡ ትኩስ አስከሬን ጋ በድብቅ ሄደው አስከሬኑን በማወደስ እና በማሞጋገስ የማስነሳት ኃይል እንዳላቸው ስለሚታሰብ የተቀበረ አስከሬን እስከ ሦስት ወራት ድረስ የሚጠበቀው ከእነሱ ነው፡፡ ( አቶ መልኬ ኬላጊ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡*

### 3.6.8 የሚጥል በሽታ

በየትኛውም የሰው ልጅ የአኗኗር ሥርዓት ውስጥ በሽታ አብሮ የሚኖር እና በልዩ ልዩ ምክንያቶች የሚከሰት ነው፡፡ ነገር ግን አንዳንድ የበሽታ ዓይነቶች በብሔረሰቡ እምንት፣ አስተምሕሮ እና ግንዛቤ የየራሱ ትርጉም እና ፍቺ ይሰጠዋል፡፡ አንዳንድ የበሽታ ዓይነቶች ሥር ከሰደደ የማኅበረሰብ እምነት የተነሳ እጅግም የሚፈሩ እና ከበሽታነትም በላይ በቁጣነት እና በመርገምነት ጭምር የሚታሰቡ ናቸው፡፡ በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ የሚጥል በሽታ ከበሽታዎች ሁሉ በተለየ መልኩ የሚታይ የበሽታ ዓይነት ነው፡፡ ይኸ በሽታ ለምን በአካባቢው በብዛት እንደሚከሰትም እስከ አሁን ሳይንሳዊ የሆነ ምክንያት አልተሰጠውም፡፡ ከአጎራባች አካባቢዎች እና ብሔረሰቦች ዘንድም ይኸ በሽታ ብዙም የሚታይ አይደለም፡፡ በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ የሚጥል በሽታ በብዛት የሚከሰት የበሽታ ዓይነት ነው፡፡ ይኸ በሽታ በብሔረሰቡ አባላት ዘንድ የአምላክ ቱማ ቁጣ እና የክፉ ሥራ ምልክት ተደርጎ ሲታሰብ የኖረ ነው፡፡ በሽታው በንክኪ ይተላለፋል በሚል እምነት አንድ በየሚጥል በሽታ የተያዘን ሰው ቀርቦ

የሚነካው የለም፡፡ አንድ ሰው በድፍረት ወይም በአጋጣሚው በበታው የተያዘውን ሰው ከነካው በሽታው/ቁጣው በነካው ሰው ላይም ይተላለፋል ተብሎ የሚታመን በመሆኑ የነካው ሰው የመገለል እጣው ወዲያው የሚፈጸምበት ይሆናል፡፡ አቶ ሻልታ ስለበሽታው ከዚህ በታች ያለውን ያብራራሉ፡፡

> *የሚጥል በሽታ የአምላክ ቁጣ እንደሆነ ተደርጎ ሲታመን ነው የኖረው፡፡ በበብሔረሰቡ በሽታው በስፋት የሚከሰት ይሁን እንጅ ለምን በሽታው በኛ አካባቢ በብዛት እንደሚከሰት የሚያውቅ የለም፡፡ የሚጥል በሽታ የያዘው ሰው የተረገመ እና አንዳች ክፉ ነገርን በብሔረሰቡ ዘንድ እንደሚያመጣ ተደርጎ የሚቆጠር ነው፡፡ ማንኛዋም እናት ልጇ የሚጥል በሽታ እንደያዘው ካመነች ወይ ከጨከነች አንቃ ትገድላለች ወይም ልጇን ለመግደል የሳሳች እናት ሰው ሳያይት በበሽታ የተለከፈውን ልጅ በድብቅ ከአካባቢዋ አርቃ ጥላ ትመለሳለች፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011ዓ.ም. ባቹማ)*

የመኤኒት  ብሔረሰብ አባላት የሚጥል በሽታን የአምላክ ቁጣ አድርገው ከማመናቸው በተጨማሪ፣ በበሽታው የተያዘውን ሰው ፈጥነው ካላስወገዱት ወይም ከከአካባቢው ካላራቁት መዘዙ ለሌሎቹም እንደሚተርፍ ያምናሉ፡፡ የአካባቢው ሰው ላይ፣ ምርታቸው ላይ፣ ከብቶቻቸው እና ሌሎች የሕይወት መስተጋብራቸው ላይ አደጋ እንደሚያመጣ ስለሚታሰብ በሽታውን የሚያስወግዱ እና የሚያርቁ ሰዎችም አሉ፡፡

> *የሚጥል በሽታ በኛ አካባቢ በብዛት የሚከሰት በሽታ ነው፡፡ ብሔረሰቡ የሚያምነው በሽታው የአምላክ ቁጣ አድርጎ ነው፡፡ በጣም የሚፈራ በሽታ ነው፡፡ በንክኪ ይተላለፋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በሽታው አምላክ ቱማ ቁጣ እንደሆነ እና በዚህ በሽታ የተያዘ ሰው በቤት ውስጥ ካለ ቶሎ ማስወገድ እንደ መፍትሔ የሚታይ ነው፡፡ ይሄ በማኅበረሰቡ ላይ ጭምር መጥፎ ዕድል የሚያመጣ፣ ማኅበረሰቡን ለማይታወቁ ክፉ ዕድሎች የሚያጋልጥ፣ ከብቶች እንዳይረቡና በበሽታ እንዲያልቁ፣ እህል እንዳይኖር ምድር በረከቷን እንዳትሰጥ የሚያደርግ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ በዋናነትም በዚህ በሽታ የተያዘን ሰው የሚያስወግዱ ከማኅበረሰቡ የተውጣጡ አካላት አሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ብርሃኑ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)*

የመኤኒት ብሔረሰብ አባላት ምንም እንኳን የሚጥል በሽታን የአምላክ ቁጣ አድርጎ በማመን ለዘመናት ልጆቹን ሲገድል ቢኖርም ጥቂት የማይባሉ እናቶች

ደግሞ ልጆቻቸውን አርቀው በመጣል እንዳይሞቱ ሲያደርጉ ኖረዋል፡፡ አቶ በድሉ ይሄንኑ ሀሳብ እንዲህ ይገልጹታል፡፡

> *ማኅበረሰቡ በበሽታው የተያዘን ሰው በእግዜር ቁጣ እንደተያዘ እና እንደመርገም ስለሚቆጥረው መፍትሄ አድርጎ የሚወስደውም በበሽታ የተያዘውን ሰው ማስወገድ ነው፡፡ ይሄንን መርገም ብለው የሚያምኑትን ከአካባቢው ለማስወገድ ሥራ የሚሰሩ ሰዎች አሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ በሽታው ሕፃናትን የሚያጠቃ ስለሆነ የታመሙትን ህጻናት በአፍና በአፍንጫቸው አፈር በመጠቅጠቅ እንዲወገዱ ይደረግ ነበር፡፡ ይኼ ቀደም ባሉት ጊዜያት እና አሁንም በጣም ቆላ በሆኑት አካባቢዎች አልፎ አልፎ የሚደረግ ነው፡፡ በአብዛኛው እናቶች ልጆቻቸውን ለመግደል ስለሚሳሱ አርቀው ይጥሏቸው ነበር፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡*

የሚጥል በሽታ በመኤኒት አካባቢ በስፋት የሚከሰት በሽታ መሆኑን፣ ማኅበረሰቡ በሽታው የእግዜር ቁጣ እንደሆነ እና መፍትሔውም ልጆቹን መግደል ወይም ማስወገድ እንደሆነ እንደሚያምን ከተለያዩ አካባቢዎችም የተጣሉ ህፃናትን አቶ ኤሊያስ ዶጊሶ የተባሉ የሕግ ሰውና እና ጋዜጠኛ "ያካር" በተሰኘና በዞኑ በሚታተም ጋዜጣ ላይ ካወጡት በኋላ ትልቅ ርዕስ ሆኖ መግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በበሽታው ላይ ትኩረት አድርገዋል፡፡

> *ይኸ እንደቁጣ እና እንደመአት የሚታይ የሚጥል በሽታ በአካባቢው በስፋት መከሰቱ ከታወቀ እና የመገናኛ ብዙኃን በተለይም "ያካር" የተሰኘ ጋዜጣ በብዛት የተጣሉትን ልጆች ፎቶ አስደግፎ ካወጣ በኋላ ከፍተኛ ትኩረት አግኝቷል፡፡ ልዩ ልዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ እና የመንግሥት አካላት በሽታው በመነካካት የሚተላለፍ አለመሆኑን ለማሳወቅ ከፍተኛ ሥራ ሠርተዋል፡፡ በዚህም ከፍተኛ ለውጥ መጥቷል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሕዝቡ ከድሮው የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ ለውጦችም እየታዩ ነው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡*

የአቶ ብርሃኑን አባባል የሚጠናክሩት አቶ በድሉ ልዩ ልዩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ለበሽታው ትኩረት ለሰጡት በኋላ በበሽታ የተጎዱትን ወደ አንድ አካባቢ በማስፈር በማኅበረሰቡ ግንዛቤ እና የአስተሳሰብ ለውጥ ላይ የመጣውን ዕድገት እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

> *በሽታው በስፋት መኖሩ ከታወቀ በኋላ መንግሥት እና የተራድዖ ድርጅቶች በወረዳዎቹ ዋና ዋና ከተሞች እና እስከ ቤንች ማጂ ዞን ዋና ከተማ ሚዛን ተፈሪ ድረስ የተጣሉትን እና በየመንገድ ዳር*

*ይኖሩ የነበሩትን በበሽታው የተያዙ ህጻናት በመሰብሰብ በባቹማ እና በሻሻ ከተሞች መካከል ባለ ጫት በተሰኘ ቦታ በማስፈር እና እንዲቋቋሙ በማድረግ ትልቅ ለውጥ መጥቷል፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ አባላትም የልጆቹን በአንድነት እና በጤና መኖር ሲያዩ፣ በሽታው በመነካካት የሚተላለፍ ቢሆን የሚያግዟቸው ሰዎች ላይም ይተላለፍ ነበር በማለት ትልቅ የግንዛቤ ለውጥ እያመጡ ነው፡፡ አሁን አሁን ልጆቻቸውን መግደል እና አርቆ መጣል እየተተወ መጥቷል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡*

በአጠቃላይ የሚጥል በሽታ አሁን ድረስ የክፉ ነገር ምሳሌ እና መርገም ተደርጎ የሚወሰድ የበሽታ ዓይነት ነው፡፡ የደጋው አካባቢ ኗሪ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሽታው የፈጣሪ ቁጣ አለመሆኑን እየተቀበለ ቢሆንም በቆላው አካባቢ ግን እምነቱ አሁንም ድረስ እንዳለ ነው፡፡

## 3.7 ማኅበረሰባዊ ተቋም

በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ ከስልሳ በላይ ጎሳዎች ይገኛሉ፡፡ እኒህ ጎሳዎች የየራሳቸው የጎሳ መሪ፣ ወይም ንጉሥ አላቸው፡፡ አንድ የጎሳ መሪ የራሱን ጎሳዎች የሚያስተዳድረው ራሱ ነው፡፡ እንዲህ በመሆኑም እነዚህን ጎሳዎች ሁሉ ጠምሮና ደምሮ የሚገዛ አንድ ወጥ የሆነ መሪ የለም፡፡ እንደ አቶ ብርሃኑ እና አቶ በድሉ ገለጻ ከእነዚህ ከስልሳ በላይ ከሆኑ ጎሳዎች ውስጥ "ቦሊ፣ ማጂና፣ ኩታ፣ ጃና፣ ማጂና፣ ወጀራንታ፣ ሻልሺ፣ ጋርዎ፣ ጊስማሮ፣ ለማ፣ ዳጋን የተሰኙት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ብርሃኑ ወርቁ፣ እና አቶ በድሉ ካሳ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡

የመኤኒት ብሔረሰብ በተለያዩ የጎሳ መሪዎች የሚመራና የሚተዳደር በመሆኑ አንድ እና ጠንካራ ማዕከላዊ አስተዳደር ፈጥሮ መታየት እንደልቻለ፣ የራሱ የሆነ ፖለቲካዊ ትስስር እንዳልኖረው Aweke ይገልጻሉ፡፡ "መኤኒቶች የጠነከረ የእርስበርስም ሆነ የፖለቲካ ትስስር የላቸውም፡፡ እያንዳንዱ የመኤኒት ጎሳ የራሱ ሆነ መሪ፣ ማለትም ኮሞሩትስ አላቸው፡፡" (Aweke, 2007፣111)

መኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ ከስልሳ በላይ ጎሳዎች ያሉ ሲሆን ሁሉም በባላባቶች ወይም በጎሳ መሪዎች የሚመሩ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ  እንደ ባላባቶች ሁሉ ቃልቾችና የአገር ሽማግሌዎች ህዝቡን በመምራት፣ በመገሰጽና በመምከር

ትልቁን ድርሻ እየተጫወቱ ይገኛሉ፡፡ (በድሉ ካሳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 2008 ዓ.ም፣ ባቹማ)

## 3.8 ባሕላዊ የፍትሕ ሥርዓት

የመኤኒት ብሔረሰብ ለዘመናት ራሱን በራሱ ሲያስተዳድርባቸው የኖረባቸው ባህላዊ የፍትሕ ሥርዓታት አሉት፡፡ እነሱም ኮሞሩት፣ ቃልቻ፣ እና የሀገር ሽማግሌዎች ናቸው፡፡

### 3.8.1 ኮሞሮት

ኮሞሮት ጎሳ መሪ ማለት ሲሆን ሁሉም ጎሳዎች የራሳቸው መሪ፣ ወይም ኮሞሩት አላቸው፡፡ በአንድ ጎሳ ውስጥ የመጨረሻው እና ትልቁ የሥልጣን እርከን የኮሞሩቶች ነው፡፡ በሥራቸው ያለውም ጎሳ የእነሱን ትዕዛዝ የማክበር እና የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡ የኮሞሩቶች ሥልጣንም የሚመነጨው ከአምላክ እንደሆነ ስለሚታመን ስዩመ- አምላክ መሆናቸው ሁሉም የጎሳው አባል ይቀበላል፡፡ "ኮሞሩት የሚመረጠው በአምላክ ቱማ ፈቃድ ነው፡፡ ኮሞሩቶች ባሕላዊም ሃይማኖታዊም ገጽታ አላቸው፡፡ አንዳንድ ኮሞሩቶች ዝናብ የማዝነብ ሥልጣንም አላቸው፡፡ እነሱ በአምላክ እና በሕዝቡ መካከል ያሉ ተደርገው ይታመናሉ" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ በድሉ ካሳ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡ አንድ ኮሞሩት የሥልጣን ዘመኑ የሚያበቃው ሲሞት ብቻ ነው፡፡ እርሱ ሲሞትም የሚቀጥለው ኮሞሮት በአምላክ ፈቃድ ይተካል፡፡ "ኮሞሩት እስካልሞተ ድረስ ሥልጣኑን ጠብቆ ይኖራል፡፡ እርሱ ሲሞት ከልጆቹ ውስጥ አምላክ ቱማ የመረጠውና የፈቀደለት ልጅ ሥልጣኑን ይረከባል" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ በድሉ ካሳ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡

ኮሞሩቶች ከተራው ማኅበረሰብ ገለል ያሉ፣ ጽሞናን የሚያዘወትሩ፣ የሚመገቡትን የሚመርጡ፣ በክንዳቸው ላይም የኮሞሩትነት መገለጫ የሆነ የዝሆን ጥርስ እና አምባር በክንድ ላይ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ አንድ ኮሞሩት ሲሞት ተተኪው የሚመረጥበትን ሥርዓትና ሂደት አቶ በድሉ እና አቶ ብርሃኑ እንደሚከተለው ያብራሩታል፡፡

*ኮሞሩት ከሞተ በኋላ ወደ ቀብር ሳይሄድ የእርሱ ልጆች እና የቅርብ ሰዎች እንዲሁም የአካባቢ ሽማግሌዎች ይሰበሰባሉ፡፡ ሁሉም በጸጥታ ተቀምጠው ዓይኖቻቸውን ጨፍነው፣ የእጆቻቸውን መዳፍ ጨብጠው እንዲቀመጡ ይደረጋሉ፡፡ ከዚህ በኋላ አምላክ ቱማ የመረጠው ሰው በእጁ ምልክት ይዞ ይገኛል፡፡ ይሄ የተመረጠ ሰው እጆቹ ተከፍተው ሲታዩ የፍየል በጠጥ፣ የስንዴ፣ የማሽላ ወይም ሌላ ተመሳሳይ አዝርዕት ይዞ ይገኛል፡፡ ይሄንንም የሚያረጋግጥ የተመረጠ ሽማግሌ ሥርዓቱን ይመራል፡፡ አምላክ ቱማ የመረጠው ሰው ከታወቀ በኋላ ቀጣዩ ንጉሥ/ ኮሞሩት አባቱ ያደርግ የነበረውን የዝሆን ጥርስ እና አንባር በክንዱ ላይ ያደርጋል፡፡ በዚያው ቀን ወራሹ ከታወቀ በኋላ፣ እሱ በቤት ውስጥ ሲቀር ሌሎቹ አባታቸውን ለመቅበር ይሄዳሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ብርሃኑ ወርቁ እና አቶ በድሉ ካሳ፣ ህዳር 2010ዓ.ም ባቹማ)፡፡*

ኮሞሩቱ በጎሳው ውስጥም ይሁን ከሌሎች ጎሳዎች ጋር የሚፈጸሙ ግጭቶችን በመፍታት፣ የጎሳውን ውስጣዊ እና ውጫዊ መስተጋብር በማስጠበቅ፣ ፍትሕን እያሰፈነ ሕዝቡን ይመራል፡፡

### 3.8.2 ኘራይ

አብዛኛው የመኤኒት ብሔረሰብ አባል በባሕላዊ ሃእምነት ያምናል፡፡ በመሆኑም ኘራይ በስፋት የሚገኝ አንድ የፍትሕ ሥርዓት ማካሄጃ ተቋም ነው፡፡ በአማኞቻቸው ዘንድ ኘራይዎች ሁሉን የማወቅ ሥልጣን እንዳላቸው የሚታመኑ፣ የተፈሩ፣ እና የተከበሩም ናቸው፡፡ ከዘመናዊው የፍትሕ ሥርዓት ጋርም በጋራ የሚሠሩ እና የታወቁም ናቸው፡፡ አቶ ሻልታ ይሄንኑ ሲገልጹ "በመኤኒት፣ በአብዛኛውና በቆላው ኗሪ ኘራይ በጣም የሚፈራ እና የሚከበር ነው፡፡ ከእሱ የሚሠወር ነገር እንደሌለ፣ ጥፋትንም መደበቅ ከፍተኛ ቅጣትን በራስና በቤተሰብ ላይ እንደሚያመጣ ይታመናል፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ሻልታ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡

በመኤኒት ብሔረሰብ በአብዛኛው እማኝ እና ማስረጃ ለማይገኝላቸው እና በስውር ለተፈጠሩ ችግሮች መፍትሔ የሚሰጠው አካል ይሄው የኘራይ የፍትሕ ሥርዓት ነው፡፡ ጉዳዩ ከሚታየው ይልቅ ወደማይታየው ወደ ሥነ- ልቡናዊ እና ምግባራዊ ጥያቄዎች ስለሚያደላ ነው፡፡ በኘራይ ፊት የሚቀርብ ተበዳይ ጉዳዩ ማስረጃ ስለማይቀርብበት ኘራዩ በውቃቢው እና ባለው ኃይል በጉዳዩ መፍትሔ እንዲያበጅለት የሚጠይቅበት፣ ተከሳሽም ቀርቦ መሃላ እና እርግማንን

የሚቀበልበት ሥርዓት ነው፡፡ ተከሳሽ ዋሽቶ ከሆነ ዘሩ ከምድር ተጠራርጎ እንዲጠረግ፣ ወይም ተለቅልቆ እንዲደፋ እንዲምል ይደረጋል፡፡ "ኘራይ በጣም ስለሚፈራ የተካካዱ ሰዎች በፊቱ ቀርበው ይጠየቃሉ፡፡ ጉዳዩን እንዳደረገ የተጠረጠረ ሰው በኘራዩ ፊት ተጠርቶ ይምላል፡፡ መካካድ ካለም ተጠርጣሪ የኘራዩን ግቢ ጠርጎ፣ ወይም በቀርከሃ ላይ (እንደ ማስታጠቢያ የሚገለግል )ያለ ውኃ አለቅልቆ እንዲደፋ ይደረጋል" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ሻልታ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡ ይሄንን ሀሳብ ኘራዩ አወቀም ይገልጹታል፡፡ "መሀላ ከባድ ነው፡፡ ብዙዎቹ ከፊቱ ሲቀርቡ እውነቱን ይናገራሉ፡፡ አልፎ አልፎ ዋሽተውና ምለው የሄዱ ሰዎች የደረሰባቸውን ቅጣትና የቤተሰብ እልቂት አይተው ያኔ ዋሽተንህ ነበር፣ ቀጣኸን ፣ አሁን ማረን እንክሳለን ብለው ይመጣሉ፡፡ ለመንግሥት አሳልፌ የሰጠኋቸውም አሉ" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ አወቀ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡

### 3.8.3 የሀገር ሽማግሌዎች

የአካባቢ ሽማግሌዎች የባሕላዊ የፍትሕ ሥርዓትን በማስፈጸም ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ ቀለል ያሉ ግጭቶችን፣ አልፎ አልፎም እንደ ሰው መግደል ያሉ ከባድ ወንጀሎችን በመዳኘትና ፍትሕን በመስጠት ማኅበረሰቡን ያገለግላሉ፡፡ እንደ አቶ ዋየች ገለጻ "ሽምግሌዎች ብዙ ጊዜ ቀለል ያሉ፣ የቤተሰብ እና የጎረቤታሞች ችግሮችን በመፍታት ዳኝነት በመስጠት የሚያገለግሉ ሲሆን፤ እንደ የግድያ ዓይነት ከባድ ግጭቶችንም በመፍታት ይሠራሉ፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ዋየች፣ ህዳር 2010ዓ.ም ባቹማ)፡፡

በአጠቃላይ የመኤኒት ብሔረሰብ አባላት ከላይ ባየናቸው መንገዶች በባሕላዊ የፍትሕ ሥርዓታቸው አማካይነት፣ ከቀላል እስከ ከባድ፣ በግልጽ ከሚፈጸም እስከ የተሠወረ ወንጀል ድረስ ያውን ችግር በመፍታት ሕዝቡ ሰላምና ደህንነቱ ተጠብቆ እንዲኖር በማድረግ ሕልውናቸውን አስጠብቀዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. የመኤኒት ብሔረሰብ የአፈጣጠር ሚት

የመኤኒት ብሔረሰብ የአፈጣጠር ሚት የሚጀምረው ከአምላክ ቱማ ወይም የሪ ነው፡፡ ቱማ ወይም የሪ የመኤኒቶች አምላክ ከመሆኑም በተጨማሪ ሰማይና ምድርን፣ የሰውን ልጅ እና ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ እሱ እንደሆነ ይታመናል፡፡

> *በመጀመሪያ አምላክ ቱማ ነበረ፡፡ እሱ መኖሪያው በሰማይ ነበር፡፡ አምላክ ቱማ ሌላ ስምም አለው፡፡ የሪ በመባልም ይጠራል፡፡ አምላክ ቱማ ሰማይና ምድርን ፈጠረ፡፡ ወንዙን፣ ተራራውን፣ ሜዳና ሸለቆውን፣ ሁሉንም እርሱ ፈጠረ፡፡ በምድርም ላይ ያሉትን ፍጥረታት ሁሉ ፈጠረ፡፡ አምላክ ቱማ ከዚህ በኋላ የመጀመሪያ የሆነውን ሰው፣ የመኤኒቶችን ሁሉ አባት በምድር ላይ ፈጠረው፡፡ የመጀመሪያውን ሰው ናያሞንን በምድር ላይ ፈጠረው፡፡ የፈጠረው ሰው ናያሞንን መኤኒት ብሎም ስም አወጣለት፡፡ መኤኒት ማለት ሰው ማለት እንደሆነም ነገረው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ብርሃኑ ወርቁ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡*

አምላክ ቱማ መጀመሪያ የፈጠረውን ሰው ናያሞን ብሎ ስም እንዳወጣለት ሁሉ፣ እሱም ለወለዳቸው ልጆቹ ስም አውጥቶላቸዋል፡፡ "ከዚያም የናያሞን ዘር በምድር ላይ በዝቶ እንዲኖር፣ ልጆችንም ከእሷ እንዲያገኝ ሚስት ፈጠረለት፡፡ ናያሞን እና ሚስቱ በተከታታይ ሦስት ወንድ ልጆችን ወለዱ፡፡ የመጀመሪያ የሆነውን ልጃቸውን "ባንጃ" በማለት ስም አወጡለት፡፡ ሁለተኛውን ልጅ "ቦሹ" ብለው ሰየሙት፣ ሦስተኛውን ልጅ ደግሞ "ኮሊ" ብለው ጠሩት" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ በድሉ ካሳ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡

በዚህ ሁኔታ የሚጓዘው የመኤኒት ብሔረሰብ የአፈጣጠር ሚት በአምላክ ቱማ ፈቃድ ወደዚህ ምድር የመጡት ሰዎች፣ በተለይም ናያሞን እና ሚስቱ ተከታታይ ልጆችን በማፍራት በተፈጠሩባት ምድር መብዛት መቀጠላቸውን ይተርካል፡፡ ይሄንኑ የትረካ ምዕራፍ ይዘን ስንጓዝ፣ በአምላክ ፍቃድ በምድር ላይ እየበዙ ለሄዱት ልጆች አምላክ ቱማ እንዴት ባለው ጥበብ እና ኃይል በምድር ላይ መኖር እንዳለባቸው፣ አንዱም ከአንዱ በተለየ ሁኔታ እንዴት ተከባብረው መኖር እንደሚችሉ ጥበብና ኃይል ይሰጣቸዋል፡፡ አቶ ብርሃኑ አምላክ ቱማ ለናያሞን ልጆች ልዩ ኃይልን እንደሰጣቸው ይናገራሉ፡፡ "ናያሞን እና ሚስቱ

ልጆችንም ወለዱ፡፡ ዘራቸውም እንዲሁ መብዛት ጀመረ፡፡ አምላክ ቱማ አንድ ቀን የናያሞንን ሦስት ወንድ ልጆች ሰብስቦ፣ በዚህ ምድር ላይ ሲኖሩ፣ በምን ጥበብ እና ኃይል መኖር እንዳለባቸው ነገራቸው" (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡ አቶ በድሉም ሦስቱ ልጆች ስለ ተሰጣቸው ኃይልና ሥልጣን እንዲህ ይላሉ፡፡

> *አምላክ ቱማ የመጀመሪያውን ልጅ ባንጃን ጠርቶ በምድር ላይ ሲኖር፣ የእሱ መከበሪያ፣ ዋና መተዳደሪያ ጥበብ ዝናብን የማውረድ እንደሆነ ነገረው፡፡ የባንጃ ዘር ዝርያ ሁሉ በዚህ መክሊት እንዲተዳደሩ፣ ሰማይን የመዝጋትም ሆነ የመክፈት ሥልጣን እንዲኖራቸው ፈቀደለት፡፡ መኤኒት የሆነ ሁሉ ቱማን አክብሮ እንዲኖር፣ ባንጃንም አክብሮ በዝናብ ላይ ኃይል እንዲኖረው፣ ስለመረጠው በዘሮቹ ሁሉ እንዲከበር፣ ወንድሞቹንም ይሁኑ የእሱን ዘሮች በማያከብር መኤኒት ላይ ሰማይን እንዲዘጋባቸው፡፡ ነገር ግን ተጸጽተው በለመኑት እና ይቅርታ በጠየቁ ጊዜ መልሶ ዝናብ እንዲያወርድላቸው ኃይልን ሰጠው፡፡ ከእሱ በኋላ የሚመጣው የዘሩ ተከታይ ሁሉ ይሄንን ውርስ እየተቀበለ እንዲኖር ፈቀደለት፡፡ ባንጃ አምላክ ቱማ የሰጠውን ጥበብ አድንቆና አመስግኖ ተመለሰ፡፡*
>
> *አምላክ ቱማ፣ ሁለተኛውን የናያሞን ልጅ ቦሹን ወደ ፊቱ እንዲቀርብ አድርጎ እሱ ደግሞ በእንስሳት፣ በአራዊት እና በነፍሳት ላይ እንዲሰለጥን፣ ሥልጣን በእነሱ ላይ እንዲኖረው፣ መተዳደሪያው እንዲያደርጋቸው ፈቀደለት፡፡ ቦሹ የቱማ ፍጥረቶች የሆኑትን እንስሳትን፣ አራዊትን እና ነፍሳትን እንዲያዝ፣ እንዲገስጽ፣ እንዲያሰማራ፣ በእነሱ ላይ ንጉሥ እንዲሆን ፈቀደለት፡፡ መኤኒት የሆነ ሁሉ ባያከብረው ቢያስከፋው፣ የመረጠውን እና ኃይል የሰጠውን ቱማን አቃሏልና በአራዊቱ፣ በእንስሳቱ እና በነፍሳቱ እንዲቀጣቸው ነገረው፡፡ ነገር ግን ምህረትን በጠየቁ ጊዜ ያሰማራቸውን እንዲሰበስብ አስገነዘበው፡፡ ቃል ኪዳኑም ለልጅ ልጅ እንዲተርፍ እሱና ዘሩም ለአምላክ ቱማ ተገዢ ሆነው እንዲኖሩ ነገረው፡፡*
>
> *ሦስተኛው የናያሞን ልጅ ኮሊ ወደ አምላክ ቱማ ቀርቦ፣ እሱ ደግሞ በምድር ላይ ባሉ ዕፅዋት ላይ እንዲሰለጥን፣ ገንዘቡ እንዲያደርጋቸው፣ የልምላሜ ንጉሥ እንዲሆን ሥልጣን ሰጠው፡፡ የእሱም ቃል ኪዳን እንደ ወንድሞቹ ሁሉ፣ ለዘሩ ሁሉ የተጠበቀ እንደሚሆን ነገረው፡፡ ሦስቱም የናያሞን ልጆች በምድር ላይ እየበዙ፣ ከአምላክ ቱማ በተሰጣቸውም ሥልጣን ሕዝባቸውን እያስተዳደሩ መኤኒቶች ባሉበት ሁሉ እስከዛሬም እየተገለገሉ ይኖራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም ባቹማ)፡፡*

ከላይ የቀረበው የአፈጣጠር ሚት ትረካ የሚገልጸው፣ የመኤኒት ብሔረሰብ አፈጣጠር "ከምንም ነገር መፈጠር" በሚለው የፈጣጠር ሚት ምዳቤ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡ ሚቱ እንደሚያስረዳው የመኤኒት ምድርና ሰማይ፣ የሚታየውና የማይታየው ሁሉ፣ የሰው ልጅን ጨምሮ የተፈጠረው ኃይል ባለው፣ ሁሉን ማድረግ በሚችለው አምላካቸው በቱማ ነው፡፡ ሚቱ ምድርና ሰማይ፣ የሚታየውና የማይታየው ፍጥረታት እንዴት ባለው ሂደት፣ እንዲሁም በመቼ እና በምን አኳኋን እንደተፈጠሩ ባይገልጽም የፈጣሪያቸውን ማንነት እና የመጀመሪያው የመኤኒቶች አባት ናያሞን መሆኑን ይገልጻል፡፡ የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖት የአፈጣጠር ሚቶች የመጀመሪያው የሰው ፍጥረት አዳም/አደም እንደሆነ እንደሚገልጹት ሁሉ ለመኤኒቶች ናያሞን የመጀመሪያው የሰው ዘር ነው፡፡ አዳም እና ሚስቱ ሔዋን አቤልና ቃየል የተሰኙ ልጆችን እንደወለዱ ሁሉ ናያሞን ደግሞ ሦስት ወንድ ልጆች እንደወለደ የአፈጣጠር ሚቱ ያስረዳል፡፡

የቀዳሚዎቹ የመኤኒት ብሔረሰብ አባላት፣ የባንጃ፣ የቦሹ እና የኮሊ ዘሮች በጊዜ ሂደት በተለያዩ አካባቢዎች መኖራቸውን ቀጠሉ፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች እና አጋጣሚዎችም ቀያቸውን እየለቀቁ፣ ወንዝ እየተሻገሩ፣ ጋራ እያቋረጡ በተለያዩ አካባቢዎች ሠፈሩ፡፡ በተለይም በመኤኒት ጎልድያ እና በመኤኒት ሻሻ ወረዳዎች በዋንኛነት እንዲሁም በጉራ ፈርዳ ወረዳ በጥቂቱ ከተሙ፡፡ አቶ ሻልታ ይሄንኑ ሲያብራሩ፡፡

> *መኤኒቶች ከጥንት፣ ከአምላክ ቱማ ከተፈጠርን ዘመን ጀምሮ፣ እየበዛን፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች ከቀያችን እየፈለስን፣ ብዙ ርቀትን እየተጓዝን፣ ወንዝና ተራራ እያቋረጥን በሻሻ፣ በጌሻ፣ በባቹማ፣ በጋችት፣ በሌሎችም ወረዳዎች ሰፈርን፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን አምላክ ቱማ፣ ኮሞሩቶች ወይም የጎሳ መሪዎችን ስለሰጠን አንድ ኮሞሩት ሲሞት ከልጆቹ ውስጥ አምላክ ቱማ የመረጠው እየተተካ እየመራ፣ የተለያዩ ችግሮች፣ በሽታዎች ሲያጋጥሙን ተአምራትን የሚያደርጉ፣ ዝናብ እያዘነቡ፣ በሽታ እየተከላከሉ፣ የሰው፣ የአራዊትም ይሁን የነፍሳት ድንገተኛ አደጋ እና ጥቃት ሲመጣብን ቱማ ኃልና ሥልጣን የሰጣቸው ሰዎች፣ ብዙ ተአምራትንና ድንቅን እያደረጉ እዚህ ደርሰናል ( ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር፣ 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡*

በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ የአንድ ጎሳ አባል የሆኑ ሰዎች ጋብቻ ስለማይፈጽሙ፣ የራሳቸው ከሆነ ጎሳ ጋር አይጋቡም፡፡ በዚያው ልክ የጎሳ ስብጥሩም እየጨመረ፣ ከአምላክ ኃይልን እንደተቀበሉ የሚታመንባቸውም ጎሳዎችም በዘራቸው እያስተላለፉት እየበዙ መጥተዋል፡፡ ትውልድ ትውልድን እየተካውም አምላክ ቱማ ለመረጣቸው የሰጠው ኃይልና ጥበብም እስከ ዛሬ ድረስ እንደተጓዘ ይታመናል፡፡ አቶ በድሉ ካሳም ይሄንኑ ይገልጻሉ፡፡

> *እንደ ብሔረሰቡ ሥርዓትና እምነት፣ ጋብቻ የራሱ ሥርዓት አለው፡፡ በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ በአንድ ጎሳ መካከል ጋብቻ አይፈጸምም፡፡ በመሆኑም አንዱ ጎሳ ከሌላው ጎሳ ጋር እየተጋባ፣ የተለያዩ ጎሳዎችም እየተፈጠሩ ሄዱ፡፡ በዚያው አንጻርም አዝናቢ ከሆነው የባንጃ ዘር፣ በእንስሳትና በአራዊት ላይ ሥልጣን ካለው የቦሹም ሆነ በምድር ዕፅዋት ላይ ከተሾመው ከኮሊ ዘር የሚመዘዙ ሌሎች ጎሳዎች እየበረከቱ ሄዱ፡፡ ጎሳዎቹም በዚያው ልክ ከአምላክ ቱማ የተሰጠውን ሥልጣን ለልጅ ልጆቻቸው እያስተላለፉት በተለያዩ አካባቢዎች መኖራቸውን ቀጠሉ፡፡ አሁንም እየኖሩ ነው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር 2010ዓ.ም፣ ባቹማ)*

አቶ ብርሃኑ ወርቁ እና አቶ በድሉ ካሳ በዚህ ዘመን የሚያውቋቸውን የዝናብ ንጉሥ እና ንግሥቶች፣ ከነሚኖሩበት አካባቢ ጭምር በስም ጠርተው እንደሚከተለው ይጠቅሷቸዋል፡፡ “በጣም ታዋቂ ከሆኑት እና በዚህ ዘመን ካሉት አዝናቢዎች ውስጥ፣ ሻያ ይጠቀሳል፡፡ ሻያ በጌሻ አካባቢ ያለ ነው፡፡ ኬኒ ቀኛዝማች ጋሊ ደግሞ በሻሻ አካባቢ ነበሩ፡፡ ሻያም ሆነ፣ ኬኒ ቀኛዝማች ጋሊ የጎሳ መሪዎች ጭምር ናቸው፡፡ ሌማው ጃና የሚባሉ የዝናብ ንግሥትም በባቹማ አቅራቢያ ባለ ቀበሌ ውስጥ አሉ” (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር 2010ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡

በመኤኒት ብሔረሰብ የአፈጣጠር ሚት እሳቤ ዝናብ የማዝነብ ኃይል የተሰጠው የባንጃ ዘር፣ በጊዜ ተዋረድ እና በጋብቻ ሂደት ውስጥ ከባንጃ ዘር በተጨማሪ ሥልጣኑን ሌሎች እያጋሩ ኖረዋል፡፡ ከአምላክ ቱማ የሚሰጠው ዝናብ የማዝነብ ኃይል ከልጅ ወደ ልጅ የሚተላለፈው በዘር ነው፡፡ በአንድ አካባቢ ያለ ዝናብ አውራጅ በዘመኑና በአካባቢው ሥራውን ሲሠራ የኖረ ሰው ሲሞት፣ ከልጆቹ በኩሩ ሥራውን ይወርሳል፡፡ በመኤኒት ብሔረሰብ በባቹማ ወረዳ በኮላይ እና በጠንክር ቀበሌዎች ድንበር የሚኖሩትና በዝናብ አዝናቢነታቸው የሚታወቁት ወ/ሮ ሌማው ጃና ዝናብ የማዝነብንና

እንዳይዘንብም የማድረግ ሥልጣንን ያገኙት ከእናታቸው በውርስ መሆኑን ይናገራሉ፡፡

> *እኔ የአዝናቢ ዘር ነኝ፡፡ ጎሣዬ ዝናብ አዝናቢ ጎሣ ነው፡፡ ጎሣዬ ወዳጃደራይታ ነው፡፡ ይሂ ዘር ከጥንት አዝናቢዎች ወገን የመጣ ዘር ነው፡፡ በአካባቢያችን ዝናብ ሲጠፋ፣ ድርቅ ሲመጣ፣ ሕዝቡ ሲቸገር በአካባቢው ዝናብ ስታወርድ የነበረች እናቴ ነበረች፡፡ እናቴ በአካባቢው በጣም ተከብራ የምትኖር ትልቅ ሴት ነበረች፡፡ እኔ እርሷ የምታደርጋቸውን ሥራዎች ሁሉ እያየሁ ነበር ያደግሁት፡፡ እናቴ ስትሞት እኔ ተረከብኩ፡፡ እኔ የመጀመሪያ ልጅ ነኝ፡፡ እናቴ ስትሞት ቀበርናት፡፡ ከዚያ በኋላ ዝናብ ማዝነቡን ቀጠልኩት፡፡ ያኔ ገና ልጃገረድ ነበርኩ፡፡ አላገባሁም ነበር፡፡ በደርግ ጊዜ ነበር፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በዚህ አካባቢ ዝናብ ማውረድ ሥሥራ ኖርኩ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ኮላይ)፡፡*

በአንፃሩ በዚያው በኮላይ አካባቢ በዝናብ አዝናቢነታቸው ታዋቂ ከነበሩት ውስጥ አንዱ የነበሩት ሰው ሦስተኛ ልጅ የዝናብ ማዝነብ እጣ ፈንታ ወደ እሱ እንዳልተሸጋገረ እና ይኸውም እሱ ለአባቱ ሦስተኛ ልጅ በመሆኑ የመጣ እንደሆነ ይናገራል፡፡ ‘‘እኔ ተወልጄ ያደኩት እዚህ ኮላይ ነው፡፡ አባቴ በጣም ታዋቂ አዝናቢና የዝናብ ባላባት ነበር፡፡ አባቴ ሲሞት አዝናቢነቱን የወረሰው ታላቅ ወንድማችን ነበር፡፡ እሱ ድንገት ሲሞት ልጅ አልነበረውምና በዚያው ቀረ” (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ኮሬ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ኮላይ)፡፡



ከግራ ወደ ቀኝ አስተርጓሚው አቶ ብርሃኑ ወርቁ፣ የአዝናቢው ልጅ አቶ ኮሬ  እና  አጥኚው (ፎቶ በአቶ በድሉ ካሳ)፡፡

አቶ ኮሬ አምላክ ቱማ መኤኒቶችን፣ ዝናብንና አዝናቢዎችን እንዳስተሳሰራቸው ያምናሉ፡፡ አፈጣጠራቸው ከዝናብ፣ ከከብቶችና ከዕፅዋት ጋር የተጋመደ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ማንኛውም ሰው ማዝነብ እንደማይችልና ጉዳዩ ከተፈጥሮ እና ከፈጣሪ ጋር የተያያዘ መሆኑን እሳቸውም ሆነ የአካባቢያቸው ሰው አጥብቆ እንደሚያምን ገልጸው፣ አምላካቸው ቱማ መኤኒቶችን ሲፈጥር እንዴት እና በምን መኖር እንደሚችሉ አዘጋጅቶ እንደሆነ፣ ለሰው ልጅችም ቀዳሚው ነገር ዝናብ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ዝናብ ከሌለ ምድር ምንም ዘር እንደማትሰጥ፣ ወንዞች እንደማይኖሩ፣ ወንዞች ከሌሉ ከብቶች የሚግጡት ሳርም ሆነ፣ ለምግብነት የሚውል ዛፍ እንደማይኖር አብራርተው አዝናቢ ስለነበሩት አባታቸው፣ ከእናታቸው የሰሙትን ትረካ እንዲህ ያቀርሉ፡፡

> *የተመረጡ ታላላቅ ሰዎቻችንም ከአምላካችን የተሰጣቸው ኃይል አለ፡፡ የእኔ አባት አዝናቢ ነበር፡፡ ትልቅ አዝናቢ ነበር፡፡ ሕይወቱ እንደማንኛውም ዓይነት ሰው አልነበረም፡፡ ከንግግሩ ቁጥብ፣ የሚበላቸው ምግቦች የተለዩ እና የተመጠኑ ነበሩ፡፡ ከብዙ ሰው ጋርም ግንኙነት የለውም የሚገናኘው ከጥቂት ረዳቶቹ ጋር ነው፡፡ ብዙ ጊዜውን የሚያጠፋው በዝምታ ነው፡፡ ዝም ብሎ ቁጭ ይላል፡ ፡ የሚረብሸው ነገር አይፈልግም፡፡ እየጸለየ የሚያሳልፍ ዓይነት ሰው ነው፡፡ ከአምላክ ቱማ ጋር በደንብ የሚገናኝና የሚያወራ ሰው ነው፡፡ አባቴ የሆነ የሆነ ሰዓት ላይ የሚያወራው ነገር አለው፡፡ ወደ ውጪ ይወጣና ወደ ጨረቃ ፊቱን አዙሮ ያወራል፡፡ ጥቂት ጊዜ ለማዳመጥ ሞክሬ ነበር፡፡ የሚሰማው የአባቴ ድምጽ ብቻ ነው፡፡ ግን ንግግር እንደሆነ ያስታውቃል፡፡ የአባቴ ድምጽ የፍርሃት እና የታዛዥነት ዓይነት ነው፡፡ አሁን አድጌ ሲገባኝ ስለ ሕዝቡ አምላክ ቱማ ጋር እየተነጋገረ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ከጥንትም የአዝናቢ ዘር ነው፡፡ በኛ አካባቢ ያለው ሕዝብ በየዓመቱ የተመጣጠነ ዝናብ እንዲያገኝ የሚያደርገው አባቴ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ አልፎ አልፎ ሰው ስለሚያጠፋ እና አባቴንም ይሁን አምላክን ስለሚያስቆጣ ቅጣት ይላክባቸዋል፡፡ የእኔ አባት ዝናብ እንዳይኖርም እንዲኖርም ማድረግ ይችላል፡፡ እሱ የተመረጠ ሰው ነው፡፡ ሁሉም ይሄንን ያምናል፡፡ ካጠፋና ችግር ካጋጠመውም መጥቶ ይቅርታ ይጠይቃል፡፡ (ዝኒ ከማሁ)፡፡*

እንደ አቶ ኮሬ ገለጻ አዝናቢነት ረጅሙን የብሔረሰብ የአጠጣጠር ታሪክ መሠረት አድርጎ የመጣ እና ለዚሁ የተመረጡ ሰዎችም ኃይሉን የሚያገኙት ከአምላክ መሆኑን ነው፡፡ የአባታቸው የአኗኗር ሥርዓትም ተመስጧዊ እና ጥሞና የተሞላበት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ይሄም አባታቸው ከቱማ ጋር ስለሚገናኙ ራሳቸውን በተለየ ቅድስና ለማኖር እንደሚጥሩ እንደሚያስገነዝብ ይገልጻሉ፡፡

ከፈጣሪ የሚሰጠው ኃይል በምድር እና በሰማይ እንደሚሠራ፣ ኃይል የተቀበሉ ሰዎችም አስፈላጊ ነው ብለው ባመኑት ሰዓትና ጊዜ የተሰጣቸውን ኃይል መጠቀም እንደሚችሉ ትረካቸው ያስረዳል፡፡ በክርስትና ሃይማኖት ትረካ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነብዩ ኤልያስ ፀሐይን በገባኦን ምድር እንዳቆመ፣ ጨረቃን በኤላሞት ሸለቆ እንደገታ እንደሚተርክ ሁሉ በመኤኒትም ዝናብ እንዳይዘንብ ማድረግም ሆነ እንዲዘንብም ማስቻል የተመረጡት ሰዎች ሥራ እንደሆነ የአቶ ኮሬ ትረካ ይገልጻል፡፡

> *እኔ የአሥራ ሁለት ዓመት አካባቢ ልጅ እያለሁ በኛ አካባቢ ከነበረች አንዲት አዝናቢ ጋር የሆነውን አስታውሳለሁ፡፡ ሴትየዋም የአዝናቢ ዘር ናት፡፡ አዝናቢ ናት፡፡ የእኔም አባት አዝናቢ ነው፡፡ ሁለቱ ግን በጎሳ የተለያዩ ናቸው፡፡ በተዋሰነ አካባቢ ነው የሚኖሩት እና አንዳንዴ ሕዝቡም ማንኛቸው ይሻላሉ የሚል ጥያቄ አለው፡፡ አንዳንዶች አባቴን አንዳንዶች እሷን ይላሉ፡፡ ወደ እሷ አካባቢ ያሉትም ሴትየዋን የማስበለጥ ነገር ነበራቸው፡፡*
>
> *አንድ ቀን ግን ሁለቱም ተገናኙ፡፡ የተገናኙበት ምክንያት ዝናብ በአካባቢው መጥፋቱ ነው፡፡ በእሷ አካባቢ ያለውም በእኛ አካባቢ ያለውም ሰው መፍትሔ ፈልጎ ወደ ሁለቱም ጋ ሄደ፡፡ በዚህ ጊዜ ሁለቱም የሚገናኙበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ያኔ በሁለቱም አጎራባች ቀበሌ ያለው ሰው አንድም ሳይቀር ወጣ፡፡ ያኔ እኔ ከአባቴ ኮኮ/ረዳት ጋር አብሬ ወጣሁ፡፡ ሕዝቡ ዙሪያውን ሆኖ በጭንቀትና በፍርሃት ተውጦ ያየል፡፡ አባቴ እና ሴትየዋ ተገናኝተው ትንሽ አወሩ፡፡ በኋላ ላይ አባቴን ጠይቄ ምን እንዳወሩ ነግሮኛል፡፡ ያወሩት ዛሬ አምላክ ቱማ ኃይሉን የሚገልጥበት ቀን ነው፡፡ ኃይልሽ ይታያል እንዳላት ነግሮኛል፡፡ እሷም በተመሳሳይ የእሱን አዝናቢነት ለማየት እና በአካባቢው ማን እውነተኛ አዝናቢ እንደሆነ የሚታይበት ቀን መሆኑን እንደጠየቀችው ነግሮኛል፡፡ ጉዳዩ የፉክክር የሚመስል ቢሆንም ሁለቱም ግን በእርግጠኛነት እንደሚያደርጉት እምነት ነበራቸው፡፡ (ዝኒ ከማሁ)፡፡*

አቶ ኮሬ እንደገለጹት አንዳንዴ በአንድ አካባቢ ከአንድ በላይ የሆኑ አዝናቢዎች ሊኖሩ መቻላቸውን ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አጋጣሚ ደግሞ ቢያንስ በአማኞቹ ዘንድ የሚፈጥረው የሀሳብ ልዩነት መኖሩን እንረዳለን፡፡ አንዳንዴ ልዩነቱ በራሳቸው የልዕል ተፈጥሮ ኃይልን በያዙት እና አንዳንዴ ደግሞ በእነሱ አቅራቢያ ባለው ሰው አመለካከት የሚፈጠር ነው፡፡ በእስራኤላውያን የአፈጣጠር ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያ ምዕራፎች ላይ የምናገኛቸው የሙሴ እና

የተገዳዳሪዎቹ ታሪክም መነሻው ይሄው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሙሴ በአሮን እጅ ተአምራትን በማከናወን እንጨትን ወደ እባብነት ሲቀይር፣ ተገዳዳሪዎቹም ይሄንኑ እንዳደረጉ የብሉይ ኪዳን ትረካዎች ያስረዳሉ፡፡ (ዘጸአት 4፣ 4 - 5) በመኤኒትም እንዲሁ ሊፈጠሩ የሚችሉ አጋጣሚዎች መገኘታቸውን የአቶ ኮሬ ተከታዩ ትረካቸው ያስረዳል፡፡

> *. . . ከዚያ ሴትየዋ የእኔን አባት "እውነተኛ አዝናቢ ከሆንክ እስኪ በዚህ ትይዩ /በእጁ ቀጥታ መስመር እያሳየ/ ቀጥ አድርገህ አዝንብ" አለችው፡፡ አባቴም ከኮኮው ጋር ተነጋገረ እና የሚደረገውን ሥርዓት አድርጎ፣ በኮኮው አማካይነት በታረደ ዶሮ ደም እግሮቹን እና የእጅ ክንዶቹን ከተቀባ በኋላ ወደ አምላክ ቱማ ጸለየ፡፡ ወዲያው ኮኮው ከወንዝ በሾርቃ/ ቅል ያመጣውን ቀዝቃዛ ውኃ ደም በነካው አካሉ ላይ አፍስሶለት ታጠበው፡፡ አባቴ እንደታጠበ ወዲያው ከየት እንደመጣ የማይታወቅ ኮረት በረዶ የመሰለ ዝናብ ሴትየዋ አዝንብ ባለችው አቅጣጫ ቀጭን መሥመር ሠርቶ እንደ ሽቦ አጥር አድርጎ አዘነበ፡፡ ያኔ ሕዝቡ ሁሉ መሬት ሲደፋ እና ሲጮህ ትዝ ይለኛል፡፡ እኔ ተደፍቼ ነበር፡፡ ዝናቡ ሦስት አራት ደቂቃ ያህል ዘንቦ አበቃ፡፡ ከዚያ ሁሉም ከተደፋበት ተነስቶ ቀጣዩን ነገር አየ፡፡ ቀጥሎ የሆነው የእኔ አባት ሴትየዋን በተራዋ እሱ ባዘነበበት ተቃራኒ አቅጣጫ እንደሱ አድርጋ እንድታዘንብ ጠየቃት፡፡ ሴትየዋም በኮኮዋ አማካይነት አባቴ ያደረገውን ዓይነት አደረገች፡፡ ፊቷን አዙራ ደሙን በጭኖቿ ላይ አፈሰሰች፡፡ እሷም የሆነ ጸሎት ነገር አድርጋ የእሷ ኮኮ/ረዳት ቀዝቃዛው ውኋ አፈሰሰባት፡፡ ሴትየዋ ታጥባ ሳትጨርስ በተባለው አቅጣጫ ጥቁር ደመና ግጥም ብሎ ዝናብ ይወርድ ጀመር፡፡ ነገሩ በቦታው ለነበርነውም አስደንጋጭ ነበር፡፡ እሷም በአባቴ ተቃራኒ እንደ የሽቦ አጥር አድርጋ ዝናቡን አዘነበችው፡ ፡ ሰው አሁንም መሬት ተደፍቶ እየተንቀጠቀጠ ለመናቸው፡፡ ሴትየዋ እና አባቴ ጥቂት ካወሩ በኋላ ከረዳቶቻቸው ጋር ወደየ ቤታቸው ተመለሱ ከዚያ ቀን በኋላ ዝናብ በዝናብ ሆነ፡፡ ግን ከዚያ በፊት ረጅም ጊዜ አልዘነበም ነበር፡፡ ከዚያ ዘነበ፡፡ አባቴን የሚያመሰግኑ ብዙ ሰዎች ቤታችን ይመጡ ነበር፡፡ ብዙ ስጦታ ሲያመጡ ትዝ ይለኛል፡፡ እህል ያመጡ፣ ማር ያመጡ፣ ልብስ ነገር ያመጡ ነበሩ፡፡ አባቴ ከዝናብ ጋር የተሳሰረ በርካታ ታሪክ አለው፡፡ ግን ሁሌም ይሄንን የዝናብ ሥራ የሚሠራው የአምላክ ቱማ ቃል ኪዳን እንደሆነ እና እሱም ከአባት አያቶቹ የተረከበው እንደሆነ ይናገር ነበር፡፡ መኤኒት ሲፈጠር ከዝናብ፣ ከከብቶች እና ከምድር ጋር ነው፡፡ (ዝኒ ከማሁ)*

ዝናብ አዝናቢዎች፣ ከአምላክ ቱማ እንደተመረጡ እና መኖራቸውም ለማኀበረሰቡ ዋና ጥቅም እንዳለው የሚያምኑ ናቸው፡፡ ማኀበረሰቡም እነሱ በፈጣሪ ትዕዛዝና ምርጫ የተለዩ፣ የተመረጡ፣ የችግር ግዜ ደራሽ እንደሆኑ አምኖ ይቀበላል፡፡ አክብሮም ይኖራል፡፡ ማኀበረሰቡ ዝናብ ከሰማዩ ላይ የሚርቀው አንድም አምላክ ቱማ ሲቆጣቸው፣ አንድም አዝናቢዎች ራሳቸው ሲቆጡ እና ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማዩን ሲለጉሙት እንደሆነ ያምናሉ፡፡ አካባቢውን ድርቅ ሲመታው እና ዝናብ ሲጠፋ፣ ወንዝና ጅረቶች ሲነጥፉ፣ ልምላሜ ሲርቅ፣ ለሰውም ይሁን ለእንሰሳ የሚሆን ምግብ ሲጠፋ፣ ማኀበረሰቡ ለአቤቱታና ለምልጃ ወደ አካባቢው አዝናቢዎች ይሄዳል፡፡

"እንግዲህ ከአካባቢው ላይ ዝናብ ይጠፋል ተብሎ የሚታመነው በሁለት ምክንያት ነው፡፡ አንዱ አምላክ ቱማ በኛ በመኤኒቶች ላይ ሲቆጣ፣ አንደኛው ደግሞ በእሱ የተመረጡት አዝናቢዎቹ በተለያየ ምክንያት በሕዝቡ ላይ ተቆጥተው እንዳይዘንብ ሲያደርጉ ነው፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ብርሃኑ፣ ግንቦት 2011፣ ባቹማ) የኮላይ ቀበሌ ሊቀመንበር የሆኑት እና የአዝናቢዋ የወ/ሮ ሌማው ጃና የቅርብ ዘመድ አቶ ገብሬ እንደሚከተለው ያጠናክሩታል፡፡

> *"እኛ የምናምነው በሁለት ምክንያች ዝናብ ከአካባቢው እንደሚጠፋ እና ድርቅ እንደሚመጣ ነው፡፡ በአንደኛ ደረጃ የፈጠረን አምላክ ቱማ በኛ ተቆጥቶ ሊቀጣን፣ ሊያስተምረን፣ ወይ ሊወቅሰን ሲፈልግ እንዳይዘንብ ሲያደርገው ዝናብ ይጠፋል፡፡ ሁለተኛውና ደግሞ አዝናቢ የሆኑ ሰዎች በሕዝቡ ተበድለናል፣ ተከፍተናል፣ አዝነናል ሲሉ፣ ሰማዩ ላይ ደመና እንዳይኖርና እንዲሸሽ፣ እንዳይዘንብ፣ ደመናው ከአካባቢው እንዲጠፋ ሲያደርጉ ነው' (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ኮላይ)፡፡*

በመኤኒት ብሔረሰብ እምነት ሥርዓት ውስጥ ከሁለቱ በአንደኛው ምክንያት ዝናብ ከጠፋ ሁለቱንም ወገኖች፣ አምላክ ቱማን እና አዝናቢዎቹን ይቅርታ በመጠየቅና እርቅ በማውረድ ዝናብ እንዲመጣ ወይም እንዲዘንብ ለማድረግ ይጣራል፡፡

> *ዝናብ እንዳይዘንብ ያደረገው አምላክ ቱማ ከሆነ አካባቢው ጭር ይላል፡፡ ሰብሉ ይደርቃል፣ የዘሩት አይበቅልም፣ ውሎ አድሮ ትልቅ ችግር ይፈጠራል፡፡ በመሆኑም ሁኔታው በዚያው እንዳይቀጥልና የሰውም ሆነ የእንስሳት እልቂት እንዳይከሰት፣*

*ከአካባቢው በኀሳቸው፣ በባላባትነታቸው፣ በሃይማኖት መሪነታቸው ወይም በእድሚያቸው፣ ትልልቅ የሚባሉ ሰዎች ተመርጠው ወደ አዝናቢዎች ይሄዳሉ፡፡ ከዚያም እናንተን በድለናችሁ ከሆነ ይቅርታ አድርጉልን፣ ታረቁንና ዝናብ ይጣል፡፡ ዝናቡ እንዳይዘንብ ያደረገው አምላክ ቱማ ከሆነ ደግሞ እናንተ በኛ ፈንታ ይቅርታ ጠይቁልንና እንዲዘንብ አድርጉልን ብለው ይጠይቋቸዋል፡፡ ያኔ የዝናብ ንጉሦች ወይም ንግሥቶች ችግሩን ስለሚያውቁት፣ እንዲዘንብ ያደርጋሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ ብርሃኑ፣ 2011፣ ግንቦት፣ 2011ዓ.ም፣ ባቹማ)*

ሽማግሌዎች ይቅርታ ጠይቀውና መማለጃ አቅርበው ዝናብ እንዲዘንብላቸው እንደሚያደርጉ አቶ ገብሬም ያስረዳሉ፡፡ ‹‹የሄዱት ሽማግሌዎች አዝናቢዎች የተከፉበትን ሁኔታ ሰምተው፣ በሕዝቡ ስም ይቅርታ ጠይቀው የሆነ ስጦታ ይሰጧቸውና ይታረቃሉ፡፡ ከዚያ አዝናቢዎቹ ከአምላክ ኃይል የተሰጣቸው ስለሆኑ መስዋዕት አቅርበው እና ጸሎት ነገር አድርገው ያዘንቡታል (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011፣ ኮላይ)



ከግራ ወደ ቀኝ አጥኚው እና የኮላይ ቀበሌ ሊቀመንበር እንዲሁም የወ/ሮ ሌማው ጃና ዘመድ አቶ ገብሬ (ፎቶ በአቶ ብርሃኑ)፡፡

የዝናብ ንጉሦች/ንግሥቶች ራሳቸዉን ለማኅበረሰቡ እንደተሰጡ የአምላክ ቱማ አገልጋዮች አድርገው ስለሚያምኑ፣ ለአካባቢው ዝናብ እንዲጥል ከማድረግ በላይ ባላቸው ስልጣንና በተቸራቸው የልዕለ ተፈጥሮ ኃይል ጥበብ፣ ዝናብ ከተፈለገው በላይ በዝቶ ምርት እንዳይበላሽ፣ ሰብሉን በማሳው ላይ እንዳያረግፈው የማድረግ ተግባራቸውን እንደሚወጡ ይታመናሉ፡፡ አቶ በድሉ ይሄንን የአዝናቢዎቹን የተመጣጠነ የዝናብ ዑደት አስፈጻሚነት እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

> *"እነሱም ራሳቸውን ቆጥበው እና ከሌላው ሰው ገለል አድርገው፣ የጽሞና ኑሮ የሚኖሩ ናቸው፡፡ ሥራ ሲሠሩም ሆነ አብዛኛው ግንኙነታቸው በረዳታቸው በኮኮ አማካይነት ነው፣ በሰው እና በቱማ መካከል የአስታራቂነት ሚና እንዳላቸው ነው የሚታመነው፡፡ የአዝናቢዎች ዋና ሚና ዝናብ እንዳይጠፋ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ በዓመት ውስጥ የሚጥለው ዝናብ ተመጣጣኝ እንዲሆን ማድረግም እንደሆነ በማኅበረሰቡ ዘንድ ይታመናል" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ በድሉ ግንቦት 2011፣ ኮላይ)፡፡*

አዝናቢዎች በማኅበረሰቡ አኩርፈው ወይም ተቆጥተው አንዴ ዝናብ እንዳይዘንብ ካደረጉ በኋላ ያለ ስህተት ከሚተገብሯቸው ሥራዎቻቸው ውስጥ አንደኛው ማንኛውንም የሰውነታቸውን ክፍል ቀዝቃዛ ውኃ እንዲይነካቸው መጠንቀቅ ነው፡፡ "አዝናቢዎች ገላቸውን በቀዝቃዛ ውኃ አይታጠቡም፡፡ ጨርሶም ፊታቸውን ላይታጠቡ ይችላሉ፡፡ ቀዝቃዛ ውኃ ካልነካቸው ደግሞ ዝናብ አይዘንብም፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ኮሬ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ኮላይ) አዝናቢዎች ዝናብ እንዳይዘንብ ሲፈልጉ በቀዝቃዛ ውኃ ያለመታጠብ፣ የሁሉም አዝናቢዎች ተግባር እንደሆና ራሳቸውንም ከሰው እንደሚያገልሉ አቶ ሻልታም ያስረዳሉ፡፡ "አንዳንዶቹ ደግሞ ረጅም ጊዜ ከቤት አይወጡም፤ እንዳይዘንብ ሲፈልጉ ፈጽሞ ገላቸውን በቀዝቃዛ ውኃ አይታጠቡም" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡

የአዝናቢዎቹ ገላቸውን በቀዝቃዛ ውኃ አለመታጠብ ዋና ምክንያቱ ቀዝቃዛ ውኃ ከነካቸው የአሠሩት እንደሚፈታ፣ ያደረቁት ሰማይ በደመና እንደሚሞላ እና ዝናብም እንደሚጥል በመታመኑ ነው፡፡ አቶ ቢኒያም ይሄንኑ ሀሳብ ሲገልጹ "አዝናቢዎቹ ዝንብ እንዳይዘንብ ሲፈልጉ በቀዝቃዛ ውኃ አይታጠቡም፡፡ ቀዝቃዛ ውኃ ከነካቸው ዝናብ ይጥላል ብለው ያምናሉ" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ቢኒያም፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ሼቤንች)፡፡

ዝናብ ከጠፋ በኋላ፣ ከአካባቢው የተውጣጡ ሽማግሌዎች ወደ አዝናቢዎች ሄደው አዝናቢዎችን ይቅርታ ይጠይቃሉ፡፡ በማንኛውም መንገድ ላደረሱት ጥፋት ሕዝቡን ወክለው ይለምናሉ፡፡ አዝናቢዎችም የሽማግሌዎቹን ተማጽኖ ሰምተው፣ ዝናብ እንዲዘንብ የሚያከናውኑት ሥርዓት አለ፡፡ በዚህ በሚያከናውኑት ድርጊት እነሱ የሕዝቡን በደል ተቀብለው፣ በደም በመቀባት እና በቀዝቃዛ ውኃ በመታጠብ ስርየት ያስወግዱታል፡፡ "አዝናቢዎቹ ዝናብ እንዲመጣ የሚያበጃጁት ነገር አለ፡፡ ዶሮ የማረድና መስዋዕት የማቅረብ ነገር ነው፡፡ በዶሮው ደም አካላቸውን ይቀባሉ፣ ወዲያው ዝናቡን ለማምጣት ወንዝ ወርደው ይታጠባሉ፡፡ ያንን ሲያደርጉ ዝናብ ይጥላል" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ሻልታ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም ባቹማ)፡፡ የደም የመስዋዕት እና የወንዝ ውኃ ትስስርን አብራርተው የሚገልጹት ደግሞ በሐምሌ ወር 2010 ዓ.ም በኮላይ ቀበሌ ዝናብ ያዘነቡትን ሌማው ጃና፣ በቅርበት የሚያውቋቸውና የአንድ ጎሣ አባል የሆኑት የኮላይ ቀበሌ ሊቀመንበር አቶ ገብሬ ናቸው፡፡ "ዝናቡን ለማዝነብ ሲፈልጉ መሰዋዕት ያደርጋሉ፡፡ ዶሮ ካረዱ በኋላ እግራቸውን በደሙ እንዲቀባ ያደርጋሉ፡፡ የተቀባውን ደም ወደ ወንዝ ወርደው ሲታጠቡት ወዲያው ዝናቡ ይጥላል፡፡ እኛ ቀበሌም በዝናብ ንግሥቷ ሌማው ጃና የሆነው እንደዚሁ ነው፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ኮላይ)

አዝናቢዎች ሰማይን የሚለጉሙት፣ አካባቢውን በፀሐይ ንዳድ እንዲቃጠል የሚያደርጉት ሆነ፣ ዝናቡ እንዲመጣና እንዲጥል የሚያደርጉት ኮኮ ከተሰኘ ረዳታቸው ጋር በመሆን ነው፡፡ የኮኮዎችን ማንነት አቶ ብርሃኑ እንዲህ ይገልጹታል፡፡ "ኮኮ ማለት ዋናውን ሥራ የሚሠራውን ሰው የሚያግዛቸው፣ ወይም ሥራውን ሲሠራ ሥራ የሚታዘዘው ሰው ማለት ነው፡፡ ዋና ተግባሩም ረዳትነት ነው" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት ቀን 2011ዓ.ም፣ ኮላይ)፡፡

በደቡብ ክልል በቤንች ማጂ ዞን፣ በመኤኒት ጎልዲያ ወረዳ፣ ሥር ካሉ የአቅራቢያ ቀበሌዎች በአንዱ በሆነችው ኮላይ ቀበሌ በ2011 ዓ.ም ዝናብ ጠፍቶ የድርቅ አደጋ ተፈጥሮ እንደነበር ገብሬ ያስረዳሉ፡፡

> *በ2011 ዓ.ም. የእርሻ ጊዜ፣ ገበሬው ባለው መሬት ላይ ዘሩን ዘርቶ የዝናቡን መምጣት ይጠባበቃል፡፡ እኔም በእርሻ መሬቴ እና በቤቴ ጓሮም ዘርቼ እየተጠባበቅሁ ነበር፣ ግን ዝናብ ጠፋ፡፡ ሁኔታው ተስፋ አስቆራጭ ነበር፡፡ በወቅቱ ተዘርቶ ካልበቀለ መጪው ጊዜ*

*ሁሉንም ሰው ለችግር የሚዳርግ፣ ድርቅንም የሚጋብዝ ነበር፡፡ ሕዝቡ ሁሉ ግራ ተጋባ፣ እና በዚያ ሰዓት ገዛኸኝ የተባለ የቀበሌያችን ፖሊስ ዝናቡን እንዳይዘንብ ያደረጉት፣ በኮላይ እና በጠንክር ቀበሌ መካከል የሚኖሩት አዝናቢዋ ወ/ሮ ሌማው ጃና እንደሆኑ ነገረን፡፡ እሱ ይሂንን ያለው የዝናብ መጥፋቱ እኛ አካባቢ ብቻ በመሆኑ በአዝናቢዎች ታግዶ ነው በሚል ሀሳብ ነው፡ ፡ ከዚያ ብዙ ተወያይተንበት ጉዳዩ ሲጣራ በእርግጥም እሱ እንዳለው ሆኖ ነው የተገኘው (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም ኮላይ)፡፡*


በፖሊሱ የተነሳው ጥርጣሬ ብዙዎቹ ስለጉዳዩ እንዲወያዩ አድርጓል፡፡ በኮላይ አካባቢ ሰማይ ጠፍ የሆነው፣ ደመናም ከሰማዩ ላይ ያልታየው፣ በዝናብ ንግሥቷ ትዕዛዝ እንደሆነ ታምኗል፡፡ ይሂንንም ጉዳይ ራሳቸው አዝናቢዋ ሌማው ጃና ያረጋግጡታል፡፡ "ዝናቡ እንዳይዘንብ ያደረኩት አውቄ ነው፡፡ ምክንያቱም እኔን ሁሉም ረስተውኛል፡፡" (ሌማው ጃና 2011 ዓ.ም፣ ኮላይ)



የዝናብ ንግሥቷ ሌማው ጃና እና ኮኮ የሚሰኘው ረዳታቸው፡፡ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡

አዝናቢዋ ሌማው የኮላይን ምድር በፀሐይ ያደረቁበት ምክንያት፣ እርሳቸው በዝናብ አዝናቢነታቸው ለአካባቢው ሕዝብ በየዓመቱ ዝናብ ሲሰጡ፣ ሰው ግን ይሄንን ሥራቸውን እና ውለታቸውን ስለረሳው፣ የሚገባቸውን ክብርም ሆነ የሚያስፈልጋቸውን ቀለብ አለመስጠቱ እንደሆነ አስር አለቃ ግርማ ይገልጻል፡፡ "አዝናቢዋን ሌማው ጃና ለምን እንዳይዘንብ እንዳደረጉ ስጠይቅ፣ እኔ ለአካባቢው ሰው ዝናብ አዝንቤላቸው፣ እነሱ እያረሱ፣ እኔ እየራበኝ፣ እነሱ ዝም ስላሉኝ ነው፡ ፡ እኔ አሁን አቅመ ደካማ ሆኜ፣ መከበርና መጠየቅ ሲገባኝ ዝም ስላሉኝ ነው፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011ዓ.ም፣ ኮላይ)

ለዝናብ ማጥፊያነት ወይም ዝናቡ አካባቢው ሰማይ ላይ እንዳይኖር ለማድረግ አዝናቢዋ ከሚጠቀሙት ውስጥ የዕፅዋት ዘሮች መኖራቸውን አቶ ኮሬ እንዲህ ይገልጸዋል፡፡ "የሆነ የቅጠል ዓይነት አለ፡፡ እሱን የሆነ ቦታ ላይ ይተክሉታል፡፡ ከዚያ ዝናብ 'አይምጣ፣ ደመናው ይራቅ፣ ፀሐዩ ይበርታ' ይላሉ፡፡ በቃ ከዚያ በኋላ ዝናብ አይጥልም፡፡ ደመናም አይኖርም፡፡ ድንገት ደመና ቢኖር እንኳን ይበተናል፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ኮላይ)



አስተርጓሚው አቶ ብርሃኑ ወርቁ፣ ድምድማች የተሰኘውን ቅጠልና ሰንበሌጥ፣ ይዘው (ፎቶ በአጥኚው)፡፡

አዝናቢዋ ሌማው ጃና በኮላይ ምድር ዝናብ ቀርቶ ደመና በሰማይ እንዳይታይ ዳስ የተሰኘውን የሳር ዓይነትና ድምድማች የተባለውን የዛፍ እንጨት አንድነት ወደ ሰማይ አድርገው ከሰቀሉ በኋላ "ዝናብ አይምጣ፣ ደመናው ይራቅ፣ ፀሐዩ ይበርታ" ብለው ወደ ቤታቸው እንደገቡ እና ከዚያ በኋላ ፊታቸውን ሆነ ሰውነታቸውን ቀዝቃዛ ውኃ እንዳይነካው በጥንቃቄ ወቅቱን እንዳሳለፉ እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

> *ፀሐይ ሳትወጣ ተነስቼ፣ ዳስ የሚባለውን እንደ ሰንበሌጥ ያለ ሳር ፈልጌ፣ ድምድማች በተባለው እንጨት ላይ አስሬ፣ እንጨቱን ወደ ሰማይ አድርጌ መሬት ላይ ተከልኩ፡፡ ከዚያ ለአምላካችን ለቱማ ሰው ረስቶኛልና፣ አስርቦኛልና ዝናብ አይምጣ፣ ቱማ ደመናውን አርቅ፣ ፀሐዩ በዚህ አካባቢ ይበርታ አልኩ፡፡ በቃ እኔ በአምላክ ቱማ ቃል ያለኝ፣ የወደጀደራይታ ዘር ስለሆንኩና ዝናብ ለእኛ ስለሚታዘዝ፣ እነሱንም ስለተቆጣሁ፣ ፀሐዩ ብቻ መጣ፡፡ ዝናቡንም አጠፋሁት፡፡ ከዚያ በኋላ ሰውነቴን የምታጠበው ውኃ አፍልቼ ነው፡፡ ቀዝቃዛ ውኃ ሰውነቴን ፈጽሞ አልነካኝም (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011፣ ኮላይ)*

ጉዳዩ እውን ከሆነ በኋላ ይቅርታ ለመጠየቅ ከሄደው የሽማግሌዎች ስብስብ ውስጥ አብሮ የነበረው ግርማ ለሌማው ጃና ምክር ሰጥቷቸው እንደነበር ይገልፃል፡፡ "እኔ አሁን የኮላይ ቀበሌ ፖሊስ ከመሆኔ በፊት፣ በአጎራባቹ ጠንክር ቀበሌም በፖሊስነት ሰርቻለሁ፡፡ ወ/ሮ ሌማው ደግሞ ድንበር ላይ የሚኖሩ በመሆናቸው በደንብ እንተዋወቃለን፡፡ ከእኔ ጋር ያላቸው ግንኙነት ጥሩ ነው፡፡ እኔ እመክራቸዋለሁ፡፡ ያኔም እህል እንዳይጠፋብን ነግሬያቸዋለሁ፡፡ እሳቸው የሚያስፈልጋቸውን ቢጠይቁ ሕዝቡም ሆነ መንግሥት እንደሚረዳቸው ነግሬያቸው ተቀብለውኛል" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ኮላይ)



አስር አለቃ ግርማ፣ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡

ሌማው ጃና ከፍቶኛል ባሉት ምክንያት፣ የኮላይ ቀበሌን ሰማይ ዘግተው ሦስት ወራት ከቆየ በኋላ፣ ከአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎችን ጨምሮ የተውጣጣ ቡድን ወደቤታቸው ሂዶ እንዲያዘንቡ ብዙ የማግባባት ሥራ ከሠራ በኋላ ሴትየዋ ተስማምተው ሌላው ወደ ኮላይ ቀበሌ መጥተዋል፡፡ ይቅርታ ለመጠየቅ እና ለማግባባት ከሄደው ቡድን ውስጥ የነበሩት አቶ ኬላጊ ቃጅዎ እና አቶ ገብሬ ስለ ሁኔታው ተመሳሳይ ሀሳብን እንዲህ ይገልጸሉ፡፡ "የዝናብ ንግሥቷን ለማምጣት ሽማግሌዎችን ጨምሮ ከሃያ የማያንስ ሰው ነው የሄደው፡፡ ይቅርታ ጠይቀን አምጥተናቸዋል" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2010ዓ.ም፣ ኮላይ)፡፡

የሌማው ጃናን ለማዝነብ መምጣት የሰማው የቀበሌውና የአካባቢው ሰው ከገበያና ከሥራ ቦታ እየተጠራራ ተሰብስቧል፡፡ በወቅቱ ሻይ ቤት የነበራትና ሻይ መሸጧን ትታ ወደ ሥፍራ ያመራችው ወ/ሮ ትዕግሥት የወቅቱን ሁኔታ በቡድን ውይይት ላይ እንዲህ ገልፀዋለች፡፡ "እኔ ዝናብ እንዳይመጣ ያደረጉት አንዲት ወደ ተራራ አካባቢ የሚኖሩ ሴት ናቸው ሲባል ሰምቼ ነበር፡፡ ሊያዘንቡት መጡ ሲባል ላይ መጣሁ (የቡድን ውይይት፣ ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ.ም፣ ከ10፡00 - 12፡00፣ ኮላይ)

በኮላይ ቀበሌ በሽምግልናቸው ተከባሪ እንደሆኑ የሚናገሩት እና ወ/ሮ ሌማውንም በማግባባት ሚና እንደነበራቸው በቡድን ውይይቱ ላይ ሀሳባቸውን የሚገልጹት አቶ ኬላጊ ቃጅዎ አዝናቢዋ ሌማው ጃና በሽማግሌዎቹ ይቅርታ ጠያቂነት እና የተሰበሰበውም ሕዝብ እንዲያዘንቡ መፈለጉን በመረዳታቸው፣ የመኤቶች አምላክ ቱማም ዛሬም ድረስ ከእነሱ ጋር መኖሩን ለማሳየት በመወሰን ለማዝነብ እንደፈለጉ እንደገለጹላቸው ተናግረው፡፡ ሌማው ዝናብ ለማዝነብ ያደረጉትን ሂደትም እንዲህ ይተርኩታል፡፡

> *ከተስማሙ በኋላ ኮላይ መጡ፡፡ ቀትሩ እስኪያልፍ ከቆዩ በኋላ በግምት ስምንት ሰዓት አካባቢ ዶሮ ተገዝቶ እንዲመጣላቸው ጠየቁ፡፡ እኛም ለሰዎች ነገርንና ጥቁር የሆነ ትንሽ ዶሮ ተገዝቶ ቀረበላቸው፡፡ ዶሮውን የተቀበለው ረዳታቸው ኮኮው ነው፡፡ አዝናቢዋም ከከተማው ራቅ ብለው ሲሄዱ ኮኮው ተከተላቸው፡፡ እኛም ቀስ ብለን ተከተልን፡፡ የከተማው ሰውም ተከተለ፡፡ ኮኮው እና እሳቸው ከሰው ራቅ ብለው ወንዝ አካባቢ ደረሱ፡፡ እኛም ሰውን ከዚያ በኋላ እንዳይጠጋ አደረግን፡፡ ኮኮው ዶሮውን አረደው፡፡ ከዚያም የሴትየዋን ሁለት እግሮች እስከ ባታቸው ድረስ በዶሮው ደም ቀባባቸው፡፡ እንደጨረሰ ዶሮውን አርቆ ወረወረው፡፡ ከዚያ በኋላ ሴትየዋ ወደ ወንዙ ሲጠጉ ፖሊሶች ብቻ ተከተሏቸው፡፡ እኛ ከጋራ ባሻገር እንደቆምን አዝናቢዋ ወደ ወንዙ ውስጥ ገቡ፡፡ ከዚያ ደም የነካው እግራቸውን በውኃው ታጠቡ፡፡ የሆነ ነገር እንደሚናገሩ ከአፋቸው ንቅናቄ ተረድቻለሁ፡፡ እጃቸውንም ወደላይ ወደላይ ያደርጉ ነበር፡፡ አፍታም አልቆዩ ታጥበው እንደወጡ ከየት እንደመጣ የማይታወቅ ጥቁር ደመና መጣ፡፡ በዚያው ፍጥነት ደግሞ የተጠራቀመ ብዙ ዝናብ፣ ዶፍ ዝናብ ጣለ፡፡ ከዚያው ሳንንቀሳቀስ ነው መጣል የጀመረው፡፡ እኛም ከዝናብ ለመጠለል ተሯሯጥን፡፡ መቼም ይሄ የቱማ ኃይል የተገለጠበት ነው፡፡ (የቡድን ውይይት፣ ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ.ም፣ ከ10፡00 - 12፡00፣ ኮላይ)*

የአዝናቢዋ ሌማው ጃና የዝናብ ማውረድ ድርጊት በኮላይ ቀበሌ በጠራራ ፀሐይ የተከናወነ ነው፡፡ ብዙዎችንም አስደንቋል፡፡ ድርጊቱ ሲካሄድ የቀበሌው ሰው ከሥራም፣ ከገበያም ተሰብስቦ ነበር፡፡ እንደ አቶ ኬላጊ አባባል በዚያ ሥፍራ እና ቦታ የተገለጠው የአምላካቸው የቱማ ኃይል ነው፡፡ ቱማ አስቀድሞ ለመኤኒቶች የገባውን ቃል ኪዳን አሁንም እንደሚፈጽም የተረዱበት ነው፡፡ አዝናቢዋ ጥቁር ዶሮ ተሰጥቷቸው በኮኮው አማካይነት አርደው፣ ደም

በሰውነታቸው ላይ ተቀብተውና ወንዝ ወርደው ዝናብ ማዝነባቸውን በዚያው አካባቢ ሆኖ ያየው ሌላው ሰው ግርማ ስለ ድርጊቱ የሚከተለውን ይገልጻል፡፡

> *በመጀመሪያ ዶሮ እናርዳለን አምጡ አሉ፡፡ ከዚያ ጥቁር ዶሮ ተሰጠ፡፡ ረዳቱ አረደና ደሙን እሳቸዉ እግሮች ላይ ቀባ፡፡ ከዚያ እዚህ[6] ቆሊ ወንዝ ገቡና የሆነ ነገር እያሉ ታጠቡ፡፡ እዚህ ድረስ አብሬያቸው መጥቻለሁ፡፡ ገዛኸኝ የተባለውም ፖሊስ አብሮኝ ነበር፡፡ ሴትየዋ እዚህ ታጥበው እንደወጡ ከወንዙ ሦስት ርምጃ እንደራቁ፣ ከባድ የሆነ ዝናብ ዘነበ፡፡ ከየት እንደመጣ ሁላችንም አላወቅንም፡፡ ከዚያም በኋላ ሕዝቡ ሴትየዋ በትክክል የዝናብ አምላክ ናቸው፡፡ ዝናብ ያስጠፋሉ ያስመጣሉም ብሎ ሲነጋገር ነበር፡፡(ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011ዓ.ም፣ ቆሊ ወንዝ ዳር)*



አዝናቢዋ ሌማው ጃና የታጠቡበት፣ ኮላይ ቀበሌ የሚገኘው ቆሊ ወንዝ፣ (ፎቶ በአጥኙው)

ወ/ሮ ሌማው ጃና ለሦስት ወራት ያልነበረውን ዝናብ ማምጣታቸው ግርምትን የፈጠረባቸው በወጣትነት ዕድሜ ውስጥ ያሉት የአካባቢው ኗሪዎችም በእለቱ የሆነውን በማስታወስ እነደሚከተለው ይገልጹታል፡፡ ‹‹እኛ ተራራው ላይ ቆመን ሴትየዋ ወንዝ ሲገቡ በርቀት አየን፡፡ ወዲያው ደግሞ እያወራን ሳለ

[6] ቃለመጠይቁን ያደረግነው ከወንዙ ዳር ስለነበረ፣ በእጁ እያመላከተ ስላወራ ነው፡፡

ኃይለኛ ዝናብ በአካባቢው ወረደ፡፡ መሬቱ ጭቃ በጭቃ ሆነ፡፡ እኔም እየተደበደብኩ ወደ ቤት ተመለስኩ፡፡" (የቡድን ውይይት፣ ወ/ሮ ትዕግሥት፣ ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ.ም፣ ከ10፡00 - 12፡00፣ ኮላይ)

፡፡ የዝናቡን ከባድነት በንግድ ሥራ የምትተዳደረው ወ/ሮ ጊብዚኒም እንዲህ ገልፃዋለች፡፡ "ንፋስ ያለው ኃይለኛ ዝናብ ነው የዘነበው፡፡ ዝናቡ እየመታኝ መጠለያ ፍለጋ ወደ መንደሮቹ ሮጥሁ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ 2011 ዓ.ም ኮላይ)

የአዝናቢዋ ዋዕይ ለበላው የኮላይ ቀበሌ ዶፍ ዝናብ ማዝነብ፣ በሕዝቡ ውስጥ ደስታን በመፍጠሩ ጥቂት የማይባል ሰው የተቻለውን ያክል ገንዘብ እያዋጣ መስጠቱን ወ/ሮ ትዕግሥት እንደሚከተለው ትገልፃለች፡፡ "ዝናቡ በግምት አስራ አምስት ደቂቃ አካባቢ ከጣለ በኋላ፣ ሰዎች ያገኙትን ብር ማዋጣት ጀመሩ፡፡ እኔንም ጠይቀውኝ ሁለት ብር ሰጥቻለሁ፡፡ ዝናቡን ላወረዱት ሴት የሚሰጥ" (የቡድን ውይይት፣ ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ.ም፣ ከ10፡00 - 12፡00፣ ኮላይ)፡፡

ግርማም ሕዝቡ ለአዝናቢዋ ያደረገውን ስጦታ በመግለጽ ያጠናክራል፡፡ "ከዚያ ሰው በታላቅ ደስታ ብር እየለቀመ ለሴትየዋ ሰጠ" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ኮላይ)፡፡ አዝናቢዋ ሌማው ጃና ስለ አዝናቢነታቸው እና በእነሱ እና በአምላክ ቱማ መካከል ያለውን ትስስር በሚከተለው መልክ ገልጸውታል፡፡

> *በምድር ላይ ስንኖር አምላካችን ቱማ ለእኛ የዝናብን ጥበብ ሰጠን፡፡ ዝናብ ማዝነብ ለኛ ከአምላክ ቱማ የተሰጠን ጸጋ ነው፡፡ እኛ የዝናብ አማልዕክት ነን፡፡ የኛ ዘሮች ሲያዘንቡ ኖረዋል፡፡ ዝናብ የኛ ታዛዥ እንዲሆን ያደረገው አምላካችን ቱማ ነው፡፡ ፀሐይም ይሁን ስንል ፀሐይ ይሆናል፡፡ እኛ በዝናብ እንድንከበር የሚያደርገን ቱማ ነው፡፡ እኔ ወደዚህ ስመጣ በአካባቢው ላይ እንዳይዘንብ በግቢዬ የተከልኩትን ድምድማችና ሳሩን ከቦታው ነቅዬ አምጥቼ ቆሊ ወንዝ ውስጥ ጣልኩት፡፡ ሰማይን ዝናብ አምጣ፣ ዝናብ ልቀቅ አልኩት፡፡ ለይቅርታው ደሙን በእግሬ ላይ ተቀብቼ፣ በቀዝቃዛ ውኃ ሰውነቴን ታጠብኩ፡፡ እናም የታሰረው ተፈታ፣ ዝናብም መጣ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011፣ ኮላይ)፡፡*



የዝናብ ንግሥቷ ሌማው ጃና ከአጥኝው እና ከአስተርጓሚው ጋር ቃለ መጠይቁ በተደረገበት የኮላይ ቀበሌ (ፎቶ በአቶ በድሉ ካሳ)፡፡

በመኤኒት ብሔረሰብ የዝናብ ጉዳይ ዋና እና ቀዳሚ የማንነት መገለጫ ነው፡፡ አምላክ ቱማ መኤኒቶችን ፈጥሮ ካኖራቸው በኋላ የእሱን በቅርበት መኖር ለመረዳት እና ለማወቅ እንዲችሉ ዝናብ ዋና ምስክራቸው ሆኗል፡፡ ዝናብ ሲርቅና ሲጠፋ እንደተጣላቸው፣ ዝናብ ሲኖር እና ምድሩን ሲያረሰርስ ደግሞ እንደተታረቃቸው ይረዱበታል፡፡ የፈጠራቸው አምላክም የእለት ከእለት ትስስሩን በሾማቸው እና ስልጣን በሰጣቸው ሰዎች ወይም ኮሞሮቶች አማካይነት ይገልጽላቸዋል፡፡ ለዚህም ከባንጃ የተነሳው የአዝናቢነት ኃይል ዛሬ የመኤኒትን ምድር ሞልቷል፡፡ በርካታ ኮሞሮቶችም የዝናብ አዝናቢዎች እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ዛሬም ድረስ በአዝናቢነታቸው የሚታወቁ ታላላቅ ኮሞሮኞች መኤኒቶች ባሉበት አካባቢ ሁሉ እንዳሉ  አቶ ሹማቻኤዳ ውለጌ ይሄንኑ በሚከተለው መልኩ ያብራራሉ፡፡

> እኛን የፈጠረ ቱማ፣ ሰማይን በደመና፣ ምድሪቷን በቅጠል፣ ዙሪያችንን በምንወዳቸው ከብቶች፣ ሞልቶልን ነበር፡፡  የሆነ ግዜ ግን በእኛው ጥፋት ተቆጣን፡፡ ለጥፋታችን ሰማዩን አደረቀው፣ ምድሪቷም ጠሚን አደረች፣ ከብቶቻችን በርሃብ አለቁ፡፡ ከዚያ እኛም ተሰደድን፡፡ ከዚያ በኋላ በያለንበት ቱማ አብሮን እንዳለ የምናውቀው በሰማዩ ነው፡፡ ከላይ በሚታየው ደመና ነው፡፡ ደመና

ከሌለ ቱማ የለም፡፡ አዝናቢዎቻችን ለምነው ሰማዩን በውኋ እንዲሞላልን ያደርጉልናል፡፡ ዛሬ በመኤኒት ብዙ አዝናቢዎች አሉ፡፡*(ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ጥቅምትእሸት)፡፡*

በአጠቃላይ የመኤኒት የአፈጣጠር ሚት የሚያስረዳው አምላክ ቱማ መኤኒቶችን መፍጠሩን ነው፡፡ እንደ ብሔረሰቡ ሰዎች እምነት የሥነ ፍጥረት መጀመሪያቸው በኦሞ ሸለቆ አካባቢ እንደሆነ ነው፡፡ በዚያ ስፍራ አምላክ ቱማ የመጀመሪያ የብሔረሰቡን አባት ናኦሚን አንደፈጠረ እንዲሁም ልጆቹ እንደተከተሉ፡፡ የናያሞን ሦስት ወንደ ልጆች በአምላክ ቱማ ፊት ቀርበው መክሊት እንደተቀበሉ የሚያትት ሲሆን፣ ጥንት እንደተጀመረ የሚታመነው ይኼው ጥበብ እና የሰው መተዳደሪያ ዛሬም ድረስ እንዳለ፣ እሱም ለፈጣሪያቸው እና ለአፈጣጠራቸው ዋቢ ተደርጎ ይታመናል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5. የመኤኒት ብሔረሰብ መንፈሳዊ ሚት

በመኤኒት ብሔረሰብ መንፈሳዊ አስተምህሮ እና አስተሳሰብ፤ ምድሪቷን፣ በምድሪቷ ውስጥ የሚኖሩትን፣ ሰማዩን እና በሰማይ ውስጥ ያለውን ሁሉ የፈጠረው አምላክ ቱማ ነው፡፡ መኤኒቶችንም የፈጠረው ቱማ ነው፡፡ ቱማ አስቀድሞ የመኤኒቶችን የመጀመሪያ አባት የሆነውን ናያሞንን ፈጥሯል፡፡ ናያሞንን ሦስት ወንድ ልጆች የወለደ ሲሆን፣ ከልጆቹ በማስከተልም አንዱ አንዱን እየተካ፣ ትውልድ ትውልድን እያበዛ እና እየተቀባበለ ዛሬ ላይ እንደደረሱ ይታመናል፡፡ በዚሁ ልክ የብሔረሰቡ አባላት ለማንኛውም የሕይወት መስተጋብራዊ ጥያቄዎቻቸው ሁሉ መልስ ሰጪ፣ ሁሉን የሚችለው እና የሚያደርገው አምላክ ቱማ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ የብሔረሰቡ መንፈሳዊ ሚት የተመሠረተው በዚሁ የእምነት ትረካ ላይ ነው፡፡ "የመኤኒት አምላክ ቱማ ነው፡፡ ሰማይና ምድርንም የሠራው ቱማ ነው፡፡ ዘሮቻችን ከጥንት ጀምሮ አምላክ ብለው ያስረከቡን ቱማን ነው፡፡ ቱማ ሁላችንንም ያኖረናል" (ዋየች ጃሻ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 2008 ዓ.ም፣ ጨበራ)፡፡

የመኤኒት የመንፈሳዊ ሚት ትረካ እንደሚያስረዳው መኤኒቶች ከአምላክ ቱማ ጋር ባላቸው የእምነት ግንኙነት ታሪክ ውስጥ የተለያዩ አቀራረቦችን አሳልፈዋል፡፡ በጥንቱ የአፈጣጠር ዘመናቸው መጀመሪያ አካባቢ የነበሩት መኤኒቶች ከአምላክ ቱማ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ነበራቸው፡፡ በፊቱ ቀርበው ጥያቄ ጠይቀው መልስ ተሰጥቷቸዋል፣ በቀጥታ የአምላካቸውን ድምጽ ሰምተው እሱን እያመለኩ የኖሩበት ዘመንን አሳልፈዋል፡፡ ቀዳሚዎቹ የመኤኒት ሰዎች የመጀመሪያው የናያሞን ልጆች በአምላካቸው በቱማ ፊት ቀርበው ራሳቸውን እና ሕዝባቸውን የሚያስተዳድሩበትን ጥበብና ኃይል ተቀብለዋል፡፡ ይሁን እንጅ በጊዜ ሂደት መኤኒቶች ቅርባቸው ከነበረው አምላካቸው ተራርቀው፣ እነሱም በሥራቸው ለቅጣት እና ለስደት ተዳርገዋል፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ የእምነት ሚትም ከዚሁ ዘመን ክስተት ጋር የተያያዘ ትረካ አለው፡፡ ከአምላክ ቱማ ጋር የነበራቸው መስተጋብርና የእምነት ግንኙነት መልክ፣ መኤኒቶች ለቅጣት

ከተዳረጉበት ዘመን በፊት እና በኋላ የራሱን ገጽታ ይዟል፡፡ አቶ ቻካም ሚሮ የሚከተለውን ይገልጻሉ፡፡

> *በጥንቱ ዘመን አምላክ ቱማ የሚያስፈልገንን ሁሉ አሟልቶ ሰጥቶን የኛ ሥራ በደስታ መኖር ነበር፡፡ በተለይ የምድርን ምርት በሰበሰብን ሰዓት ትልቅ የደስታ ጊዜ እናካሂዳለን፡፡ ይሄ ሥርዓት ጥንትም አሁንም ድረስ የዘለቀ ነው፡፡ በጥንቱ ዘመን ወሩ ለእኛ ለመኤኒቶች የደስታ ጊዚያችን ነው፡፡ ከብቶቻችን ወፍረው፣ ላሞቹ አግተው፣ ፍየሎቹ በርክተው የሚገኙበት፣ በጓሮና በዱር ያለው ፍሬ መሬት የሚሞላበት፣ እንስሳቱ፣ አውሬው ሁሉ የሚጠግብበት፣ ወንዞቻችን ጎደለው ጥርት ብለው የሚፈስሱበት ጊዜ ነው፡፡ እኛም በመብላት፣ በመጠጣትና በጨዋታ ቱማን እናመሰግናለን፡፡ ብዙ ወጣቶች ይጋባሉ፡፡ ሴት ልጅ የዳረ አባት፣ በልጁ በሚደርሰው ጥሎሽ ዘመዶቹን ሁሉ ያጠግባል፡፡ አንዳንዱ አባት ለሴት ልጁ የሚያስጥለው የከብት ብዛት እስከ ሰላሳ ስለሚደርስ የቅርብ ዘመድ የሆነ ሁሉ ከብት ይካፈላል፡፡ ይሁን እንጅ በሆነ ጥንት/ዱሮ ጊዜ በኛ ሰዎች፣ በመኤኒቶች የተሠሩ ጥፋቶች በዙ፡፡ ቱማ ተቀየመ፡፡ ቱማ መኤኒቶችን ተቆጣ፡፡ ከዚያ በኋላ እሱ ጥሏቸው ጠፋ፡፡ እነሱም ተቸገሩ፣ በጣም ከባድ ችግር ሆነ፡፡ ሰዎቹ መኖር አቃታቸውና ተሰደዱ፡፡ መኤኒት ያኔ ሌላ አሁን ሌላ ሆነ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ኩዱም)*

በመኤኒት የመንፈሳዊ ሚት ትረካ ውስጥ፣ ዘመናትን ከፍሎ ማየት እና እምነታዊ ሚትን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በተለይም ብሔረሰቡ ጥንት ከነበረበት አካባቢ (ደቡብ ኦሞ አካባቢ) ከለቀቀበት እና ለስደት ከተዳረገበት ምክንያት ጋርም የሚያያዙ ትረካዎች መኖራቸው ሀሳቡን ይበልጥ ለማየት ገፊ ምክንያት ይሆናል፡፡

## የመኤኒቶች ጥፋት እና የአምላክ ቱማ ቅጣት

በጥንቱ ዘመን አምላክ ቱማ በኮሞሩቶች እና በኘራዮች አማካይነት ሕዝቡን እያስተዳደረ ይኖር ነበር፡፡ ቱማ አስቀድሞ መኤኒቶችን የሚኖሩበትን ምድር አዘጋጅቶ፣ የሚያስፈልጋቸውን ዝናብ እና ከብት ሰጥቶ ሲያኖራቸው በነበረበት በቀዳሚ ዘመን፣ መኤኒቶች በቁጥር በርክተው በሀብት ዳብረው ኖረዋል፡፡ ነገር ግን በጊዜ ሂደት አምላክ ቱማን እና መሪዎቻቸውን የሚያስከፉ ልዩ ልዩ ተግባራትን ማከናወን በማብዛታቸው ከአምላክ ቱማ ከፍተኛ የሆነ

ቅጣት ገጥሟቸዋል፡፡ በዚያ በጥንቱ ዘመን አምላክ ቱማ ሁሉን አዘጋጅቶ በሚያኖራቸው ጊዜ መኤኒቶች አምላክ ቱማን የሚያስቀይሙ ሥራዎችን አብዝተው ሠሩ፡፡ መገዳደል፣ መዘራረፍ እና ሌሎች ተግባራትን በማድረጋቸው ቱማ በድርቅ፣ በረሀብ፣ በበሽታ እንደቀጣቸው እና ጭራሽኑም ከለምለም አካባቢያቸው እንዲሰደዱ እንዳደረጋቸው ትረካዎቹ ያስረዳሉ፡፡ የጥንቱን አኗኗር እና የተከሰተውን ዋየች ጃሻ በሚከተለው መልኩ ይገልጹታል፡፡

> *ጥንት አባቶቻችን ሲነግሩን የኛ በጣም የሩቅ የሩቅ አባቶቻችን፣ ሁሉ የሞላላቸው ነበሩ፡፡ የነበራቸው ምድር በልምላሜው ተወዳዳሪ አልነበረውም፡፡ በሁሉም ወገን ለምለም የሆነ ምድር ላይ ነበር ያስቀመጣቸው፡፡ ያኔ በኛ በመኤኒቶች ምድሪቷ ብቻ ሳትሆን በምድር ላይ የተሰጠን ሁሉ ብዙ እና አስደሳች ነበር፡፡ የከብቶቻችን ብዛት ስፍር ቁጥር አልነበረውም፡፡ በጣም ብዙ ብዙ ከብቶች በምድራችን ላይ ነበሩ፡፡ ሀገሩ ሁሉ፣ ሜዳው ሁሉ ከብት ነበር፣ ያኔ ጋብቻ እንኳን ሲፈጸም አንድ ወንድ በትንሹ ሰላሳ እና አርባ ከብት ጥሎሽ ሰጥቶ ነው አንዲትን ሴትን የሚያገባት፡፡ አንድ ወንድ ደግሞ ሀብታም ከሆነ አምስት ድረስ ሚስቶች ሊያገባ ይችላል፡፡ ይሄ ሥርዓት ጥንትም የነበረ ነው፡፡ በከብቶቻቸው ብዛት የተከበሩ እና ሀብታም የሆኑ መኤኒቶች የሚያገቧት ሴት ልጅ የትልቅ ሰው፣ የተከበረ ሰው ልጅ ከሆነች ጥሎሹ ሊጨምር ይችላል፡፡ በዚህ መልኩ አንድ ሰው አርባ እና ሃምሳ ከብት ድረስ ጥሎሽ እየጣለ ሚስቶች ሲያገባ ክብሩ ብዙ ነበር፡፡ ያኔ ከብቱ ብዙ ነው፡፡ ያኔ ምድራችን ለም ነበር፡፡ ማር በየጫካው፣ በየቤቱ እንደልብ የሚገኝበት ጊዜ ነበር፡፡ አምላክ ቱማም ከሰማይ ዝናቡን፣ ከምድር ከብቱን እና አካባቢውን ይጠብቅና ለምለም ያደርግ ነበር፡፡ በተለይ ከህዳር ወር በኋላ አካባቢ ትልቅ የደስታ ጊዜ ይደረግ ነበር፡፡ ምርት በደንብ የሚገኝበት ቀየው ለዓይን የሚያምርበት ጊዜ ነው፡፡ የልጃ ገረዶች እና የጎረምሶች የደስታ ወቅት ነው፡፡ በብዛት የሚተጫጩበት ጊዜ ነው፡፡ አምላክ ቱማ በደንብ የሚመሰገንበት ጊዜ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የኛ ሰዎች፣ የጥንቱ ጊዜ የነበሩት ማለት ነው፡፡ ደስታቸው እየበዛ፣ መከባበራቸው እየጠፋ፣ በሆነ ባልሆነው አምላክ ቱማን እያስቀየሙ፡፡ አምላክ ቱማ ጠባቂ አድርጎ የሰጠንን ዋና ዋና ሰዎችን ኮሞሮቶችን፣ አዝናቢዎችን፣ ኘራዮችን መዋሸት፣ መደበቅ፣ ማቃለል፣ እርስ በርስም መጨካከን፣ በረባው ባልረባው መገዳደል፣ አንዱ የአንዱን ሚስት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ፣ በአጠቃላይ ቱማ የማይወዳቸውን እና የሚያዝንባቸውን ሥራዎች እየሠሩ ሲመጡ፣ አምላክ ቱማም በእነሱ እየተቆጣ፣ በኮሞሮቶች እና በኘራዮች እየቀጣቸው ይሄድ ጀመር፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 2008 ዓ.ም. ፣ ጨበራ)*

በብዙ የመንፈሳዊ የሚት ትረካዎች ላይ እንዲህ ዓይነት ተመሳሳይ ታሪኮች ይገኛሉ፡፡ አምላክ ለሰው ልጆች አስቀድሞ ምቹ፣ ሁሉ ነገር የተሟላላትና ፀጋዋ የበዛን ምድር መስጠቱ ይገለጻል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካም እንዲሁ ለሰው ቀድማ የተሰጠችው ገነት ሁሉ ነገር የተሟላላት በረጃጅምና በትላልቅ ወንዞች የተከበበች እንደሆነች[7]፣ በውስጧ ያሉት ዕፅዋትም ይሁኑ ሌሎች ለሰው መጠቀሚያነት የተፈጠሩት ሁሉ በብዙ በረከት የተሞሉ እንደሆኑ ይተረካል፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ በዚህ ምቹ እና ለእሱ ተስማሚ እንደሆነች በሚነገርባት የተፈጠረባት ዓለም ውስጥ ከተፈጥሮ እና ከራሱ ጋር ተስማምቶም ሆነ የፈጠረው አምላክ በመረጠለት የሕይወት ጎዳና መሄድን አልተቀበልም፡፡ የሰው ልጅ ውስጠዊ ፍላጎቱ እየገፋው ከአምላኩ ፈቃድና ሀሳብ ውጭ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜም ደግሞ አምላክ የቅጣት በትሩን አንስቶ የፈጠረውን ይረግማል፣ ይቀጣል፡፡ የእስራኤል ሕዝብ ከመጀመሪያዋ ገነት ጀምሮ በርካታ ጊዜ ባድማና ርስቱን ለቅቆ ብዙ ጊዜ ለስደት ተዳርጓል፡፡ በግፆች ለአራት መቶ ሰማኒያ ዓመታትም እንዲሁ ፍዳውን ያየበት ዘመን እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል፡፡ የመኤኒት ሕዝብም አምላኩን ቱማን በማስቀየሙ እና በማሳዘኑ ቅጣቱን እንደተቀበለ የብሔረሰቡ ሚት ይተርካል፡፡

> *. . . ይሁን እንጅ አሁን የጥንት ሰዎች በደስታ እና በተድላ የሚያኖራቸውን አምላክ እየረሱ እያስቀየሙ ሲመጡ፣ የአምላክ ቱማ ቁጣም በመኤኒቶች ላይ መጣ፡፡ በመጀመሪያ የሰማይ አፍ ተዘጋ፡፡ በፊት ሀገሩ ሁሉ ዝናብን እንዳልጠገበ፣ ኋላ ጠብ አልል አለ፡፡ ዝናብም ጠፍቶ ፀሐይ ብቻ የመኤኒቶችን ምድር አነደደው፡፡ የነበሩበት ምድር የሚያቃጥል በረሀ እየሆነ መጣ፡፡ ማደሪያ የሌለው እና በየመንገዱ የሚያድረው ከብት ሁሉ መንምኖ በቁሙ መውደቅ ጀመረ፡፡ ታይቶ የማያቅ በሽታ፣ እንደ ወባ ያለ እና ወረርሽኝ ያለ ሰውን መታው፡፡ የሰውም፣ የከብቱም ህፃናቱ በያሉበት በራብ ሞቱ፣ እናቶች የሚበሉት ቅጠል እንኳ ስላጡ ልጆቻቸው ሲሞቱ ዝም ብለው ተመለከቱ፡፡ በወቅቱ ምንም በአካባቢው የሚበላ ስለጠፋ ብዙ ሰዎች ይሄንን የአምላክ ቱማን ቁጣ ለመሸሽ አካባቢውን ለቅቀው ፈለሱ፡፡ በወቅቱ ጥቂቶች ብቻ ከአካባቢው አንለቅም፣ አምላክ ቱማ እንደተቆጣን እንዲታረቀን በኮሞሮቶች፣ በኘራዮች፣ በሽማግሌዎች እንለምነዋለን አሉ፡፡ መጀመሪያ እነሱን ይቅርታ ጠይቀን፣ እነሱ ምሕረት እንዲያወርዱልን እንለምናለን ብለው ቀሩ፡፡ አብዛኛው ግን*

[7] *የሁለተኛውም ወንዝ ስም ግዮን ነው፤ እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከብባል (ኦሪት ዘፍጥረት 2፣ 13)፡፡*

*አካባቢውን ለቅቆ ምግብ ወደሚያገኝበት፣ ጥቂት የተረፉ ከብቶችን እና ልጆችን ይዞ ስደት ገቡ፡፡*

*እኛ መኤኒቶች ያኔ በአምላክ ቱማ ላይ ባደረስነው ጥፋት ስለተቀጣን፣ አካባቢያችንን ለቅቀን ለመሰደድ በቃን፡፡ በወቅቱ ከአካባቢው አንለቅቅም ብለው የቀሩ ጥቂት ዘሮቻችን በጥንቱ አካባቢ እንዳሉ ይነገራል፡፡ ከእነሱ ውስጥ ደግሞ ጥቂት ተጉዘው ለከብቶቻቸው የሚሆን ምግብ ሲያገኙ በየደረሱበት የቀሩ ወገኖቻችን አሉ፡፡ አብዛኛው መኤኒት ግን ስደቱን ቀጥሎ ዛሬ በተለያየ አካባቢ ይኖራል፡፡ ዛሬ ያለበት አካባቢ የመጣው ያኔ ነው፡፡ በዋናነት መኤኒት ጎልዲያ እና መኤኒት ሻሻ ያለው ሰው ያኔ የመጣ ነው፡፡ ስደቱ ነው ያመጣው፡፡ በሌሎች ወረዳዎችም ተበታትኖ ያለው ሰው አብዛኛው መኤኒት ነው፡፡ የጥንት አባቶቻችን አምላክ ቱማ የሰጣቸውን በረከት ጠብቀው፣ ሳይገዳደሉ፣ ሳይሰራረቁ፣ የሰው ሚስት ሳይነኩ፣ እሱን እያመሰገኑ መኖር ነበረባቸው፡፡ እንዲመሩን የሰጠንን ኮሞሮቶች፣ ኙራዮች፣ ሸማግሌዎች እየተለማመጥን እና እየታዘዝናቸው ባለመኖራችን የመጣብን ቅጣት ነው ዛሬም ድረስ የሚከተለን፡፡ (ዝኒ ሀማሁ)*



አቶ ዋየች ጃሻ፣ (ፎቶ በአጥኚው)

በመኤኒቶች የቀደመ ሕይወት ዙሪያ እንደ ዋየች ሁሉ ተመሳሳይ ገለጻ የሚሰጡት ደግሞ አቶ ኦይትሉዋ ፋጂዎ ናቸው፡፡ ኦይትሉዋ በጥንት ጊዜ

መኤኒቶች ከአምላክ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንደነበራቸውና አምላክ ቱማም ለሰው ልጅ የሚያስፈልገውን ምድር እንዘጋጀላቸው ይገልጻሉ፡፡ አክለውም ምድሪቷ ደረቅ እንዳትሆን ለሰው ምቹ እንድትሆን ከላይ ከሰማይ ዝናብን፤ ከዘመን ዘመን፣ ከጊዜ ጊዜ ስለሰጣቸው አካባቢያቸው በብዙ ደን የተሸፈነ ለምግብነት የሚሆኑ እጅግ ብዙ ፍራፍሬዎች እና የሚበሉ አራዊት እንደነበሩ ያብራራሉ፡፡  ኦይትሉዋ ሲያጠቃልሉ፣ ሰው በሠራው መጥፎ ሥራ አምላክ ተቆጥቶ በሕዝቡ ላይ ባመጣው ቅጣት፣ የተከሰተውን ችግር፣ ችግሩ ያስከተለውን መከራ እና የታየውን ውጤት በሚከተለው መልኩ ይገልጹታል፡፡

*አምላክ ቱማም ከሰዎች ጋር በጣም ቅርብ ነበር፡፡ ቃል በቃል የሚያወሩትም ነበሩ፡፡ ትዕዛዝን የሚቀበሉም ነበሩ፡፡ የተቀበሉትን ትዕዛዝ ለሰው በማውረድ ይሄንን አታድርጉ ይሄንን አድርጉ የሚሉ ነበሩ፡፡ ከእሱ ከቱማ ጋር ቃል በቃል የሚያወሩ ነበሩ፡፡ አምላክ ቱማ የፈጠረው የመጀመሪያው ሰው፣ ልጆቹ፣ ልጅ ልጆቹ ሁሉ ይነጋገሩ ነበር፡፡ ነገር ግን ሰው ሁሉ ነገር ሲሟላለት ችግር ነው፡፡ በጊዜ ሂደት መኤኒት አምላኩን እየረሳ መጣ፡፡ ኮሞሮትና አዝናቢ የሆኑ ሰዎች አታድርጉ የሚሏቸውን ነገሮች የሚያደርጉ በዙ፡፡ ለምሳሌ መገዳደል በዛ፣ የሰው ሚስት ጋር መተኛት መጣ፣ የአንዱን ንብረት አንደኛው መዝረፍ ጀመረ፡፡ አንድ ሰው ሲገደል ሌላኛው እየተበቀለ፣ ጥላቻና ግድያው እየሰፋ ሄደ፡፡ አንድ ሰው ሰው ከገደለ መልሱ መልሶ የዚያን ሰው ወይም ወገን የሆነውን ሰው መግደል፣ ንብረቱን ማቃጠልና መዝረፍ፣ ሴትም ይሁን ሕፃንም ይሁን፣ አቅመ ደካማም ይሁን መግደል ብቻ ሆነ፡፡ እህሉን በተገኘበት ማቃጠል ሆነ፡፡ ወንዶችም ሴቶችን ለማግባት እና ብዙ ሚስት እንዲኖራቸው ሲፈልጉ ለጥሎሽ የሚሆን ከብት ለማግኘት መጀመሪያ አኀራባች ወደሆኑ ሕዝቦች በመሄድ በመታኮስና በመጋደል ከብቶች ዘርፈው መምጣት ጀመሩ፡፡*

*እየቆየ ዝርፊያው እርስ በርስ ጭምር ሆነ፡፡ በዚህ ሁሉ ቱማ የመረጣቸው መሪዎች ሕዝቡን ከክፉ ድርጊቱ እዲቆጠብ፣ አምላክ ቱማን ከማስከፋት እንዲተው ምክር ይመክሩ ነበር፡፡ የጥንቱ ሰው ብዙ የሞላለት እና የተረፈው የደላው በመሆኑ አልቀየር አለ፡፡ ክፋቱ እየበዛ መጣ፡፡ አምላክ ቱማንም ሆነ በእሱ የተመረጡ አዝናቢዎችን፣ በምድር ዕፅዋት ላይ ሥልጣን ያላቸውን፣ በከብቱ እና በእንስሳው ላይ በረከት የሚመጡትን ሰዎች ማስቀየም ጀመሩ፡ ፡ ተመክሮ ተመክሮ የማይመለስ ሰው በመጨረሻ መቀጣቱ አይቀርም፡፡ አምላክ ቱማም ያደረገው ይሄንን ነው፡፡ የጥንቱን ሰው በብዙ ነገር ቀጣው፡፡ በበሽታ ቀጣው፣ በወረርሽኝ ፈጀው፡፡ በድርቅ ቀጣው፣ እንኳን ሰው ከብቱ የሚያኝከው አጥቶ ረገፈ፡፡ ኮሞሮቶች እንኳን ቢለምኑት ቱማ አልሰማቸውም፡፡ ሕዝቡም፣ ከብቱም መርገፍ ሲጀምር ስደት አማራጭ ሆነ፡፡ የተሰደደውም የበረታው*

> *ነው፡፡ አብዛኛው በየመንገዱ ወድቆ ነው የቀረው፡፡ ብዙ ከብት የትም ቀርቷል፡፡ ርሀቡ ከባድ እንደነበር አባቶቻችን ይነግሩናል፡፡ የመኤኒት ሕዝብ የሚሰደድ ሕዝብ አልነበረም፡፡ ነገር ግን አምላኩን በማስቀየሙ ተቀጥቷል፡፡ በደስታ ከሚኖርበት፣ ሁሉ ከሞላበት ምድር ምንም የሌለው ሆኖ ተሰደደ፡፡ ከኦሞ ጥግ ተነስቶ የሚበላ ፍለጋ ብዙ ተንከራተተ፡፡ ቢያለበት ተበተነ፡፡ የየጎሳ መሪው በፈለገበትና በተጓዘበት ሌላው ተከትሎ ተሰደደ፡፡ በየጫካው የቀረው ብዙ ነው፡፡ ጎሳውን ተከትሎ እግሩ በደረሰበት ቦታ ሁሌ እየተጓዘ እርስ በርሱ ተለያየ፡፡ የተጠፋፋው ብዙ ነው፡፡ (ዝኒ ከማሁ)*

እንደ ብሔረሰቡ የመንፈሳዊ ሚት ትረካ የመኤኒት ሕዝብ በማጥፋቱ ከነበረበት ቦታ በርሀብ  ምክንያት መሰደዱ ብቻ ሳይሆን፣ በየቦታው ተበታትኖ ለመቅረቱም መንስኤ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በረጅሙ የስደት ጉዞ ውስጥ የብሔረሰቡ አባላት በየደረሱበት በመበጣጠስና በመከፋፈል ተለያይተዋል፡፡ ለዚህም ጥሩ አብነቱ በስደት ወቅት ከአካባቢያቸው ተለይተውና ለብቻቸው ተቆርጠው የቀሩት “ቺሪም” እና “ሜላ” በመባል የሚጠሩት የብሔረሰቡ አባላት ናቸው፡፡ ሁለቱ ከብሔረሰቡ ተለይተው በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ናቸው፡፡ የብሔረሰቡ የጥንት ሰዎች በሠሩት ስህተት የደረሰባቸው ቅጣት መሰደድ ብቻ ሳይሆን እስከ ዛሬ ድረስ የዘለቁ በሽታዎችም በዚያን ጊዜ የመጡ እንደሆነ አቶ ኦይትልዋ ገልጸው በብሔረሰቡ ውስጥ በብዛት የሚከሰቱት ወባ እና የሚጥል በሽታዎችም ያኔ የመጡ መሆናቸውን ያብራራሉ፡፡

> *. . . አሁን ድረስ አልጠፉ ያሉ እና ቁጣ የሆኑ በሽታዎች የተፈጠሩት ያኔ ነው፡፡ ለምሳሌ የሚጥል በሽታ ትልቅ ቁጣ ነው፡፡ የመኤኒትን ብሔረሰብ አባላት በየጊዜው የሚመታ በሽታ ነው፡፡ የጥንት አባቶች ሲናገሩ ይሄ በሽታ ያኔ አምላክ ቱማ በተቆጣ ጊዜ የመጣ ነው፡፡ ምክንያቱም የክፉ እጣ ምሳሌ ነው፡፡ የሚጥል በሽታ ያለበት ሰው በማኅበረሰቡ ውስጥ እንደተረገመ ተደርጎ የሚቆጠረው ለዚህ ነው፡፡ አስፈሪ ቁጣ ስለሚመጣ በበሽታ የተያዘውን ሰው ቶሎ የማስወገድ የሚፈጸመው ለዚህ ነው፡፡ የያኔው ቁጣ ይሄ ብቻ አልነበረም፡፡ ዛሬ ወባ የሚባለው በሽታም የመጣው ያኔ ነው፡፡ ወባ የሚባለው የንዳድ በሽታ እንዲሁ ያኔ በተሠራው ክፉ ሥራ የመጣ ነው፡፡ አምላክ ቱማ በወባ የሚቀጣው ለዚህ ነው፡፡ አንዳንድ ኮሞሮቶች ለዚህ የታዘዙ ናቸው፡፡ አሁንም ቢሆን የሕዝቡን ክፉ ሥራ አይተው ሕዝቡን በንዳድ ይመቱታል፡፡ የወባ ንጉሦች አሁንም በየቦታው አሉ፡፡ የጉንዳን ንጉሦችም አሉ፡፡  ከክፉ ሥራው እስኪመለስ ድረስ ይቀጡታል፡፡ ኋላ ሕዝቡ ተሰብስቦ ይቅርታ ሲጠይቅ በሽታው እንዲቀርለት ይደርጋሉ፡፡*

*ሕዝብ አሁንም ድረስ አጥፊ ነው፡፡ አምላክ ቱማም በየጊዜው በኮሞሩቶች፣ በታላላቅ የእምነት መሪዎች ወይም ኘራዮች አማካይነት ሕዝቡ ከክፉ ሥራው እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡ መኤኒት ለአምላኩ በሥርዓት ሲታዘዝ በደስታ እና በተድላ ይኖራል፡፡ ክፉ ሥራው ሲያይል ለጠላቶቹ ጭምር አሳልፎ ይሰጠዋል፡፡ እርስ በርስም መስማማቱ ይጠፋል፡፡ ኮሞርቶቹ ግን ሁል ጊዜ ለሰው ደግ ነገርን ያደርጋሉ፡፡ ከአምላክ ለማስታረቅ ይጥራሉ፡፡ አጥፊዎችንም ለይተው ይቀጣሉ፡፡ ኮሞሮቶች ከአምላክ ጋር እየተለማመኑ የሚበጀውን ለሕዝቡ ያደርጋሉ፡፡ እነሱ ተጠብቀውና ራሳቸውን ለይተው የሚኖሩ ናቸው፡፡ የሚበሉትን እና የሚጠጡትን ለይተው የሚኖሩ ናቸው፡፡ ከእነሱ በታችም ኮሞሮት በይቶ የሚባሉ አሉ፡፡ ሥራቸው በሕዝቡ እና በኮሞርቶች መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር መንገዱን ማመቻቸት እና ልዩ ልዩ ሥራዎችን ማከናወን ነው፡፡ የኮሞርቶቹ ረዳቶች ናቸው፡፡ ኮኮም ይባላሉ፡፡ ትዕዛዝትን ያስተላልፋሉ፡፡ ውሳኔዎችን ያስፈጽማሉ፡፡ አጥፊዎች እንዲቀጡ ያደርጋሉ፡፡ የተበደሉ ጉዳያቸውን ሲያቀርቡ ወደ ኮሞርቶች ያደርሳሉ፡፡ ውጤቱንም መልሰው ያሳውቃሉ፡፡ ኮሞሩቶች ከአምላክ ጋር እንደሚገናኙት ሁሉ እነሱም ከኮሞሩቶች እና በሰዎች መካከል ሆነው ያገለግላሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ባሮ)*



**አቶ ኦይትሉዋ ፋጂዎ፣ (ፎቶ በአጥኚው)**

አምላክ የፈጠራቸው ፍጡሮቹ ከሕግና ከትዕዛዙ ሲወጡ መቆጣቱ፣ መገሰፁ እና መርርም ሲል ማጥፋቱን የተለያዩ የእምነት ሚቶች ተርከዋል፡፡ በዚያው መጠን ፍጡራኑ ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ ሲጠይቁ አምላክ እንደሚሰማቸው፣ ፊቱን እንደሚመልስላቸው፣ ምሕረቱን እንደሚሰድድላቸው ተጽፏል፡፡ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይቅርታ መጠየቅና መጸለይ ምሕረትን እንደሚያሰጥ በነቢያቱ አንደበት እንደሚከተለው መናገሩን መጽሐፍ ቅዱስ ይተርካል፡፡ "ምድሪቱን ይበላ ዘንድ አንበጣን ባዝዘው፣ ወይም በሕዝብ ላይ ቸነፈር ብሰድድ፣ በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፣ ፊቴንም ቢፈልጉ፣ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፣ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፣ ሃጢአታቸውንም እፈውሳለሁ" (2ኛ ዜና 7፡13)፡፡

የመኤኒት የመንፈሳዊ ሚት ትረካም እንደሚያስረዳው፣ መኤኒቶች ለምለም ከነበረው የጥንቱ አካባቢያቸው ተሰድደው በየቦታው ተቆራርጠው መኖር ከጀመሩ በኋላም አምላካቸውን ቱማን ከማመስገን አለማቋረጣቸውን ነው፡፡ ዛሬም ድረስ አምላካቸውን ቱማን በኮሞሮቶቻቸው እና በባሕል ሃይማኖት መሪዎቻቸው ወይም ኘራዮች አማካይነት አማላጅነት ያመልኩታል፡፡ ቱማ መኤኒቶችን መፍጠር ብቻ ሳይሆን፣ የሚኖሩበት ምቹ ምድር እና የአየር ጠባይን፣ ዝናብን፣ አዝርዕትን፣ እንስሳትን፣ አራዊትን እና ነፍሳትን ሁሉ ለመጠቀሚያነት ሰጥቷቸዋል፡፡ የመኤኒቶች አምላክ ቱማ ሁሉን ካዘጋጀና ካመቻቸ በኋላ እየተዋለዱ ሲበዙ እያንዳንዱ በጎሳ በመሪው አማካይነት እንዲተዳደር የጎሳ መሪዎች ሃይማኖታዊ ኃላፊዎችም ጭምር ሆነው ሕዝቡን እንዲመሩ እንዳደረገ ይታመናል፡፡ ኮሞሮቶች የዓለማዊው እና የመንፈሳዊው ሥልጣን ባለቤቶች ሆነው ከአምላክ ቱማ የታዘዙ ነገሮችን ለሕዝቡ እያሳወቁ፣ ሕዝቡም በተቸገረ እና የአምላኩ እገዛ ባስፈለገው ሰዓት በእነሱ አማካይነት ጥያቄው እየተፈታለት፣ ችግሩ እየተቃለለት ኖረዋል፡፡

በብሔረሰቡ እምነት አምላክ ቱማ መኖሪያው በሰማይ ሆኖ ዛሬም ድረስ በእያንዳንዱ መኤኒት ልብ ውስጥ እንደሚያድር ይታመናል፡፡ አቶ ብርሃኑ ወርቁ የአምላክ ቱማን በሁሉ መገኘት እንዲህ ይገልጹታል፡፡

> *በመኤኒት ዘንድ አምላክ ቱማ ይኖራል ተብሎ የሚታመነው በሰማይ ነው፡፡ የጥንት ሰዎች ከቱማ ጋር ቃል በቃል ይነጋገሩ*

> *እንደነበር አባቶቻችን ያስረዳሉ፡፡ የመጀመሪያ የሆኑ መኤኒቶች ማለት ነው፡፡ እሱ አምላክ ጥንትም ይሁን አሁን ከሁላችን ጋር አለ ብለን እናምናለን፡፡ ቱማ በሰማይ ይኑር እንጅ በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ የሚያድር ነው፡፡ ከእኛ ጋር መገናኘት ሲፈልግ በኮሞሮች እና በሃይማኖት አባቶች በኩል ያገኝናል፡፡ የአምላክ ሥራ ሰዎቹን ማኖርና መምራት ስለሆነ እሱ ለእኛ ለመኤኒቶች አንዴ የሚያስፈልገንን ሁሉ ሰጥቶናል፡፡ እሱ ቀጥታ ከኮሞሩቶች ጋር ይገናኛል፡፡ እኛም ኮሞሮቶቻችንን እናገኛቸዋለን፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ባቹማ)*

አምላክ ቱማ መኤኒቶችን በኮሞሮቶች አማካይነት ይቆጣጠራል፡፡ ኮሞሮቶች ከአምላክ ቱማ ጋር የሚነጋገሩ ብቻ ሳይሆን ፣ ከሚመሩት ሕዝብ ጋርም በጠበቀ ግንኙነት ያላቸው የሰዎችን ልመናና ፈቃድ ለአምላክ ቱማ የሚደርሱ ጭምር ናቸው፡፡ በእነሱ እና በሰው መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያካሂዱት ከሥራቸው የራሳቸው መንፈሳዊ እና ዓለማዊ ሹመት ባላቸው፣ እነሱን በሚያገለግሉ እና ኮሞሮት በይቶ በተሰኙ ረዳቶቻቸው አማካይት ነው፡፡

> *ኮሞሮቶች የተለዩ እና የተመረጡ፣ ራሳቸውን በጽሞና እና በትዕግስት የሚያኖሩ ናቸው፡፡ እንቅስቃሴያቸው የተመጠነ፣ የአኗኗር ሥርዓታቸው ቁጥብነት የሞላው ነው፡፡ በተለይ የጥንት ኮሞሮቶች ክብራቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ቃላቸው የሚደመጥ፣ ቁጣቸው የሚፈራ ነው፡፡ እነሱን ዝም ብሎ መቅረብም አይቻልም ነበር፡፡ እነሱም በየአልባሌው ቦታ አይገኙም ነበር፡፡ የራሳቸው የክብር ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ አገልጋዮች አላቸው፡፡ እነሱን ማግኘት የሚቻለውም በቀጠሮ እና በሥራቸው ባሉ አገልጋዮቻቸው አማካይነት ነው፡ ተፈጥሯዊም ይሁን ሰው ሠራሽ ችግር ሲያጋጥመን የምንሔኸው ወደ ኮሞሮቶቻችን ነው፡፡ እነሱ ደግሞ አምላክ ቱማን ለምነውና ይቅርታ ጠይቀው ያስታርቁናል፡፡ ሕዝቡም ጥፋት ካጠፋ የአካባቢ ሽማግሌዎችን መርጦ ይቅርታ እንዲደረግለት ወደ ኮሞሮቶች ይልካል፡፡ ሽማግሌዎቹ ኮሞሮት በይቶ የተሰኙትን ረዳቶች አግኝተው ችግራቸውን ያስረዳሉ፡፡ በእነሱ አማካይነትም ጉዳዩ ኮሞሮቶች ጋር ይደርሳል፡፡ ችግሩም ይፈታል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ወ/ሮ ቦልጃ ገሲዮ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ኤራ)*

ኮሞሮት በአምላክ ፈቃድ ሕዝብን እንዲያስተዳድር የሚመረጥ ሲሆን ስልጣኑም የዕድሜ ልክ ነው፡፡ አንድ ኮሞሮት ሲሞት አምላክ ቱማ የመረጠው በሥርዓት ውስጥ አልፎ የአባቱን ቦታና ሥልጣን በመረከብ ዓለማዊ እና መንፈሳዊ ኃላፊነቱን ይጀምራል፡፡ ኮሞሮቶች ኃይልና ሥልጣን ከአምላክ ቱማ የሚሰጥ ሲሆን ተአምራትና ድንቃ ድንቅን እንደሚያደርጉ ይታመናል፡፡

በብሔረሰቡ እምነት የኮሞሮቶች አንደበት እና እጅ/ መዳፍ ከፍተኛ ክብር ያላቸው እና ተአምራቶችም የሚገለጡባቸው ናቸው፡፡ የተሰጣቸው ኃይልም ከንግግራቸው በተጨማሪ በእጃቸው/ በመዳፋቸው ላይ እንደሚገለጥ ይታመናል፡፡ አንድ ኮሞሮት ሲሞት ወራሹ ልጅ የሚረከበው እና በእጅ ለይ የሚደረገው አምባር የኃይሉ መገለጫ እንደሆነም ይታመናል፡፡ አንዳንዴ በአካባቢ የሚፈጠሩና የማኅበረሰቡን አኗኗር የሚረብሹ ነገሮች ሲከሰቱ የሚቋጩት በኮሞሮቶች ፊት ቀርቦ እጃቸውን በመምታት እና መህላ በመፈጸም ነው፡፡ የኮሞሮቶችን እጅ ይዞ የማለ የሚናገረው እውነተኛውን ነገር እንደሆነ ይታመናል፡፡ በድፍረት ወይም በሌላ ምክንያት የኮሞሮቶችን እጅ መትቶ የማለ እሱም ሆነ የእሱ ዘር ማንዘሮች ከፍተኛ አደጋ ውስጥ እንደሚወድቁና እጣ ፈንታቸው መጥፎ እንደሚሆን ያምናሉ፡፡ በመኤኒት ብሔረሰቡ ውስጥ አንድ ያልተጻፈ ግን በአብዛኛው መኤኒት ልቡና ላይ የታተመ ሀቅ አለ፡፡ እሱም እውነትን መናገር ነው፡፡ አንድ መኤኒት ለሠራቸው ሥራዎች፣ ለአጠፋቸው ጥፋቶች ወይም ለገጠሙት ክስተቶች እውነት የመናገር ልማድ አለ፡፡ ይሄንን እውነትን የመናገር እና የሠሩትን ያለመደበቅ ጉዳይ አቶ በድሉ ካሳ እንዲህ ይገልጹታል፡፡ "በመኤኒት ዘንድ ውሸት የለም፡፡ መኤኒት ከገደለ ገደልኩ ይላል፣ ከሰረቀ ሰረኩ ይላል፣ ከደፈረ ደፈርኩ ይላል፡፡ ምክንያቱም አምላክ ቱማ ሁሉን ያያል፣ ሁሉን ይቆጣል፣ በሁሉ ላይ ይፈርዳል፡፡ ኮሞሮቶችም ሆኑ ኘራዮች የተሰወረውን ነገር ያውቃሉ፡፡ ቁጣቸው በዋሸው ሰው እና በዘሮቹ ላይ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ባቹማ) ይሁን እንጂ መኤኒቶች ሁሉ አንዱ ከአንዱ ባለው የጠባይ ልዩነት፣ በህይወት ውጣ ውረድ ላይ እንደሚያዳብረው የግል ሰብዕና፣ እንደ ፈጸመው ወንጀል ክብደትና እንደሚያስከትለው ውጤት አልፎ አልፎም ቢሆን እውነትን መደበቅ ይስተዋላል፡ ፡ ይኼ እውነትን መደበቅ ግን የመጣው ከጊዜ በኋላ እና ግለሰብ በሚያዳብረው የግል ገጠመኙ እና ከሌሎች ማኅበረሰቦች በሚወርሰው ልማድ መሆኑን አቶ በድሉ ጨምረው ይገልጻሉ፡፡

> *ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንዳንዶቹ መዋሸትን እየተለማመዱ መጥተዋል፡፡ እንደ እኔ የዚህ መነሻው ከሌላው ማኅበረሰብ ዘንድ የሚለመድ ጠባይ ነው፡፡ ዘመኑ አንዱን ከአንዱ የሚያቀራርብ ነው፡፡ ከተሞች እየተስፋፉ ነው፡፡ በአብዛኛው ወጣቶች ናቸው ለዚህ የሚጋለጡት፡፡ በቅርብ ወዳሉ ትልልቅ ከተሞችም ይሄዳሉ፡፡*

*እዚያ ብዙ ጥሩ ያልሆኑ ነገሮችን አይተው ይመጣሉ፡፡ ውሸትም የተለመደው በዚህ መልኩ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡*

የአቶ በድሉን አባባል ወ/ሮ ኮያ ታይሲ ያጠናክሩታል፡፡ ኮያ እውነትን ስለመናገር የሚከተለውን ይገልጻሉ "በኛ በመኤኒት ውሸት የለም፤ እውነትን ነው የምንናገረው፡፡ ለምሳሌ አንዷ ሴት ባሏ ካልሆነ ወንድ ጋር፣ ማንም ሳያይት የሥጋ ግንኙነት ብታደርግ ለባሏ ትናገራለች፣ አትዋሽም፡፡ ወንዱም ቢሆን ያደረገውን ለሽማግሌ ይናገራል፡፡ እኛ ዘንድ ውሸት የለም፡፡ አምላክም፣ በአምላክ የተሰጡንም ይቀጡናል" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ወጅናሌሙ)፡፡

በዘመናት የኑሮ መስተጋብሩ እውነትን መናገር አንድ እሴቱ በሆነው የመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ ቀስ በቀስ አንዳንዶች ውሸትን የተለማመዱበትን እና በድፍረትም መዋሸት ስለመጣበት መንገድ አቶ ጸሎጋ ጎርጌ የሚከተለውን ይናገራሉ፡፡ "በውሸታቸው ራሳቸውንም ሆነ ቤተሰቦቻቸውን ያስጨረሱ አውቃለሁ፡፡ ይሄንን ጠባይ ግን ያመጡት እና በመኤኒት ውስጥ እያስፋፉ ያሉት ወደ ከተማ ደጋግመው የሚሄዱና ከሌሎች የከተማ ሰዎች ጋር የሚውሉ ሰዎች ናቸው፡፡ በተለይ ወጣቶቹ አዳዲስ ልማዶችንና ጠባዮችን የሚቀስሙ በመሆኑ እነሱ ይበዛሉ፡፡ በሥራ እና በልዩ ልዩ መንገድ አልፎ አልፎ ወደ አካባቢያችን ከሚመጡ ሰዎችም ይማራሉ" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ሀዱባ)፡፡

በኮሞሮት ፊት ሀሰትን ይዞ በድፍረት መቆም፣ በውሸት መማል በርካታ ችግሮችን እንደሚያመጣ እና የሚመጣው ጣጣ ማለቂያ የሌለው እንደሚሆን ይታመናል፡፡ በሽታ፣ ወረርሽኝ፣ ሞት፤ ሰውን፣ እንስሳትን፣ ዕፅዋትን፣ ሰብልን እና በሀሰት የማለው ሰው ዙሪያ ያሉ ማንኛውንም ተያያዥ ነገሮች የሚያጠቃ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ መከራ በጊዜ የተገደበ ሳይሆን ከወራት ወራት፣ ከዓመት ዓመታት የሚሻገር፣ ከቦታ ቦታ የሚኖር ነው፡፡ ተከትሎ የሚጓዝ ነው፡፡ አቶ ካንጋ ባሩኚ በአንድ ወቅት የእሳቸው የቤተሰብ አባል የሆነ ሰው የኮሞሮቶችን እጅ መትቶ በሀሰት በመማሉ በእሳቸው እና በዘሮቻቸው ላይ ስለደረሰው አሳዛኝ ቅጣት ከዚህ በታች ያለውን ይገልጻሉ፡፡

*ጠቡ የተነሳው ቀደም ብሎ በነበረ የደም ጉዳይ ነው፡፡ በእርግጥ ያኔ ከኛ ወገን አንድ ሰው በመገደሉ መረር ያለ ጠብ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ብዙ የታየበት ግድያ ነበር፡፡ የሞተው ወጣት በመሆኑ ወንድሞቹም ሆነ ዘመድ አዝማዶቹ ለመበቀል ጥረናል፡፡ የገዳይ ወገኖች ግን ፈጠን ብለው ሽማግሌ ላኩ፡፡ መጀመሪያ ቢደበራን (የመቀበሪያውን ከብት) ላለመቀበል ብዙ አሻፈረኝ ብለን ነበር፡ በኋላ ባሕል ነውና፣ ሕግ ነውና፣ የመኤኒት መተዳደሪያ ነውና ተቀበልን፡፡ ቀጥለን ቤዴጄኑን (የጦር መመለሻውን ከብት) ተቀበልን፡፡ ይሁን እንጅ ልጃገረዲቱ እና ቀሪዎቹ ከብቶች ዘገዩ፡፡ በዚህ ምክንያትም ሌላ ብጥብጥ ሊነሳ ሆነ፡፡ በብዙ ጥረትና ልፋት ኮሞሮቶቹ አሻውን አስከፈሉ፡፡ ልጃገረዲቱ ተከፈለች፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጊዜም አሻው አልተሟላም፡፡ አንድ ከብት ቀረ፡፡ አሻው መከፈል የነበረበት በአንዲት ልጃገረድ እና በሰባት ከብት ነበር፡፡ ኋላ ሽማግሌዎቹም የገዳይ ወገኖችን ለመጨረሻ ጊዜ አስጠንቅቀው ካልሆነ ድጋሚ አሻው ፈርሶ መበቃቀል ሊከሰት እንደሚችል ተናገሩ፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የእነሱንም ልፋትና ጥረት የነሳቸውንም ክብር የሚነካ እንደሆነ በመንገር በጥቂት ወራት ውስጥ እንዲከፍሉ ነገሯቸው፡፡ ችግሩ የተከሰተው ይሄኔ ነው፡፡ የገዳይ ወገኖች የአሻውን ክፍያ ቀሪ አንድ ከብት መክፈል አቅቷቸው ሳይሆን ሆን ብለውና በንቀት ጉዳይ እንደሆነ ታወቀ፡፡ ይሄንን የሰማው የሟች ወንድም ቴአው (የሟች የመጀመሪያ ወንድም) ነው፡፡ እርቁን የፈጸመ፣ ከገዳዩ ጋር አንጀት የተባጠሰ ቴአው ነው፡፡ ገዳዩ በአንድ ገበያ ላይ ጠጁን ጠጥቶ በሞቅታ አላስፈላጊ ነገሮችን ሲነጋገር ቆይቶ የሟች ወንድምን ሲያየው የአሻውን ቀሪ ከብት ሊከፍለው እንደማይችል እና ቀስ ብሎ ከብዙ ዓመት በኋላ ሊከፍል እንደሚችል፣ ምክንያቱም እሱ ሁለተኛ ሚስት ለማግባት አሥራ ሁለት ከብቶች ስለሚያስፈልጉት አሻውን እንደማይከፍል ይነግረዋል፡፡ የሟች ወንድምም ይሄ በባሕላችን ልክ እንዳልሆነ እና አሻውን መክፈል ግዴታው እንደሆነ፣ ያንን የማያደርግ ከሆነ ግን ከባድ ቅጣት ሊደርስበት እንደሚችል ይነግረዋል፡፡ ጉዳዩ በዚህ ተጀምሮ መካረር ላይ ሲደርስ ሽማግሌዎች ነገሩን አብርደው ገዳይ አሻውን መክፈል ግዴታው እንደሆነ ይነግሩታል፡፡ ይሄንን የማያደርግ ከሆነ ምስክር ሆነው እንደሚቆሙ እና ከሀገር እንደሚገለል ያስረዱታል፡፡ ሰውዬው ግን ጥጋበኛ እና ደም የጠማው ዓይነት በመሆኑ እንዳሻው ሲፎክር እና ሲሸልል ቆይቶ ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡ (ዝኒ ከማሁ)*

በመኤኒት ብሔረሰብ ዘንድ ከአሻ ተሟልቶ አለመከፈል ጋር የተያያዙ በርካታ ትረካዎችን ማግኘት ይቻላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ገጠመኝ በብዙ ቦታ ይከሰታል፡፡ የዚህ አንደኛው ምክንያት አሻ ከፋዮቹ የአሻ ከብትን ለመክፈል ቤተዘመድ እንዲያዋጣላቸው ስለሚያደርጉ እንደሆነ ዋየች ጃሻ ይገልጻሉ፡፡ “እንኳን ከብቶቹ ገዳይ ልጅ ከሌለው ወይም በገዳይ ቤት ለአሻ የምትከፈል /የምትሰጥ ልጃገረድ ከሌለች እስከ ሰባት ቤት ድረስ ተፈልጎ ልጃገረድ ለአሻ

ትከፈላለች ትከፈላለች፡፡ ከብቶችም ከሌሉት እንዲሁ ተዋጥተው ይከፈላሉ” (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር፣ 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡ በሚች ወገንም ያለው ታሪክ ተመሳሳይ ነው፡፡ ለአሻ የሚከፈሉት ከብቶችን ቤተ ዘመድ ይከፋፈላቸዋል፡፡ በመሆኑም የቀሩ ከብቶች ካሉ ጠያቂው ፊት የሚቀድመው የቤተሰብ አባል ይሁን አንጅ ተሚልተው እንዲከፈሉ ግፊቱ እና ውትወታው የሁሉም ይሆናል፡፡ በአንጻሩ ካልተከፈሉ ደግሞ ጠቡ ቀጣይ ለመሆን ዕጣው ሰፊ ነው፡፡ አንዳንዴም አሻ ከፋዮቹ የሚች ወገንን በመናቅ፣ ወይም ምንም አያመጡም በሚል ሀሳብ ወይም ከብቶቹን ለራስ ለመጠቀም በመፈለግ አሻውን ሲያዘገዩ ተዳፍኖ የነበረው ችግር አገርሽቶ ሌላ እልቂት እና ሌላ ግድያ ይቀጥላል፡፡

> *ይኼ ከሆነ በኋላ የኛ ወገን የሚቹ ወንድም ቴአው ማለት ነው፣ ቀስ እያለ ሰውዬው በሌለበት ወደ አካባቢው ቀረብ እያለ በደንብ ስለ ሰውዬው ሲሰልል ይቆያል፡፡ ከዚያ በኋላ በእርግጥም ሰውዬው የቸገረው ሳይሆን ሰው የናቀ እና አውቆ ሰውን ወደ ስህተት የሚከት ሰው ነበር፡፡ ይኸ የሚች ወንድም ከዚያ በኋላ ቂሙን ቋጥሮ ሲዘጋጅ ቆይቶ አንድ ወቅት ላይ ሰው ሳያየው ወደ ገዳይ መንደር ገስግሶ በሰውዬው ቤት ላይ እሳት ይለቅበታል፡፡ ያኔ በቦታው የነበሩት ህፃናት ነበሩ እና እሳቱን ቶሎ መከላከል አልተቻለም፡፡ ብዙ ጥፋት ጠፋ፣ ብዙ ጉዳት ደረሰ፡፡ በዚህ ጥፋት ውስጥ ትልቁ ጉዳት የሆነው የሰውዬው ቤት መቃጠል፣ የሰበሰበው ምርት መውደም አይደለም፤ በዚህ እሳት በቤት ውስጥ ያለች ህፃን በእሳት ተለብልባ እንዳትሆን ሆና ሞተች፡፡*
>
> *የሆኖ ሆኖ ሰዎቹ ሀዘናቸውን ካወጡ በኋላ ይሄንን ድርጊት ሊፈጽመው የሚችልን ሰው ለማወቅ ፍተሻ ተነሳ፡፡ በዚህ እልቂት አጠቃላይ የጎሳው ሰዎች ለበቀል ተነሱ፡፡ ማንም ይሁን ማን ይሄንን የሠራውን ሰው ጎሳ ለማጥፋት በያለበት ተዘጋጁ፡፡ እኛም የቆየ ቂርሾ ስለነበረን የራሳችንን ዝግጅት አደረግን፡፡ እነሱ ይሆናሉ የሚል አንዳንድ ወሬም ይመጣ ጀመር፡፡ በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎቻችንን፣ ህፃናትንና ሴቶችን ለመከላከልና ከጥፋት ለመጠበቅ ማሸሽ ጀመርን፡፡ የሚሆነው አይታወቅም ብለን ከኛ ወገን ይሄንን ድርጊት የፈጸመ ይኖር እንደሆነ ሁሉንም ጠየቅን፡፡ ይሁን እንጅ ማንም ይሄንን ድርጊት ፈጽሚያለሁ ያለ ሰው ጠፋ፡፡ በሌላ ወገን ሰውዬው ከብዙ ሰዎች ጋር በተለያየ ምክንያት ጠብ ውስጥ የገባ በመሆኑ ከማንኛው ወገን ችግሩ እንደተፈጠረ ለማወቅ አልተቻለም፡፡ ሌሎች ጎሳዎችም ሁኔታው ስላስፈራቸው እንደኛው ጉዳዩን በንቃት ማየታቸውን እና ራሳቸውን ከጥቃት ለመከላከል መዘጋጀታቸውን ቀጠሉ፡፡*
>
> *እንዲህ ዓይነቶቹ ችግሮች ከውስጥ ብቻ ሳይሆን ከውጭም ሊከሰቱ የሚችሉ ናቸው፡፡ ከኛም ከመኤኒቶች ውጭ ተፈጽሞ እንደሆነም*

*መታወቅ ነበረበት፡፡ ከሱርማ፣ ከካፋ፣ ከቤንች ወይም ከሌላ አጎራባች ሕዝቦች ጥቃቱ ተሰንዝሮ እንደሆነም መታወቅ ነበረበት፡፡ ጉዳዩ እየሰፋ ሲመጣ ኮሞሮታችን የሕዝቡን እና የአካባቢውን ደህንነት ማስጠበቅ ስለነበረበት እነሱ ሄደው ከሰሱ፡፡ የደረሰባቸው ጥቃት ማንነቱን ባላወቁት አካል በመሆኑ ይታወቅልን አሉ፡፡ ይሁን እንጅ በአንደኛነት የጠረጠሩት የእኛን ጎሳ ነው፡፡ ምክንያቱም ከዚህ በፊት ተከፍሎ ያላለቀ አሻ በመኖሩ እና ከኛ ወገን ካለው የሚች ወንድም ጋር በመነጋገራቸው ነው፡፡*

*ከዚህ በኋላ ኮሞሮቱ ዐዋጅ ጠራ፡፡ በዚያ አካባቢ የሚኖር ማንኛውም ሰው፣ መኤኒት ይሁንም አይሁን፣ ቤንች ይሁን አማራ፣ ካፋ ይሁን ዲዚ ሌላው ሁሉም እንዲሰበሰብ ተጠራ፡፡ ያኔ በሀገር የቀረ ወንድ ሴት የሚባል የለም፣ ሁሉም ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን የደረሰ ሁሉ ኮሞሮቱ ወደ ወደተቀመጠበት ቦታ መጣ፡፡ በኛ አካባቢ እና እምነት እንዲህ ዓይነቱ ዐዋጅ ሲጠራ እና የኮሞሮትን እጅ በመሀላ ለመምታት ሲታዘዝ ከቤት መቅረት አይፈቀድም፡፡ ባልም፣ ሚስትም፣ የደረሱ ልጆችም ይመጣሉ፡፡ ያኔ እኔም፣ የእኔ ቤተሰብና ዘመዶችም ሁሉ ሄድን፣*

*መሀላው በማለዳ ነው የተጀመረው፡፡ እኛ ጆንበር ልትጠልቅ አካባቢ ነው ኮሞሮቱ ፊት የቀረብነው፡፡ ከእኛ በፊት ወጣቶቹ እየቀረቡ ይምላሉ፡፡ የሚንቀጠቀጡ፣ የሚለፈልፉ፣ የሚርጮኹ፣ ብቻ በፍርሃት የሚርዱ ሁሉ ነበሩ፡፡ በኋላ ይሄ የኛ የሚች ወንድም ቴአው ደርሶ መሀላውን ፈጸመ፡፡ ኮሞሮቱም አስቀድሞ እሱ ሊሆን ይችላል የሚል እምነትና ግምት ስለነበረው ደጋግሞ ጠየቀው፣ ልጁም ደጋግሞ መሀላውን እንዳላደረገ የኮሞሮቱን መዳፍ ይዞ ማለ፡፡ ኮሞሮቱም እጁን ይዞ ዓይኖቹን እያየ እንዲምል አደረገው፡፡ ልጁም ማለ፡፡ ሁላችንም ደስ ብሎን ከኛ ወገን እንዲህ ዓይነቱ መዘዝ ባለመምጣቱ ተደስተን ወደ ቤት መጣን፡፡ ኮሞሮቱም ይሄ ነገር ከኛ ውስጥ ከሆነ መዘዙ በአድራጊው እና በደባቂው፣ በዘሩ እና በጎሳው ላይ ይድረስ ብሎ ረገመ፡፡ እነሱም አንዴ ለኮሞሮት ነግረዋልና፣ መዳፍ አስመትተዋልና ውጤቱን በቅርብ እንደሚያዩ አምነው ተመለሱ፡፡ እንግዲህ በኛ እምነት የኮሞሮትን እጅ ከመታን በኋላ ሁሉም ይረግባል፡፡ አምላክ ቱማ በእነሱ አድሮ ጥፋተኛውን ስለሚቀጣው፣ ማንም ያለ ፍርሃትና ስጋት ሥራውን ይሠራል፣ ኑሮውን ይቀጥላል፡፡ ከዚያ በኋላ ይሄ የኛ ወገን የሆነ ልጅ በአካባቢው ብዙም ሳይቆይ ወደሌላ አካባቢ ሄደ፡፡ ስላላገባ ወደፈለገበት መሄዱ ማንንም አላሳሰበም ነበር፡፡ አንዳንዴ ወጣቶች እንዲህ ያደርጋሉ፡፡*

የልዕለ ተፈጥሮ አጋዥነትና ኃይል በዘወትራዊው ሕይወታቸው የሚገለጥባቸው ሰዎች በሰውነት ክፍላቸው/ አካላቸው ወይም ከእነሱ በሚወጣ ቃል ብቻ፣ ወይም ደግሞ በለበሱት ልብስና በያዙት ቁሳቁስ ላይ ኃይል አድሮ ታላላቀ ተአምራት ይከናወናሉ፡፡ ሙሴ በአሮን እጅ በኩል ብዙ ተአምራትን

እንዳደረገ የእስራኤላውያን የመንፈሳዊ ሚት በብዛት ይገልጣል፡፡ በኦሪት ዘመን ከተከናወኑት ተዛማጅ ትረካዎች ውስጥ የነብዩ ኤልያስ ደቀመዝሙር የነበረው ነብዩ ኤልሳዕ ከነብዩ ኤልያስ በተሰጠው መጠምጠሚያ/ሽርጥ የዮርዳኖስን ወንዝ እንደከፈለው ታሪኩ ያስረዳል፡፡ ከሐዲስ ኪዳን ትረካዎች ውስጥ በመጀመሪያው የሐዋርያት የመሰባሰቢያ እና በአንድነት የመኖር ሀሳብ ውስጥ ጥርጣሬ የገባቸው ባልና ሚስት ንብረታቸውን ሁሉ ሸጠው ለቡድኑ እንዲያስገቡ የሚያዘውን ደንብ ይጠራጠሩታል፡፡ ኋላም ከሸጡት የተወሰነውን ገንዘብ ከቤታቸው ደብቀው ሲመጡ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በተሰጠው ፀጋ የልባቸውን ምስጢር እንዳወቀባቸው እና ትዕዛዝንም በመጣሳቸው ባልና ሚስቱ በየተራ መሞታቸውን ይተርካል፡፡ ይህ የሚት ትረካ በአምላክ የተመረጡት ሰዎች የሰውን ልቡና እና ሀሳብ እንደሚያውቁ እንዲሁም ቅጣታቸውሞት ለእንደሚደርስ ነው፡፡ በመኤኒት ብሔረሰብም የአምላክ ኃይል እንዳደረባቸው የሚታመንባቸው ሰዎችን መዋሸት እና መደበቅ ቅጣቱ ከፍተኛ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ አቶ ካንጋ ባሩኚ በኮሞሮቶች ፊት ቀርቦ በውሸት የማለ ሰው ያጋጠመውንና የደረሰበትን እንዲህ ይተርካሉ፡፡

> *በኛ ላይ ችግሩና መዓቱ መከሰት የጀመረው ወር ሳይቆይ ነው፡፡ የዚያ ልጅ እናትና እህት ተከታትለው ሞቱ፡፡ በሦስት ቀናት ውስጥ ነው የሞቱት፡፡ ያኔ ብዙ ሰው ተደናገጠ፡፡ ቀጥሎ የሰውዬው አጎት፣ የሌላው አጎቱ ልጆች ተከታትለው ሞቱ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ እልቂት ሲከሰት በኛ ልማድ አንድ የተደበቀ እና የተሠራ ስህተት እንደሚኖር እናምናለን፡፡ በተለይ ሁላችንም የደነገጥነው የልጁ አባት በሦስት ቀን የሆድ በሽታ ሲሞት ነው፡፡ እንደወረርሽኝ ነው የሆነው፡፡ ያኔ እኔ አንጀት በደንብ እንዲነበብ ታዋቂ ዘሐይለጨለቆ (አንጀት አንባቢ) አስጠራሁ፡፡ የቀብሩ እለት አንጀቱን በደንብ አስነበብኩ፡፡ እንደጠረጠርኩት ነበር፡፡ አንጀት አንባቢው የተሠራና የተደበቀ ሥራ፣ ሃጢያት እንዳለ ነገረን፡፡ እውነቱ ካልወጣ፣ ሞቱ ገና እንደሚቀጥል ነገረን፡፡ እዚያው አንጀቱን እያነበበ፣ እያየ እና ምልክቱን እያሳየን ሞታችን እንደሚቀጥል ነገረን፡፡ ያኔ ሁሉም የኛ ዘሮች ተሰብስበው ምን ሊሆን ይችላል በሚለው ተወያየን፡፡ ሁላችንም በቅርቡ የማልነው መሀላ ስላለ ከዚያ ጋር የተገናኘ ሊሆን እንደሚችል አምነን ያንን ልጅ ከሄደበት እንደሚመጣ ማፈላለግ ጀመርን፡፡ ሰው በሰው ስናጠያይቅ ስናጠያይቅ ጉራፈርዳ ይኖር እንደነበር ተሰማ፡፡ እዚያም ያየው ሰው እንዳለ ስናፈላልግ፣ የሆነ ቀን ራሱ እብድ መስሎ መጣ፡፡ ፈጽሞ ያ የምናውቀው ልጅ አልነበረም፡፡ ራሱን ስቷል፡፡ የሚቀባጥር ሰው ሆኗል፡፡ በሽታው አንዴ ሄድ አንዴ መለስ የሚል ነበር፡፡ አንዴ ከአንድ ቦታ ቁጭ ብሎ ሳይንቀሳቀስ ይውላል፡፡ ደግሞ ለቀቅ*

> *ሲያደርገው ብረር ብረር ይለዋል፣ ገደሉ ሁሉ ሜዳ፣ ወንዙ መንገድ ይመስለዋል፡፡ ከጧት እስከ ማታ ይለፈልፋል፡፡ በመጣ በሳምንቱ መለስ ሲልለት ወደኮሞሮቱ እንድንወስደው እና የደበቀው ሃጢያቱ ያመጣበት ጥፋት እንደሆነ ነገረን፡፡ ያኔ እኔም ምን እንዳደረገ አጥብቄ ጠየኩት፡፡ ወደኮሞሮቱም ልወስደው እንደምችል ነገርኩት፡፡ እሱም የወንድሙን ገዳይ ለመበቀል፣ አሻውን ከፍሎ ባልጨረሰው የገዳይ ቤት ላይ እሳት እንደ ለኮሰ እና ሰዎቹ በቃጠሎው እንደሞቱ፡፡ በዚህ ሰበብ በተጠራው የመሀላ ቀን ኮሞሮቱ ሲጠይቀውና ሲያስምለው መዳፉን መትቶ መዋሸቱን ነገረኝ፡፡*
>
> *ከዚያ በኋላ እኔ የሀገር ሽማግሌዎችን ወደኮሞሩቱ ላክሁ፡፡ ይቅርታ እንደምንፈልግ፣ የሠራነው ሃጢአት እየቀጣን መሆኑን እና በሕዝቡ ፊት ይቅርታ ለመጠየቅ እንድምንፈልግ ተናግሬ መልዕክተኞች ላክሁ፡፡ ሽማግሌዎቹም በሁለት ቀናት ውስጥ መልስ ይዘው መጡ፡፡ እኔና ታናሽ ወንድሜ፣ እና ሌሎች ዘመዶች ሆነን ያንን ቴአውን የመነመነ ሰውነቱን በእንጨትና እንጨት ላይ አጋድመን ይዘን ሄድን፡፡ ይሄ ልጅ ገና ወደኮሞሮቱ ሲቀርብ መለፍለፍና መቀባጠር ጀመረ፡፡ የሠራውን ሥራ ሁሉ አንድ በአንድ ተናዘዘ፡፡ ከዚም የኛ ወገን የሆነ ሁሉ ተጠርቶ እንደገና ከእርግማን ነጻ እንዲሆን በኮሞሮቱ ፊት እየቆመ ተማጸንን፡፡  ኮሞሮቱም ከፍተኛ ቅጣት ቀጣን፡፡ ለአካባቢው ምሳሌ እንድንሆን ነው፡፡ ወደ አምስት ከብቶች ካሳ ከፍለናል፡፡ ያ ልጅ፣ ቴአው ግን ብዙም ወራት አልቆየ ራሱን ወንዝ ውስጥ ወርውሮ የአዞ ምግብ ነው የሆነው፡፡ ወንዝ ሲገባ እና አዞዎች ሲቀራመቱት ያዩ ከብት ጠባቂዎች መጥተው የሆነውን ነግረውናል፡፡ ክፉ ሥራ መጨረሻው ይሄ ነው፡፡ ዋና ዋናውን፣ የማስታውሰውን ተናገርኩ እንጅ ህፃናት ሞተዋል፣ ሴቶች ብዙ ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ መዘዙ ብዙ ዓመት ነው የተከተለን፡፡ ከእኛ ጋር መጋባት እስኪፈሩ ድረስ እንድንገለል አድርጎናል ድርጊቱ፡፡ የኮሞሮት እጅ የተቀደሰ ነው፡፡ ተአምራት የሚሠራበት ነው፡፡ ያ ልጅ ያቃለለውና የዋሸው ይሄንን ነው፡፡ አንዳንድ ወጣቶች ወደ ከተማ እየሄዱ አንዳንድ ልማዶችን ከሌሎች ስለሚማሩ የራሳቸውን እምነትና ባሕል ማራከስ ይሠራሉ፡፡ አምላክ ግን ሁሌም ይቀጣቸዋል፤ ይቀጣናል (ዝኒ ከማሁ)፡፡*

የኮሞሮቶች እጅ/መዳፍ መምታት የአምላክ ኃይልና ክብር ፊት የመቆም ያህል ተደርጎ ይታሰባል፡፡  አምላክ ሁሉን አዋቂ እንደሆነ እና የፈጠራቸው ፍጡራን የሚያደርጉትንም ሆነ የሚያስቡትን የሚያውቅ፣ ነገሮች ከመደረጋቸው በፊትም ሆነ ከተደረጉ በኋላ በማን እና ምን እንደተደረጉ ሁሉን የሚያይ እንደሆነ ይታመናል፡፡ እንደዚሁ ሁሉ የአምላክ ቱማ መንፈስ ያረፈባቸው ኮሞሮቶች በእሱ መንፈስና ኃይል ታግዘው ነገሮችን እንደሚያውቁ ይታመናል፡፡ በመሆኑም በፊታቸው የሚቆም ሰው በተለይም በድብቅ እና በስውር ሰውን፣

ወይም አካባቢውን የሚጎዳ ነገር አድርጎ ለመሀላ ከተጠራ እውነቱን ለመደበቅ አቅም ያጣል፡፡ ብዙዎች በቁርጥ ሰዓት እውነቱን እንደሚናገሩ አቶ ጳስጋላ ቢጎሉኚ በሚከተለው መልክ የሰሙትን ይተርካሉ፡፡

*በድሮ ጊዜ ነው፡፡ እኔ ልጅ ነበርኩ በጊዜው፡፡ በኛ አካባቢ አንድ ትልቅ ሰው ሰባት ከብቶች ጠፉት፡፡ ሰውዬው ደግሞ ብዙ ወንድ ልጆች ያሉት በመሆኑ ዝርፊያውን ለማወቅ አካባቢውን አስጨነቁት፡፡ ጉዳዩ ቀስ በቀስ በሁሉ ደረሰ፡፡ በዚያ ዘመን ደግሞ ከጎረቤት አካባቢዎች እየመጡ ከብት ወደራሳቸው የሚወስዱ እና የሚሰርቁ ስለነበሩ ጉዳዩ ትኩረት ጭንቀት ፈጠረ፡፡ አንዳንዱ ከብቶቹን የነዱት ከጎረቤት ወረዳ የመጡት ናቸው እና እኛም ወደ እነሱ እንሂድና ያገኘነውን ከብት ዘርፈን እንምጣ የሚል ሀሳብ አመጣ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ስርቆሹ ምናልባት እርስ በርስ ከሆነ ሰው ክልል ሄደን ሌላ እልቂት እናመጣለንና መጀመሪያ ውስጣችን ይጣራ ብለው ምክር ሰጡ፡፡ ሽማግሌዎች ተሰብስበው ብዙ መከሩ፡፡ ዘራፊውን ለማወቅ ብዙ ጥረት ተደረገ፡፡ ከብቶቹ የተዘረፉበት ሰውዬ ጠብና ግጭት እንዳለው እና እንደሌለው ብዙ ተጣራ፡፡ ሰውዬው ደግ የሆነ ሰው፣ ጠብ የማይወድ እንዲያውም አስታራቂ ነበር፡፡*

*በኋላ ሽማግሌዎች ተሰብስበው ከብቶቹ ከራሳችን በሆነ ሌባ መወሰዳቸውን እና አለመወሰዳቸው ለማጣራት ወደ ኮሞሮቱ ዘንድ ጉዳዩን አቀረቡት፡፡ ምክንያቱም ጎሳውን የሚያስተዳድረው፣ አዝናቢው እና የሚመራን እሱ ስለነበረ ጉዳዩን እሱ እንዲፈታው ሄዱ፡፡ እሱም ይህን ዓይነት ሌብነት በውስጣችን ባለ ሰው መፈጸሙን እና አለመፈጸሙን ለማወቅ ሁሉ እንዲሰበሰብ አስነገረ፡፡ ነፍስ ያወቀው ሴት ወንዱ በተቀጠረበት ቦታ መጣ፡፡ እሱም ዝርፊያውን የፈጸመ ሰው ከኛ ከሆነ በደንባችን መሠረት ጥፋቱን እንዲያምን ይቅርታ እንዲጠይቅ፣ ለጥፋቱም ካሳ እንዲሰጥ ተናገረ፡፡ በአካባቢያችን ዘልቆ ስርቆሹን የፈጸመ ከሌላው የመጣ ከሆነም እንዲታወቅ መሀላ እንዲፈጸም አዘዘ፡፡ ሁሉም ሰው እየቀረበ፣ መዳፍ እየመታ መሀላ ፈጸመ፡፡ ከአባቴ ጥቂት ዘግይቶ የቀረበ አንድ ሰው ወደ ኮሞሮቱ ፊት ሲቀርብ ሰውነቱ መርገፍገፍ ጀመረ፡፡ መቃጠል ጀመረ፡፡ ከኮሞሮቱ እግር ስር ወድቆ የእሱን እጅ በሀሰት እንደማይመታ እና ስርቆሹን እሱ እንደፈጸመ ተናገረ፡፡ ስርቆሹን መፈጸሙ ብቻ ሳይሆን ከብቶቹን በአንድ ቦታ እንዳጎራቸው እና የት እንደሚገኙ ተናገረ፡፡ ያ ሰው ዕድሜው ሰላሳ የሚጠጋ ነበር፡፡ በእሱ ጦስ ብዙ ሰው ከእርሻው፣ ከገበያው ተጓጉሏል፡፡ የኛዎቹ ወደ አጎራባች ሰዎች ሄደውና አጸፋ መልሰው ቢሆን ኖሮ፣ ሌላ ጠብ ሌላ ደም መፋሰስ ይፈጠር ነበር፡ ፡ ብቻ ማንም በኮሞሮት ፊት ሲቀርብ እውነቱን ይናገራል፡፡ መኤኒት የሆነ እንዲህ ነው፡፡ እስከመጨረሻው ቢደብቅ እንኳን በኮሞሮት ፊት አይዋሽም፡፡ አምላክን እንደመዋሸት ነው*

*የሚቆጠረው፡፡ አባቴ የነገረኝ ሌላም ተመሳሳይ ታሪክ አለ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ቂራ)፡፡*

በብሔረሰቡ አንዳንድ ኮሞሮቶች የዝናብ አዝናቢነት ሥልጣን ያላቸው ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በእንስሳት እና በነፍሳት፣ በአዝርዕት እና ዕፅዋት ላይ ሥልጣን ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ኮሞሩቶች ደግሞ የባሕል ሃይማኖት መሪዎች ኘራዮች ጭምር ይሆናሉ፡፡ ይሂም የመኤኒቶች አምላክ ጋር ያለውን የእምነት ትስስር ያጠናከረ ነው፡፡ ኘራዮች ወይም የባህል ሃይማኖት መሪዎች ሌላው የአምላክ ቱማ አገልጋዮች እና መንፈሱ ያደረባቸው፣ ለሕዝቡ የተሰጡ መንፈሳዊ ኃይል ያላቸው እንደሆኑ ይታመናል፡፡ እነዚህ የባሕል ሃይማኖት መሪዎች አንዳንዴ ኮሞሩቶች ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ያልሆኑ ናቸው፡፡

ስለ የባሕል ሃይማኖት መሪዎች ወይም ኘራዮች ሁለት የተለያዩ ሃማኖታዊ የሚት ትረካዎች ይቀርባሉ፡፡ የአንደኛው ወገን ትረካ ኘራዮች ወይም የባሕል ሃይማኖት መሪዎች የመኤኒቶች የጥንትና ነባር ሃይማኖትን የተከተሉ ሳይሆን በሂደት እና በጊዜ የመጣ ከሌላ የአጎራባች ሕዝቦች የተወረሰ ልማድ እንደሆነ አድርጎ ያቀርባል፡፡ ሁለተኛው ትረካ ደግሞ የባህል ሃይማኖቱ እና ኘራይነት ከጥንቱ የመጣ፣ መሪዎቹም በቱማ የተመረጡ እና ኃይል የተሰጣቸው መሆናቸውን ይተርካል፡፡ ለዚህም ብዙ ኮሞሩቶች አዝናቢዎች እና የባህላዊ የሃይማኖት መሪዎች መሆናቸውን በመጥቀስ የሚከራከሩም አሉ፡፡

ስለ ኘራዮች ወይም የባሕል ሃይማኖት መሪዎች የሚነገሩትን ሁለት የተለያዩ ሃይማኖታዊ የሚት ትረካዎች በቅደም ተከተል መመልከት በሚቱ ላይ ያለውን መረዳት ያሰፋል፡፡ በመሆኑም ከሁለቱም ወገን ያሉ የሚት ትረካዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም በኘራዮች ማመን ወይም የባሕል ሃይማኖቱ መሠረት ከአጎራባች ወረዳ ሕዝቦች የመጣና የተወረሰ እንጅ የመኤኒት ነባር የሃይማኖት ሥርዓት አይደለም ከሚሉ ትረካዎች ውስጥ ከዚህ በታች ያሉትን በመረጃ ሰጪዎቹ አማካይነት ማየት ይቻላል፡፡ ኘራይነት በውሰትና በመዋረስ ከሌላ ቦታ የመጣ መንፈስ መሆኑን የሚገልጹት ወ/ሮ ሞናይ ጋሹ ናቸው፡፡ ሞናይ በኘራይ ማመን ከአምላክ ቱማ የመጣ እንዳልሆነ እና ከአምላክ ቱማ የመጣው ኮሞሮትነት እንደሆነ በሚከተለው ትረካቸው ያብራራሉ፡፡

*በኘራይ ማመን የመጣው በቅርብ ጊዜ እንደሆነ እና የመኤኒት የጥንት አምልኮ እንዳልሆነ የሚናገሩ አባቶች አሉ፡፡ እንዲያውም ልማዱ የመጣው ከካፋ ዞን ካሉ ኘራዮች አንደሆነ ነው የሚታመነው፡፡ እዚያ በርካታ ኘራዮች አሉ፡፡ በተለይ በጣም ጥንታዊ የሆኑ እና መንፈሳቸውን ለብዙ ያዋረሱ ታላላቅ ኘራዮች እዚያ አሉ፡ የኛዎቹ እዚያ ሂደው መንፈሱን ተቀብለው ነው የሚሠሩት፡፡ እዚያ በጣም ታዋቂ የሆነ እና ለብዙዎች መንፈሱን ያካፈለ ኘራይ አለ፡፡ በእርግጥ ስሙ እና እሱን መፍራት በብዙዎች ዘንድ አለ፡፡ የኛ ዘሮች በፍልሰታቸው ጊዜ ወደ በርካታ አካባቢዎች ተጉዘዋል፡፡ ለከብቶቻቸው የግጦሽ ሳር ጨሌ ፍለጋ ብዙ ተጉዘዋል፡፡ ለራሳቸው የሚበሉትን ፍለጋ ረጅም የሚባል ስደት አድርገዋል፡፡ አንዳንዶቹም ወደተለያዩ አጎራባች ሕዝቦች ተቀላቅለዋል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አጋጣሚ ነው በኘራይ ማመንን ያመጣው አንጂ የመኤኒት ነባር እና የጥንት ሃይማኖት በቱማ መመን ነው፡፡ ቱማ የመረጣቸው ኃይል የሰጣቸው ኮሞሮቶችን ነው፡፡ አሁን እኛ የምናምነው የምንከተልው፣ የሚሉትን ትዕዛዝ የምንፈጽመው የኮሞሮቶችን ነው፡፡ እያንዳንዱ ኮሞሮት ከጥንት የመጣ ዘር አለው፡፡ ከመሠረቱ የጀመረ፡፡ ከዚያ አንዱ አንዱን ሲተካው አብሮ ኃይሉ እና ሥልጣኑ ይተላለፋል፡፡ አንድ አባት ለልጁ ያወርሳል፡፡ ያኔ ሲያወርሰው የቱማ ፈቃድ ያለበት ልጅ ነው የሚመረጠው፡፡ ሰዎች ስለወደዱ ወይም የተወሰኑ ሰዎች የፈለጉትን ልጅ አይመረጥም፡፡ ቱማ የፈቀደው ሰው ነው የሚመረጠው፡፡ እሱ ለፈለገው እና ለመረጠው ምልክቱን ይሰጠዋል፡፡ በእጁ ምልክቱን ጨብጦ ይገኛል፡፡ የቱማ ፈቃድ መሆኑ የሚታወቀው ያኔ ነው፡፡ የሰው ምርጫ አይደለም፡፡ ከዚያ የአባቱ የሆነ እና አባቱም ካባቶቹ የተረከበው የኃይል መገለጫ አምባር በክንዱ ላይ ያደርጋል፡፡ በቃ ከዚያ በኋላ አምላክ ቱማ ሥራውን ሁሉ በእሱ አማካይነት ይሠራል፡፡ እንጂ በኘራይ ማመን የጥንት ሃይይማኖት አይደለም፡፡ በእርግጥ የኛ ሰው ኘራይ አማኝ ነው፡፡ በሁሉም አካባቢ ቢኬድ በኘራይ ያምናል፡፡ እነሱም ብዙ ሥራዎች እና ተአምራቶችም ይሠራሉ፡፡ ግን ይኸ ዓይነቱ እምነት የጥንት አይደለም፡፡ በኋላ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች ሌሎች ሃይማኖቶችም መጥተዋል፡፡ ብዙ ሰው ያላቸው ሃይማኖቶች በኋላ በኋላ መጥተዋል፡፡ ይሁን አንጅ መኤኒት አብዛኛው አምለካኩ ቱማ፣ አስተዳዳሪዎቹ እና አስታራቂዎቹ ኮሞሮቶች ናቸው፡፡* (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ጀሙ)፡፡



ከግራ ወደ ቀኝ አጥኚው እና ወ/ሮ ሞናይ ጋሹ፣ (ፎቶ አቶ ብርሃኑ)፡፡

በሌላ ወገን ኅራይነት የጥንት፣ እነሱም የቱማ አገልጋዮች እንደሆኑ፣ የመኤኒቶች ሃይማኖት ከጥንትም በኅራዮች የሚታመን እንደሆነ የሚያስረዱ ትረካዎች አሉ፡፡ አብዛኛው ሰውም የባሕል ሃይማኖት ተከታይ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በኅራዮች ማመን ከጥንት የመጣ፣ የመኤኒት ብሔረሰብ አባላት ለስደት ከመዳረጋቸው በፊት የነበረ እንደሆነ የመንፈሳዊ ሚት ትረካው ያስረዳል፡፡ ኅራይ አወቀ ፎሮሾዋ ኅራይነት ከጥንት ከመሠረቱ የመጣ እና የመኤኒት እምነት መሠረት ያለው እንደሆኑ ያብራራሉ፡፡ ኅራይነትን ወደሌላ ሀሳብ የሚያስጠጉ እና ኮሞሮትነትን ብቻ የሚያደርጉ ሰዎች፣ ብዙ ኮሞሮቾች ኅራዮች እንደሆኑ ያለመረዳታቸው እንደሆነ በሚከተለው ትረካቸው ያስረዳሉ፡፡

> *ኅራይነት ወይም የባሕል ሃይማኖት ከአምላክ ቱማ የተሰጠ ኃይል ነው፡፡ ሥልጣኑን ማንም ሰው ስለፈለገ የሚያገኘውም አይደለም፡፡ ይሄ ዓይነቱ መንፈሳዊ ሐላፊነት ቱማ ለመረጠው ሰው የሚሰጠው ኃይል ነው፡፡ በእያንዳንዱ ኅራይ ላይ የሚወርድ ኃይል አለ፡፡ ያ ልዩ ኃይል እውነትን የሚገልጥ፣ የተሠወረውን የሚመረምር፣ አጥፊውን የሚከታተል እና የሚቀጣ ልዩ ኃይል ነው፡፡ በመኤኒት*

*እየበዛ የመጣ ልማድ አለ፡፡ ለምሳሌ ሰው ሰውን ዝም ብሎና በተራ ምክንያት ይገድላል፡፡ ሰው ተሰውሮና ተደብቆ ሰው ይገድላል፡፡ ማንም ሳያየው አድብቶ፣ ሰዓትና ቀን ጠብቆ ይገድላል፡፡ ስርቆሽም እንዲሁ ነው፡፡ አንዱ የአንዱን ከብት ነድቶ ይሄዳል፡፡ አንዱ የአንዱን ንብረት በስውር ይሰርቃል፡፡ እንደዚህ ሲሆን ማንም ስለማያየው ማስረጃ አይቀርብበትም፡፡ ተበዳይ የሚጠረጥረውን እከሌ ነው ቢል የሚሰማው የለም፡፡ ስላላየ ማስረጃ አይቆጠርበትም፡፡ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ዛሬ የመጡ አይደሉም፡፡ ጥንትም የነበሩ ችግሮች ናቸው፡፡ ጥንትም ሰው ሰውን በስውር ይገድላል፣ አንዱ የአንዱን ከብትና ንብረት ይሰርቃል፡፡ ስለዚህ ጥንትም አንዲህ ዓይነቱ ችግር ይፈታ የነበረው በኀራዮች ነው፡፡ ጥንትም ኀራይነት ነበረ፡፡ አምላክ ከሁሉም ጋር እየገባ ችግሮችን አያስተካክልም፡፡ ኀራይነት ያኔም አለ፡፡ ብዙ የጎሳ መሪዎች ኀራዮች ናቸው፡፡ ብዙ ኮሞሩቶች አዝናቢም ናቸው ኀራዮችም ናቸው፡፡ ታዲያ ይሄ ምንን ያሳያል? ኀራይነትን ለምን ፈለጉት? ምክንያቱም ዝናብን የማውረድ፣ ሌላም ታላላቅ ሥራ መሥራት የሚችሉ እና የተመረጡ ናቸው፡፡ ስለዚህ ተጨማሪ ነገር አያስፈልጋቸውም ነበር፡፡ ግን መንፈሳዊ ኃይልና ሥልጣንም ተደርቦ ስለተሰጣቸው ነው፡፡*

*ለምሳሌ እኔ ኀራይነትን ያገኘሁት በውርስ ነው፡፡ ውርሱ የመጣው ከአባቴ ነው፡፡ እኔ ልውረስ ስላልኩ የአባቴ ኃይል ወደእኔ አልመጣም፡፡ መንፈሱ ከአባቴ ልጆች መሀከል እኔን ስለመረጠኝ ነው፡፡ እኔ የተመረጥኩት በቱማ ፈቃድ ነው፡፡ ሌሎች ወንድሞቼ አልተመረጡም፡፡ አባቴም የተመረጠው እና ኃይሉ የተላለፈለት ከአባቱ ነው፡፡ እሱም ከወንድሞቹ መሀል ስለተመረጠ ነው፡፡ አያቴም ከዚያ በፊትም የነበረው ሰው ኃይሉን የተቀበሉት እንዲሁ ነው፡፡ ስለዚህ ኀራይነት ከጥንትም የነበረ ነው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ አወቀ ፎሮሾዋ፣ ግንቦት፣ 2011 ዓ.ም፣ ጨበራ)*

አወቀ ፎሮሹዋ እንደሚስረዱት ለእሳቸው የተላለፈው ኃይል መሠረቱ አምላክ ነው፡፡ ኃይሉ በውርስ የሚተላለፍ ነው፡፡ ለዚህም መረጃ አድርገው ራሳቸውን ያቀርባሉ፡፡ የኮሞሮቶችንም ሥራ ማነጻጸሪያ አድርገው ይናገራሉ፡፡ በእርግጥም ብዙ ዝናብ አዝናቢ ኮሮሞቶች አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች በአምላክ ቱማ ፈቃድ ኃይል እንደተሰጣቸው የሚታመኑ፣ እንደተሰጣቸው መክሊት በተፈጥሮ ላይ ማዘዝ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡ ይሁን እንጂ ከእነሱ ውስጥ ቁጥራቸው በጣም ቀላል የማይባሉቱ ኀራይነትን ደርበው ይሠራሉ፡፡ ኀራይነት መሠረቱ ከአምላክ ካልሆነ እነዚህ በአምልክ ቱማ ከመጀመሪያው የመኤኒቶች አባት ዘመን ጀምሮ ኃይልን የተቀበሉ ሰዎች ባላቸው የኮሞሮትነት ሥልጣን ላይ ለምን ይደርቡታል? የሚለው ጥያቄ ጠንን ያለ መልስ ይሻል፡፡ ምክንያቱም እንዚህ

ሰዎች መመረጣቸው፣ መከበራቸው እና ሌሎች መገለጫዎቻቸው ተመሣሣይነት አለው፡፡ የጥንት፣ ኾራዮችም በአምላክ ፈቃድ የመጡ፡፡ ሥልጣናቸው በሕይወት እስካሉ ድረስ የሚያገለግል፣ በሞት ሲለዩ ኃይላቸው አምላክ ቱማ ለፈቀደው የሚተላለፍ አድርገው ከሚያስቡት ውስጥ የአቶ ኮርዲ ሆይሺጊን ትረካ አንዱ ነው፡፡

*ለምሳሌ በእኛ በመኤኒቶች የባሕል ሃይማኖት የሚከተል ሰው ኾራዮችን በጣም የሚፈራም የሚያከብርም ነው፡፡ ምክንያቱም ኾራዮችን መዋሸት ብዙ ቅጣት ያመጣል፡፡ አንድ ጊዜ የኔ ዘመድ የሆነ ሰው፣ የእህቴ ባል ነው፡፡ ሧት ሚስቱ ወደ ከብቶቹ ስትሄድ ከወለደች አስር ቀን ያልሞላት ላሙ እና የወለደችው ጥጃ ሞተው ተገኙ፡፡ ሞተው ሳይሆን ተገድለው ነው፡፡ የእህቴ ባል የከብቶቹን መሞት እንዳወቀ ማን ሊገድላቸው እንደሚችል ጠረጠረ፡፡ የጠረጠረው ሰው ከሁለት ቀን በፊት ገቢያ መሀል ያለ ጠጅ ቤት የተጋጨው በቅርብ የሚኖር ሰው ነበር፡፡ ለካ ሰውዬው ቂሙን እንደቋጠረ ኖሮ ምቹ ሁኔታ ሲያገኝ የዘመዴን ከብቶች ይመርዛቸዋል፡፡ የሚገድል ነገር እንዲበሉ ያደርጋቸዋል፡፡ የወለደችው ከብት እና የምትጠባው ጥጃ ላይ ነው መርዙን የሰጠው፡፡ በዚህ ምክንያት ነው የሞቱት፡፡*

*በኋላ የእህቴ ባል ወደ ኾራይ ሄደ፡፡ የደረሰበትን በደል ነግሮ የሚጠረጥረውን ሰው ማንነት እና ለጥርጣሬ ያበቃውንና የተጋጬበትን አጋጣሚ ተናገረ፡፡ ኾራዩም የሆነውን በጥሞና ካዳመጠ በኋላ ተጠርጣሪው እንዲመጣና እንዲጠየቅ ወሰነ፡፡ እናም በረዳቶቹ አማካይነት አስጠራው፡፡ ገዳዩ ጥሪ እንደደረሰው አልመጣም ብሎ አንገራገረ፡፡ ምክንያቱም የሠራውን ሥራ ያውቃልና ነው፡፡ ከዚያም ለሁለተኛ ጊዜ እንዲመጣ ሰው ተላከበት፤ ሰውዬው አሁንም አልመጣም ብሎ በዚያው ቀረ፡፡ እንዲያውም አዲስ ሃይማኖት መያዙን እና መቼም እንደማይመጣ ሰው ላከ፡፡ ከዚያ ኾራዩ የእኔን ዘመድ በቃ አንተ ሥራህን ጨርሰሃል፣ እኛ እንዲመጣ ጠርተነዋል፡፡ የወደደውን መርጧል፡፡ እኛም የወደድነውን እናድርግ፡፡ አሁን አንተ ወደ ቤትህ ሂድ ከዚያ የሚሆነውን ጠብቅ አለው፡፡ እኛም የተባለውን ሰምተን ተመለስን፡፡ ከዚያ ጥቂት ወራት አለፉ፡፡ ምንም የሆነ ነገር አልነበረም፡፡ እንዲያውም ሰውዬው የባሰ የሚያናድድ እና ለግድያ የሚያነሳሳ ነገር ማድረግ እና መተንኮስን ሥራው አደረገ፡፡ እኛም የኛን ሰው እንዲረጋጋ እና አንዴ ለኾራዩ ስላሳወቀ ፍርዱን በዚያው ያግኝ ብለን ዝም አልን፡፡*

*ሁለተኛው ወር እንዳለፈ በዚያ ሰውዬ ቤት አንድ አሳዛኝ ነገር መጣ፡፡ በግምት የስምንት ዓመት የሚሆን ልጁ ከገደል ተንሸራትርቶ ወደቀ፡፡ ምንም ምንም አልተረፈውም እንደወደቀ ነው ልጁ የሞተው፡፡ በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው የሆነው፡፡ ያ*

*ሁላችንም ነን ያዘንነው፡፡ ቀጠለና አባቱን የራሱ በሬ ሆዱ ላይ ወጋና ቀድዶ ገደለው፡፡ ያኔ በዚህ ሰውዬ ላይ የመጣው መዓት በፊት አጥፍቶ በመደበቁ እና ኻራይ ሲጠራው አለመሄዱ እንደሆነ አወቅን፡፡ ከዚያ አንዳንድ ሰዎች የሠራኸው ክፉ ሥራ ቢኖር ነው ብለው ሲነግሩት ምንም እንደሌለ ሁሉ ደብቆ ዝም አለ፡፡ አላምንበትም አለ፡፡ አባቱ በሞተ በሳምንቱ ደግሞ ምን እንደነካው ሳይታወቅ እሱ መራመድ እያቃተው መጣ፡፡ እግሮቹ ቀስ በቀስ ተሸመቀቁ፡፡ ሕመሙ እያየለበት ሄዶ አልጋ ላይ ወደቀ፡፡ ያኔ እግሩ ሲያዝ እኅቱን ጠርቶ የሠራው ክፉ ሥራ እንዳለ፣ ደብቆ እንደቆየ፣ ይኼ ሁሉ መዓትና ቁጣ የወረደበት በጥፋቱ እንደሆነ ነገረው፡፡ ኻራይ ሲጠራው አልመጣም ብሎ መቅረቱን እና መረገሙን አስረዳው፡፡ ከዚያ ጉዳዩን ለእኅቱ ከተናገረ በኋላ፣ እኅትዬው ወደ ኻራዩ ዘንድ ሄዶ የሆነውን ሁሉ አስረዳው፡፡ ተጨማሪ ጥፋት፣ ተጨማሪ ሞት እንዳይመጣ፣ ይቅርታ እንዲያደርግላቸው ብዙ ልመና አደረገ፣ ብዙ ደጅ ጠና፡፡ ኋላ ኻራዩም እንዲመጣ ፈቀደለት፡፡ ያኔ መልዕክተኛ ለእህቱ ልጅ እንዲመጣ ነገረው፡፡ እኛንም አስጠራን፣ ብዙ የአካባቢው ሰውና ዘመድ አዝማድ ተሰበሰበ፡፡ የእነሱም የእኛም የጎሳ አባል፣ ዕድሜው ከፍ ያለው ሁሉ መጣ፡፡ ሰውዬው በእንጨት ቃሬዛ ላይ ሆኖ ቀረበ፡፡ ምን ጥፋት አንዳጠፋ እና ምን እንደሰወረ ተጠየቀ፡፡*

*የመጀመሪያ ጥፋቴ ነው ያለው የኔን ዘመድ ሰክሮ መጋጨቱን እና መሳደቡን ሲሆን ሁለተኛው በዚህ ንዴት የሰውዬውን ላም እና ጥጃ እንዴት ግቢ ቤታቸው ድረስ ሄዶ የሚገድል መርዝ እንደሰጣቸው ተናገረ፡፡ መርዙን ከከተማ እንዳስመጣው፣ ማን እንደሰጠው፣ ከብቶቹን የገደላቸው መሆኑን አመነ፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ ኻራይ ሲያስጠራው አልመጣም ማለቱን እና ይሄም ጥፋቱ መሆኑን ተናገረ፡፡ በመጨረሻም ይሄ ሁሉ በደልና ቅጣት የደረሰበት በሠራው ሥራ መሆኑን እና ይቅርታ እንዲደረግለት ለመነ፡፡ ኻራዩም በሰውዬው ጥፋት ሌሎቹን ጭምር ለችግር የዳረገው እሱ በመሆኑ ከበሽታው በቶሎ እንደማይድን ነገረው፡፡ ከዚህ በኋላ ግን የእሱ የሆኑ ዘመዶቹ አደጋ እንደማይደርስባቸው አስረዳው፡፡ እሱ ግን በጥፋቱ ጥቂት ጊዜ እንደሚቀጣ ነገረው፡፡ ለሠራውም ሥራ ብዙ ብር ካሳ እንዲከፍሉ ወሰነባቸው፡፡ ላሚና ጥጃዋ ተገዝተው እንዲተኩ ብቻ ሳይሆን ሌላም ወደ ሁለት ሺ ብር የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ጣለባቸው፡፡ ዘመድ አዝማዱ ሁሉ አፈረ፡፡ ቁጣውና እርግማኑ እነሱንም የሚጨምር በመሆኑ በሳምንት ውስጥ የተጠየቁትን ሁሉ ከፍለው እንዲጨርሱ አዘዛቸው፡፡ ይኽ ቃሉ ባይጠበቅ ደግሞ ከዚህ የከፋ መከራና ቅጣት እንደሚጠብቃቸው አስጠነቀቃቸው፡፡ ከዚያ በኋላ እኛም ኻራዩን አመስግነን ወጣን፡፡ ያ ሰውዬ እንደተባለው በጣም ብዙ ጊዜ ታሞ ታሞ በመጨረሻም ሞተ፡፡ የገደለው ደግሞ ንዳድ ነው፡ ፡ በወባ በሽታ በሳምንት ውስጥ ሞተ፡፡*

*ይሂ የሚያሳየው የሃይማኖት መሪዎቻችን በትክክል እኛን እና ሕዝቡን የሚጠቅም ሥራ የሚሠሩ መሆናቸውን፣ አምላክ ቱማ የሰጣቸው ኃይል ያለ መሆኑን እና ከእነሱም የሚሠወር ነገር እንደሌለ ነው፡፡ አጥፊ ውሎ አድሮም ቢሆን የጥፋቱን ዋጋ እንዲያገኝ ያደርጉታል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ቡክቱ)፡፡*



ከግራ ወደ ቀኝ አጥኝው፣ ከመሐል ኘራይ አወቀ ፎሮሾዋ እና አስተርጓሚው አቶ ብርሃኑ ወርቁ፣
ፎቶ በአቶ በድሉ ካሳ፡፡

እንደ ብሔረሰቡ አባላት እምነት ኘራዮች ካላቸው ቅድስና አንጻር ሁሉን ነገር መመርመር የሚያስችል ኃይል አላቸው፡፡ በተለይ የተሰወረን የመግለጥ እና የተደበቀን የማስወጣት ኃይል፡፡ በእነሱ ፊት እንዲቀርብ የታዘዘ ማንኛውም የብሔረሰቡ አባል ጥሪያቸውን አክብሮ መገኘት ግዴታው ነው፡፡ አንድ ሰው ከተጠራ በፊታቸው ቀርቦ የተጠራበትን ምክንያት ጠይቆ ይረዳል፡፡ በሀሰት ተከስሶም ከሆነ ጉዳዩ ሀሰት መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ ምክንያቱም ኘራዮች የማኅበረሰቡን ሰላም እና ደኅንነት የማስጠበቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው በራሳቸውም ይሁን በሕዝቡ ስለሚታመን ነው፡፡ በዘመናዊው የፍትሕ ሥርዓት አንድ ሰው ከፖሊስ መጥሪያ ቢደርሰው አልመጣም ማለት እንደማይችለው ሁሉ፣ የኘራይን ጥሪም ማክበር በብሔረሰቡ አባላት ዘንድ የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡ ጥሪያቸውን አለመቀበል፣ ወይም አናንቆ መቅረት ዋጋ እንደሚያስከፍል እና

በአምላክ ዘንድም እንደሚያስጠይቅ፣ ውሎ አድሮም የአጥፊው መዘዝ ለቤተሰቡ እና ለዘመድ አዝማዶቹ እንደሚደርስ ይታመናል፡፡

ስለ ኘራይነት ታላቅነት፣ በአምላክ ቱማ ፈቃድ ነገሮችን እንደሚያከናውን ከሚያምኑት እና በዚህም ያዩትን እና ያጋጠማቸውን ከሚተርኩት ውስጥ አቶ ሹማቻኤዳ በርግዋ አንዱ ናቸው፡፡ በአንድ ወቅት በራሳቸው ሕይወት ውስጥ ያጋጠማቸውን ሁኔታ፣ ኘራይ ጋር የሄዱበትን ምክንያትና አጋጣሚ፣ በኘራዩ ፊት ቀርበው የሆነውን ነገር እና ውጤቱን ይተርካሉ፡፡ ጉዳዩን የፈጸመቿው የእሳቸው ልጅ፣ በአሁን ጊዜ ራቅ ወዳለ ሥፍራ ለአንድ ሰው አራተኛ ሚስት ሆና እየኖረች እንደሆነ ገልጸው፣ ልጃቸው በአንድ ወቅት የአካባቢዋ ሴት ጋር ወደ ገበያ ሄደው ከተመለሱ በኋላ፣ ጓደኛየዋ "ብር ጠፋኝ" ብላ ጠብ መነሳቱንና በዚህም በኘራይ ፊት መጠራቷን እና የታሪኩን ፍጻሜ እንዲህ ይገልጹታል፡፡

> *ዋናው የጠብ መነሻ ገበያ ሽጬ 'በጨርቄ የቋጠርኩትን ብር ወስዳብኛለች፣ ይሄንን ያደረገች እሷ ነች' የሚል ነው፡፡ እኛም ሽማግሌዎችም ልጃችንን አድርጋ እንደሆነ ጠየቅን፤ ልጅም እንዳላደረገች ተናገረች፡፡ በኋላ ሴትየዋ ኘራይ ጋ እሄዳለሁ ብላ ሄደች፡፡*
>
> *በሁለተኛው ቀን ልጄ ኘራይ ጋ እንድትቀርብ ሰው ተላከባት፡፡ በእነዚህ ቀናት እኔም ልቤ እሺ ስላላለኝ ከአንዴም ሁለት ጊዜ ልጄን ጠይቂያት ነበር፡፡ እሷ ግን ምንም የምታውቀው ነገር እንደሌለ ተናገረች፡፡ ከሦስት ቀን በኋላ አንድ ዘመድ አዝማድ አልቀረም እኛም ሄደን በኘራዩ ፊት ቀርባ ተጠየቀች፡፡ ይሁን እንጅ ፊቷ ላይ ድንጋጤ፣ ፍርሃት ብቻ ነበር፡፡ 'ዓይኔን ግንባር ያድርገው አለች፣ አላየሁም' አለች፡፡ ያኔ ኘራዩ 'የሚበጅሽን ምረጪ' አለና በሾርቃ ውኃ እንዲመጣ አዘዘ፡፡ ትልቅ ሾርቃ ላይ ውኃ ተደርጎ ቀረበ፡፡ ኘራዩም እንድትቆም አድርጎ ፊቷን ወደ እኛ እንድታደርግ አደረገ፡፡ ከዚያም "በይ እኔ አልወሰድኩም፣ አልዋሸሁም፣ ወስጄ አልወሰድኩም ብዬ ከሆነ፣ ዋሽቼ ምዬ ከሆነ በዚህ ሾርቃ ውስጥ እንዳለው ውኃ እኔንም ሆነ ዘሮቼን አለቅልቆ ይድፋኝ፣ ውጪም ወጥቼ ግቢውን እንደምጠርገው መጀመሪያ እኔን ኋላም ዘሮቼን ይጥረግ፣ ከምድር ያጥፋ" በይ አላት፡፡ ከዚያ ልጄ ምን እንደነካት አላውቅም መንቀጥቀጥና ማልቀስ ጀመረች፡፡ ወዲያው ሰማይ ወጥታ በኘራዩ ፊት ፈረጠች፡፡ እግሩ ስር ወድቃ እየተንከባለለች ይቅርታ ጠየቀች፡፡ 'ደፍሬ ዘሮቼን አላስጨርስም' አለች፡፡ ለካ ያኔ እሷም በስካር መንፈስ ያችም በተዘናጋችበት ሰዓት ነው ጉዳዩን የፈጸመችው፡፡ ገንዘቡን መውሰዷን አመነች፡፡ ልጄ የዚያን ቀን በኘራዩ ፊት የሾርቃ ውሃ አለቅልቃ ደፍታ ቢሆን ኖሮ ሁላችንም እናልቅ ነበር፡፡ ዘራችን ነበር የሚደፋው፣*

*እኛ ነበርን እንደ ግቢው ቅጠል ከምድር የምንጠረግ፡፡ ምክንያቱም ሰርቃለቻ፣ አረቄው አደፋፍሯት የሰው ገንዘብ ወስዳለች፡፡ በመጨረሻ ገንዘቡን ካስቀመጠችበት አውጥታ ሰጠች፡ ፡ ባሏም ብዙ ካሳ ከፈለ፡፡ ከዚያ በኋላ ነው ቢጋብቻ ሰበብ አካባቢውን ጥላ የራቀችው፡፡*

*እዚህ ኘራይ የአምላክ ያክል የሚታይ ነው፡፡ ምንም ልትሰውር አትችልም፡፡ መጥፎ ሥራን የሚያስቀሩ ናቸው፡፡ አምላክ እነሱን ባይሰጥ እና ኃይሉ ባይኖራቸው ምን እንሆን ነበር፡፡ አንዱ አንዱን እየገደለ፣ እየቀማ ችግራችን ብዙ ይሆን ነበር፡፡ ቱማ ግን እነሱን ሰጠን፡፡ አኖረልን፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ጢይጉይ)፡፡*

የመኤኒት መንፈሳዊ ሚት እንደሚያስረዳው ከመጀመሪያው የእምነት ዘመን፣ ከአምላክ ቱማ ጋር በቅርበት ከነበሩበት ዘመን አንስቶ፣ በኮሞሮቶች እና በባሕል ሃይማኖት መሪዎች እየታመኑ፤ የሚፈልጉትን እየጠየቁ፣ ከተከለከሉት እየተቆጠቡ ኖረዋል፡፡ ወደ ቅርብ ዘመን ሲመጣ እና በሂደት መደበኛ የሆኑ ሃይማኖቶች ወደ አካባቢው በመግባታቸው በጥቂቱም ቢሆን አማኞች አሏቸው፡፡ እነዚህ የኦርቶዶክስ ክርስትና፣ የእስልምና እና የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ መኤኒቶች የየእምነቶቹን ዶግማ እና ቀኖና የሚያራምዱ ሆነዋል፡ ፡

# ምዕራፍ ስድስት

## 6. የመኤኒት ብሔረሰብ የባሕል መስተጋድላን ሚት

በዚህ ርዕስ ሥር አራት የተለያዩ የመስተጋድላውያን ሚቶች ቀርበዋል፡፡ ነፍሳትን የሚያዝዙና አምላክ ቱማ በነፍሳት ላይ ስልጣን የሰጣቸው የወባ ንጉሥ፣ እንስሳትን የሚያዝዙ እና አምላክ ቱማ ስልጣኑን በእንስሳት ላይ የሰጣቸው የዝንጀሮ ንጉሥ፣ አሻ በነባር ልማድና ሥርዓት መከፈል አለበት በሚል የታገለው አቶ ጥጋቡ እና የሚጥል በሽታ የፈጣሪ ቁጣ አይደለም ብለው የተጋደሉ ሴቶች ሚቶች ቀርበዋል፡፡

### 6.1 የወባ ንጉሥ

በመኤኒት ብሔረሰብ የአፈጣጠር ሚት አምላክ ቱማ መጀመሪያ ለፈጠረው ሰው ለናያሞን ልጆች ከሰጠው ቃል ኪዳን አንዱ እና ለኮሊ የተሰጠው ጥበብ ፍጥረታትን የማዘዝ ሥልጣን ነው፡፡ ከዚሁ ዘር የሚመዘዘው አንዱ የሴላ ኮራይ ዘር የወባ ንጉሥነት እንደተሰጠው ይታመናል፡፡ የያርጣ ቀበሌው ቻሪ አንዱ ንጉሥ ናቸው፡፡

> *በብሔረሰቡ አጠራር የወባ ንጉሥ የሚባሉ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህ ንጉሥች፣ ሥልጣኑን ከአምላክ ቱማ በዘር ዘሮቻቸው አማካይነት ያገኙት ነው ተብሎ የሚታመን ነው፡፡ በተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ የወባ ንጉሦች ይኖራሉ፡፡ የየአካባቢው ሰዎች የሚያከብሯቸውና የሚታዘዙላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ የወባ አስተላላፊ ትንኞን እና ራሱን ወባ የተሰኘው በሽታ ለእሱ የሚታዘዙላቸው ወይም የሚገዙላቸው ናቸው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ በድሉ ካሳ፣ የካቲት፣ 2011፣ ያርጣ)፡፡*



የካቲት 8 ቀን 2011 ዓ.ም. ከጧቱ 4፡00 - 5፡00፣ የያርጣ ቀበሌ ኗሪዎች፣ የቡድን ውይይት በተደረገበት ወቅት አቶ በድሉ ካሳ ሲያስተረጉሙ፣ (ፎቶ በአቶ ብርሃኑ ወርቁ)፡፡



የካቲት 8 ቀን 2011 ዓ.ም. ከጧቱ 4፡00 - 5፡00፣ የያርጣ ቀበሌ፣ የቡድን ውይይት በተደረገበት ወቅት አጥኚው የመወያያ ጥያቄዎቹን ሲያቀርቡ (ፎቶ በአቶ ብርሃኑ ወርቁ)፡፡

ከአካባቢው ቆላነት የተነሳ ወባ የሚቀሰቀስበት ወራት እንዳለና በእነዚህ ወራት ሕዝቡን የሚጠብቁትና በወባ ከመርገፍ የሚታደጉት የወባ ንጉሣውያን እንደሆኑ

የያርጣ ቀበሌ ኗሪው ጉነማሎ በናሻ ይገልጣሉ፡፡ "የኛ አካባቢ በጣም ፀሐያማ ነው፡፡ ቆላ ነው፡፡ ወባ አያጣውም፡፡ ስለዚህ በዚህ በሽታ እንዳንጠቃ፣ የወባው ንጉሥ ይጠብቀናል (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011 ዓ.ም፣ ያርጣ)፡፡

የወባ ንጉሥ ሥራውን የማይዘነጋ ሲሆን የሕዝቡን ደህንነት ተግቶ ከወባ የሚጠብቅ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ፀጋውን አብዝቶ የሰጠውና ሕዝቡን በፀጋው እንዲጠብቅ ያደረገው የመኤኒቶች አምላክ ቱማ መሆኑን ያምናሉ፡፡ የወባ ንጉሥ የሚሠራውን ሥራና አምላክ ቱማም ለምን ይሄንን ኃይል ለእሱ እንደሰጠ ሕዝቡ ስለማያውቅ አክብሮ ይይዘዋው ቃሉንም ይሰማል፡፡

ወ/ሮ ኦድሉ አርካሻ፣ የወባ ንጉሦችን አምላክ ቱማ ባይሠጣቸው ኖሮ፣ ወባ ብቻ ጨርሶ ሊያጠፉቸው ይችል እንደነበር ያምናሉ፡፡ እነሱም ይሄንን ስለሚያውቁ የወባ ንጉሥን በታላቅ ክብር እንደሚያዩ፣ ቃላቸውንም እንደሚያከብሩ ይገልፃሉ፡፡ "ቱማ የወባውን ንጉሥ ባይሠጠን፣ ወባ ጨርሶ ያጠፋን ነበር፡፡ እኛ እናከብራቸዋለን፣ ቃላቸውንም እንፈጽማለን" (የቡድን ውይይት፣ የካቲት 8 ቀን 2011 ዓ.ም፣ ከጧቱ 4፡00 - 500፣ ያርጣ)፡፡ የያርጣ ቀበሌ ኗሪ እና የአካባቢውን የወባ ንጉሥ በቅርበት እንደሚያውቁ የሚናገሩት ፖሊስ ማናቻ አምላክ ቱማ ለመኤኒቶች የተለያዩ በፍጥረታት ላይ ኃይል ያላቸው እና የሚያከናውኑት የሚሳካላቸው፣ የአምላክ ያህል የሚከበሩ ሰዎች መኖራቸውን ጭምር ይገልጣሉ፡፡ "ለሰዎቹ ኃይልን የሰጣቸው የሰማይ አምላክ ቱማ ነው፡፡ እነሱ በፍጥረታት ላይ፣ በተለይም በተሰጣቸው ጉዳይ ላይ ኃይል አላቸው፡፡ በመሆኑም ቃላቸው የሚከበርና ያሉትም የሚሆንላቸው ናቸው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011 ዓ.ም፣ ያርጣ)፡፡

በያርጣ ቀበሌ ውስጥ በወባ ንጉሥነታቸው አንዳንዶቹ ደግሞ አምላክ በማለት የሚጠሯቸውና የሚታወቁት አቶ ቻሪ ናቸው፡፡ "በኛ አካባቢ ወባን የሚያዘው ቻሪ ነው፡፡ እሱ ለእኛ የተሰጠ የወባ ንጉሣችን ነው፡፡ አምላክ ቱማ ነው የሰጠን" (የቡድን ውይይት፣ ወ/ሮ ኦድሉ አርካሻ፣ የካቲት 8 ቀን 2011 ዓ.ም፣ ከጧቱ 4፡00 - 500፣ ያርጣ)፡፡

የቻሪ የወባ ንጉሥነትም ይሁን አምላክነት የሚመነጨው፣ በዘር ነው፡፡ ጥንት፤ የብሔረሰቡ ታሪክ ሲጀምር እንስሳትን፣ አራዊትን እና ነፍሳትን የማዘዝ ስልጣን፣

ለናያሞን ሁለተኛ ልጅ ለሆነው ለቦሹ እንደተሰጠ ይታመናል፡፡ ለቦሹ እና ለዘር ዝርያዎቹ የተሰጠው ቃል ኪዳን ሲወርድ ሲዋረድ መጥቶ ለሴላ ኮራይ ዘርም በመድረሱ፣ የወባ ንጉሥነት ስልጣን እንዳላቸው የአካባቢው ሰው እምነት አለው፡ ፡ "እዚህ ያለነው የሴላ ኮራይ ዘሮች ነን፡፡ የሴላ ኮራይ ጎሳ ነን፡፡ ቻሪ የሴላ ኮራይ ዘር ነው፡፡ ከጥንት ዘመን ጀምሮ የወባ አምላክ ዘር ነን" (ቃለ መጠይቅ፣ ጉነማሬጮ በናሻ፣ የካቲት 2011 ዓ.ም ያርጣ)፡፡

በያርጣ እና በአካባቢው ወባ ሊነሳ የሚችለው በሁለት ምክንያቶች ብቻ እንደሆነ የአካባቢው ኗሪዎች ያምናሉ፡፡ አንደኛው ምክንያት የወባው ንጉሥ ቻሪን ሕዝቡ ካስቀየመ፣ ንጉሡ ወባን በማዘዝ ሊቀጣቸው ከፈለገ ሲሆን፣ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ራሱ አምላክ ቱማ በሠሩት ጥፋት ተቆጥቶ ሊቀጣቸው ከፈለገ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ወባ እንደማይመጣባቸው ኦድሉ አርካሻ በቡድን ውይይቱ ወቅት ገልጸዋል፡፡ "ወባ የሚወጣብን በኛ ችግር ነው፡፡ አንደኛ በአንድ ጎሳ ውስጥ ጋብቻ ሲፈጸም፣ የጎሳዎቻችንን መሪዎች ወይም ኮሞሩቶቻችንን ካላከበርን፣ ሽማግሌዎቻችንን ካላከበርን እና በዚህ ሥራችን አምላክ ቱማን ስናስቀይም፤ ሌላኛው ደግሞ በተለያየ ምክንያት ቻሪን ስናስከፋው ነው" (የቡድን ውይይት፣ የካቲት 8 ቀን 2011 ዓ.ም፣ ከጧቱ 4፡00 - 500፣ ያርጣ)፡፡

በአካባቢው እምነት በሁለቱ ምክንያች የብሔረሰቡ አባላት ጥፋት ከፈጸሙ ቅጣታቸውን እንደሚቀበሉ እና የወባ ንጉሡ በተቆጣ ጊዜ የወባ ትንኞቹን በቃሉ በማዘዝ በሽታን እንደሚሰድድ ይገልጻሉ፡፡ ሽማው ጀኒዮ የወባው ንጉሥ ምን ብሎ እንደሚቀጣቸው እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡ "የወባው አምላክ ሲቆጣ፣ ቤቱ ሆኖ ትዕዛዝ በቃሉ ይናገራል፡፡ የወባ አምጪዎቹን 'ውጡ ሰውን ንደፉ፣ ጥፋተኞችን ቅጡ፣ በሽታው ይጠንክር፣ ሰውን ይቅጣ' ብሎ ያዘዛቸዋል፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ቀን 2011፣ ዓ.ም ያርጣ)

በብሔረሰቡ እምነት የወባ ቅጣቱ በአምላክ ፈቃድም ይሁን በቻሪ ቁጣ ከመጣ፣ መዳኛው ራሳቸው የወባው ንጉሥ ወይም አምላክ ቻሪ ናቸው፡፡ ማናቻ ይሄንኑ ይገልጻሉ፡፡ "ቱማ ምድሪቷን ሲቆጣ፣ የወባ በሽታ ይከሰታል፡፡ ይሄንን በሽታ የሚያቆመው እና ሕዝቡን የሚያድነው ቻሪ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011 ዓ.ም፣ ያርጣ)፡፡



ከግራ ወደ ቀኝ ወ/ሮ ኦድሉ አርካሻ እና አቶ ጉነማጬ በናሻ፣ ወ/ሮ ኦድሉ በቡድን ውይይት ወቅት አስተያየት ሲሰጡ፣ የካቲት 8 ቀን 2011 ዓ.ም፣ ከጧቱ 4፡00 - 500፣ 2010ዓ.ም፣ ያርጣ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡

ወባ በተከሰተ ጊዜ ለመከላከያነት የሚውለው ዋናው ነገር ነጭ ኖራ ሲሆን፣ የሚገኘውም ከአካባቢው ብዙ ባልራቀ ሥፍራ ላይ ነው፡፡ ኖራውን የሚያመጣው ደግሞ ራሱ የወባው ንጉሥ ወይንም እርሱን በረዳትነት የሚያግዘው ኮኮ የሚሰኝ የማዕረግ ስም ያለው ረዳቱ ነው፡፡ “የሚቀባን ኖራ ነገር ነው፡፡ ነጭ ዐመድ ነገር ነው፡፡ የሚመጣው ከዚያው አካባቢ ሲሆን ንጉሡ ራሱ አልያም ኮኮው ነው፡፡” (የቡድን ውይይት፣ ኦድሉ አርካሻ፣ የካቲት 8 ቀን 2011 ዓ.ም፣ ከጧቱ 4፡00 - 500፣ ያርጣ)፡፡

ለወባ መድኃኒትነት የሚውለው ነጭ ኖራ መሆኑንና በአቅራቢያው ካለ አካባቢ መምጣቱን በመግለጽ የወ/ሮ ኦድሉን ሀሳብ የሚያጠናክሩት ሌላ ሰው በወባው ንጉሥ ቻሪ በተደጋጋሚ ኖራ የተቀቡት ጉነማጬ በናሻ ናቸው፡፡ “ነጬን ኖራ ብዙ ጊዜ ኮኮ ያመጣዋል፡፡ እራሱ ንጉሡ ቻሪም ሊያመጣው ይችላል፡፡” የቡድን ውይይት፣ የካቲት 8 ቀን 2011 ዓ.ም፣ ከጧቱ 4፡00 - 500፣ ያርጣ)፡፡ ከአካባቢው ብዙም ያልራቀው ኖራ በንጉሡ ወይንም በረዳቱ ኮኮ አማካይነት ከመጣ በኋላ

ወባ የተያዙትም ሆኑ ገና እንዳይያዙ የሚፈልጉት ሁሉ በሰልፍ ቀርበው በምራቅ የተላቆጠውን/ የተለወሰውን ኖራ ግንባራቸውን ይቀባሉ፡፡

ብዙዎቹ የያርጣ ኗሪዎች በሁለት ምክንያት፣ አንድም መኤኒቶችን የፈጠረው እና ለዘር ዝርያቸው ኃይልና ጥበብን ሰጥቶ የሚያኖራቸውን አምላክ ሲያስቀይሙ፣ አንድም ሕዝቡን በጥበባቸው እያገዙ በአምላካቸው እና በመኤኒቶች መካከል በመሆን የማስታረቅ ሥራን እየከወኑ የኖሩትን የልዕለ ተፈጥሮ ኃይል የተቸራቸውን ቻሪን በማስቀየማቸው ያርጣ ቀበሌ በተደጋጋሚ በወባ በሽታ እንደተመታ በኗሪዎቹ ይታመናል፡፡ ኗሪዎቹ በሽታው ሲበረታባቸው፣ አቅምና ጉልበት ሲነሳቸው፣ ሞት ክንዱን አፈርጥሞ ሲነጣጥላቸው፣ እጆቻቸውን ለይቅርታ በመዘርጋት ለአምላክ ቱማም ሆነ ለወባው ንጉሥ ቻሪ ተማጽኖ አቅርበዋል፡፡ ንጉሡም የፈውሱን ኖራ በምራቃቸው ለውሰው ከንዳድና ከሞት ታድገዋቸዋል፡፡ ኦድሉ አርካሻ ይሄንኑ በቡድን ውይይቱ ላይ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

> *ጊዜውን አላስታውስም ግን ከአምስት ዓመት አይበልጥም፣ ክፉ ወባ ተነሳ፡፡ በጥቂት ጊዜ ብዙ ሰው አረገፈ፡፡ ህጻኑም፣ ትልቁም፣ ወንዱም ሴቱም ወደቀ፡፡ እኛም ሰዎች ወደ ቻሪ ልከን ጠየቅን፡፡ ከዚያ ነጭ ነገር፣ ኖራውን ግንባር ግንባራችንን ቀባን፡፡ እኔም ግንባሬን ተቀባሁ፡፡ የቀባኝ ቻሪ ነው፡፡ ይሄንን ያደረኩት ወባ ስለያዘኝ ነበር፡፡ ከዚያ ብዙም ሳልቆይ ተሻለኝ፣ ዳንኩት በእሱ ነው፡፡ ያዳነኝ ቻሪ ነው (የቡድን ውይይት፣ ኦድሉ አርካሻ፣ የካቲት 8 ቀን 2011 ዓ.ም፣ ከጧቱ 4፡00 - 500፣ 2010 ዓ.ም፣ ያርጣ)፡፡*

በአንድ ወቅት ከፍተኛ የወባ ቁጣ በተቀሰቀሰበት እና ብዙ ሰው በሞተበት ጊዜ፣ በቻሪ ግንባራቸው ላይ ኖራ ተቀብቶላቸው ወባ ፈጽሞ እንዳልያዛቸው የሚገልጡት ደግሞ ሽማው ጆኒዮ ናቸው፡፡

> *የሆነ ቀደም ያለ ጊዜ ነው፡፡ ከፍተኛ ወባ መጣ፡፡ ቻሪ ጋ ሰው ሁሉ ተሰበሰበ፡፡ ወባ የያዘውም፣ እንዳይዘውም የፈራው ሁሉ ተሰበሰበ፡፡ በኛ አካባቢ ያልመጣ ሰው አልነበረም፡፡ ተራዬ ሲደርስ ኖራውን በጣቶቹ ነክቶ፣ በምራቁ እንትፍ አለበትና 'ሰላም ሁኑ፣ ወባ አይንካችሁ' ብሎ ቀባኝ፡፡ ሴቱም ወንዱም አንድ ላይ ሆነን ነው የተቀባነው፡፡ ያኔ ታሞ የነበረ ብዙ ሰው ዳነ፡፡ እኔን ግን ወባ አልያዘኝም (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011፣ ያራጣ)፡፡*

እንደ ወ/ሮ ኦድሉ አርካሻ እና ሽማው ጆኒዮ ሁሉ በያርጣ ቀበሌ፣ በወባ ንጉሡ በቻሪ እጅ ኖራ ተቀብተው፣ እስከ አምስት ዓመታት ድረስ ምንም በሽታ በአካባቢው አለመነሳቱን በቡድን ውይይቱ ላይ የገልጹት ደግሞ ጉነማጬ በናሻ ናቸዉ፡፡ “ወባ ሲነሳ ሰብሰብ ብለን ግንባራችን ላይ ኖራ ይቀባናል፡፡ ኖራውን በምራቁ እያራሰ ይቀባናል፡፡ ከዚያ ወባ ከአካባቢያችን ይርቃል፡፡ አንድ ጊዜ ሲሠራልን ከሦስት እስከ አምስት ዓመታት ይጠብቀናል፡፡ (የቡድን ውይይት፣ የካቲት 8 ቀን 2010 ዓ.ም፣ ከጧቱ 4፡00 - 500፣ ዓ.ም፣ ያርጣ)

በአጠቃላይ በያርጣ አካባቢ ያለው የወባ ንጉሥ ሕዝቡን ከወባ እየጠበቀ እንደሚኖር ይታመናል፡፡ በተፈጥሮ ወይንም በአደጋ ሕይወቱ ሲያልፍ ከሱ ዘር የበኩር ልጅ ስልጣኑን ተረክቦ የወባ ንጉሥነቱን ይቀጥላል፡፡ በአምላክ ቱማ ፈቃድ በንጉሡ ቸርነት የያርጣና አካባቢው ሰው ሲያጠፋ በወባ እየተቀጣ፣ ደግ ሲሠራ ከወባ እየተጠበቀ እንደሚዘልቅ ዘመን የተሻገረው የአፈጣጠር ሚት ይተርካል፡፡




አጥኚው ወደ ያርጣ ቀበሌ ሲጓዝ፣ (ፎቶ በአቶ በድሉ ካሳ)፡፡

## 6.2 የዝንጀሮ ንጉሥ

በመኤኒት ብሔረሰብ የአፈጣጠር ሚት አምላካቸው በሆነው ቱማ ረድኤት ተፈጥሮንም ሆነ ፍጥረታትን ማዘዝ እንደሚቻል ይታመናል፡፡ በምድር ላይ ከሚኖሩት እንስሳትና ነፍሳት ለበጎም ይሁን ለጥፋት ዓላማ ለማዋል የሚችሉ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ተከብረው የሚኖሩ በርካቶች ናቸው፡፡

በብሔረሰቡ የተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ የዝንጀሮ ንጉሥ የሚባሉ አሉ፡፡ ዝንጀሮ ለእነሱ እንደሚታዘዝ፣ ድምጻቸውንና ትዕዛዛቸውን እንደሚፈጽም ይታመናል፡፡ በመኤኒት ጎልዲያ ወረዳ፣ በጎማ ቀበሌ የሚኖሩት አቶ ሴላ የዝንጀሮ ንጉሥ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡ ይሄም ስጦታ የተቸራቸው ከአምላክ ቱማ ሆኖ ከዘር ዘራቸው ሲወርድ የመጣ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡



ዝንጀሮ ንጉሡ አቶ ሴላ፣ (ፎቶ በአጥኚው)

"እኔ የኩታ ዘር ነኝ፡፡ የኩታ ዘር የዝንጀሮ ንጉሥ ነው፡፡ በሁሉም የመኤኒት አካባቢ ከዝንጀሮ ጋር ተያይዞ ሥራ የምንሠራው የኩታ ዘሮች ነን፡፡ ኃይሉን የሠጠን፣ ያከበረንም ቱማ ነው፡፡ እኛ ስንናገር ዝንጀሮዎቹ ይሰሙናል፡፡ (አቶ ሴላ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጨበራ)

እንደ አቶ ሴላ አገላለጽ ከኲታ ዘር ውጪ የዝንጀሮ ንጉሥ የሚሆን እንደሌለ ሁሉ የኲታ ዘሮች ደግሞ ከዝንጀሮ ውጪ ወይም ሌላ ነገሮች ላይ የተለየ ስጦታና ኃይል የላቸውም፡፡ "የኲታ ዘሮች የምናዝዘው ዝንጀሮዎችን ብቻ ነዉ፡፡ ከዚያ ውጪ ሌላ ሥራ አንሠራም፡፡ እኛ ዝናብ የማውረድ ወይም ሌላ አንሠራም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ አምላክ ቱማ እሱን ለእኛ አልሰጠንም (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጨበራ)

በብሔረሰቡ እምነት ሁሉም ከአምላካቸው ቱማ የተሰጠው ድንቅ የማድረግ እና ፍጥረታትንም ይሁን ተፈጥሮን የማዘዝ ሥራ ከብሔረሰቡ አፈጣጠር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አምላክ ቱማ ሰማይና ምድርን ከፈጠረ በኋላ፣ በምድሪቱ ላይ እንዲኖር የፈጠረው ናያሞን እና ሚስቱ ለወለዷቸው ልጆች ከሰጣቸው፣ ለትውልደ ትውልድ የሚሸጋገር ቃል ኪዳን የሚመዘዝ ነው፡፡ አንዱ ጎሳ ከአንዱ ጎሳ ጋር እየተጋባ በርክተው  የሚኖሩባትን ምድር በዝተው እንደሞሏት ሁሉ፣ ቃል ኪዳኑም ለልዩ ልዩ ጎሳዎች መዳረሱ ይታመናል፡፡

የዝንጀሮ ንጉሡ አቶ ሴላ፣ እንደሚገልጹት የዝንጀሮ ንጉሥነት ከአያት ቅም አያታቸዉ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው፡፡ እሳቸውም ይሄንን በዝንጀሮ ላይ ሰልጥኖ መኖርን የተማሩትና የወረሱት ከአባታቸው ነው፡፡ "ግሊናሪ የተባለ የአባቴ አባት ይሠራ ነበር፡፡ ዝንጀሮዎች ይታዘዙለት ነበር፡፡ ከዚያ አባቴ ተተካ፡፡ አባቴ ሲያረፍ እኔ ተተካሁ፡፡ የእሱን ፈለግ ተከትዬ እየሠራሁ ነው፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ሴላ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጨበራ)

አቶ ሴላ ወደ ዝንጀሮ ንጉሥነት የመጡት፣ የ15 ዓመት ልጅ እያሉ አባታቸው ከዚህ ዓለም ካለፉ ከሁለተኛው ቀን ጀምሮ እንደሆነና ስልጣኑም የበኲር ልጅ በመሆናቸው በአካባቢው ሽማግሌዎች ፊት በተከናወነ ሥርዓት እንደወርሱት ይገልጻሉ፡፡ ህዝቡም ቃላቸዉን እንደሚጠብቅ ያምናሉ፡፡ ነገር ግን ህዝቡ ክብራቸውን ባይጠብቅ እና የሚያስከፋቸውን ነገር ቢያደርግ፣ የአካባቢውን ሰብል በዝንጀሮ መንጋ አስወርረው እህሉን ሊያስጠፉት እንደሚችሉ ይናገራሉ፡፡

> *ይሄንን ሥራ መሥራት የጀመርኩት በዐሥራ አምስት ዓመቴ ነው፡፡ አባቴ ሲሞት በሁለተኛው ቀን ኮሞሩቶችና ሌሎች ሽማግሌዎች ከቤት መጡ፡፡ አባቴ ከወለዳቸው አምሥት ልጆች ውስጥ እኔ የበኲር ልጅ ነኝና ተመረጥኩ፡፡ የቡና ቅጠል፣ በጨሞ ተፈልቶ*

*በቀርከሀ ተደርጎ እንድጠጣ ተደረገ፡፡ ከሞሩቶቹም መረቁኝ፡፡ ከዚያ በኋላ ኃላፊነቱን ተረከብኩ፡፡ አባቴም ቀደም አድርጎ ስለ ዕፅዋት እና ሞሲት አሠራር አሳይቶኝ ነበርና እኔም ስተካ በጎማ እና አካባቢው ቀበሌ ሥራውን ቀጠልኩ፡፡ እኔ የምሠራውን ደንብ[8] ዝንጀሮዎቹ እንደሚሰሙ ህዝቡ ያምናል፡፡ ስለዚህም ያከብረኛል፡፡ ነገር ግን ሕዝቡ ቢያስቸግረኝና ብናደድ፣ ዝንጀሮዎቹን ቀጥታ ዛሬውኑ አመጣቸዋለሁ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ሴላ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጨበራ)*

ከአባት ወደ ወንድ በኩር ልጅ የሚተላለፈዉ የዝንጀሮ ንጉሥነት ወደ ሴቶች ሊያልፍ እንደማይችልና የግድ በኩርና ወንድ ልጅ እንደሚያስፈልግ የሚገልጹት ደግሞ አቶ ዋየችና አቶ ዶጋች ናቸዉ "ስልጣኑ የሚተላለፈዉ ለበኩር ልጅ ሆኖ፣ የግድ ወንድ መሆን አለበት፡፡ ለሴት አይሠጥም፡፡ ይሄንን ሥራ ሴት አትሠራም፡፡" (ዋየች፣ ዶጋች፣ የካቲት ቀን 2011 ጨበራ)

አቶ ዋየች ዳሻ፣ ለእያንዳንዱ አካባቢ የየራሱ የዝንጀሮ ንጉሥ እንዳለ፣ በእሱ ግዛት አካባቢ ያሉ ዝንጀሮዎች በጠቅላላ እንደሚገዙለት እንደሚታመን እንዲህ ይገልጻሉ፡፡ "እዚህ ጎማ ቀበሌ ላይ ያሉት ዝንጀሮዎች ይሰሙታል፡፡ የሌላኛዉ ቀበሌ ደግሞ በዚያዉ በቀበሌያቸው ነው፡፡ የሻሪያው ቀበሌ የዝንጀሮ ንጉሥ በሻሪያ ይሠራል፡፡ የዱማ ቀበሌውም የሚሠራው በዚያው በዱማ ቀበሌ ነው፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ዋየች ዳሻ፣ የካቲት ቀን 2011 ዓ.ም)

የዝንጀሮ ንጉሦቹ በየግዛታቸው አገልግሎቱን እንደሚሠጡ፣ በህዝቡም ከበሬታ እንዳላቸውና እንደሚታመኑም የሚገልጹት ደግሞ ወ/ሮ ሲቡይ ናቸው፡፡ "በኛ አካባቢ ያለው የዝንጀሮ ንጉሥ የሚከበር ነው፡፡ ሥራውንም ይሠራልናል፡፡ የሌላውም በራሱ አካባቢ ይሠራል" (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011 ዓ.ም ጎማ)

የአካባቢው ሰው አዝመራው በዝንጀሮዎቹ እንዳይበላበት፣ ዝንጀሮዎቹን እንዲይዝለት፣ ምግባቸውን እንዲሰጥለት፣ ንጉሦችን እንደሚጠይቅ የሚናገሩት ደግሞ አቶ ወቲመጉት ናቸው፡፡ "ሰዉ በፈለገ ጊዜ ሽማግሌዎችን ወደ ንጉሡ ልኮ፣ የዝንጀሮች ንጉሥ ለዝንጀሮዎቹ የሚበሉትን እንዲሰጥ፣ አዝመራ እንዳያጠፉ ይለምናል (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጨበራ)

---

[8] ደንብ ማለት ዝንጀሮዎች ሰብል እንዳያጠፉ የሚደረግ ክንውን ወይም ሥራ ማለት ነው፡፡

ከላይ ካለው በተጨማሪ የዝንጀሮ መንጋ በሆነ አጋጣሚና ምክንያት የደረሰውን እህል ማጥፋትና መብላት ቢጀምር ፣ የአካባቢው ሰው ዱር ቤቴ ብሎ አዝመራውን መጠበቁ የግድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ቀንና ለሊት አዝመራ እየጠበቁ፣ ከዝንጀሮ መንጋ ጋር እየታገሉ መቆየት አዳጋች ስለሚሆን ወጣቶችና አቅም ያላቸው አዝመራቸውን ለመጠበቅ በየማሳው ዳር ውለው ሲያድሩ፣ የተመረጡ ሽማግሌዎች ወደ ዝንጀሮው ንጉሥ ይሄዳሉ፡፡ ሽማግሌዎችም ቀርበው አንድም እሱን አስከፍተውና አስቀይመው ከሆነ ይቅር እንዲላቸውና ዝንጀሮዎቹን እንዲያርቅላቸው፤ አንድም ቁጣው የመጣው ከአምላክ ቱማ ከሆነም እርሱ አማልዶ ለዝንጀሮቹም ምግባቸውን ሰጥቶ እንዲመልሳቸው እንደሚጠይቁ ሴላ ይገልፃሉ፡፡

> *"ችግር ከተፈጠረ እና ዝንጀሮዎች ጉዳት ማድረስ ከጀመሩ፡፡ ሽማግሌዎች እኔ ዘንድ ይመጣሉ፣ 'ተቀይመኸን ከሆነም ይቅር በለን፣ ቱማም ጨክኖብን ከሆነ ይቅር እንዲለን ለምንልን፣ ዝንጀሮዎቹን መልስልን፣ የራሳቸውን ምግብ ባሉበት ስጥልን' ብለው ይመጣሉ፡፡ እኔም የሚገባኝን ሥራ አሠራለሁ፡፡ በሰማይ ያለው ቱማ ደግ ነው፡፡ ይቅር ይላል፡፡ ቁጣውን ይመልሳል፡፡ ይታረቀናል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጨበራ)፡፡*

እንደ ብሔረሰቡ ነባር እምነት ማንኛውም ከባድ ችግር የሚፈጠርባቸው በሚሠሩት መጥፎ ሥራ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ለዚህ ደግሞ አምላክ ቱማ የመታረቂያ መንገዱን በሰዎቹ አማካይነት እንደሰጣቸው ያምናሉ፡፡ ችግር ተፈጥሮ ችግሩን ያስወግዳሉ ተብለው የሚታመኑት ሰዎች መፍትሔ ከሰጡ በኋላ ችግሩ እንደሚወገድላቸው ያምናሉ፡፡ የዝንጀሮ መንጋም የአካባቢውን አዝመራ እንዳያጠፋ ንጉሡ የሚሠራውን ሥራ ከሠራ በኋላ ዝንጀሮዎች ድጋሚ ወደ ማሳው እንደማይመጡ ይታመናል፡፡ ለእነሱ የሚሆነውን ምግብም እርሱ ንጉሡ በያሉበት እንዲደርስ ያደርጋል፡፡ የዝንጀሮ መንጋን ለመከላከል በማሳው አካባቢ በሰብል ጥበቃ የተሠማሩ ኅበዛዝትም ለጨለማ መግፈፊያ የሚያበሩትን እሳት አጥፍተው ወደ ቀያቸው በደስታ ይመለሳሉ፡፡ ህዝቡም ሰብሉ በደረሰ ጊዜ የወደደውን ያህል እህል ወይንም ደግሞ ልብስና ገንዘብ ለዝንጀሮው ንጉሥ በስጦታ መልክ ያቀርባል፡፡

"በቆሎ ወይም ማሽላ የዘሩ ሰዎች ሥራው ስለተሠራላቸውና ዝንጀሮዎቹም ከጫካቸው ስለሚቀሩላቸው እህል ሸጠው ለንጉሡ ስጦታ ነገር ይሰጣሉ" (ቃለ

መጠይቅ፣ ዋየች፣ የካቲት 2011ዓ.ም) ለዝንጀሮ ንጉሡ የሚሰጠው ስጦታ አንዳንዴ የልብስ እንደሚሆንም ወ/ሮ ኮያ ይገልጣሉ፡፡ ‶የሚሰጠው ስጦታ እንደሰጪው፣ እንደሰው የሚለያይ ነው፡፡ እህል ገበያ አምጥተው ሸጠው፣ ለንጉሡ እና ለኮኮሰው ልብስ ገዝተው የሚሰጡም አሉ‶ (ቃለ መጠየቅ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጨበራ)፡፡

በጉማ ቀበሌ በዝንጀሮ ንጉሥነታቸው የሚታወቁትና የሚታመኑት አቶ ሴላ፣ ሥራዉን ከአባታቸዉ ተረክበዉ መሥራት የጀመሩት በዐሥራዎቹ አጋማሽ እድሜ ላይ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ አቶ ሴላ በአካባቢው የሚነሳውን የዝንጀሮ መንጋ የማዘዝ ሥልጣን እንዳላቸው ቢያምኑም ማኅበረሰቡ አስከፍቷቸው ስለማያውቅ እሳቸውም ለመቅጣት ዝንጀሮዎቹን ልከው እንደማያውቁ ይናገራሉ፡፡ ይሁን እንጅ በቅርብ ጊዜ የዝንጀሮ መንጋ ከፍተኛ ጥፋት አድርሶ እንደመለሱት ይሄም የቅርብ ጊዜ ትዝታቸው እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

“የጎማ ቀበሌና አካባቢዉ ህዝቡ አክብሮ ስለሚያኖረኝ በእኔ በኩል ቅጣት ደርሶ አያውቅም፡፡ የዛሬ ሰባት ዓመት ገደማ ግን ጥፋት ተከስቶ ተከላክያለሁ፡፡” (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጨበራ) ወ/ሮ ሲቡይም ጊዜውን በማስታወስ የሚከተለውን ይገልጻሉ፡፡ ‶ጊዜዉ ትዝ አይለኝም፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት ነው፡፡ በርካታ የዝንጀሮ መንጋ መጥቶ ማሽላውን ቅርጥፍ አድርጎ በላ፡፡ ኋላ ግን ንጉሡ ደንቡን ሠርቶ መለሳቸዉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጎማ)



ወ/ሮ ሲቡይ፣ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡

በመኤኒት ብሔረሰብ፣ በመኤኒት ጎልድያ ወረዳ፣ በጎማ ቀበሌ ከሰባት ዓመታት በፊት የዝንጀሮ መንጋ አዝመራ ወርሮ ብዙ ጥፋት ማድረሱንና ሽማግሌዎቹ ወደ ዝንጀሮው ንጉሥ ቀርበው ዝንጀሮዎቹን ወደ መጡበት እንዲመልሱላቸው ጠይቀው፣ ሥራውን እንደሠሩት የሚናገሩት አቶ ሴላ ሽማግሌዎቹ ከጠየቋቸው በኋላ ያደረጉትን ሥራ እንዲህ ይገልጹታል፡፡

> *ሰዎቹ ከጠየቁኝ በኋላ ከኮኩው ጋር በመሆን ደንቡን አከናወንን፡፡ መጀመሪያ ኮኩው ትንሽ አንበጣ ከድንጋይ ሥር ፈልጎ እንዲያመጣ አደረኩ፡፡ አንበጣ የዝንጀሮዎች ምግብ ነው፡፡ ዝንጀሮ ከዛፍ ዛፍ እንደሚዘልል፣ አንበጣን ዘላይ ነው፡፡ ዝንጀሮ አንዴ ከብቦ ማሳ እንደሚያወድም፣ አንበጣም አንዴ ከብቦ አውዳሚ ነው፡፡ ስለዚህ የዝንጀሮ ቀለቡ አንበጣው ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ጋልግሊት[9] ቆረጥሁ፡፡ ጋልግሊቱ ቁመቱ እስከ አምስት ሜትር የሚደርስ ነው፡፡ እሱን ከቆረጥን በኋላ ሙሲት ሠራን፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ሴላ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጨበራ)*

እንደ ዝንጀሮ ንጉሡ አገላለጽ ሙሲት መሥራት ማለት ሁለት እንጨቶችን በማፋጨት እና በማጋጨት እሳት እንዲቀጣጠል ማድረግ ነው፡፡ ይሄ እሳትን በሰበቃ የማምጣት ዋና ትርጉም ዝንጀሮ አዝመራቸውን እንዳያጠፋባቸው እየጠበቁ የሚውሉት ገበሬዎች አመሻሽ ላይ እሳት አቀጣጥለው ስለሚያመሹ፣ እነሱን የተመለከተ እንደሆነ አቶ ዋየች ይገልጻሉ፡፡ "ሙሲቱ የሚሠራው በየአዝመራው አካባቢ ያሉት ዝንጀሮ ጠባቂ ሰዎች፣ ምሽት ምሽት ላይ እሳት ስለሚያነድዱ ነው፡፡ የዝንጀሮው ንጉሥ እሳቱን አቀጣጥሎ መልሶ ሲያጠፋው የእነሱም እሳት ይጠፋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011 ዓ.ም)

የአቶ ዋየችን የተምሳሌታዊ ፍቺ የሚያጠናክሩት አቶ ሴላ ሙሲት ሠርተው መልሰው ሲያጠፉ በየአካባቢው ያሉ ጠባቂዎች መልዕክቱን ተረድተው ወደ ቤታቸዉ እንደሚመለሱ ይገልፃሉ፡፡ ይሄም ልባዊ ተግባቦትና ግንኙነት በአምላክ ቱማ በኩል የሚደርስ የእምነት መሠረትም እንደሆነ በብሔረሰቡ አባላት ይታመናል፡፡

> *"ሞሲቱን ከሠራን በኋላ የበራውን እሳት መልሼ አጠፋዋለሁ፡፡ ያኔ ዝንጀሮ ለመጠበቅ በያለበት ውሎ የሚያድረው ሁሉ ማታ ላይ ያነደደው የእሱ እሳት ይጠፋል፣ የሁሉም ሰዎች እሳት አንድ ጊዜ ድርግም ብሎ ይጠፋል፡፡ ያኔ በያለበት ወጥቶ ያድር የነበረው*

---

[9] ጋልግሊት የተባለ የሐረግ ዝርያ ወይም ዓይነት ነው፡፡

*ሁሉ፣ የእሳቱ መጥፋት የእኔ መልዕክት መሆኑን ተረድቶ ወደየ ቤቱ ይመለሳል፡፡ ከዚያ ደቂቃ በኋላ የዝንጀሮ ጥበቃ ይቀራል፡፡ አምላክ ቱማም የሁሉንም ዝንጀሮዎች እግር ወደዚያ ማሳ እንዳያመራ ያደርጋል" (አቶ ሴላ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጨበራ)*

የዝንጀሮ ንጉሡ እና ረዳቱ ኮኮ ሙሲት ሠርተው ከጨረሱ በኋላ ኮኮው ከፊት ንጉሡ ከኋላ በመሆን ጋልግሊት የተሠኘውን ሐረግ በትከሻቸው ፊትና ኋላ ይዘው፣ ካሉበት ሠፈር በመራቅ፣ ረጅም መንገድ በመጓዝ ጥቅጥቅ ጫካ ወዳለበት ያመራሉ፡፡ በዚህ ሁሉ ጉዞ ውስጥ ደግሞ ኮኮው ትንሿን አንበጣ በግራ እጁ መዳፍ በጥንቃቄ እንደያዘ፣ ንጉሡም አምላክ ቱማ ጉዟቸውን እንዲያቃና፣ ሥራቸው እንዲፈጽም እየጠየቁ  ነው፡፡ በአንድ ወቅት የአካባቢው የዘመተውን የዝንጀሮ መንጋ እንዴት እንዳስቀሩት ሴላ እንደሚከተለው ይተርካሉ፡፡

*አንዴ ማልደን በመነሳት እና ስንቃችንን ይዘን፣ ኮኮው አንበጣዋን በመዳፉ ውስጥ እንዳደረገ፣ እኔ ከኋላ  እሱ ከፊት፣ ሐረጉን በትከሻችን ፊትና ኋላ ይዘን፣ ቀኑን ሙሉ ጫካ ለጫካ፣ ጥሻ ለጥሻ ተጓዝን፡፡ ስንሄድ እኔ ቱማ ለአባቶቻችን እንዳደረገ እንዲያደርግልኝ፣ ለአያቴ ግሊናሪ እና ለአባቴ እንዳደረገው እንዲያደርግልኝ እየለመንኩ ነበር፡፡ ሲመሽ እኔ ሐረጉን በጫካ ውስጥ ስጥል፣ ኮኮው ከመንገድ ዳር፣ ወይም እርሻ ካልሆነ ቦታ ድንጋይ ፈልጎ፣ አንበጣዋን በድንጋይ ሥር አስቀመጠ፡፡ ከዚያ እኔን ለዚህ ሥራ የመረጥከኝ ቱማ ዝንጀሮዎቹ ከጫካ እንዳይወጡ አድርግ፡፡ ሰውህ እንዳይራብ፣ እንዳይቸገር አድርግ አልኩ፡፡ ዝንጀሮዎቹን እናንተም ምግባችሁን አስቀምጬላችኋለሁና ከድንጋይ ሥር አንበጣ እየፈለጋችሁ ብሉ፡፡ የሰው እህል አትብሉ ብዬ ተናገርኩ፡፡ ከዚያ ስለመሸ ምግባችንን፣ ራታችንን እዚያው በልተን፣ ከዚያው ከጫካ አደርን፡፡ በማግስቱ ፀሐይ ሳትወጣ ተነስተን ወደ አካባቢያችን በሌላ መንገድ መጣን፡፡ በቃ ከዚያ ጊት ጀምሮ የዝንጀሮ መንጋ በአካባቢው ሰብል ላይ ብቅ ብሎ አያውቅም፣ እስከ ዛሬም ተመልሰው ከሰው እህል አልገቡም፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጨበራ)*

የዝንጀሮ ንጉሡ ከሰባት ዓመታት በፊት በሠሩት ሥራ ዝንጀሮዎች ዳግም ወደ ማኅበረሰቡ ማሳ ገብተው ጥፋት እንዳላደረሱ ከሚናገሩት ውስጥ ወ/ሮ ሲቡይ አንዷ ናቸው፡፡ "ያኔ ደንቡ ከተሠራ በኋላ እስከ አሁን ድረስ ዝንጀሮዎች ወደኛ ማሳ መጥተው አያውቁም፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጎማ)

የዝንጀሮ ንጉሡ ሥራቸውን ሠርተው በመመለሳቸው፣ ዝንጀሮዎቹም ያሏቸውን ተረድተው ከአዝመራ ጥፋት በመታቀባቸው ተደስተናል ያሉት የአካባቢው

ኗሪዎች ለንጉሡ ስጦታዎችን በወቅቱ እንደሰጧቸው እና ከዚያ ወዲህ ግን ከክብር ውጪ ተጨማሪ ስጦታዎችን አለመቀበላቸውን አቶ ሴላ ይገልጻሉ፡፡ “ያኔ ደንቡ ስለተሠራላቸው የአካባቢው ሰዎች ደስ ብሏቸው ልብስ ገዝተው ሰጥተውኛል፡፡ እኔም ተቀብያለሁ፡፡ አንዴ ሠርቻለሁ፣ በየዓመቱ የምንጠይቀው ነገር የለም” (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጨበራ)፡፡

አቶ ሴላ ከሰባት ዓመት በፊት የዝንጀሮ ንጉሥነታቸውን ካስመሰከሩ በኋላ አልፎ አልፎና በየአጋጣሚው ከዝንጀሮዎች ጋር በመንገድ ሲገናኙ የነገሯቸውን እንዳይረሱ፣ ያስቀመጡላቸውን ምግብ ብቻ እንዲበሉ ለዝንጀሮዎቹ እንደሚነግሯቸው ይገልጻሉ፡፡ “ከዝንጀሮዎች ጋር በምንገናኝበት አጋጣሚ እነሱ ሮጠው ሲሄዱ፣ የሰው እህል እንዳትነኩ፡፡ ድንጋይ ሥር ያሉትን አንበጣዎች እየለቀማችሁ፣ የጫካውን ቅጠላ ቅጠል በጥሳችሁ ብሉ እንጂ የሰው እህል እንዳትነኩ እላቸዋለሁ፡፡” (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጨበራ)

በአርባው አጋማሽ እድሜ ላይ ያሉት፣ በጎማ ቀበሌ የሚከበሩት፣ የኩታ ዘሩ የዝንጀሮ ንጉሥ አቶ ሴላ የዝንጀሮ ንጉሥነታቸው ከአምላክ ቱማ የተሰጣቸው በመሆኑ ጥንትም ሆነ ዛሬ እንደሚከብሩና እንደሚፈሩ፣ ተጽዕኖ ያደረሰባቸው የመንግሥትም ሆነ የሃይማኖት ተቋም እንደሌለ ይገልጻሉ፡፡ “ሁሉም ጥቅሙን ስለሚያውቁ ቀጥሉ፣ ‘ዝንጀሮን ያዝልን’ ብለው ያበረታታሉ እንጂ የሚቃወመን የለም፡፡ ስጦታውም የአምላካችን የቱማ ነውና ሁሉም ይቀበላል፡፡” (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011ዓ.ም፣ ጨበራ)



የዝንጀሮ ንጉሡ በቃለ መጠይቅ ወቅት፣ ጨበራ (ፎቶ በአቶ በድሉ ካሳ)፡፡

## 6.3 የባሕል መስተጋድል አቶ ጥጋቡ

የመኤኒት ብሔረሰብ እሴቶች ከሆኑት ውስጥ እንደምሰሰሶ ከሚቆጠሩት ውስጥ አንዱ የግድያ እርቅ ሥርዓቱ አሻ ነው፡፡ አሻ መነሻው አንዲህ ነው ወይም በዚህ ጊዜ ነው የሚል መረጃ ባይኖርም ከጥንት አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ብሔረሰቡ በውስጡ በሚነሱ ግጭቶች ሳቢያ እንዳይጠፋፋ የሚያደርግ ዘመናት የተሸገረ ሚት ነው፡፡ በብሔረሰቡ የሕይወት መስተጋብር ውስጥ ለመፈጠር በጣም ቀላል ነገር ግን የተፈጠረውን ችግር ለማረምና ለማስተካከል የሚስከፍሉት ዋጋ ከባድ የሆኑ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነሱም የሰው መግደል እና የራስ ያልሆነች ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኑነት መፈጸም ናቸው፡፡ አቶ ብርሃኑ ወርቁ እነዚህ ሁለት ክስተቶችን በተመለከተ የሚከተለውን ያብራራሉ፡፡

> *በመኤኒት ውስጥ ሰው ሰውን በተራ እና በድንገት ጸብ ይገድላል፡፡ ተናደድኩ ብሎ፣ ሰከርኩ ብሎ መገዳደል በስፋት አለ፡፡ ይህ ግድያ ግን የሚያስከትለው ጦስ እና ግድያውን ለማብረድ የሚደረገው ልፋት ቀላል አይደለም፡፡ ከፍተኛ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ አንድ ሰው አውቆም ይሁን ሳያውቅ ነፍስ ካጠፋ የሚክሰው ነፍስ ነው፡፡ ግድያው በግለሰቦች መካከል ቢፈጸምም እዚህ ግለሰብ ብሎ የሚያቆም ነገር የለም፣ ችግሩ ወደ ጎሳ ነው የሚያድገው፡፡ የጎሳ*

> *ጠብ ይሆናል፡፡ ያንን ግድያ ለማቆም፣ መበቃቀል እንዳይኖር ሴት ልጅ፣ ልጃገረድ በገዳዮች ቤተሰብ፣ ቤተ ዘመድ ውስጥ ተፈልጋ በአሻ ትከፈላለች፡፡ ትሰጣለች፡፡ ከከብቶች ጋር ተደባልቃ ትሰጣለች፡፡ የራስ ካልሆነች ሴት ጋርም እንዲሁ በመጠኖም በመገፋፋት ስህተት ይሰራል፡፡ ያኔ ሚስት የሠራችው ስለማትደብቅ ለባሏ ትነግረዋለች፡፡ ባል ለበቀል እንዳይነሳ ጉዳዩን የፈጸመው ሰው ሴቷን ማጠብ አለበት፡፡ በደም የማጠብ እና የማንጻት ሥርዓት ይካሄዳል፡፡ (ቃለመጠይቅ፣* የካቲት 2011፣ *ያርጣ)፡፡*

የአቶ ብርሃኑን አባባል የሚያጠናክሩት አቶ ሻልታ ታዬም እንዲህ ይላሉ፡፡

> *በመኤኒት አንድ ሰው የራስ ካልሆነች ሴት ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ከፈጸመ ሴቷ እንደማትደብቅ ስለሚያውቅ ለመካስ ይዘጋጃል፡፡ ሽማግሌዎች ፊት ይቀርባል፡፡ ጉዳዩን ማድረግ አለማድረጉን ለማረጋገጥ በግ ወይም ፍየል ተገዝቶ ይመጣና ይታረዳል፡፡ አንጀት አንባቢዎቹ ጉዳዩ መደረግ አለመደረጉን አንጀት ውስጥ ያያሉ፡፡ ካደረገው ሴቷን በታረደው በግ ወይም ፍየል ደም ያጥባል፡፡ ለባሏ በሬ ይክሳል፡፡ ተጨማሪ ሽማግሌዎች የሚወሱንበትን ያክል ገንዘብ ይከፍላል፡፡ ይህ ሁሉ የኢኮኖሚ ጫናን ይፈጥራል፡፡ መገዳደል ከሆነ ደግሞ ሴት ወይም ልጃገረድ ፍለጋው ከባድ ነው፡፡ ከቤት ሴት ከሌለች ሰባት ቤት በዘመድ አዝማድ ውስጥ ትፈለጋለች፡፡ ሲሰሩት እንደሚቀል፣ ሲመልሱት ቀላል አይደለም፡፡ (ቃለመጠይቅ፣* የካቲት 2011፣ ባቹማ*)፡፡*

ብሔረሰቡ ለሚፈጠሩ ግጭቶች እና ማኅበረሰቡን አደጋ ላይ ሊጥሉ ለሚችሉ ችግሮች ከደነገጋቸው ሕጎች ውስጥ አሻ (የሰው መግደል ዕርቅ ሥርዓት) አንዱ ነው፡፡ ይሕ ሥርዓት ለዘመናት መልኩን ሳይቀይር በሰባት ከብት እና በአንዲት ልጃገረድ ሲፈጸም ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጅ ይህ ለውጥ ከተቃወሙት እና ካልተቀበሉት አንዱ አቶ ጥጋቡ… ነበሩ፡፡ አሻው ለዘመናት ሲሠራበት ገዳይ ለሟች ወገኖች ሰባቱን ከብት እና ልጃገረዲቱን ከሰጠ በኋላ ጉዳዩ ይደመደም ነበር፡፡ በቅርብ ጊዜ ወዲህ ጉዳዩ በአሻ ሥርዓት ቢያልቅም ገዳይ እንዲታሰር የሚያደርገው ሕግ አንዱ ሲሆን ሁለተኛው ልጃገረድን ለደም ካሳነት መክፈል እንዲቀር እና በሷ ፋንታ ተጨማሪ ሰባት ከብት ማድረግ ነው፡፡ አቶ ጥጋቡ በአጋጠማቸውና በፈጸሙት ግድያ ምክንያት የምዳኘው በነባሩ ባሕል ነው በማለት ብዙ ውጣ ወረዶችን አልፈዋል፡፡ አሁንም በቆላው የመኤኒት ክፍል ያለው ሰው የእሳቸውን ዓይነት ሀሳብ እንደሚያራምድ እና እንደባሕል

መስተጋድል የሚያያቸው በርካታ ነው፡፡ አጠቃላይ ታሪኩን እራሳቸው ከዚህ በታች ባለው መልክ ይተርኩታል፡፡

> *ጉዳዩ የተፈጠረው በቆየ ጸብ ምክንያት ነው፡፡ እንደደሚታወቀው መኤኒት ሰው ከገደለ እርቁ በአሻ የሚፈታ ነው፡፡ የመኤኒት ዋና መገለጫው አሻ ነው፡፡ አሻን ደግሞ ፈጣሪ ያበጀልን ሥርዓት ነው፡ ፡ አሻ ዝም ብሎ የመጣ እና የተፈጠረ ሥርዓት አይደለም፡፡ የጥንት አባቶቻችን ይሄንን ሥርዓት ሲሰሩት ዝም ብለው አይደለም፡፡ ሰፊ ምክንያት አላቸው፡፡*
>
> *በአንድ ወቅት እኔ የሆነ የግድያ ሁኔታ ያጋጥመኛል፡፡ ከኛ ሰው ይሞታል፡፡ እናም እኛም ፈጥነን በገዳይ ወገኖች ላይ ጥፋት እንደምናደርስባቸው ስለሚያውቁ ወደ ግድያ ከመግባታችን በፊት የገዳይ ወገኖች "አጥፍተናል እንክሳለን" ብለው መለኮሞሮቶች አሻዋዎች ነገሩ (የአሻ ሥርዓትን የሚያስፈጽሙ)፡፡ ኮሞሮት አሻዎች ቶሎ ብለው በመሀል ገቡ፡፡ እነዚህ በመሃል የገቡት ኮሞሮት አሻዎች ከእኛም ሆነ ከገዳይ ጎሳ ያልሆኑ እና የእኛ ጎሳም የሚያከብራቸው የሌላ ጎሳ አባላት ናቸው፡፡ መኤኒት ሰው ሲገድል ሁሌ እንዲህ ነው፡፡ የትኛውም ኃይለኛ የተባለ ጎሳ፣ የትኛውንም ዓይነት ግድያ ይፈጸም አንዴ ኮሞሮት አሻዎቹ ጫልኩታቸውን ይዘው (ረዘም ያለ ዘንግ) በመሀል ከገቡ ማንንም መንካት አትችልም፡፡ እነሱን ተላልፎ አንዳች አድርጋለሁ የሚል ከአስታራቂ ጎሳዎቹ ጋር ሌላ ጠብ ውስጥ ይገባል፡፡ ደም እመልሳለሁ፣ እበቀላለሁ ብሎ ሌላ ደም ያመጣል፡፡ እነዚያ እንደተናቁ ስለሚቆጥሩ ከገዳይ ወገኖች ገር ያብራሉ፡፡ ሁለት ጎሳ ሆነው ያጠቁሀል፡፡ እንኳን አይደለም ከእነሱ ከራስህ ጎሳም ወቀሳ ይደርስብሀል፡፡ ስህተት ነዋ፡፡ ሥርዓት ማፍረስ ነዋ፡፡ ጥንቱኑ አባቶቻችን የሠሩት ይሄንን ለማስቀረት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ድፍረት ብዙ ውድቀት ያመጣል፡፡ ጥፋቱም ሰፊ ነው፡፡ ለማንኛውም በእኛም መሀል ኮሞሩቶቹ ገቡ፡፡ የእኔ አባት ደግሞ በጀግነንነቱ፣ በዘሩም ቢሆን የተፈራ እና የተከበረ ነበር፡፡ ማንም የሚሽቆጠቆጥለት ሰው ነበር፡፡ ጀግና እና ኃለኛ፣ ታዋቂ እና የተፈራ ሰው ነበር፡፡ ብቻ እኛም እንደዚያ የምንፈራ ነበር፡፡ ኋላ እኛ ደማችንን ሳንወጣ አስታራቂዎቹ ስለገቡ በሀገር ወግና ልማድ መዳኘታችን የግድ ሆነ፡፡ ያኔ እኔም ወግ ነውና የመኤኒት ሥርዓት ነውና ምንም ያህል ቁጭትና እልህ ቢይዘኝም መቀበል ግድ ነውና ሁላችንም አሻውን ተቀበልን፡፡ እንግዲህ በአሻ ሥርዓት ስትታረቅ ነፍስ ስለጠፋብህ ነፍስ ነው የምትካሰው፡፡ በመኤኒት ነፍስ ያጠፋ ነፍስ ነው የሚክሰው፡፡ ነፍስ ስል ሰው ገድሏል እና ሰው ይሰጣል፡፡ ያ ሚች በሕይወት ቢኖር ብዙ ሥራ የሚሠራ*

ነው፡፡ እርሻ ቢኖረው፣ ከብት ቢያረባ ትልቅ ሥራ ነው፡፡ ያልወለደ ከሆነ ይወልዳል ዘር ይተካል፡፡ ዘሩን ያበዛል፡፡ እናም ነፍስ ከጠፋ ነፍስ መካስ የግድ ነው፡፡ እንዲያ ነው የኛ ሥርዓት፡፡ አሻ የሚከፍል ሰው ነፍስ ብቻ ሳይሆን ሌላ ተጨማሪ ካሳም ይሰጣል፡፡ ሰባት ከብት ይሰጣል፡፡ ሰባት ከብት እና አንዲት ልጃገረድ መስጠት አለበት፡፡ እንደዚያ ነው የአሻ ሥርዓት፡፡ መሆንም ያለበት እንደዚያ ነው፡፡ እና በዚያ ሰዓት እኛ ስለተበደልን በሀገር ልማድ መሠረት አሻው ተከፈለን፡፡ ነገር ግን አሻው ጨርሶ አልተከፈለንም፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንዲህ ይደረጋል፡፡ አሻ ከፋዩ የሚከፍላቸውን ከብቶች ጨርሶ ላይከፍል ይችላል፡፡ ኮሞሮቶቹ ደግሞ የሚች ወገንን አጥብቀው ይለምናሉ፡፡ እኛን አምናችሁ ያለውን ተቀበሉ፣ ቀሪውን ይከፍላል የሀገር ወግ ነው፡፡ የመኤኒት ሥርዓት ነው ይላሉ፡፡ ብዙ ጊዜ እንዲህ ይደረጋል፡፡ የማይቀረው ግን የመቀበሪያው እና የጦር መመለሻው ከብት እና እድሜዋ ለጋብቻ የደረሰው ልጃገረድ ናት፡፡ ሁሉም አንዴ አይከፈልም፡፡ ሁለቱ ከብቶች ቀደም ብለው ይከፈላሉ፡፡ ከልጅቷ ጋ ደግሞ፣ ልጅቷ የተሰጠች ቀን አምስቱ ከብቶች አብረው ይሰጣሉ፡፡ ያ እለት ነው እርቁ የሚሰምረው፡፡ ያን እለት የሚች ወንድም እና ገዳይ ዓይን ለዓይን የሚተያዩበት፣ አንጀት የሚባጠሱበት እና የሚበሉበት ነው፡፡ ጸባቸው እንደወንዝ ውኃ የሚወርድበት ጦር ወደሰማይ የሚሰካበት፣ ደም ተራምደው የሚሻገሩበት ቀን ነው፡፡

ይሁን እንጅ አንዳንዴ ቀሪዎቹ ከብቶች አይሚሉም፡፡ እና ቀስ ብሎ እንዲከፍል ኮሞሮት አሻዎቹ ያግባባሉ፡፡ እኛንም እንደዚሁ አግባቡን፡፡ እንቢ ብለን ወዲያው እንዲከፈለን ጥረን ነበር፡፡ ግን ቀሪ አንደ ከብት ገዳዩ ጥቂት ጊዜ ወስዶ እንዲከፍል እኛማ ተስማማን፡፡ ይሁን እንጅ ያ ሰው ቃሉን አልጠበቀም፡፡ አሻውን አላከበረም፡፡ ቀሪውን ከብት ሊሰጠኝ አልቻለም፡፡ በአዚህ ምክንያት ቂም በውስጤ አድጎ ኖሯል፡፡ ሳየው መበሳጨት እጀምራለሁ፡፡ አሻውን አጠናቅቀህ ክፈል ስለው እሺ እያለ ወደማሾፍ መጣ፡፡ ይሂ ደግሞ ያው የሆነ አጋጣሚ ሲገኝ ወደ ስህተት ይመራል፡፡ እኔም አንድ ቀን አገኘሁትና ከዚህ በላይ ልታገሰው እንደማልችል ነገርኩት፡፡ እሱም እንደቀድሞ የረባ መልስ ሳይሰጠኝ ቀረ፡፡ ተናደድኩ፡፡ ራሴን አልተቆጣጠርኩም በጦር ወግቼ ገደልኩት፡፡ አሻ አስከፍላለሁ ብዬ ራሴ አሻ ከፋይ ሆንኩኝ፡፡

በኋላ አሻውን ለመክፈል በዘመዶቼ በኩል ጥረት ማድረግ ቀጠልኩ፡፡ መንግሥት ግን ይያዝ አለኝ፡፡ አሻ ቢከፍልም

መታሠር አለበት አለ፡፡ አሻ ከከፈልኩ በኋ አልታሠርም አልኩ እኔ፡፡ እኔ ያኔ ወደቆላው ወረድኩ እና በየኮሞሮት ገበታ አጥቤ ገባሁ፡፡ እዚያ ቆላው ላይ ያሉትም ሀሳባቸው እንደ እኔ ነው፡፡ "አሻው ከተከፈለ ተከፈለ፡፡ ለምን እስር ይኖራል?" አሉ፡፡ እንም እኔም እዚያው ቀረሁ፡፡ ዘመዶቼ አሻን ከፍለዋል፡፡ መኤኒት አንዴ ተሳስቶም ሆነ አውቆ ስህተት ከሠራ ሠራ ነው፡፡ አስቀድሞ ሰው ስህተት እንደሚሠራ ይታወቃል፡፡ ከዚያም ከስህተቱ የሚወጣበት መንገድ አስቀድሞ ተቀምጧል፡፡ ዛሬ አዳዲስ ሕግ ከማምጣታቸው በፊት እኛ እኮ ኖረናል፡፡ ዘር ማንዘሮቻችን ኖረዋል፡፡ የጎደለብን ነገር አልነበረም፡፡ አሻ ለእኛ የኖረ ባሕላችን እና ልማዳችን ነው፡ ፡ በእሱ እየተዳኘን ኖረናል፡፡ ሚች በሕይወት ቢኖር ሊጠቅማቸው ለሚችላቸው ሰዎች እርዳታ ናቸው የሚሰጡት ከብቶች፡፡ በመጀመሪያው ከብት ሚች ተጠቅልሎ ይቀበርበታል፡፡ በሁለተኛው ከብት ጦር ይመለስለታል፡፡ በቀሪዎቹ ከብቶች ቤተሰብ ዘመድ አዝማድ ይጠቀምባቸዋል፡፡ ጥፋትህን አውቀህ የሚያስታርቁ ሰዎችን ይዘህ ከሚች ቤተሰብ ጋ ብቻ ሳይሆን ከመላው ጎሳ ጋር ታርቀህ ከዚያ በኋላ ሴት ልጅ ሰጥተህ እንደገባ ታሰር ማለት ልክ አይደለም ብዬ ነው እኔ አልታሰርም ያልኩት፡፡ ሴቷ ልጅ እኮ የሚች ወገኖች ጋር ከሄደች በኋላ ትገባለች፡፡ በአሻ የእርቅ ሥርዓት ላይ ልጃገረዲቱን እናቷ አምጥታ ለሽማግሌዎች ትሰጣለች፡፡ ሽማግሌዎች ተቀብለው ለሚች ወገኖች ሲሰጧት ከፍተኛ ደስታ ይሆናል፡፡ በቦታው ያሉት የሚች ወገኖች በደስታ ይጮኻሉ፡፡ ልጃችን ተነሳ ይላሉ፡፡ ሚቹ ከሞት እንደተነሳ፣ ሕይወት እንደቀጠለ እናምናለን፡፡ ይቺ ሴት ነገ ልጆች ትወልዳለች፡፡ ዘር ይቀላቀላል፡፡ ይሄንን ሥርዓት ነው ሊለውጡት የተነሱት፡፡ እና እኔም ያኔ እምብኝ ብዬ በዚያው ቀረሁ፡፡ በኋላ ቆላውን ወድጄው ቀረሁ፡፡ ቀስ እያለ መንግሥትም እያሳደደ ሲያስቸግረኝ፡፡ ሊይዘኝ አንዳንዴ ፖሊሶች አንዳንዴ ሠራዊት ሲያዘምትብኝ እኔም ተፋላሚ ሆኘ ቀረሁ፡፡ ቆላ ያለውን መኤኒት ለማግባባት እና እኔን አሳልፎ እንዲሰጣቸው ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም ግን መኤንት ወዳጁን አሳልፎ አይሰጥም፡፡ አሻ አልከፈለም ብለው አስወርተዋል፡፡ ግን ዘመዶቼ መክፈላቸውን ሁሉም ያውቃል፡፡ ይታሠር የሚሉትን ግን ማንም አልተቀበላቸውም፡፡ እንዲያውም ብዙዎቹ እንዲሁ አንታሰርም እያሉ ወደ ቆላው ይወርዱ ጀመር፡፡ እሱ እንዲህ ስላደረገ እኛም እንደ እሱ እንሆናለን የሚሉ ብዙ ሆኑ፡፡ ትልልቆቹም ነባሩ ባሕል የቆየው የመኤኒት ልማድ ምንም አልጎዳን፣ አንፈልግም ብለው ነበር፡፡ እኔም ከዚያ አልፌ በሌሎቹም የምታወቅ ሆንኩ፡፡ እንዲያው መኤኒት በተበደለበት ቦታ ሁሉ መገኘት ጀመርኩ፡፡ መኤኒት ከአጎራባቾቹ ጋር ሲጣላ፣ ከብት ሲዘረፍበት፣ ሲገደል ቀድሜ

*በመድረስ የሚቀጣውን መቅጣት ጀመርኩ፡፡ ያወ ምንግሥትም ፍለጋውን ሲያጠናክር እኔም ራሴን ለመከላከል ስጥር ብዙ ዓመታት አለፈ፡፡ እንዲያውም አንዳንዴ ሽፍታ ነው እያሉ የሚያስወሩ ነበሩ፡፡ ያው ልማዱ ይከበር በማለቴ ነው ስሙ የወጣልኝ፡፡ በመጨረሻም መንግሥት ራሱ ምክንያት ፈጥሮ፣ አመራር ከሆኑ የመኤኒት ፖሊሶች ጋር ብዙ ውይይት አድርገን፡፡ እኔም ወደ ወጣሁበት ተቀላቀልኩ፡፡ መሳሪያየን እንደያዝኩ፡፡ ክብሬን ሳያጓድሉ፡፡ ከትንሽ እስከ ትልቅ ተሰልፎ አቀባበል ተደርጎልኝ ነው ወደ ከተማ የገባሁት፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011፣ ያርጣ)፡፡*

አቶ ጥጋቡ ነባሩ የአሻ ሥርዓት ብቻ መካሄድ አለበት በማለት አዲሱን አስተሳሰብ ከተቃወሙ በኋላ በብዙዎች ዘንድ እንደ ታላቅ ጀግና እንደሚታዩ የሚገልጹት ደግሞ ብርሃኑ ወርቄ ናቸው፡፡ አቶ ብርሃኑ ወርቄ የአቶ ጥጋቡ ዝናና ተሰሚነት ቀስ በቀስ እየጨመረ መምጣቱን እና እንደመኤኒት ዋና ጀግና እንደሚታዩም ታሪኩን ከዚህ በታች ባለው ገለጻቸው ያስረዳሉ፡፡

*አቶ ጥጋቡ የአጎቴ ልጅ ነው፡፡ እሱ በአንድ አጋጣሚ ሰው ገደለ፡፡ ቀደም ብሎ ከኛ ወገን ሰው ተገድሎ ነበር፡፡ እናም እንደ መኤኒት ደንብ እኛም አሻ ተከፈለን፣ እርቅም ወረደ፡፡ ይሁን እንጅ የገዳይ ወገኖች አሻውን ሙሉ በሙሉ አልከፈሉም ነበር፡፡ የቀረ ከብት ነበር፡፡ ጥጋቡ ደግሞ የቀረውን ከብት ክፈለኝ ብሎ ሰውዬውን ጠየቀ፡፡ ሰውዬው የሚያናድደውን ዓይነት መልስ ሲሰጠው ገደለው፡፡*

*ያው እንግዲህ እኛ ጋ ሰው የገደለ፣ ነፍስ ያጠፋ ነፍስ ይክሳል፡፡ ጥጋቡም ያንን ጉዳይ ሳይቋጭ ቆላ ወረደ፤ ቆላ ገባ፡፡ ትንሽ ቆይቶ እኛ እኔ ከፈልኩ፤ የእኛ ዘመዶች ከፈልን፡፡ ይሁን እንጅ ጥጋቡ የመኤኒት ብሔረሰብ ወግና ልምድ አሻ መክፈል ነው፤ ከዚያ በኋላ የመጣው ገዳዩን ማሠር ተገቢ አይደለም ብሎ በዚያው ቀረ፡፡ አሻፈረኝ አለ፡፡ እዚያ ላይ ከዚህ ብዙ ግፊት መጣበት፣ እሱም አሻፈረኝ አለ፡፡ ቆላ ቆላውን ይዞት ከረመ፡፡ ቆላም ከዋና ዋና የጎሳ መሪዎች ጋር ይተዋወቃል፣ ይወደዳል፡፡ እነሱም አሻን ካወጣ መታሠር የለበትም፤ ደንቡን ፈጽሟል፣ እኛም ጋ የሚሠራው ይሄ ነው አሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ከዚህ እሱን እጅ ለመያዝ ተሞክሯል፡፡ እሱ ግን አልተያዘም፡፡ እንዲያውም ዝናው እየጨመረ፣ ታዋቂ እና ተፈሪ እየሆነ ሄደ፡፡ እንኳን በመኤኒት በሌላውም የታወቀ ሆነ፡፡ ብዙ ወጣቶችም እንደ እሱ ጀግና ለመሆን፣ አልደፈር ባይ ለመሆን እስኪፈልጉ ድረስ ታዋቂ ሆነ፡፡ ስሙ በአምስት አጎራባች*

*ብሔረሰቦች ጭምር ታዋቂ ሆነ፡፡ በቆላው አካባቢ በሚፈጠሩ የአጎራባች ሕዝቦች ጸብ ውስጥ በእርቅ ሲፈታ ዋና እና የማይጠፋ ሰው ሆነ፡፡ አንዳንዶቹ በተለይ ሊይዙት በሂዱ ፖሊሶች እና ወታደሮች ላይ ባገኘው ድል እና ባለመሸነፉ ምሳሌ ያደርጉት ጀመር፡፡ ያው ብዙ ቆየ፡፡ እሱን መያዝ የሚቻል አልሆነም፡፡ ምንም ዓይነት ማባበያ ቢመጣ እሱን አሳልፎ የሚሰጥ ሰው የለም፡ ፡ እንዲያውም እያሳሳተ መንገድ የሚሰድድ፣ ቀድሞ ለእሱ ምስጢር የሚያደርሰው ነው የሚበዛው፡፡ ብቻ በጣም ታዋቂና ተፈሪ ሆኖ ኖረ፡፡ እስከ ላይ ያሉ የክልል አመራሮች ጭምር ዝናውን ያውቃሉ፡፡ ለአፋቸው ዝቅ ዝቅ ለማድረግ ቢፈልጉም በልባቸው ግን የሚፈሩት ሰው ነበር፡፡ ከቆላ ቆላ ፈጥኖ የሚንቀሳቀስ፣ ነገሮችን ቀድሞ የሚረዳ እና በጣም ደፋር ሰው ነው ጥጋቡ፡፡ ትንሽ ስለተማረ፣ የፖለቲካ እውቀትም ስለነበረው ነገሮችን ቀድሞ ይረዳል፡፡ አሻው በዚያው በነባር ልማዱ ይከፈል የሚል እምነት ነበረው መጀመሪያ፡፡ አባቶቻችን የሰጡን፣ ለዘመናት የኖርንበት ልማድ እሱ ነው የሚል ሀሳብ ነበረው፡፡*

*ጥጋቡ ብዙ ሰው የሚያውቀው ነው፡፡ አንዳንድ ወጣቶች ስለ እሱ ስለሚሰሙ የሆነ ችግር ቢፈጠር እንደ እሱ ወደቆላው መሄድ እንደሚችሉ ያስባሉ፡፡ አንዳንዴ ጥጋቡ በዚህ አካባቢ ታየ የሚል መረጃ ይመጣና እሱን ለመያዝ ኃይል ይንቀሳቀሳል፡፡ ችግሩ ገና ከዚሁ ኃይሉ ሲንቀሳቀስ እሱ መረጃ ይደርሰዋል፣ ቦታ ይቀይራል፡፡ ተዘጋጅቶ ይጠብቃል፡፡ በመጨረሻ እሱ አሸናፊ ይሆናል፡፡ ያው አካባቢው ደግሞ በደን የተሸፈነ፣ ሰበርባራ እና ለመደበቂያ ምቹ ነው፡፡ ያኔ ምንም ዓይነት መንገድ አልነበረም፡፡ ሰው እንኳን ይኖርበታል ተብሎ የማይታሰብ አካባቢ ነው የነበረው፡፡ የመኪኒት ቆላ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ አንዳንድ ቦታ ሰርዶው፣ ሰንበሌጡ በሰው ቁመት ልክ የሚሆን ነው፡፡ እና በዚያ ውስጥ መፈለግ ከባድ ነው፡፡ በዚያ ላይ እሱ ብልህ ነው፡፡ እየቆየ ሲሄድ መኪኒቶች የሚመኩበት ሰው እየሆነ መጣ፡፡ በዚያ አካባቢ ያሉ ማለቴ ነው፡፡ አንዳንዴ ከአጎራባች ወረዳዎች ሰዎች ይመጡና ከብት ዘርፈው ይሄዳሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ዝም ብለው ሰው ይገድላሉ፡፡ በዚህ መሐል መኪኒት ሲጠቃ ደም የሚመልሰው እና ጥቃትን የሚያስቆመው እሱ ሆነ፡፡ ፈጥኖ አንድ ሥራ ይሠራል፡፡ ከመሰለው የትም ገብቶ የተሰረቁትን ከብቶች ይዞ ይመጣል፡፡ ካሰኘው የአጠቁትን ሰዎች እጥፍ ጥቃት አድርሶባቸው ይመለሳል፡ ፡ (ቃለመጠይቅ፣ የካቲት 2011፣ ያርጣ)፡፡*

የባሕል የመስተጋድላውያን የማኅበረሰባቸውን ወግና ልማድ፣ ባሕልና ታሪክ ላይ ሥራቸው መሠረት አድርጎ የሚነገር የተጋድሎ ታሪክ ያላቸው ሰዎች ላይ

እንደሚያጠነጥን ሁሉ የአቶ ጥጋቡም ታሪክ ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ዘመናዊው ዓለም ስለ የባሕል መስተጋድላውያን ባለው እሳቤ ዓለም አቀፋዊ ዝና ያላቸውንና የዓላማቸውን ተጋሪዎች ከጎናቸው ያሰለፉ ሰዎችን በዚህ ሥር መድቧቸዋል፡፡ ለዚህ ጥሩ አብነት ከሆኑት ውስጥ አንዱ ኦሳማ ቢላደን ነው፡፡ ይህ ሰው ለአሜሪካኖቹ በጥቁር መዝገባቸው ውስጥ በጉልህ የተጻፈ "አሸባሪ" እና በሕግ የሚፈለግ ሲሆን፣ ለአብዛኛው የዐረቡ ዓለም ደግሞ ሁነኛ የነጻነት ተፋላሚ ነው፡፡ ይህ ሰው በሁለት ተቃራኒ ወገኖች ውስጥ ሁለት የተለያየ ትረካ አለው፡፡ ለአንደኛው ወገን ብርሃን ሲሆን ለሌላው ወገን ጨለማ ነው፡፡ በአንደኛው ወገን የሚነገረው ጭካኔው፣ በሌላኛው ወገን የሚተረከው ደግሞ ምትክ የሌለው ተጋድሎው ነው፡፡

ከላይ እንዳየነው ሁሉ አቶ ጥጋቡም ለመኤኒቶች እና በአሻ ነባር ሥርዓት ብቻ መተዳደር አለብን ለሚሉ ተፋላሚ፣ ለሌሎቹ ደግሞ አመፀኛና ሕግ አፍራሽ ናቸው፡፡ አቶ በድሉ ካሳ የአቶ ጥጋቡ የባሕል መስተጋድልነት ለመኤኒት ብሔረሰብ ማንነት መከበር ያደረጉትን አስተዋጽዖ ሲገልጹ "ቀደም ባለው ጊዜያት መኤኒትን እንደሰው የማይቆጥሩ፣ ዝቅ አድርገው የሚዩ አካላት ነበሩ፡፡ መኤኒት በተለያየ ስም ሲጠራ የኖረውም ለዚህ ነው፡፡ ቲሽና፣ ሻቅላ..፣ ወዘተ የሚባሉ ልክ ያልሆኑ ስያሜዎችን ብሔረሰቡ አሳልፏል፡፡ እንዲህ እንደ ጥጋቡ ዓይነት ሰዎች መምጣታቸው ለመከበሪያነት ጠቅሟል (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011፣ ያርጣ)፡፡

## 6.4 የባሕል መስተጋድልት ወ/ሮ ኮራይ

የሚጥል በሽታ በብሔረሰቡ ዘንድ እንደ እርግማን እንደ መጥፎ ዕጣ የሚቆጠር ነው፡፡ አብዛኞቹ የመኤኒት እናቶች የወለዷቸውን ልጅ ይሄንኑ ርግማን በመፍራት ታንቀው እንዲሞቱ ፈርደውባቸዋል፣ አንጀታቸው አልችል ያሉ እናቶች ደግሞ ማንም ሳያያቸው ከመኖሪያ ቀያቸው አርቀው ለአውሬ እና ለእጣ ፈንታቸው ጥለዋቸው መጥተዋል፡፡ በሽታው ተላላፊ እንደሆነ መታመኑ ደግሞ ችግሩን የባሰ አስከፊ አድርጎታል፡፡ እናት በድንገት የታመመ ልጇን ለመርዳት እንኳን ትፈራለች፡፡ የመጀመሪያው ፍራቻዋ በሽታው ወደ እኔ ይተላለፋል የሚለው ሲሆን ሁለተኛወ ፍራቻ ደግሞ እሷ ልጇን ከነካች እሷ ተረግማለች፣

ተለክፋለች ተብሎ ስለሚታመን ያይዋት እንድትገለል ያደርጓታል፡፡ የእሷ እጣ ፈንታ አንደ ልጇ መጣል ነው፡፡

ነገር ግን የሚጥል በሽታ በንክኪ የማይተላለፍ መሆኑን እየሰሙ የመጡ አንዳንድ እናቶች ልጃቸውን ከመግደል አርቆ ወደ መጣል፣ ከተቻለም ወደ ከተማ ወስዶ ሌሎች አዝነው እንዲያሳድጉት ባይቻል፣ የመንግሥት ተቋማት ባሉበት (ቴሌ፣ መብራት..) አካባቢ የግንብ አጥር ተጠልለው መኖር እንዲችሉ ለማድረግ ጥለው ይመጣሉ፡፡ አቶ ቢጎሎኝ በርጉዋ ስለ ሚስትታቸው እህት ታሪክ የሚከተለውን ይናገራሉ፡፡

*ሴትየዋ የሚስቴ እህት ናት፡፡ ኮራይ ትባል ነበር፡፡ እዚሁ ያርጣ አካባቢ ነበረች፡፡ ሻርማ ወንዝን ተሻግራ ኗሪ ነበረች፡፡ ባሏም ማክቪ ይባላል፡፡ አሁን በሕይወት የለም፡፡ ሦስት ልጆች ነበሯቸው፡፡ እናም አንድ ቀን ትንሽዋን ልጅ ክፉ ነገር ይገጥማታል፡፡ በድንገት ትወድቃለች፣ አረፋ ያስደፍቃታል፡፡ ያው ርግማኑ ነው፡፡ ክፉ እጣ ነው፡፡ ታመመች፣ ወደቀች፡፡ በዚህ ጊዜ የኔ ሚስት እና እህቷ ዱር ውለው መመለሳቸወ ነበር፡፡ የኛ ቤት ከእነሱ ሻገር ብሎ ስለነበር በዚያው ሲደርሱ ሁለቱም ልጇቷ ስትንፈራፈር ይደርሳሉ፡፡ ያቺ ሴት ከመደንገጧ የተነሳ ምኑንም ምኑንም ሳታውቅ ሄዳ ልጅቷን ከወደቀችበት ታነሳታለች፡፡ እናት ስለሆነች ደንግጣ ነው፡፡ ነካቻት፡፡ እንዲያውም አፏን በእጇ ጠራረገችው አሉ፡፡ ይሄኔ የእኔ ባለቤት ጮኸች ልጅቷን እንዳትነካ ብታስጠነቅቃትም አልሰማቻትም፡፡ ያኔ የኔይቱም እንደደነገጠች ሁሉን ጥላ ወደቤቷ መጣች፡፡ እኔም ግቢ ውስጥ ዛፍ ሥር ተቀምጬ ከአንድ ጓደኛዬ ጋ ስለገቢያ እያወራን ነበር፡፡ የሚስቴን ድንጋጤ አይተን ደነገጥን፡፡ ምን እንደተፈጠረ ስንጠይቅ የማይሆን ነገር ሆኗል፡፡ ሴትየዋ ነክታለች፡፡ እሷም ላይ እርጉም ነገር ተላልፏል፡፡ ይሄ የአምላክ ቁጣ ነው፡፡ ምልክት ነው፡፡ ከጥንት ጀምሮ ያለ ነው፡፡ እንዲህ ያለ ነገር ሲገጥም ቶሎ ብሎ ማስወገድ፣ ከአካባቢው ማራቅ ነው፡፡ ሌሎች መበከል የለባቸውም፡፡ ያቺ ሴት ግን ወደኋላ ስንሰማ ወደ ከተማ ጨበራም፣ ባቹማም የሚወራ ነገር እየሰማማች ልቧ ተንኮል ተሞልቷል ለካ፡፡ መቼም ዘመዴ ናትና ቢያንስ ሌላ ሰው ሳይሰማ ይሄንን እርግማን ታርቅ ብለን እኔና ሰውዬው ከእህቷ ጋር ሆነን ለመምከር ሄድን፡፡ ሴትየዋ ግን ምን እንዳስመለከታት አላውቅም፣ ልጅቷ አረፋዋ ከተት ሲልላት*

> *ልቧ ሌላ ነገር አስቧል ለካ፡፡ እኛም የሆነው ነገር ለእሷም፣ ለቤተሰቧም፣ ለእኛም ጭምር መጥፎ ነገር የሚያመጣ ስለሆነ እንድታስወግድ፣ እኛም ብንሆን ልናስወግድ እንደምንችል ነገርናት፡፡ መቼም አምላክ ቱማ እንዲህ ዓይነቱን ቅጣት ሲያመጣው መቀበል ነው፡፡ ይሄ ደግሞ የእሷ ብቻ አይደለም፡፡ ብዙ ሰው ያጋጥመዋል፡፡ ልጆቹን በግዜ ማስወገድ ነው፡፡ ኋላ ባለቤቴ፣ የእሷ እህት ስትነግረኝ ለካ፡፡ እዚያ ከተማ እንዲህ ያሉትን ሰብስበው የሚያሳድጉ እንዳሉ ሰምታለች አሉ፡፡ ምን እሷ ብቻ አንዳንዶቹ ሰምተዋል፡፡ ኋላ ባሏ ሲጠበቅ ሳይመጣ ቀረ፡፡ እንግዲህ ገቢያ ሄዶ በዚያው አድሮ ነው፡፡ እኛም ስለ እሷ እያሰብን ሲነጋ አንዳች ነገር እናደርጋለን እያልን አነጋን፡፡ እኔ አስብ የነበረው ለእሷ ነው፡፡ ባሏ ይሄንን ሲሰማ ምን ያደርጋል፣ ነክተዋለች፡፡ መኤኒት ደግሞ አይደብቅ ብዬ ነበር የማስበው፡፡ ኋላ ስንሰማ ለካ እሷ በሽታው አይተላለፍም የሚል አሁን የመጣ ትምህርት አለ እሱን ቀስማለች አሉ፡፡ ከየገበያው፣ ከየመንገዱ ሰምታለች፡፡*
>
> *ጧት እንደነጋ እኔና ጓደኛዬ ሆነን የሚሆነው ለማድረግ ብንሄድ ከቤት ማንም የለም፡፡ ቀሪዎቹ ልጆች ብቻ ናቸው፡፡ እኛ እናታቸው ወዴት እንደሄደች ስንጠይቅ ማንም የሚነግረን ጠፋ፡፡ ኋላ እህቷ ሴትየዋ ልጇን ይዛ ወንዝ ተሻግራ መጥፋቷ ነገረችን፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ጉድ አሁንማ በርክቷል፡፡ የመንግሥት ሰዎችም አልፎ አልፎ መምጣት ጀምረዋል፣ ወሬያቸው ሁሉ ይሄው ነው፡፡ አንዴ ፈጣሪ አይጣላ፣ ከሆነ ምን ይደረጋል፡፡ ሌላውን ማዳን ነው አንጅ ለምን አምላክንስ፣ ኘራዮችንስ፣ ሽግሌዎችንስ ታስቀይማለህ፡፡ ይሄ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ የኖረ ነው፡፡ ይሄው እንዲህ ዓይነቱ ክህደት ከመጣ በኋ ሴቱ ሁሉ ልቡ ተሰቅሏል፡፡ የእሷን ሁኔታ ያወቁ ሁሉ የሚሠሩት እንደሷ ነው፡፡ በዚሁ እርግማን ሲጠቁባቸው እንደ እሷ ወንዝ እየተሻገሩ ወዲያ ወደባቹማ መፈርጠጥ ሆኗል ሥራቸው፡፡ ያቺ መርዘኛ ሴት ናት እንግዲህ ሁሉን የበከለች፡፡ ይሄው ያኔ የጠፋች እስከ አሁን አየናት፣ በዚህ አለች የሚል ሰው የለም፡፡ የተከለችው ክፉ ሥራ ግን አካባቢውን አለቀቀውም፡፡ እንዲያውም እርግማኑ ጨምሮ የሚታመመው በዝቷል (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት* 2011፣ *ያርጣ)፡፡*

የባሕል መስተጋድልቷ ወ/ሮ ኮራይ ከነባሩ የመኤኒት ባሕልና እምነት ጋር የተጋደሉ ሴት ናቸው፡፡ በተለይም ያርጣ ከተሰኘው ቀበሌ አንጻር ተጋድሏቸውን

ለመረዳት የኮራይን የባሕል መስተጋድልትነት ለማወቅ ያስችላል፡፡ ያርጣ የተሰኘው አካባቢው/ቀበሌ ከቀሪው የመኤኒት ብሔረሰብ አካባቢዎች እና ከሀገሪቱ ጋር በኦፊሴል የተቀላቀለው በ2003 ዓ.ም ነው፡፡ "ያርጣ ቀበሌ ሰፊ ሕዝብ መኖሩ የታወቀው በ2003 ዓ.ም. ነው፡፡ ከዚያ በፊት በጫካ ውስጥ ጥቂት ቤተሰቦች ሊኖሩ እንደሚችሉ በአቅራቢያው ባሉ አንዳንድ ሰዎች ቢገመትም መደበኛ በሆነ መልኩ ከማንም ጋር ተገናኝተው አያውቁም ነበር፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ብርሃኑ፣ የካቲት 2011፣ ያርጣ)፡፡ አቶ ጉነማሮ በናሻም ይሄንኑ ጉዳይ ያጠናክሩታል፡፡" እኛ ያርጣ የምንኖረውን ሰዎች ፊት ሌሎቹ አያውቁንም ነበር፡፡ እኛም አልፎ አልፎ ጫካ ጥሰን፣ ወንዝ ተሻግረን ወዳደረሰን ቦታ እንሄድ ነበር፡፡ አሁን መንግሥቱ ተቀብሎናል" (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011፣ ያርጣ)፡፡

በያርጣ ጥቅጥቅ ደን መሐል ያሉ የቀበሌው ኗሪዎች ከተቀረው ዓለም ጋር የሚገናኙበት መንግሥታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበረሰባዊም ይሁን መሰል ጉዳዮች አልነበረም፡፡ የሚተዳደሩት በራሳቸው ነባር ልማድ እና እምነት፣ በኮሞሮቶቻቸው፣ በኘራዮቻቸው እና በሽማግሌዎቻቸው ትዕዛዝ ሥር ነው፡፡ ወ/ሮ ኮራይ የዚህ ማኅበረሰብ ውጤት ናቸው፡፡ የወረሱት ልማድ፣ ባሕል ወይም ሃይማኖት ነባሩን ሥርዓት ነው፡፡ ይህ ነባር ሥርዓት ደግሞ እንዲገዙ እና በሥርዓት ውስጥ እንዲያድሩ የሚያስገድዳቸው ነው፡፡ ይሁን እንጅ ኮራይ ከተቀረው ዓለም ጋር በሀሳብ እና በተግባር ቅርርብ የፈጠሩ ናቸው፡፡ ለዚህም ማሳያው የሚጥል በሽታ የሚተላለፍ አለመሆኑን መረዳታቸው እና በበሽታው የተያዙ ልጆች በሰላም እየኖሩ መሆኑን ማወቃቸው ነው፡፡

ኮራይ የልጃቸውን በሚጥል በሽታ መያዝ ሲያውቁ ከነባሩ የብሔረሰቡ እምነት ጋር መላተማቸው ግልጽ ሆኖላቸዋል፡፡ በአጠገባቸው ሰው መኖሩ ደግሞ ዕጣፈንታቸውን መራር እንዳደረገባቸው መረዳት ቀላል ነው፡፡ ምስክር የሚሆንባቸው ሰው ባይኖር ምናልባትም የገጠማቸውን ችግር በድብቅ መፍትሄ ሰጥተው የልጃቸውም ሆነ የእሳቸውን ሕይወት ይቀጥሉ ነበር፡፡ ነገር ግን የተጋድሎ ጥሪያቸው የመጣው ከማኅበረሰቡ ጋር በመሆኑ ሊሸሽጉም፣ ሊሸሽጉም ዕድል አልነበራቸውም፡፡ ኮራይ የማኅበረሰቡ እምነት ልጃቸውን እንዳይነጥቃቸው እና እንዳይቀጥፍባቸው፣ አፈር በአፍና በአፍንጫዋ ከትቶ እንዳይገድልባቸው በማሰብ የሚመጣውን መራራ ጽዋ እስከወዲያኛው ለመጋፈጥ ቆርጠው ልጃቸውን ከአፈር ላይ አንስተው ታቅፈዋል፡፡ ለተጋድሏቸው ውርደትን፣ እርጉም መባልን፣

መገፋትን፣ መነወርን አሜን ብለው ሲቀበሉ፣ ከማኅበረሰቡ፣ ከቤተ ዘመዱ፣ ከቤተሰባቸው ለመነጠል ዕጣ ፈንታቸውን ተጋፍጠዋል፡፡ የኖረውንና የፀናውን ሥርዓት ለመጋፈጥ ተነስተዋል፡፡

የፈጣሪን ፍጡር በዚህ መልኩ ባለው ልማድ እና የእርግማን ቅኝት ላለማፍረስ የገነቡትን፣ ወግ ማዕረግ ያዩበትን፣ የተዳሩበትን፣ የወለዱ የከበሩበትን፣ የሕይወት መስተጋብር ንደዋል፡፡ ወደ አዲስ እና ወዳላወቁት ሰፊ ዓለም ሁለት ነፍስን በተስፋ አንቀልባቸው አዝለው፣ በታያቸው የአዲስ ሕይወት ወጋገን ተመርተው፣ ባገኟት የዕድል ስንጥቅ ለማለፍ ተጉዘዋል፡፡

ነባሩ ልማድ እሳቸውንም ልጃቸውንም የሚቀጣ በመሆኑ ኮራይ ባለቤታቸው በሌለበት፣ ቀሪ ልጆቻቸውን እና ኑሯቸውን ጥለው ከእጣፈንታቸው ታግለው ወደ አዲሱ ዓለም ተጉዘዋል፡፡ ያ የሄዱበት አዲስ ዓለም እንደኖሩበት ዓይነት የጸጥታ እና የእርጋታ ዓለም እንደማይሆን ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጅ የነባሩን ልማድ ሠንሠለቶች በጣጥሰው፣ ሕይወታቸውን እና ቀሪ ዘመናቸውን ከኖሩበት ዓለም አፋትተው፣ ገድላቸውን እና እንቢባይነታቸውን ለተቀረው ወገናቸው ትተው ተጉዘዋል፡፡

መስተጋድልቷ አምላካቸው ቱማ ከእንዲህ ዓይነቱ መዓት በተአምራቱ እንደሚያተርፋቸውና የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤቱን ተማምነው በእግር የያርጣዎችን ምድር፣ በልቡና የአሮጌውን አስተሳሰብ ድንበርና ቅጥር ዘልቀው ተሻግረዋል፡፡ ለልጃቸው በሚማሰው ጉድጓድ አሮጌውን እምነት ቀብረው፣ ለእሳቸው በሚንጠለጠለው ገመድ ትናንታቸውን ሰቅለው ከባሕሉም፣ ከእምነቱም ተዋድቀው በተጋድሏቸው ሌሎች ተከታዮቻቸውን አፍርተው መስተጋድልት ሆነው ተጉዘዋል፡፡

ምናልባትም በያርጣ አካባቢ ዛሬ ዛሬ እንዲህ ዓይነቱን የሞት ጥሪ ተገዳድረውና ታግለው ያሸነፉ እንደ ወጣት ሞናይ ዓይነት መስተጋድልት የተወለዱት ከወ/ሮ ኮራይ የአሮጌው ሕይወት ሞት ላይ ሊሆን እንደሚችል የቀጣይዋ ወጣት መስተጋድልት የያርጣ ቀበሌዋ ሞናይ ታሪክ ሊመሰክር ይችላል፡፡ በአጠቃላይ እንደአንድ መስተጋድል የገድሉን ጥሪ፣ ጥሪውን ያለመቀበልን ትንቅንቅ፣ በጥሪው ቅጥር ውስጥ መዝለቅን፣ በመጨረሻው በውጤት መመለስ የሚሉትን የCambel

(1964)ን የመስተጋድላውያን ደረጃዎች ያሚሉ መስተጋድልት ናቸው ወ/ሮ ኮራይ፡፡

## 6.5 የባሕል መስተጋድልት ሞናይ

ሰው ሥፍራውን መስሎ ማደጉ ተፈጥሯዊ ሂደት ነው፡፡ በያርጣ አካባቢ የተወለደ ማንኛውም ሰው ለዘመናት ከሌላው አካባቢ ተገልሎ ሲኖር ባዳበራቸው ማኅበረ-ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ መስተጋብሮች ተቃኝቶ ያድጋል፣ ኖሮም ያልፋል፡፡ አካባቢው ቆላማ ሲሆን ሻርማ የተሰኘው ታላቅ ወንዝም ለአካባቢው ወሰን/ መለያ ሆኖ ከማገልገሉ ባሻገር ሙቀቱን ማብረጃ አንዱ ተፈጥሯዊ ስጦታቸው እንደሆነ ያምናሉ፡፡ የሚጥል በሽታ በመኤኒት አካባቢ ለምን በብዛት እንደሚከሰት የተረጋገጠ ነገር ባይኖርም፣ በሽታው በብዛት ይከሰታል፣ የሚታመነው ደግሞ የአምላክ ቁጣ እና ተላላፊ መሆኑ ብቻ ነው፡፡ እንደ ወ/ሮ ኮራይ ከዚያው ከያርጣ አካባቢ የወጣችው ሌላዋ የባሕል መስተጋድልት ታዳጊዋ ሞናይ ስትሆን የወጣቷን ተጋድሎ አቶ በድሉ ካሳ ከዚህ በታች ባለው መልኩ ይተርኩታል፡፡

> *ታሪኩ ሞናይ የተባለች ልጃገረድ እና የአባቷ ነው፡፡ ታሪኩ የተፈጠረው በመኤኒት ጎልዲያ በያርጣ ቀበሌ ነው፡፡ በዚያ ቀበሌ የሚኖር አቶ ጎላንዳቢ የተሰኘ ሰው ልጁን የሚጥል በሽታ አመመበት፡፡ በብሔረሰቡ እና በአካባቢያችን የሚያዞር ወይም የሚጥል በሽታ የያዘውን ሰው ከእግዜር የመጣው ቁጣ ያለበት ነው በማለት ያገላሉ፡፡ አንድ ቤት ውስጥ በሽተኛ ካለ፣ የነካውን ዕቃ አይጠቀሙም፣ እዚያ ቤት የሚደርስ ሰው የለም ማኅበረሰቡ ያገልላል፡፡ (በድሉ ቃለ መጠይቅ፣ ታኅሣሥ 2011ዓ.ም፣ ባቹማ)*

ብሔረሰቡ በዚህ በሽታ የተያዘን ሰው የሚያገልልበት ምክንያት የአምላክ ቁጣ እንደሆነ ስለሚታመን በዚህ በሽታ የተያዘ ማንኛውም ሰው እጣ ፈንታው ዕድል ተርታው ከማኅበረሰቡ መወገድ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ መግፋትና መገፋት በየትኛውም ቤተሰብ ላይ ሊከሰት የሚችል አጋጣሚ ነው፡፡ ስለ ታዳጊዋ ሞናይ የተጋድሎ ታሪክ ስናስብ አንድ ግልጽ የሆነ ነገር በአካባቢው መኖሩ አይቀርም፤ እሱም ሞናይ በዚህ በሽታ ስትያዝ የመጀመሪያ የአካባቢው ልጅ አለመሆኗ ነው፡ ፡ ከሞናይ በፊት ኖረው በሽታው ስላጠቃቸው፣ በበሽታው ስለተያዙ የተገለሉ፣ ከመገለል አልፈው የእርግማን ምሳሌ ተብለው እንደ ማኅበረሰቡ እምነት እንዲወገዱ የተደረጉ ስንት ሊሆኑ እንደሚችሉ ስናስብ ብዙዎች የሞት ጥሪን

በሚቱ አማካይነት ተቀብለው፣ ባይቀበሉም እንዲቀበሉ ተደርገው ወደ አፈር መሸኘታቸውን ነው፡፡ ከሞናይ በፊት ስንት እናቶች ዘጠኝ ወር በማሕፀናቸው ተሸክመው፣ የሞት ላብ አምጠው የወለዷቸው ልጆች ለሞት እንደሰጡ ነው፡፡ የሞናይም ይሁን የእናትና የአባቷ ታሪክ ከዚሁ የሞት ጥሪ ጋር ተሳስሮ ብዙዎችን የሚያስታውስ የተጋድሎ ታሪክ ነው፡፡

እንዲህ ዓይነቱን የባሕል መስተጋድልት ሚት ትረካ ከመራራ ፅዋ ጋር የመጋጠም የሚያደርገው የማኅበረሰቡ አመለካከት በሽታው ያለበት ሰው እና እሱ በእጁ የነካው ማንኛውም ነገር ሁሉ የእርግማኑ መገለጫ እና ማደሪያ መሆኑ መታመኑ ነው፡፡ የመኤኒት ጎልድያ ወረዳ፣ የያርጣ ቀበሌው ኗሪው አቶ ጎላንዳቢ በልጃቸው ላይ በተከሰተው በሽታ የሚከተለውን መፈጸማቸውን አቶ በድሉ ካሳ እንዲህ ይተርካሉ፡፡

> *የአቶ ጎላንዳቢ ልጅ በዚሁ በሽታ ትታመማለች፡፡ ልጅቷ ከበሽታዋ ስትነቃና መለስ ሲልላት አባቷ በዚች ልጅ ምክንያት በአካባቢው ሰው እንዳይገለል ይፈራል፡፡ ከዚያ እንዳልገለል ብሎ ልጅቷን በአካባቢው ሻርማ የሚባል ትልቅ ወንዝ አለ፡፡ ባሕር አለው አዞዎች የሚኖሩበት ወንዝ ነው፡፡ ከዚያ ልጁን እዚያ ሊጥላትና ለአዞ ሊሰጣት ወሰነ፡፡ ከዚያም በዚያው ቀን ከሰአት ላይ ልጅቷን ይዞ ወደወንዙ ሄደ፡፡ ከልጁ ጋር ወደ ባሕሩ ደርሰው ሲሻገሩ አባቷ ወደኋላ ቀረት ብሎ ልጅቷን በእንጨት ገፍትሮ ወደ ባሕሩ ይጥላታል፡፡ ከዚያም እሱ ዞር ብሎ ሳያይ ወደመጣበት ይመለሳል፡፡ ይሁን አንጂ አባቷ ልጅቷን ወደ ወንዝ ወርውሮ ወደቤቱ ሲመለስ ልጅቷ ትረፊ ሲላት ለካ ዋና መዋኘት ትችል ስለነበር፣ አዞዎች ከመምጣታቸው በፊት ዋኝታ ከወንዙ ትወጣለች፡፡ እዚያ አካባቢ ሕጻናት ዋና ይችላሉ፡፡ ዋኝታ ተረፈች፡፡ ማምሻው ላይ ግን የምታድርበት ስላልነበረ ወደ ቤት መመለስ ግድ ይሆንባታል፡፡ ስለዚህ ሞናይ ወደ ቤቷ ተመለሰችና ተደብቃ አደረች፡፡*



የሻርማ ወንዝ አንድ ገጽታ፣ (ፎቶ በአጥኚው)፡፡

ገድለኛዋ ሞናይ የተረፈችው ዋና ስለቻለች ብቻ አይመስልም፡፡ ሻርማ ወንዝ በትላልቅ እና በአደገኛ አዞዎች የተሞላ ትልቅ ወንዝ መሆኑን እኔ ራሴ ለጥናት ወደ ቦታው በሄድኩበት ወቅት አይቻለሁ፡፡ እንኳንስ ከገደል ላይ ተወርውራ የተገፋች ታዳጊ ልጅ አግኝተው ይቅርና ውኃው ለጥ ባለበት አካባቢ ውኃ ለመጠጣት ያጎነበሰን እንስሳ ጠልፈው የሚጥሉ አደገኛ ፍጡራን ያሉበት ነው፡፡ ሞናይ የልዕለ ተፈጥሮ እገዛ፣ የአምላክ ቱማ ጥበቃ እንዳልተለያት ማየት ይቻላል፡፡ በሥጋ የወለዳት አባት ያኖረው ባሕል ገዝቶት ገፍትሮ እስኪጥላት ድረስ ሲጨክንባት፣ ነፍሷ እንድትተርፍ፣ ያላለቀ የሕይወት ጉዞዋን በአሸናፊነት እንድትወጣ አምላክ እንዳገዛት መመልከት ይቻላላል፡፡ በሌላ ጎኑ የሞናይ ሥጋዊ ዓለም ጠባብ እና ውስን መሆነን እናያለን፡፡ ይኸውም ከዕድሜዋ እና ከአካባቢዋ እርቃ ለመጓዝ የሚያስችል ዝግጅትም ሆነ አቅም እንዳልነበራት ያስረዳል፡፡ ለዚህም ይመስላል ወደ ተገፋችበት፣ ወደ ተጣለችበት፣ ሞት ወደፈረደባት አካባቢ፤ ለአዞ ጥርስና ከርስ ወደወረወራት አባቷ፣ ወደ የሚገፋት ማኅበረሰብ የተመለሰችው፡፡ ይሄም የተጋድሎ ታሪኳ አንዱ አንጓ ሲሆን፣ ከበሽታው ባሻገር ሞትን አሸንፋ የወጣችበት የመጀመሪያ ድሏ፣ በሌላ ጎኑ ለዳግም የሞት ጥሪ የቀረበችበት የመስዋእትነት ሜዳዋ ነው፡፡ አባቷን አቶ አቶ ጎላንዳቢም  በራሱ ብናስበው የብሔረሰቡ ሚት የሠራው ሰው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በተነጻጻሪም ጥሪወ ለእሱም ደርሶታል፡፡ ልጇን እንዲገፋት በሽታውን ከአካባቢው እንዲያርቅ፣ ቤተሰቡን እና ማኅበረሰቡን ለመጠበቅ ልጇን እንዲሰዋት የሚቱ ጥሪ ግድ ብሎታል፡፡ Brown ሚት የሚመሠረተው በአንድ ባሕል እሴቶች ላይ እንደሆነ ከገለጸ በኋላ ሚቱ በባሕል ውስጥ ስለሚፈጥረው ኃይል ሲያብራራ “በባሕል ውስጥ የግለሰብን እምነትንና አመለካከትን በአንድ የመቅረጽ ኃይል አለው፡፡ ሚት ሰዎች ከባሕላቸው ጋር ቁርኝት የሚፈጥሩበት አንድ መንገድ ነው” (Brown 2004) ይላል፡፡ አቶ ጎላንዳቢም እጣ ፈንታቸው የተሣሠረው ከዚህ በባሕሉ እሴት ላይ ከቆመው ሚት እንደሆነ እንረዳለን፡፡

የሞናይን የተጋድሎ ታሪክ እያሰብን፣ ከሷ በፊት ጥቂቶች ምናልባትም ተመሳሳይ ሙከራ አድርገው እንደሆነ እንኳን በምኞት ብንጠረጥር “ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ” የሚለውን ተረት አስታውሶ፣ የጥቂቶች ሙከራ መልሶ እጅ ከመስጠት ሊያልፍ እንደማይችል በሩቁም ቢሆን እንጠረጥራለን፡፡ ታዳጊዋ የባሕል መስተጋድልት ሞናይ ግን ሞትን በቀጣይ የሕይወት ምዕራፏም ስትታገለው እናያለን፡፡

> *ጧት ላይ አባትየው አያት፡፡ ከዚያም ተገርሞ ‘አንችን እኮ ሞተሻል ብለን እርማችንን አውጥተናል፡፡ አዞ በልቶሻል ብለን ደምድመናል፡፡ አሁን ምን ልትሠሪ ወደዚህ መጣሽ?’ ይላታል፡፡ እሷም አባቷን ለመነች፡፡ ‘እንዲህ ከምታደርገኝና ለአዞ ከምትሰጠኝ፣ እንዲህ ያለ በሽታ ያለባቸው ሰዎች፣ እዚያ ባቹማ የተሰኘ ከተማ ላይ ተጥለው ይኖራሉ፣ ይሄን ሰምቻለሁ እና ወደዚያ አድርሰኝ’ ትለለች፡፡ አባትየውም ‘ይሄንንም አላደርግም እኛ ባንቺ የተነሳ ተገልለን ከምንኖር ይልቅ ጫካ ውስጥ እንግባና ገመድ ልስቀልልሽ፣ እዚያ ገመድ ላይ ተሰቅለሽ ሕይወትሽን አጥፊ’ ይላታል፣ አባትዬው፡፡ ልጅቱም ‘ሕይወቴ አያሳዛዝንህም ወይ?’ ስትለው ‘አሁን አንቺ ኖርሽም አልኖርሽም ልዩነት የለውም፣ ብትሞቺ ይሻላል’ ይላታል፡፡ ልጅቷም ‘እንዲህ ከምታደርገኝ እንዲህ ዓይነት በሽታ የታመሙ ባቹማ ከተማ ተገልለው አይኖሩምና እዚያ ወስደህ ከተማ ብትጥለኝ እኖራለሁ ትለዋለች’፡፡ በዚህ ጊዜ አባትዬው አንድ ከብት ሸጠና ገንዘብ አስይዞ በማምጣት ጨበራ የተባለ ከተማ ላይ ይጥላታል፡፡ (በድሉ ቃለመጠይቅ፣ ታኅሣሥ 2011ዓ.ም፣ ባቹማ)*

ታዳጊዋ ሞናይ በድንገት ያጋጠማት ክፉ እጣ ከእድሜዋ በላይ ለመሆኑ ምስክር መጥቀስ አያስፈልግም፡፡ ሞት ዓይኖቹን አፍጥጦ እንደቀረባት በማወቋ

ላለመሞት ሰፊ ትግል አድርጋለች፡፡ አንድ መስተጋድልም አንዴ የገድል ጥሪው ከጠራው በኋላ፣ ጥሪውን ላለመቀበል መታገሉ የማንነቱ መገለጪያ ባህሪ ነው፡፡ ሞናይም የጠራትን ሞት ላለመቀበል መታገሏ የገድለኛነቷ መገለጫ ነው፡፡ ትግሏ ፍሬ እንዲያፈራ የአባቷን የአባትነት ልብ ለማራራት እና የተገለጠላት እውነት እንዲገለጥለት አማራጭ ያለችውን ሀሳብ አቅርባለች፡፡ በዚህም ከሞት ጋር፣ ፀንቶ ከኖረ ሚት ጋር ሰፊ ክርክርን አድርጋለች፡፡ ይህ የተጋድሎዋ አንድ አካል ከመሆኑም በላይ ላገኘችው ውጤትም ዋና መሠረት የጣለላት ነበር፡፡ ሞናይ የጀመረችውን የነባር ባሕል ሙግትና ተጋድሎ አስቀጥላ የአባቷን ልብ ጭምር ማሸነፏን እና ተጋድሎዋ ያስገኘላትን ውጤት ቀጥለን እንይ፡፡

በሞናይ የተጋድሎ ታሪክ ውስጥ የ"ይሆናል"፣ የ"ይሳካል" የፅናት ድምጽ ጎልቶ ይሰማናል፡፡ ታዳጊ አዕምሮዋ ከዕድሜዋ በላይ አብስሏት፣ ወልዶ ያሳደጋትን ሞግታ ለመርታት ችላለች፡፡ ሞናይ የሞገተችው፣ የረታችው፣ ያሸነፈችው አባቷን ብቻ አልነበረም፡፡ የኖረ እና የፀና እልፎችን ለአፈር የገበረውን የማኅበረሰቡን ልማድ ነው፡፡ ከእሷ በፊትም ሆነ በኋላ ብዙዎችን የቀጠፈውን እምነት ነው፡፡

> *ልጅቷ ሞናይ ጨበራ ከተማ ላይ አንድ ወር ያህል ትቀመጣለች፡፡ ከዚያ በኋላ ባቹማ ወደተባለው ከተማ ትመጣለች፡፡ በአጋጣሚ ይሄንን ጉዳይ የወረዳው ሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ይሰሙና ልጅቷን አምጥተው ካናገሯት በኋላ ትምህርት ቤት እንድትገባ ያደርጓታል፡፡ ባቹማ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ገብታ መማር ጀመረች፡፡ እየተማረች እያለች ደግሞ ራሷን የምታስተዳድርበት ገንዘብ ስለሚያስፈልጋት እዚሁ ባቹማ ወረዳ ሴቶችና ሕጻናት ጽ/ቤት ሥራ እየሠራች በምታገኘው ገንዘብ እየተማረች ሕይወቷን ትቀጥል፣ ትምራ የሚል ሀሳብ መጣና የጽዳት ሠራተኛ ተደርጋ ተቀጠረች፡፡ ልጅቷ ስትመጣ አማርኛ ቋንቋ መናገር አትችልም ነበር፡፡ አንድ ዓመት ስትኖር አማርኛውን ከሷ በላይ የሚናገር ጠፋ፣ ድሮ ስትመጣ አገልድማ ነበር የመጣችው አሁን ጅንስ ሱሪ ለበሰች‹ ቁመናዋ በጣም የሚያምር ነበር ሰዎች ማባበል ጀመረች፡፡ ሆቴል ገብታ መጠጣት ጀመረች፡፡ ከዛ ጫት የሚባል ቀበሌ ሆቴል የከፈተ አንድ ሰው ይዟት ሄደ ከዚያ እሱ ጋር እያለች ባል አገባች እና አሁን መኤኒት ሻሻ አካባቢ ጌሻ የሚባል ሀገር ትኖራለች፡፡ ይች ልጅ በዚያ በሽታ ስለተያዘች ባህር ውስጥ ተጥላ እንድትገደል የተፈረደባት ነበረች፡፡ ጫካ ውስጥ እንድትታነቅ ተጠይቃም ነበር፡፡ በኋላ ግን ወደከተማ መጣች ብዙ ሰዎች የእሷን ታሪክ እንዲያውቁት ሆነዋል፡፡ አንዳንዶቹ እየመጡ ያይዋት ነበር፡፡*

*የእሷ መኖር ሲታወቅ ብዙ አባቶችም ልጃቸውን ከመግደል ወደከተማ ቢያመጡ እንደሚሻል እንደምሳሌ ይቆጥሯት ነበር፡፡ የሞናይ ታሪክ ለብዙዎቹ መማሪያ ሆኗል፡፡ አንደኛ አልሞት ባይ ተጋዳይ ናት፡፡ ከሞት አምልጣለች፡፡ ሁለተኛ አባቷን አሳምናለች፡ ፡ የሴቶችና ሕጻናት ጽ/ቤቱ እሷን እንደምስክር እያደረገ ብዙ አስተምሮባታል፡፡ አንዳንድ ስልጠናዎችም ሲሰጡ የእሷ ታሪክ ይነገራል፡፡ ሁላችም በየአጋጣሚው እናወራለን፡፡ እዚህ ቢሮ አካባቢ ቢመሆኗም ታሪኳ እና ገድሏ ቶሎ እንዲታወቅ ሆኗል፡፡ ብዙ ለውጦች ያመጣ ታሪክ የሠራች ልጅ ናት (ዝኒ ከማሁ)፡፡*

ስለባሕል መስተጋድላውያን ለማጠቃለል ያህል፣ የወባ ንጉሡ ቻሪ እና የዝንጀሮ ንጉሡ አቶ ሴላ የአምላክ ኃይል በተዋረድ አንደደረሳቸው የሚያምኑ፣ ኃይሉንም ከአባቶቻቸው የተረከቡ እንደሆኑ አይተናል፡፡ እነዚህ የሃይማኖት መስተጋድላውያን በተሰጣቸው ኃይል ለተራው ሰው የማይቻለውን በመቻል ማኅበረሰባቸው ያጋጠመውን ችግር አስወግደዋል፡፡

የባሕል መስተጋድላውያኑ Cambel አንድ መስተጋድል ሊያልፏቸው የሚገቡ ደረጃዎች ብሎ ከዘረዘራቸው ዋና ዋና የጉዞ መስመሮች ውስጥ ሲያልፉ ይታያሉ፡፡ እንደ Cambel ገለጻ የመጀሪያው "የገድል ጥሪ" ሲሆን ሞናይም ይሁን ወ/ሮ ኮራይ እና አቶ ጥጋቡ አስቀድሞ ጥሪው የደረሳቸው ከነባሩ ልማድ፣ ከብሔረሰቡ ባሕል ነው፡፡ ይህ ባሕል ለዘመናት ፀንቶ የቆየ ብዙዎቹን በቀንበሩ ውስጥ ያኖረና እና የወሰነውን ቅጣትም ያስፈጸመ ሕግ ነው፡፡ የገድል ጥሪያቸው የመጣው መስተጋድላውያን "ጥሪውን ለላመቀበል መሚገት እንደሚጀምሩ" Cambel (2004፣ 14) ይገልጻል፡፡ ሞናይም ትሁን ወ/ሮ ኮራይ የመጣባቸውን የሞት እንዲሁም አቶ ጥጋቡ የእስራት ጥሪ እሺ ብለው የተቀበሉ አይደሉም፡፡ ሦስቱም ጥሪውን አልተቀበሉም ተቃውሚቸውንም ገልጸዋል፡፡ ጥጋቡ "ነባሩ ባሕል ይከበር፣ ከአሻ ውጪ አልዳኝም" ሲል፣ ነባሩ ባሕል የሞት ጥሪ አስቀድሞ የመጣባቸው የያርጣ ቀበሌዎቹ ወ/ሮ ኮራይ እና ታዳጊዋ ሞናይ ደግሞ "ሞትን አንቀበልም" ብለው ትግላቸውን ቀጥለዋል፡፡ Cambel የመስተጋድላውያኑ መጨረሻ የገቡበትን ተጋድሎ በውጤት መደምደም መቻላቸው እና ውጤቱ በድልም ይሁን በሽንፈት መጠቃለሉን ያሰምርበታል፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ የባሕል መስተጋድላውያኑም እንዲሁ ትግላቸውን ቀጥለው በአሸናፊነት ሲደመድሙ ይታያል፡፡ ጥጋቡ በድል ላይ ድል፣ በእውቅና ላይ እውቅና ደርቦ

ብዙዎችን አፍርቶ አዲስ ሕይቱን ሲቀጥል፣ ወ/ሮ ኮራይ እና ሞናይ ደግሞ ከነባሩ ልማድ ተፋትተው፣ የመጣባቸውን የሞት ጽዋ ተሻግረው ሕይወትን በአዲስ መንፈስ እና በአዲስ ዓለም ቀጥለዋል፡፡ የሦስቱም የተጋድሎ ውጤት ደግሞ በብዙዎቹ ውስጥ ስሜትን ቀስቅሶ የሀሳብም ይሁን የተግባር ተካፋዮቻቸውን በማምጣት ለብዙዎቹ አርአያ በመሆን ተጠቃሽ የባሕል መስተጋድል ለመሆን ችለዋል፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

## 7. የመኤኒት ብሔረሰብ የዳግም ውልደት ሚት

የሰው ልጅ የረጅም ጊዜ የሕይወት ምዕራፍ ውስጥ መወለድ እና መሞት ሁለት የማይነጣጠሉ የተፈጥሮ ክስተቶች ናቸው፡፡ በየትኛውም ዘመን፣ በየትኛው ቦታ የሚኖረው የሰው ልጅ በእነዚህ ሁለት የክር ጫፎች መካከል ያለውን የሕይወት ምዕራፍ አጠናቅቆ ወደ ቀጣዩ የሞት ዓለም ይሰናበታል፡፡ የዚያኑ ያክል ከሞት በኋላ ስላለው የሰው ልጅ እጣ ፋንታ እና ቀጣይ ምዕራፍ እንደየ ባሕሉ እና እንደየ ሃይማኖቱ የተለያዩ እሳቤዎች አሉት፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብም ከሞት በኋላ ስላለው ውልደትና የዳግም ሕይወት ጅማሬ የራሱ የሆነ እሳቤ እና ፍቺ አለው፡፡ በብሔረሰቡ እምነት አንድ ሰው የገሀዳዊና ነባራዊውን የሕይወት መስተጋብር፣ በአጭር ጊዜ የሕይወት ቆይታም ይሁን በአንጻራዊት በተራዘመ ጊዜ፣ ይሄንን ዓለም ይሰናበታል፡፡ ስንብቱ ግን አንደ ሰውዬው ዕድሜ እና እንደ ማኅበራዊ ማንነቱ ይለያያል፡፡

በብሔረሰቡ አስቀድሞ ለሟቹ የሚደረገው የቀብር ሥርዓት እንደሟቹ እድሜ እና ማንነት ይለያያል፡፡ የሚታዩት ልዩነቶች ከሞት በፊት ለሟቹ በሚደረጉ ሥርዓቶች፣ ሟች ከሞተ በኋ ለሟቹ የሚደረጉ ልዩ ልዩ ክንውኖች ላይ የሚታይ ነው፡፡ ብሔረሰቡ ሟች በማኅበረሰቡ ዘንድ ከበሬታ ያለው፣ በልዩ ልዩ ተግባሮቹ የሚታወቅ፣ በልጆች የከበረ እና ታዋቂነቱ ከፍ ያለ ሲሆን የቀብር ሥርዓቱም የዚያኑ ያህል የደመቀ ይሆናል፡፡

> *በመኤኒቶች ልማድ ለሟቾች የሚደረግ የአቀባበር ሥርዓት እንደ ሟቹ ማንነት ይለያያል፡፡ ህጻን ሲሞት፣ ወጣት ሲሞት ወይ ተራ ሰው ሲሞት ያለው የቀብር ሥነ ሥርዓት ከአንጋፎች እና ከከበሩ ሰዎች ጋር ይለያያል፡፡ የጎሳ መሪ ሲሞት የሚደረገው ከፍ ያለ ሥነ ሥርዓት ነው፡፡ የኃይማኖት መሪዎች ሲሞቱም እንደዚያው ከተራው ሰው በጣም የተለየ ነው፡፡ አንዳንዴ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ሲሞቱ የሟች ወገኖች አካባቢውን ለቅቀው እስከ መሄድ ይደረሳል፡፡ ተራ ሰው ሲሞት ግን እዚያው ግቢህ ውስጥ ቀብረህ ልትኖር ትችላለህ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ በድሉ፣ ህዳር፣ 2010ዓ.ም፣ ባቹማ)*

በብሔረሰቡ ልማድ አንድ ትልቅ የሚባል ሰው ሲሞት የቀብሩ እለት በርካታ ከብቶች፣ ወይፈንና ጥጃዎች ይቀጠቀጡለታል፡፡[10] "ትልቅ ሰው ሲሞት፣ በተለይም ልጆች ያሉት እና የሚታወቅ ሰው ከሆነ የሟቹ ወንድ ልጆች እና የሴት ልጆች ባሎች ከብት እያመጡ ይቀጥቅጡለታል፡፡ ከብቶቹ የሚቀጠቀጡት የቀብሩ እለት ነው፡፡" (ቃለ መጠይቅ ብርሃኑ፣ ህዳር፣ 2010ዓ.ም፣ ባቹማ) ከብቶቹ የሚቀጠቀጡት ወይም የቀብሩ እለት ግንባራቸውን በድንጋይ ተመትተው የሚገደሉት በሁለት ምክንያት መሆኑን ብርሃኑ ይገልጻሉ፡፡ ሟች ከሞት በኋላ አሁን በዚህ ምድር ባለው መልኩ ሌላ ሕይወት ይቀጥላል ተብሎ እንደሚታሰብ እንዲህ ያብራራሉ፡፡

> *ብሔረሰቡ እምነት ሟች የዚህን ዓለም አጠናቅቆ ሲሄድ፣ ለቀጣይ ሕይወቱ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ይዞ እንዲሄድ ይደረጋል፡፡ በዚያኛውም ሕይወቱ ያለችግር እንዲኖር ከብቶቹ ይከተሉታል ተብሎ ይታመናል፡፡ እንዲያውም በጥንቱ ጊዜ ልማድ ከከብቶቹ ባሻገር ለእሱ የሚሆኑ አንዳንድ የቤት ቁሳቁሶች እና ባላባት ከሆነ ደግሞ አገልጋይም አብሮት እንዲቀበር ይደረግ እንደነበር የሩቅ ታሪክ የሚውቁ ሲናገሩ እንሰማለን፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር፣ 2010ዓ.ም፣ ባቹማ)*

ይህ በቀብር ጊዜ የሚደረግ የከብቶች መቀጥቀጥ ሥርዓት ሁለት ዓይነት ጥቅም እንዳለውና አንደኛው ጥቅሙ ለቋሚዎች፣ ለቀባሪዎችና ለቤተ ዘመዶች፣

---

[10] *መቀጥቀጥ ማለት፣ ለእርድ የመጣውን ከብት ሁለት ሰዎች ቀንድ እና ቀንዱን ወይም ጆሮ እና ጆሮውን ይዘው ግንባሩን በድንጋይ እንዲመታ ያመቻቹታል፡፡ ሌላ ሰው ጥጃውን፣ ወይፈኑን ወይም በሬውን በአንድ ጊዜ ምት ሊገድለው የሚችለው ድንጋይ በሁለት እጆቹ ተሸክሞ መጥቶ በእርግብግቢቱ በኩል አስተካክሎ መሐል ግንባሩን በመምታት ይገድለዋል፡፡ በድንጋዩ የተመታው ከብት ወዲያው ጸጥ ሲል ሌሎች በሰላ ቢላዋ የከብቱን አንገት ያርዳሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የከብት መቀጥቀጥ ድርጊት በቀብር በማጠብ እና በውርስ ጋብቻ ጊዜ ይካሄዳል፡፡ ለምሳሌ በብሔረሰቡ ልማድ  አንድ ሴት የራሷ ካልሆነ ወንድ ጋር አውቃም ይሁን ሳታውቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ብታደርግ ከድርጊቱ በኋላ ጉዳዩን ሳትደብቅ ለባሏ ትነግራለች፡፡ ይሁን እንጂ ከእሷ ጋር ጉዳዩን የፈጸመውም ሰው የምታደርገውን ስለሚያውቅ እሱም ለመካስ ይዘጋጃል፡፡ የሆና ሆኖ የሴትየዋ ባል ግድያ እንዳይፈጽም በመሐል ሽማግሌ ይገባል፡፡ ከዚያ ከሴትየዋ ጋር ወሲብ ፈጽሟል የተባለው ሰው ተጠርቶ ይጠየቃል፡፡ የጉዳዩ መደረግ ወይም አለመደረጉ ግን የሚረጋገጠው በበግ ወይም በፍየል ደም አንጀት ነው፡፡ እውነቱ አንጀቱ ላይ እንደሚነበብ ይታመናል፡፡ አንባቢዎችም በሥፍራው ተገኝተው መሆን አለመሆኑን ይናገራሉ፡፡ ተጠርጣሪው ሰው ከገበያ ለስሪያ ያልደረሰ በግ ወይም ፍየል ገዝቶ ይመጣል፡፡ ይሄ ከሆነ በኋላ ያመጣውን ከብት እንዲቀጠቅጥ ይደረጋል፡፡ እዚህ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ጋር ተያይዞ ያለው ቅጥቀጣ ግን የሚካሄደው በድንጋይ ሳይሆን በእንጨት/ በዱላ ነው፡፡ የማስትሬት ዲግሪዬን በብሔረሰቡ ባሕላዊ የግጭት አወጋገድ ሥርዓት ላይ ሥሠራ እንደተረዳሁት በቀብር ጊዜ ቅጥቀጣው በድንጋይ የሚሆነው ድንጋይ በድን ነው ተብሎ ስለሚታመን ሰውዬውም መሞቱን ለማመልከት ሲሆን በግብረ ሥጋ ግንኙነት ጊዜ ግን ዛፍ የሕይወት ምሳሌ መሆኑን እና ሰዎቹም በሕይወት ያሉ መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ በሦስተኛ ደረጃ የውርስ ጋብቻንም ለማካሄድ ቅጥቀጣ ይካሄዳል፡፡ ይሄኛውም ቅጥቀጣ የሚካሄደው በእንጨት ነው፡፡*

ሁለተኛው ጥቅሙ ደግሞ ለራሱ ለሟቹ መሆኑን አቶ ቦኒ ያብራራሉ፡፡ “የሚቀጠቀጡት ከብቶች ሁለት ዓይነት ጥቅም ላይ ይውላሉ፣ አንደኛው ሥጋቸው በቀብሩ እለት ከቅርብም ከሩቅም ለተሰባሰበው ቀባሪና ሀዘንተኛ ምግብ ሲሆን፣ ሌላኛው ጥቅሙ ደግሞ ሟቹ በቀጣይ ሕይወቱ ከብቶቹን እያረባ እንዲጠቀምባቸው በማሰብ ነው፡፡” (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር፣ 2010ዓ.ም፣ ጉራ ፈርዳ)

በብሔረሰቡ እምነት ሟች ተጓዥ ነው ተብሎ በመታመኑ፣ ለጉዞ ያስፈልጉታል ተብለው ከሚዘጋጁት ነገሮች ውስጥ አንዱ እና ዋንኛው ሟች ታምሞ እንደማይድንና እንደማይተርፍ ሲገመት ቤተሰቦቹ ወተት አዘጋጅተው ነፍሱ እስክትወጣ ድረስ ይጠብቃሉ፡፡ ይህ ታማሚ ነፍሱ መውጣቷ ሲረጋገጥ ዘመዶቹ በሟቹ አፍ ወተት በማንቆርቆር ወደ ሰውነቱ እንዲገባ ያደርጋሉ፡፡ ይህ የሚሆነውም ከዳግም ውልደት እሳቤያቸው ጋር የተገናኘ በመሆኑ ነው፡፡

> *ሰው እስትንፋሱ ስትጠፋ፣ ልጆቹ ወይም ወንድሞቹ ወይም ከዘመዶቹ ውስጥ ያሉ ሟቹን ወተት ይግቱታል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ትኩስ ወተት ይሆናል፡፡ ይሄ ወተት የተጓዡ ስንቅ ነው፡፡ ከዚያም ወተቱ እንዳይፈስስ ሟቹን ዘቅዝቀው ያስቀምጡታል፡፡ የሚዘቀዘቀው ወተቱ እንዳይፈስስ እና ስንቁ በመንገድ እንዳያልቅበት፣ ሰውዬው ወደ ሌላኛው መኖሪያ በሚጓዝበት ወቅት እንዳይጠማና እንዳይጎዳ በማሰብ ነው፡፡ አሁን አሁን በደጋው አካባቢ እየቀረ መጣ እንጅ ጥንት እና አሁንም በቆላው አካባቢ ሰውም የሚቀበረው፣ በከብት ቆዳ ተጠቅልሎና ቁጢጥ ተደርጎ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ በድሉ፣ ህዳር፣ 2010 ዓ.ም፣ ባቹማ)፡፡*

በብሔረሰቡ እምነት ከአሟሟት ጋር ተያይዞ የሚደረገው ሌላው ሥርዓት፣ ሰውዬው እንደሚሞት ከታመነ ከኖረበት ቤት በማስወጣትና አዲስ ጎጆ ሠርቶ በማቆየት እስኪሞት ድረስ መጠበቅ ነው፡፡ ሰውዬው ከሞተ በኋላ ደግሞ ከሞተበት ቤት ወደ ቀብር ሲወጣ ከቤት የሚወጣው አዲስ በር ተበጅቶለት ወይም ከቤቱ ግድግዳ በአንደኛው ወገን የመውጪያ በር ተዘጋጅቶ ነው፡፡ በጎማ ቀበሌ የሚኖሩትና በባሕል ሃይማኖት መሪነታቸው የሚታወቁት አወቀ ፎሮሽዋም ይሄንን እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡

*በኛ በመኤኒቶች ትልቅ ሰው ከታመመ እና እንደሚሞት ካመንን ከኖረበት ቤት አውጥተን አዲስ ጎጆ ሠርተን እዚያ እንዲያርፍ እናደርጋለን፡፡ ምክንያቱም ትልቅ ሰው ቶሎ ካልራቀ የእሱ መንፈስ በሌሎቹ ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ አይቀርም፡፡ በሕይወት እያለ በገባበት በርም አስከሬኑን አናስወጣም፡፡ ምክንያቱም የገባበት በር የቋሚዎች፣ የነዋሪዎች በር ነው፡፡ የእሱ መኖሪያ ከእንግዲህ አዲስ ዓለም ስለሆነ ወደዚያም የሚሄደው በአዲሱ በር ወጥቶ ነው፡፡ ይሁንና ሰውዬው በድንገት አዲስ ጎጆ ሳይዘጋጅ ከሞተም እኛ[11] እስከ ሦስት ወር ድረስ በዚያ ቤት ውስጥ አንገባም፡፡ ሟቹን የምንቀብረውም እዚያው ግቢው ውስጥ ነው፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር 2010ዓ.ም፣ ባቼማ)*

በብሔረሰቡ እምነት ሟች ከተቀበረ በኋላ በሕይወት ያሉት ሰዎች ሟቹ በተቀበረበት ቦታ ላይ ጎጆ ሠርተው ለሟቹ መንፈስ የሚያስፈልገውን ምግብና መጠጥ፣ እነሱ ከበሉትና ከጠጡት ውስጥ እያቃመሱ ሦስት ወራት ድረስ የመቆየት ሥርዓት አለ፡፡ ይሄንንም የሚያደርጉት ሟች በሚቀጥለው ጉዞው የተሳካ እንዲሆን እና አስከሬኑንም አውጥተው ከሚበሉ አካላት ለመከላከል ነው፡፡ ዋየች ጃሻ የዳሱን፣ የሚደፋውን ምግብና መጠጥ ምክንያቶች እንዲህ ያስረዳሉ፡፡

*"ሰው ከሞተ በኋላ ቀብሩ ላይ ጎጆ በመሥራት እስከ ሦስር ወራት አስከሬኑን እንጠብቃለን፡፡ የምንጠብቀው አስከሬን ቆፍረው ከሚያወጡና ቃምጹት[12] ከሚባሉት ነው፡፡ በእነዚህ ጊዚያት ውስጥ ደግሞ የሟቹ መንፈስ እንዳይቆጣ፣ በሕይወት ያሉ ዘመዶቹን ተመልሶ እንዳይረብሽና በሰላም ወደሚሄድበት እንዲደርስ ከሚበላው ምግብ እና ከሚጠጣው መጠጥ በቀብሩ ቦታ ላይ በማፍሰስ መንፈሱ እንዲመገብ ይደረጋል፡፡ ሟቹም በጉዞው ሁሉ ራብና ጥማት እንዳያስቸግረው፣ ረጅሙን የአዲስ ሕይወት ጉዞ አጠናቅቆ ቅድመ አያቶቹ፣ ዘረ ማንዘሮቹ ወዳሉበት እንዲደርስ ያግዘዋል፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር፣ 2010ዓ.ም፣ ባቼማ)*

ሌላው በብሔረሰቡ የጥንት ልማድ ሟች ባላባት ከሆነ ቋሚ ዘመዶቹ አካባቢውን ለቅቀው ወደ ሌላ አካባቢ በመኃዝ መሥፈራቸው ነው፡፡ "ጥንት ባላባት የሆነ

---

[11] *አወቀ ፎሮሽዋ በዱማ በመኤኒት ጎልዲያ እና አካባቢው የታወቁ ቃልቻ ናቸው፡፡ እኛ ያሉትም የባሕል ሃይማኖት መሪዎችን ለመግለጥ ነው፡፡*

[12] *በብሔረሰቡ እምነት አስከሬን አውጥተው የሚበሉ ፍጡራን እንዳሉ ይታመናል፡፡ እነዚህም ፍጡራን ቃምጹት ተብለው ይጠራሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች አስከሬን የማይጠበቅ ከሆነ ወደ ተቀበረበት በማምራት በድብቅ እና በጨለማ ወስደው ስለሚበሉት መኤኒቶች ለሦስት ወር ሙሉ በሟች መቃብር ላይ ትንሽ ዳስ ሠርተው ይጠብቃሉ፡፡ ከሦስት ወር በኋላ ግን ቃምጹቶች አስከሬኑን እንደማይፈልጉትና ሰውዬውም ወደ አዲሱ መኖሪያ ስፍራው መድረሱን አምነው ዳሱን ያፈርሳሉ፡፡ በላዩም ላይ ዋርካ፣ ወይም ሌላ ዓይነት ዛፍ ይተክላሉ፡፡*

ሰው ሲሞት ዘመዶቹ በጠቅላላ ሥፍራውን ለቅቀው በመሄድ ሌላ ቦታ ላይ አዲስ ቤት ሠርተው ይኖራሉ፡፡ ሰውዬው በተቀበረበት ቦታ ላይም ሦስት ወራት የቆየውን ዳስ ሲያፈርሱ በቀብሩ ላይ ዋርካ ይተክላሉ፡፡ ዋርካ መትከል ግን ዛሬም ድረስ አለ›› (አቶ አወቀ ፎሮሽዋ ህዳር፣ 2010ዓ.ም፣ ባቱማ)



ባላባት በሆኑ ሰው መቃብር ላይ የበቀለ ዋርካ፣ (ፎቶ በአጥኝው)፡፡

በመኤኒት ብሔረሰብ ከሞት በኋላ ያለው ሕይወት የሚቀጥለው በአንድ የተለየ ሥፍራ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ አንዳንድ የመረጃ አቀባዮች ቦታውን በትክክል እንደማያውቁትና በተለምዶ እና በቃል ትረካ ሲወርድ ሲተላለፍ የሰሙት ግን የሞተ ሰው ወደ ‹‹ቆላ›› እንደሚሄድ እና ቦታውም ‹‹ቆላ›› እንደሚባል ነው፡፡ ‹ቆላ›› ተብሎ በሚነገረው የሙታን  ወይም የመኤኒቶች የዳግም ሕይወት መኖሪያ  ውስጥ ሟቾች ልክ እንደዚህኛው ገሀዳዊ ዓለም በአካለ ሥጋ እንደሚኖሩበት ዓይነት ልዩ ልዩ ሥራዎችን እያከናወኑ እንደሚኖሩ ይታመናል፡፡

በጨበራ ቀበሌ ያገኘኋቸውና የዝንጀሮ ንጉሥ እንደሆኑ የሚታመኑት አቶ ሴላ ይሄንን ይገልፃሉ፡፡ ‹‹ሰው ከሞተ ወደ ታች ሄዷል፤ ወደ ቆላ ወርዷል፣ ማሽላ

ሊያርስ ሄዷል ብለን እናምናለን፡፡ የሞተ ሰው፣ ከሞተም በኋላ የሆነ ቦታ በእርሻ እንደሚኖር እናምናለን፡፡ ቦታው ቱማ ያዘጋጀልን ነው፡፡” (ሴላ፣ የካቲት 2011 ዓ.ም፣ ጨበራ) ወ/ሮ ጊብዝኒም ይሄንን ሀሳብ እንዲህ ያጠናክሩታል፡፡ “ሰው ከሞተ በኋላ፣ እዚያ ቱማ ያዘጋጀው ቦታ ይኖራል፡፡ ቆላ ይወርድና ከዚያ እያረሰ ይኖራል” (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011፣ ዓ.ም)፡፡

የግርሻ ጤና ቀበሌ ኗሪ የነበሩትንና አሁን በመኤኒት ጎልዲያ በባቼማ ከተማ በመንግሥት ሥራና ኃላፊነት ላይ ያሉት አቶ ሻልታ ታዬ ሰው ከሞተ በኋላ ቃልዋ ተብሎ ነፍሱ እዚሁ ምድር ላይ በተዘጋጀ ቦታ እንደምትኖር ይገልፃሉ፡፡

> *በመኤኒት ሰው ከሞተ በኋላ ይቀበራል፡፡ ነፍሱ ግን አለች ተብሎ ነው የሚታመነው፡፡ በመኤኒት እምነት ነፍስ ወደ ሰማይ ሄዷል ሳይሆን እዚሁ ምድር ውስጥ አለ ተብሎ ነው የሚታሰበው፡፡ ሰውየው ተቀይሮ “ቃልዋ” ወይም “ቃልዋት” ተብሎ ይጠራል፡፡ በዚህ መልክ የሆነ የተዘጋጀላቸው ቦታ ላይ ይኖራሉ፡፡ በምድር ላይ በሕይወት እንዳሉበት ሁኔታ ሆነው ይኖራሉ ተብሎ ነው የሚታመነው፡፡ ሰው ሲሞትም በክብት ቆዳ ተጠቅልሎ ነው የሚቀበረው፡፡ የዚህ ዋና ሀሳብ ሰውየው ይጠቀምበታል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 2011 ዓ.ም፣ በቹማ)*


በብሔረሰቡ እምነት ሟቾች ይኖሩበታል፣ በአካለ ሥጋ እንደነበሩት ሁሉ ቀጣይ ሕይወታቸውን ይገፉበታል ተብሎ የሚታሰብበት ቦታ “ሞኡ” እንደሚባል አቶ ቦኒ ይገልፃሉ፡፡ “የመኤኒት ብሔረሰብ ሰው ከሞተ በኋላ የሚሠበሰብበትና ቀጣይ ሕይወቱን የሚኖርበት ቦታ “ሞኡ” የሚባል ቦታ ነው” (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011፣ ሚዛን አማን)

መኤኒቶች የሞተን ሰው ፊት ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ አድርገው የመቅበር ልማድ ያላቸውም ከሞት በኋላ የሚቀጥለው ሕይወት ወዳለበት አካባቢ አቅጣጫ በማመላከት እንደሆነ ቦኒ ይናገራሉ፡፡ “ወደ በመኤኒት ጎልዲያና አካባቢው ያለ ሰው ሲሞት የሚቀበረው ፊቱን ወደ ምሥራቅ አድርጎ ነው፡፡ በሌሎችም አካባቢ ያሉ መኤኒቶች ሲቀበሩ ፊታቸውን ወደ ሞኡ እንዲሆን ተደርጎ ነው፡፡” (አቶ ቦኒ፣ ህዳር፣ 2008 ዓ.ም ባቼማ) የአቶ ቦኒን ሀሳብ በማጠናከር በመኤኒት ብሔረሰብ ሟች ሲቀበር ፊቱን ወደ ሞኡ እንዲያደርግ የሚገልፁት የባቼማ ከተማ የአካባቢው ታላቅ ሽማግሌ አቶ ሞሮችም ይገልጻሉ፡፡ ‹‹እኛ ስንቀበር

ፊቱን ወደ ምስራቅ አድርገን ነው፡፡ ወደ መሂጃው በኩል፤ እሱ ከዚያ በኋላ ቀጥታ ወደ ቆላው ይወርዳል” (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር፣ 2008 ዓ.ም ባቹማ)

ሞኡ የተባለውና የብሔረሰቡ አባላት ከሞት በኋላ ያለ ሕይወታቸውን የሚገፉበት እንደሆነ የሚታመንበት ሥፍራ የሚገኝበትን አቅጣጫ የሚገልፁት አቶ ብርሃኑ ሞኡ ጉራ ፈርዳ አካባቢ እንደሚገኝና በትክክል ግን ሥፍራውን አይተውት እንደማያውቁ ይገልፃሉ፡፡ “ምኡ አለ የሚባለው ወደ ጉራ ፈርዳ ወረዳ ነው፡፡ ከኛ ትንሽ ራቅ ይላል፡፡ ግን ከመኤኒት ሻሻ ወረዳ ቀጥሎ የሚገኝ ትልቅ ተራራ ነው” (አቶ ብርሃኑ፣ ህዳር ቀን 2010 ዓ.ም ባቹማ፡፡ የሞኡ መገኛ በጉራ ፈርዳ ውስጥ መሆኑን እና በደን የተከበበ ተራራማ ቦታ፣ ምስጢራዊነት ያለው፣ ፍጹም አስፈሪ እና ወደ ሥፍራው ለመጠጋት የሚያዳግት፣ እንደሆነ አቶ ቦኒ ያስረዳሉ፡ ፡

> *“ሞኡ ያለው፣ በጉራ ፈርዳ ወረዳ ውስጥ ነው፡፡ በርካታ የመኤኒት ብሔረሰብ አባላት ከዚህ ዓለም ተለይተው የሚኖሩበት ሥፍራ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመኤኒት ነባር እምነት ከሞት በኋላ ሕይወት የሚቀጥለው ሞኡ ነው፡፡ አምላክ ቱማ ሞኡን ቀድሞ እንዳዘጋጀው ይታመናል፡፡ አሁን በሕይወት ያለ ሰው እዚያ አካባቢ ቢደርስ ይጠፋል፡፡ የሚጠፋው ግን ቦታው ስለሚያሳስትና ምስጢራዊ ስለሆነ ነው፡፡ ቦታው ያዞራል፡፡ የሚያስፈራ ግርማ አለው፡፡ በደን የተከበበ ነው፡፡ የቡና ቅጠል በብዛት አለው፣ አንድ ሰው ከዚያ አካባቢ ቅጠል ከቆረጠና በእጁ ከያዘ፣ እዚያው ካልጣለ ወዴት እንደሚሄድ ሳያውቅ እዚያው ሲዟዟር ነው ውሎ የሚያድረው፡፡ (አቶ ቦኒ-፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ሚዛን አማን)*



የሞኡ ተራራ ከፊል ገጽታ፣ (ፎቶ በአቶ ቦኒ ሀየች)፡፡

የሞኡን አስፈሪነትና ባለ ግርማነት በመግለጥ የአቶ ቦኒን ሀሳብ የሚያጠናክሩት የጉራ ፈርዳ ኗሪውና ሞኡን በርቀት የሚያውቁት አቶ ሾልዋ ናቸው፡፡ "እዚያ አካባቢ ሄጄ አውቃለሁ ወደ ተራራው ግን አልቀረብኩም፡፡ በርቀት ነው ያየሁት፡ ፡ ቦታው ዝም ብሎ የሚሄድበት አይደለም፡፡ እነሱ፤ ሿቾቹ የሚኖሩበት ነው፡፡ ክብድ የሚልና የሚያስፈራ ቦታ ነው፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም ጉራ ፈርዳ)

በሞኡ አካባቢ ዳግም ሕይወታቸውን የሚኖሩት ሥውራን የአካባቢያቸው ተክሎች እንዲነኩባቸው አይፈልጉም፡፡ በድንገትና በአጋጣሚ በቅርብ ርቀት ከሚኖሩ አርሷደሮች ወደ ሥፍራው የቀረቡ ፍየሎች ፍለጋ ወይም በሌላ አጋጣሚ ወደ ሥፍራው የቀረበና እግር ጥሎት በቦታው የተገኘ ሰው ከአካባቢው ተክል መቁረጥ አይፈቀድለትም፡፡ በአጋጣሚም ከአካባቢው ቅጠል የቆረጠ ሰው የቀጠፈውን እዚያው ጥሎ መመለስ አለበት፡፡ ካልሆነ ግን እዚያው አካባቢ ሲሽከረከር ውሎ እንዲያድር የሚያደርግ ኃይል እንዳለ ይታመናል፡፡ በአንድ ወቅት በአካባቢው እግር ጥሎት ዛፍ ቆርጦ መንገድ የጀመረ ሰው ያጋጠመውን ሁኔታ ከአካባቢው ሰዎች መስማታችን አቶ ሾልዋ እግዲህ ይገልፁታል፡፡ "አንዴ የሆነ ሰው በዚያ ቦታ ገብቶ ሲዘዋወር ዛፍ ቆርጦ ጣለ፡፡ ከዚያ በቦታው የሚኖሩት ተቆጡ፡፡ ከዚያ ሰውየው ወደ ሠፈሩ ለመመለስ ሲፈልግ መንገዱም፣

አካባቢውም ግልብጥብጥ እያለበት መመለስ ሳይችል ቀርቶ እዚያው ውሎ አደረ ሲባል ሰምቻለሁ›› (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ጉራ ፈርዳ) ቦኒም በዚሁ በሞኡ ለድንገት ደራሽ ሰው፣ ስውራኑ ምክርም እንደሚሰጡ  እንዲህ ይገልፃሉ ‹‹በአካባቢው ተሰውረው ያሉ ሰዎች የሚዟዟረውን ሰውዬ ‹አንተ ሰው የበጠስከውን ቅጠል እዚሁ ጥለህ በሰላም ሂድ› ይሉታል፡፡ እናም ይሄ በሕይወት ያለ ሰው የቀጠፈውን ትቶ ይሄዳል፡፡›› (ቃለ መጠይቅ፣ ህዳር፣ 2010ዓ.ም፣ ጉራ ፈርዳ)

> *የመኤኒት ብሔረሰብ በተለያዩ ወረዳዎች እንደመገኘቱ ሟቾች ወደ ሞኡ የሚያደርጉት ጉዞ ድካም ያለበትና ረጅም እንደሚሆንባቸው ይታመናል፡፡ የመኤኒት ጎልድያ ወረዳ የባቹማ ከተማ ኗሪው አቶ ብርሃኑ በዚህ ሀሳብ ላይ ከዚህ በታች ያለውን ይናገራሉ፡፡ ‹‹አንድ ሰው ሞቷል ብለን ልንቀብር ተዘጋጅተን፣ ከብቶች ለሟቹ ከቀጠቀጥን እና ካለቀስን በኋላ ቢነቃ ወይም ከሞት ቢመለስ መንገዱ ርቆበት፣ እሾህና ጋሬጣውን ማለፍ አቅቶት፣ ስንቁን በደንብ ሳንሰጠው ቀርቶ ተመለሰ ይባላል፡፡ (አቶ ብርሃኑ፣ ህዳር 12 ቀን 2008 ዓ.ም ባቹማ)*

በመኤኒት ብሔረሰብ እምነት አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ያለው ሕይወት የሚቀጥለው በዚሁ በምድር ላይ ለብሔረሰቡ አባላት ብቻ ተለይቶ እንደተዘጋጀላቸው በሚታመነውና ሞኡ በተባለ ቦታ ነው፡፡ የዚህን ቦታ ትክክለኛነት እና የሙታኖቹንም መኖር እንዳረጋገጡ የሚናገሩት በ70ኛ ዓመታቸው አካባቢ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው በአካለ ነፍስ እዚያው ሞኡ ደርሰው እንደተመለሱ አቶ ማዮኒ  ይናገራሉ፡፡ አቶ ማዮኒ በጉራፈርዳ ወረዳ፣ በኩቱ 03 ቀበሌ፣ በባለዱና መንደር ኗሪ ሲሆኑ፣ ከሞት በኋላ ያለውን ሕይወት አይተው እንደመጡ እንዲህ ይገልጻሉ፡ ‹‹እኔ ሞቼ ነበር፡፡ ከሞትኩ በኋላ ወደዛ ሥፍራ አያት ቅድመ አያቶቻችን ወዳሉበት ቦታ ሄጄ ነው የመጣሁት፡፡ ሞቼ ቆይቼ በኋላ ተመልሼ ነው የመጣሁት፡፡›› (አቶ ማዩኒ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ጉራ ፈርዳ)



አቶ ማዮኒ ግንቦት 2011ዓ.ም፣ (ፎቶ በአቶ ቦኒ ሀየች)፡፡

**አቶ ማይኒ ሞተው እንደተነሱ በአካባቢያቸው ባሉ ሰዎችም ይታመናል፡፡ የአካባቢው ሰዎች የሰውዬውን አሟሟትና ከሞት በኋላ ተመልሰው መምጣታቸውን በየራሳቸው ስሜት ይገልፃሉ፡፡ አቶ ቦኒ አቶ ማዮኒ ከተነሱ በኋላ ለበርካታ ጊዜ በቅርበት የሚያውቋቸው ናቸው፡፡ የአካባቢው ሰው ማዮኒን የሚመለከትበትንም፣ የሚጠራበትንም መንገድ እንዲህ ያስረዳሉ፡፡**

> *አቶ ማዮኒ የተባለ ትልቅ ሰው ሞቶ የተነሳ ነው፡፡ አቶ ማዮኒ አሁን በሕይወት አለ፡፡ ከሞተ በኋላ እዚያ ሞኡ አካባቢ ሄዷል፡፡ ሰውየው በአካባቢው ሰው በጣም ልዩ ሆኖ ነው የሚታየው፡፡ ሞቶ የተነሳ ወይም ከሙታን የተመለሰ ተብሎ ነው የሚጠራው፡፡ ሰውየው ሞቶ ከተነሳ በኋላ አምስት ዓመት አካባቢ ሆኗል፡፡ አሁን እየደከመው ነው (አቶ ቦኒ፣ ግንቦት 2011፣ ጉራ ፈርዳ)፡፡*



መረጃ ሰጪ አቶ ቦኒ ሀየች፡፡

የአቶ ማዩኒን ሞቶ መነሳትና ከሞት በኋላ በሞኡ ያለውን ሕይወት ዓይተው እንደመጡ ከሚያምኑት ውስጥ የአካባቢውና በሞቱ ጊዜ በቦታው እንደነበሩ የሚናገሩት አቶ ሾልዋ ናቸው፡፡ ሁኔታውን እንዲህ ያስረዱታል፡፡ “ማዮኒ ሞተ፡፡ እኛም ዘመዶቹም ሁሉ ልንቀብረው ተሰባስበን አለቀስን፡፡ ሳጥን አዘጋጀንለት፡፡ አልቅሰን ውለን አደርን፡፡ ዘመዶቹ ከያሉበት ተሰባሰቡ፡፡ በኋላ ግን የሞተው ሰውዬ ከሞት ነቃ፡፡ ዓይኑን ገለጠነ ተነፈሰ፡፡” (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም ጉራ ፈርዳ) የአቶ ማዮኒ ለቀብር ተዘጋጅቶ ወደ ሕይወት መመለስ በአካባቢው በነበሩት ሰዎች ላይ የፈጠረውን አመለካከት ተቃርኖ እንዳለው ከወ/ሮ ጊብዚኒ ንግግር መረዳት ይቻላል፡፡ “አንዳንዶች ሞት የጠላው ነው ይላሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ቱማ እድሜ የጨመረለትና የወደፊት ኑሮውን ያየ የታደለ ሰው ነው ይላሉ፡፡ እኔም ሞቶ እንደገና በመኖሩ እድለኛ ነው እላለሁ፡፡” (ቃለ መጠይቅ፣ ቀን 2011ዓ.ም ጉራ ፈርዳ)

በብሔረሰቡ ዘንድ ከሞት በኋላ ያለው ዳግም ሕይወት የሚቀጥለው ሞኡ በተባለው፣ አምላክ ቱማ ባዘጋጀው ቦታ መሆኑን፣ እንዲሁም ሟቾች በዚያ ሥፍራ በትክክል እየኖሩ ለመሆናቸው ምስክርነታቸውን የሚሰጡት አቶ ማዮኒ ከዚህ ዓለም በሞት ተሸኝተው ዳግም ውልደታቸውንና ዳግም ሕይወታቸውን በቀጠሉበት ጊዜ በሞኡ ካገኟቸው ውስጥ ከጓደኞቻቸው እና ከዘመዶቻቸው በተጨማሪ  አንዷ ወላጅ እናታቸው እንደሆኑና ከሳቸው በፊትም የሞቱ ወንድሞቻቸውን ማግኘታቸውን ይገልፃሉ፡፡ ‹‹እዚያ የሄድኩ ጊዜ እዚህ የነበሩ ሁለት ወንድሞቼን አግኝቻለሁ፡፡ ቀድመው የሞቱ ጓደኞቼም ነበሩ፡፡ በኋላ እናቴን አገኘኋት፡፡ እዚህ እንደነበረችው ሆና ነው ያገኘኋት፡፡ በአካባቢው በርካታ ሰው አለ፡፡ በዚህ ዓለም ስላሉት ዘመዶቻቸው ሲጠይቁኝ ቆዩ፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት፣ 2011 ዓ.ም፣ ጉራ ፈርዳ)

አቶ ማዮኒ በዳግም የሕይወት መንደር በሞኡ ተገኝተው እናታቸውን ዓይተውና አግኝተው መመለሳቸውን ሲያወሩ መስማታቸውን ጓደኛቸው አቶ ሾልዋ ይናገራሉ፡፡ "ማዮኒ ከሞት ከተነሳ በኋላ ጠይቄው እናቱን እና ሌሎች የሚያውቃቸውን ሰዎች ማግኘቱን ነግሮኛል፡፡ ሁሉም እዚህ እንዳለው ዓይነት ሥራ ይሠራሉ ብሎኛል" (አቶ ሾልዋ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም ጉራ ፍርዳ)

የአቶ ሾልዋን ዓይነት ምሥክርነት በወቅቱ ከባላቸው ሰምተው እንደነበር የሚናገሩት የአካባቢው ኗሪ ወ/ሮ ጊብዝኒ ናቸው፡፡ "አቶ ማዮኒ የሞተ ጊዜ እናቱን አግኝቷት እንደመጣ የኔ ባል ሲያወራ ሰምቻለሁ፡፡ ብቻ የሞቱትን ሰዎች ሁሉ አግኝቷቸው ነው የተመለሰው" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011ዓ.ም ጉራ ፈርዳ)

ከዛሬ አምስት ዓመት በፊት ሞተው ሊቀበሩ ሲሉ ከሞት እንደነቁ የሚናገሩት አቶ ማዮኒ የብሔረሰቡ አባላት ከሞት በኋላ የዳግም ሕይወት መንደር እንደሆነ የሚያምኑበትና  ለአንድ ቀን ውለው ያደሩበትን ሞኡ የተሰኘ ሥፍራ ምን እንደሚመስል እንዲህ ይገልፁታል፡፡

> *አካባቢው እንደዚህ እንደምንኖርበት ዓይነት ነው የሚመስለው፡፡ አኗኗር ያው እንደዚሁ ነው፡፡ ምንም ልዩነት የለውም፡፡ የሚያርስ ያርሳል የሚሠራ ሥራውን ይሠራል፡፡ ቀን ቀን ሁሉም ሰው ከዚህ ዓለም እንደሚሠራው ሥራውን*

*ይሠራል፡፡ ማታ ላይ ግን ሁሉም ሰው የለበሰው ሥጋ በአንዴ ከላዩ ላይ እርግፍ ብሎ አጥንት ብቻ ይሆናል፡፡ የሚያድረው አጥንቱ ብቻ ነው፡፡ (አቶ ማዩኒ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም፣ ጉራ ፈርዳ)*

የአቶ ማዮኒን ገለፃ ቀደም ብለው ከራሳቸው አንደበት ሰምተው እንደሚያውቁ እና ማዮኒ ከሞት ከተነሱ በኋላ በተደጋጋሚ ለሚነበኛቸው ሰው ስለ ሰውየው ሞቶ መነሳት መረጃ የሚሰጡት አቶ ቦኒ ማዮኒ ከነገሯቸው ውስጥ የሚገርማቸውን በሚከተለው መልክ ይናገራሉ፡፡ "ከማዮኒ የገረመኝ ሞኡ ያሉት ሰዎች ማታ ሲተኙ ሥጋቸው ይፈርሳል ብሎ የነገረኝን ነው፡፡ ቀን ቀን ሰው ሆነውና ሥጋ ለብሰው ውለው ማታ አጥንት ሆነው ይተኛሉ ብሎኛል፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011ዓ.ም ጉራ ፈራዳ) የአቶ ማዮኒን ሞኡ ደርሶ መምጣት ከሚያምኑት ሰዎች ውስጥ አቶ ሾልዋ ማዮኒ ከሞት የተመለሱ ጊዜ በግቢ ውስጥ የሆነውን እንዲህ ይገልጡታል፡፡

*የሚቀበርበት ሳጥን ተገዝቶ መጥቷል፡፡ እሱ የሞተው ከአንድ ቀን በፊት በመሆኑ አስከሬኑ በጨርቅ ተጠቅልሏል፡ ፡ በኋላ የሆነ ድምጽ አሰማ፡፡ የመታፈን ዓይነት ድምጽ ነበር፡፡ ቀጥሎ ንቅናቄ ነገር አሳየና በቅርበት የነበሩ ሰዎች ተጯጯሁ፡፡ እኛ ወንዶቹ ቀረብነው፡፡ በደንብ ሲንቃነቅ አየነው፡፡ ሮጬ ጨርቁን ቀዳድጄ የታሰረባቸውን ገመዶች ፈታታሁ፡፡ ቆይቶ በደንብ ተነፈሰ፡፡ ከዚያ ዓይኖቹ ተገለጡ፡፡ ቀስ እያለ ማየት ቻለ፡፡ ያኔ ሁላችንም ተደናገጥን፡፡ እኔም እንደዚህ ዓይነት አጋጥሞኝ አያውቅም እና ትንፋሽ ነው ያጠረኝ፡፡ ተጋግዘን ወደ ቤት አስገብተን ድንክ ላይ አስተኛነው፡፡ (አቶ ሾልዋ፣ 2011ዓ.ም ግንቦት፣ ጉራ ፈርዳ)*

አቶ ማዮኒ ከሞት የመነሳታቸው ምስጢር የምግብ ስህተት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ በዚህኛው ዓለም እና ከሞት በኋላ በሚቀጥለው የሞኡ ዓለም መካከል የምግብና የመጠጦች ልዩነት ባይኖርም ከሞት በኋላ ወደ ሥፍራው ለሚመጣው እንግዳ መኤኒት ግን የሚቀርብለት ምግብ የማሽላ ገንፎ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የማዮኒ እናት ይሄንን ስተው ለልጃቸው የበቆሎ ገንፎ በመስጠታቸው ማዮኒ ወደዚህኛው ዓለም እዲመለሱ ምክንያት ሆኗል፡፡

*ለእኔ ምግብ የሰጡኝ በሁለተኛው ቀን ጧት ነበር፡፡ እናቴ ናት ያቀረበችልኝ፡፡ መስጠት የነበረባት ምግብ የማሽላ ገንፎ ነበር፡፡ ግን እናቴ በምን ምክንያት እንደተሳሳተች*

*አላውቅም ያቀረበችልኝ የበቆሎ ገንፎ ሆነ፡፡ ያንን ምግብ እየበላሁ እንዳለ ከፍተኛ ጩኸት ተሰማ እኔም ጆሮዎቼን ሸፈንኩ፡፡ መሬቱን የሆነ ነገር አንቀጠቀጠው፡፡ ምግቡም ተንቀጠቀጠ አንድ የሚያስፈራ ጥቁር ሰው መጥቶ 'ይሄንን ምግብ መስጠት አልነበረባችሁም' ሲል ጮኸ፡፡ ሲጮህ አካባቢው ተናወጠ፡፡ ከዚያ በኋላ እኔ እዚህ መጣሁ፡፡ እንዴት እንደመጣሁም የማውቀው ነገር የለም (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም ጉራ ፈርዳ)፡፡*

ስለ ሞኡ ተራራ እና በውስጡ አለ ስለሚባለው የመኤኒቶች ከሞት በኋላ የሚወጥለው ሕይወት ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ በሞኡ ያለው ከሞት በኋላ የሚቀጥለው ሌላ ሕይወት የዚህኛው ዓለም ነጸብራቅ ወይም ግልባጭ እንደሆነም ይታመናል፡፡ መኤኒቶች በዚህ ምድር የሚያከናውኗቸው ማንኛውም ዓይነት የሕይወት መስተጋብር በዚያኛውም በሚቀጠጥለው ሕይወት ውስጥ የሚተገበሩ ናቸው፡፡ በአንዳንድ አጋጣሚ እና በሞት ጥሪ ወደ ስፍራው ደርሰው እንደመጡ እና በዚያ ያለውን ሕይወት እንዳዩ ከሚተርኩት ውስጥም መረዳት የሚቻለው ይሔንኑ ነው፤ የሁለቱ ዓለማት አኗኗርን ተመሳሳይነት፡፡ እድሚያቸው ሰባን ያጋመሰው የጉራ ፈርዳ ኗሪው አቶ ቡሻይ ባሩኝ ስለ ሞኡ የሚነገሩ ብዙ ሚታዊ ትረካዎችን እንደሰሙ ይናገራሉ፡፡ በተለይም እሳቸው ወላጅ አባታቸው ልጅ እያሉ ተፈጸመ ስለተባለው ሚታዊ ተረክ አባታቸው ሲጫወቱ የሰሙትን የረጅም ጊዜ ትረካ ቡሻይ እንደሚከተለው ይተርኩታል፡፡

*የቆየ ነገር ነው፡፡ በጣም የቆየ ነው፡፡ እንኳን እኔ አባቴ እራሱ ልጅ ነው የሚሆነው ያኔ፡፡ ግን እሱም ሲወራ የሰማውን ነው ሲያወራ የሰማሁት፡፡ እንግዲህ የኛ ታሪክ የሚታወቀው እንዲህ ነው፡፡ ነገር በነገር ነው፡፡ ከየት እንደ መጣን ምን ምን እንዳጋጠመን የምናውቀው በአፍ ነው፡፡ በመንገር ነው፡፡ እኔም የምናገረው የድሮ ነገር ነው፡፡ ያ ቦታ የተከበረ ነው፡፡ ብዙ እኛ የማናያቸው እና የማናውቃቸው የኛ የሆኑ ሰዎች አሉበት፡፡ ሁሉም ሰው አለበት፡፡ ቱማሂ እዚህ አኑሮህ ስትሄድ እዚያ ይጠብቀሀል፡፡ እንዲያውም ከዚህ የተሻለ የሚታረስበት፣ የሚመረትበት ነው፡፡ ሞኡ እኮ እንዲሁ እንኳን ሲታይ ውስጡ ብዙ ነገር እንዳለው ያስታውቃል፡፡*

*ከአባቴ የሰማሁት የድሮ ነገር ባልና ሚስት የሆኑ ሰዎች መንገድ ሲጓዙ ቆይተው በመጨረሻ ወደ ሞኡ አካባቢ ይደርሳሉ፡፡ ያኔ ደክሟቸው አረፍ ይላሉ፡፡ ከዚያ ሴትየዋ ለጉዳዋ ዘወር ትላለች፡፡ ያኔ ባልም ጥላ ፈልጎ ይቀመጣል፡፡ ነገር ግን ያቺ ዘወር ያለች ሴት እሷ የመሰሉ ሴቶች ታይና*

*እየተጣራች ትከተላቸዋለች፡፡ እሷ በዚህ በሷ አኳኋን ያሉ መሰሏት ነበር፡፡ እነሱ ሌሎች የዚያ የሞኡ ኗሪዎች ናቸው፡ ፡ ስትጣራ ስለማይሰሟት በሂዱበት ትከተላቸዋለች፡፡ ጥቂት ሂዳ ልትደርስባቸው ስትል ጥፍት ይሉባታል፡፡ እሷም ግራ ተጋብታ ጥቅጥቅ ያለው ዛፍ ውስጥ እንደገባች መውጫ አጥታ ስትባትል ትውላለች፡፡ በመጨረሻ ወደ አንድ ቦታ ሽርተት ብላ ስትሂድ ብዙ ሰው እንደገቢያ ያለ ሆኖ ታገኛለች፡፡ የምታያቸው እሷ ነች እነሱ አያይዋትም፡፡ ሴትየዋ በዚያው ጠፋች፡፡ ባልየው ደግሞ ሚስቱን ሲገፈልግ ሲፈልግ ቆይቶ ሲያጣት አውሬ በልቷት ነው ብሎ የማታ የማታ ከስፍራው ርቆ ወደ መንደር ይጠጋና የሆነውን ለሰዎች ይነግራል፡፡ እንግዲህ ሰዎቹ የአካባቢውን ጠባይ ያውቁ ኖሮ እሱ ልዩ ልዩ ጥያቄ ይጠይቁታል፡፡ የቡና ቅጠል ከአካባቢው ቀጥፎ እንደሆን ይጠይቁታል፣ ሌላም ነገር ይጠይቁታል፡፡ ሰውዬውም ምንም ቅጠል አለመቅጠፉን ይናገራል፡፡ ቆይቶ ቦታው መኤኒቶች ያሉበት ከሞቱ በኋላ የሚመጡበት እንደሆነ ይነግሩታል፡፡ ሴትየዋም ስላልሞተች፣ አስከሬኗንም ስላላገኘ ልትመጣ እንደምትችል ትልልቆቹ ሽማግሌዎች ይነግሩታል፡፡ ከዚያ ሰውዬው ጥቂት ይጠብቃል፡፡ በኋላ መንገደኛው ሚስቱ እንደማትመጣ ስላመነ እርሙን አውጥቶ እንደሞተች ቆጥሮ ወደ መንገዱ ይሂዳል፡፡*

*ይህ በሆነ በጥቂት ጊዜ ያቺ ሴት ከተሰወረችበት ትወጣለች፡ ፡ በአካባቢው ያሉ ልጆች ጉዳዩን ስለሰሙና የሴትየዋን መጥፋት ስለሚያውቁ እንዳይዋት እሷነቷን በመለየት መጥተው ለሽማግሌዎቹ ይነግራሉ፡፡ ሰዎችም ወደ እሷ በደረሱ ጊዜ የሰውዬው ሚስት እንደሆነች ይታወቃል፡፡ እሷም ከባሏ ጋር ወደ ስፍራው መምጣቷን እና መጠፋፋታቸውን ትናገራለች፡፡ በመጨረሻ ባሏ ጠብቋት መሂዱን ትሰማለች፡፡ እና ያቺ ሴት ከዚያ በኋላ ምን እንዳየች ስትጠየቅ ብዙ ሰው የሚኖርበት አካባቢ እንደሆነ እና በዚያ ያለው ነገር በሙሉ እዚህ አካባቢ የሚደረገው መሆኑን ትናገራለች፡፡ ጨሞ አፍልተው እንደሚጠጡ፣ የእርሻም ሥራ እንደሚሰሩ፣ ሌላም ነገር እንደሚደርጉ ትናገራለች፡፡ እዚህ ስንኖር የምናደርገው ነገር ሁሉ እዚያ አንዳለ ትናገራለች፡፡ መብል መጠጡም አንድ ዓይነት ነው፡፡ በመጨረሻ ያቺ ሴት ባሏ ጥሏት ስለሂደ ከዚያ አካባቢ አልሂድም ብላ እዚያው አንዱን አግብታ መኖሯን አባቴ ሲያወራ ሰምቻለሁ፡፡ እንዲያውም ያጎደልኩት ነገር ይኖራል እንጂ ብዙ ነገር ነበር የነገረኝ፡፡ ተዘነጋኝ፡፡ ግን ቦታው ዋንኛ ቦታ ነው፡፡ እኛም የምንሂደው እዚያ ነው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም ጉራ ፈርዳ)፡፡*



አቶ ቡሻይ ባሩኝ፣ (ፎቶ በአጥኚው)

ስለ ሞኡ ታላቅነት፣ ምስጢራዊነት መሰብሰቢያነት ከመኤኒቶች ታሪክ፣ የአቀባበር ሥርዓት ጋር አያይዘው አቶ ጌልቶ ካማና ናቸው፡፡ ጌልቶ በሞኡ ዳግም ሕይወታቸውን እየኖሩ ያሉ ሰዎች በዚህኛው ዓለም ካሉ ሰዎች ጋራ አልፎ አልፎ በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደሚገናኙ ይተርካሉ፡፡

> *መቼም እኛ የምናምነው አምላክ የፈጠራቸውን ሰዎች የትም እንደማይጥል ነው፡፡ የእኛ ታሪክ ሩቅ ነው፡፡ ከሩቅ ቦታ ነው የመጣነው፡፡ ስንመጣ በያለበት ተበታትነናል፡፡ አንዱ ከወንዝ ወዲያ አንዱ ከወንዝ ወዲህ፣ አንዱ በዚያ አንዱ በዚህ እንዲያ እያለ ነው የቀረው፡፡ ሁሉም ግን ወደዚህ ቦታ ይሰበሰባል፡፡ ቱማ የተበተነውን የሚሰበስብበት ቦታ ነው፡፡ ለዚህ ምልክቱ ደግሞ ሁሉም መኤኒት ሲቀበር ፊቱን ወዲህ አድርጎ ነው የሚቀበረው፡፡ ወዲህ ሲመጣ ብድግ ብሎ ያለስህተት እንዲመጣ ነው፡፡  ያ ባይሆን አቀባበሩ ይለያይ ነበር፡፡ እኛ የሞተን ሰው እንኳን በሕይወት እያለ በገባበት በር አናስወጣም፡፡ በሕይወት ያሉ ሰዎች በሚገቡ በሚወጡበት በር አናስወጣም፡፡ ያኛው ዓለም ሌላ ነው፣ ይሂኛው ዓለም ሌላ ነው፡፡ ሁሉም መኤኒት ጋር እንዲሁ ነው፡፡ ከጥንት ጀምሮ በያለበት ሲበተን የነበረው ሰው አሁን እዚህ አንድ ላይ ይሆናል፡፡ ለዚህም ነው ይሂ ቦታ ያለው፡፡ ይሂ ቦታ እኮ እንደሚታየው አይደለም፡፡ ሌላ የማይታይ ነገር አለው፡፡ ስፋቱ፣ ርዝመቱ፣ ጥልቀቱን ሰው አይለካውም፡፡ ቱማ ነው ያዘጋጀው፡፡ ብዙ ስውር ሰዎች እኮ አልፎ አልፎ ብቅ እያሉ በዚህ ካለነው ሰዎች ጋር ይገናኛሉ፡፡ አንዳንዴም አካባቢያቸው ሲረበሽ ተው ለማለት ብቅ ይላሉ፡፡ ሌላ ጉዳይ ሲኖራቸው ብቅ*

*ይላሉ፡፡ ያይዋቸው አሉ፡፡ ያወሯቸው አሉ፡፡ እዚያው ቦታ ሄደው እንደመጡም የሚናገሩ አሉ፡፡ ቦታው ብዙ ነገር ያለበት ቦታ ነው፡፡ ሚስጥሩ ብዙ ነው፡፡ እንዲሁ ሲታይ እኮ ያስታውቃል፡፡ ነው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 2011 ዓ.ም ጉራ ፈርዳ)፡፡* ግንቦት 2011 ዓ.ም

አቶ ጌልቶ ካማና ስለሞኡ ብቻ ሳይሆን ሞኡ ደርሰው እንደመጡ ከተነገረላቸው ውስጥ በእሳቸው ዘመን አንድ ሰው ሊቀበር ሲሰናዳ፣ ዘመዶቹ እስኪሰበሰቡ ወደ ስፍራው ሄዶ የጥንት ዘመዶቹን እና ወገኖቹን አግኝቶ እንደተመለሰ መወራቱን መስማታቸውን ጨምረው ገልጸዋል፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

## 8. የመኤኒት ሚቶች ማኅበረሰባዊ ፋይዳ

በዚህ ምዕራፍ የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶች የሚሰጧቸው ልዩ ልዩ ፋዳዎች ይገኛሉ፡፡ የመግለጥ ፋይዳ፣ የማጠናከር እና የመትከል ፋይዳ፣ የማምለጥ ፋይዳ፣ የማስተማር ፋይዳ እንዲሁም የመግታትና የመቆጣጠር ፋይዳ በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 8.1 የመግለጥ ፋይዳ

ሚት ለአንድ ማኅበረሰብ ከሚሰጣቸው ዋና ዋና ፋይዳዎች ውስጥ አንዱ፣ እንቆቅልሽ የሆኑ እና የሰው ልጅ አዕምሮ ሊደርስባቸው ለማይችላቸው የሰርክ ጥያቄዎች መልስ የመስጠት እና የመግለጥ ተግባር ነው፡፡ በአጠቃላይ በሕይወት መስተጋብር ወስጥ ሥርዓተ ዓለሙ እንዴት እንደሆነ፣ ምን እንደሆነና መቼ እንደሆነ የመግለጥ ሚናው ከፍ ያለ ነው፡፡ በዚህም የመግለጥ ተግባሩና ፋይዳው ለአማኙ ምስቅልቅሉን ሕይወት፣ በሰርክ ጥያቄ የሚባትለውን አዕምሮ ያሳርፋል፡ ፡ የመኤኒት ብሔረሰብ ሚትም ከዚህ በታች ያሉትን አንኳር የሰው ልጅ ዘለዓለማዊ ጥያቄዎች በመግለጥ ለአማኙና ባለቤት ለሆነው ሕዝብ ትልቅ ፋይዳን አበርክቷል፡፡

### የዓለምንና የሰውን አፈጣጠር የመግለጥ ፋይዳ (ምስቅልቅሉን ዓለም ሥርዓት የማስያዝ ፋይዳ

የሰው ልጅ ዘወትራዊ ጥያቄዎቹ ከሆኑት ውስጥ አንደኛው የሚኖርበትን ዓለም፣ ሰማዩን እና ምድሩን፣ ባሕሩን እና ተራራውን፣ ዕፅዋቱን እና እንስሳቱን ነፍሳቱን እና ታላላቅ ፍጥረታትን፣ የሚታየውን እና የማይታየውን ማን ፈጠረው? የሚለው ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ ቦታ የሚገድበው ጊዜ የሚወስነው ጥያቄ አይደለም፡፡ የሰው ልጅ ሁሉ ባለበት ቦታና ጊዜ የሚጠይቀው ዘመን ተሻጋሪ ጥያቄ ነው፡፡ ይሁን እንጅ እንዲህ ዓይነቱን ዘላለማዊ ጥያቄ በመጠየቅ እረፍት እና እንቅልፍ የሚያጣው የሰው ልጅን የሚያሳርፈው ከማንነቱ ጋር አስተሳስሮ የሚሰጣቸው የራሱ መልስ ነው፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ የአፈጣጠር ሚት እንዲህ ዓይነቱን ዘለዓለማዊ ጥያቄ በመመለስ ማኅበረሰቡን

ከጥያቄው ያሳርፋዋል፡፡ መልስ በመስጠት ልቡናውን ያረጋጋዋል፡፡ የመኤኒትን ሰማይና ምድርም ይሁን ይሄንን ዓለም የሠራው አምላክ ቱማ መሆኑን ሚቱ ይገልጣል፡፡ በመሆኑም ይሄንን ዓለም ማነው የፈጠረው፣ ተራራና ኮረብታው፣ ጋራና ሸንተረሩ፣ ወንዝና ጅረቱ እንዴት ሕልው እንደሆኑ በመጠየቅ ጊዜውን አያባክንም፡፡ አምላክ ቱማ ይሄንን ሁሉ በማድረጉ ዘመንና ጊዜ እየተፈራረቁ፣ ትውልድ እየተተካካ ቢሄድ የአፈጣጠር ሚቱ ይሄንን በመመለስና በመግለጥ ለማኅበረሰቡ ፋይዳው የጎላ ነው፡፡

በብዙ የአፈጣጠር ሚቶች ትረካ እንደሚታየው በመኤኒትም ተመሳሳይ ገጽታ አለው፡፡ የአይሁድና የክርስትና እምነቶች ይሄንን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣው እግኢ.አብሔር ነው ብለው እንደሚገልጹት ሁሉ፣ በዓለም ላይ ያሉ ሙስሊሞች አላህ ይሄንን ዓለም አስገኝቷል ብለው እንደሚቀበሉት ሁሉ፤ የሲዳማ ብሔረሰብ አባላት ዓለምን የፈጠረው እምላክ ማጋኖ ነው ብለው እንደሚያምኑት ሁሉ ለመኤኒቶችም ይሄንን ዓለም የፈጠረው አምላክ ቱማ ነው፡ ፡ ይሄንንም የገለጠላቸው የብሔረሰቡ የአፈጣጠር ሚት በመሆኑ የሚቱ ፋይዳ ከፍተኛ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

## በፈጣሪያቸውና በእነሱ መካካል ስላለው ግንኙነት የመግለጥ ፋይዳ

የሰው ልጅ ይሄንን ዓለም እና ራሱን ያስገኘውን ካወቀ በኋላ በእሱ እና በአምላኩ መካከል ያለውን ግንኙነት መልክ ማወቅና አንድ ዓይነት ሥርዓት ማበጀት ይፈልጋል፡፡ የይሁዳውያን፣ የክርስትና እና የእስልምና የሃይማኖት ሚቶች አምላክ፣ ለአብርሃም/ ኢብራሂም በካራን ማንነቱን እንደገለጠት ያስረዳሉ፡፡ ለሙሴም በቁጥቋጦ የተገለጠለት አምላኩ ሕግና ትዕዛዛትን ሰጥቶ ወደ ሕዝቡ እንደላከው ይገልጻሉ፡፡ የመኤኒቶችም አምላክ ቱማ ናያሞን ከወለዳቸው ሦስት ወንድ ልጆች ጋር ፊት ተገናኝቷል፡፡ እነሱም ሕዝቡን የሚያስተዳድሩበትን ኃይል እና ጥበብ እንዲሰጣቸው ጠይቀውታል፡፡ ከዚህ ትረካ የምንረዳው አምላክ ቱማ ከሰው ጋር ቃል በቃል ያወራና ይገናኝ የነበረ ቅርብ አምላክ በመሆኑን ነው፡፡ አምላክ ቱማ የናያሞን ወንድ ልጆች ጥያቄ መልሷነው፡፡ የመጀመሪያ ለሆነው ልጅ ለባንጃ የዝናብ ማውረድን ኃይል[13]፣ ለሁለተኛው ልጅ ቦሹ

---

[13] *አዳምን በገነት ውስጥ ያሉትን ሁሉ እንዲያዝዝ፣ እንዲገዛ፣ እንዲሰለጥንባቸው ሥልጣን እንደሰጠው ማለት ነው፡፡*

እንስሳት እዲታዘዙትና እንዲገዙለት የማድረግ ኃይልን፣ ለሦስተኛው ልጅ በዕፅዋት ላይ እንዲያዝዝ እና እንዲሰለጥን ኃይልና ሥልጣንን አድሏል፡፡ ይሄም መኤኒቶች አምላካቸው ቅርብ፣ የለመኑትን የማይነሳና የሚሰጥ፣ ሁሉን ማድረግ የሚችል መሆኑን ያስረዳል፡፡

በሌላ ጎኑ አምላክ ቱማ መኤኒቶች በሠሩት ክፉ ሥራ ከእነሱ መራቁን፣ ለረሀብ እና ለስደትም መዳረጋቸውን የብሔረሰቡ የሃይማኖት ሚቱ ይተርካል፡፡ በእነሱ እና በፈጣሪ መካከል ያለው ግንኙነት መሻከሩን ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ አምላክ ቱማ የፈጠራቸውን ሰዎች ፈጽሞ እንዳልጣላቸው እና እንዳልራቃቸውም ከሚቶቹ እንረዳለን፡፡ ሰው እየበደለ ፈጣሪ ይቅር እያለ መኖሩ በብዙዎች የሃይማኖት ሚት ትረካ ውስጥም የሚንጸባረቅ ነው፡፡ አምላክ ቱማም ከመኤኒቶች ሳይርቅ አስታራቂ እና ጠባቂ እንዲሆኑ ለመኤኒቶች ኮሞሮቶችንና ኘራዮችን እንደሰጣቸው ሚቱ ይተርካል፡፡ ለዚህም ነው አምላክ ቱማ መኖሪያው በሰማይ ማደሪያው በሰው ልብ ውስጥ ነው የሚሉት፡፡ ይሄም መኤኒቶች እና አምላክ ቱማ በቅርብ የሚገናኙ፣ ሲያጠፉ የሚቀጣቸው፣ በኮሞሮቶቻቸውና በኘራዮቻቸው ይቅርታ ሲጠይቁ የሚሰማቸው እንደሆነ ሚቱ ይገልጣም፡፡ በዚህም እንደብሔረሰብም ይሁን እንደግለሰብ ጠባቂ ያላቸው፣ የሚለምኑትን የሚሰጣቸው አምላክ እንዳላቸው የሃይማኖት ሚቱ በመግለጥና በማብራራት ሚናው ከፍተኛ ነው፡፡

## ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ሕይወት እንዴትነት የመግለጥ ፋይዳ

የሰው ልጅ በእለት ከእለት ኑሮው ውስጥ ከሚጠይቃቸው አንኳር ጥያቄዎች ውስጥ ሌላው ከዚህ ከገሀዱ ዓለም በኋላ ያለው ሕይወት ምን እንደሚመስል እና የተጀመረው ሕይወት እጣ ፋንታው እንዴት እንደሆነ ማወቅ ነው፡፡ አንድ ቦታ የተጀመረው የሕይወት ጉዞ ማብቂያ አለው ወይስ የለውም የሚለውን ማወቅ ነው፡፡ ጊዜ ጅማሬ እንዳለው ፍጻሜ አለው ወይስ የለውም የሚለው ጥያቄ ዋና የሕይወት እንቆቅልሹ ነው፡፡

በዶግማና በቀኖና ተቀንብበው፣ በትውፊት ዳብረው ዘመናትን ከተሻገሩት የመንፈሳዊ ሚቶች ውስጥ የክርስትናው እና የእስልምናው አስተምህሮ የዚህ ዓለም ጊዜ ጅማሬ እንዳለው ሁሉ ፍጻሜ እንዳለው ይገልጣሉ፡፡ ካለመኖር ወደ

መኖር የመጣው ይህ ዓለም እንደጨርቅ ተጠቅልሎ የሚጠፋበት የራሱ የማብቂያ ዘመን አለው፡፡ በዚህ ምድር ላይ ያለው የሰው ልጅ ሕይወት እንደየእምነትና ግብሩ ፍጻሜን እንደሚያገኝ ዘግበው ለአማኞቻቸው የጥያቄውን መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከሩቅ ምሥራቅ መነሻውን እንዳደረገው እንደ ሂንዱይዝም ዓይነቱ እና በኢትዮጵያ በጋምቤላ ክልል እንደሚኖሩት አኟዋ/ አኟዋኮች ሚት ደግሞ ሕይወት ተጀምሮ የሚያቆም ሳይሆን የሚቀጥል፣ ሕይወት ቅርጽዋን ቀይራ ዘለዓለማዊ እንደሆነች ይተርካል፡፡ በዚህም ለዘለዓለማዊ የሰው ልጅ ጥያቄ የየራሳቸውን መልስ ይሰጣሉ፡፡

በመኤኒት ብሔረሰብ የጊዜ እሳቤ እና የዳግም ሕይወት ዕጣ ፋንታ በሚት ውስጥ ተብራርቶና ይገኛል፡፡ አምላክ ቱማ የዚህች ገሀዳዊ ዓለም ኑሮ በሞት እንዲገታ አልፈቀደም፡፡ እንደ ክርስትና እና እስልምና ሃይማኖቶችም ይሄንን ዓለም አሳልፎ የሰው ልጆችን እንደ ሥራቸው በገነት እና በገሀነመ እሳት አያኖርም፡፡ ጊዜ ለመኤኒቶች ቀጣይ ነው፡፡ እያንዳንዱ መኤኒት ከሞት በኋላ ወደየት እንደሚሄድ አስቀድሞ ያውቀዋል፡፡ መኤኒቶች ሁሉ ከምድር ላይ ተሰብስበው ወደ ታወቀ እና ወደ ተዘጋጀላቸው ሞኡ ወደተባለ ሥፍራ ይሰበሰባሉ፡፡ ሞኡ ከሞት በኋላ ሕይወት የሚቀጥልበት ሥፍራ ነው፡፡ በዚህ ገሀዳዊው ዓለም የኖሩ መኤኒቶች እንደ አኗኗር ሁኔታቸው በሞኡም ሕይወታቸውን ይቀጥላሉ፡፡ የጥንት መኤኒቶች እንዲያውም ከነቁሳቁሳቸው፣ ማኅበራዊ ደረጃቸው ከፍ ያሉ ደግሞ ከእነ አገልጋዮቻቸው ይቀበሩ ነበር፡፡ መኤኒት የሆነ ሁሉ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ረጅሙን መንገድ አቋርጦ ወደ ሞኡ ስለሚጓዝ አስቀድሞ ስንቁን ያዘጋጃል፡፡ አንድ መኤኒት ሲሞት በአፉ ወተት እንዲገባና እንዳይፈስስበት ተደርጎ ይቀመጣል፡፡ ምክንያቱም ወተቱ የጉዞ ስንቁ ነው፡፡ ፊቱ ወደሞኡ ተደርጎ ይቀበራል፡፡ ይሄም እንደተነሳ ቀጥታ መንገዱን እንዲጀምር ነው፡፡ አስከሬኑ በተቀበረበት ቦታ ላይ ለሦስት ወራት ጎጆ ተሠርቶ ሕያዋን ከሚበሉትና ከሚጠጡት ጥቂት ጥቂት በመቃብሩ ላይ እየተደፋ ጉዞውን አጠናቅቆ ከቅድመ አያቶቹ ጋር እንዲገናኝ ይደረጋል፡፡ ሞተው ወደ ሞኡ ደርሰው እንደመጡ የሚናገሩት አቶ ማዮኒም አየሁት ብለው ያብራሩት ነገር ሚቾች በዚያ አካባቢ

*መኖራቸውን[14] እና ሕይወትም የገሀዱን ዓለም በሚመስል መልክ[15] እንደሚቀጥል ነው፡፡*

*በአጠቃላይ የመኤኒት ብሔረሰብ የዳግም ውልደት ሚት መኤኒቶች በጊዜ ያልተከለለ ሕይወት እንደሚኖራቸው እና ከዚህ ዓላማም በአካለ ሥጋ ሲለዩ የሚጓዙበት የራሳቸው ዳግም ሕይወት መኖሪያ ቦታ እንዳላቸው ይገልጣል፡፡ በዚህም ከሕይወት ባሻገር ስላለው ሕይወት ምንነት በመግለጽ ሚቱ ለብሔረሰቡን አባላት ሁነኛ ፋይዳን አበርክቶላቸዋል፡፡*

## *የልዕለ ተፈጥሮ እርዳታና ኃይል ስላላቸው ሰዎች፣ እንዲሁም ስለባሕል መስተጋድላውያን ሥራና ተግባር የመግለጥ ፋይዳ*

*አምላክ ቱማ ለመጀመሪያው የመኤኒቶች አባት ልጆች የሰጣቸው ኃይልና ጥበብ በእነሱ ብቻ የተገደበ ሳይሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ እየወረደ እንዲጠቀሙበት እንደሆነ የአፈጣጠር ሚቱ ይተርካል፡፡ ተፈጥሮን እና ፍጡራንን የማዘዝ ኃይል ዛሬም እንዳለ ሚቱ ያረጋግጣል፡፡ በናኦሚ የመጀመሪያ ልጅ በባንጃ የተጀመረው ዝናብን የማውረድ ኃይል ዛሬም በተለያዩ አምላክ ቱማ የመረጣቸው እና ኃይል የሰጣቸው ሰዎች እጅ እየተከናወነ ነው፡፡ የኮሊ ቀበሌዋ ወ/ሮ ሌማው ጃና ዝናብን ዛሬም ያዘንባሉ፣ የዝንጀሮ እና የወባ ንጉሡ ዛሬም በአምላክ ቱማ አጋዥነት እና በተሰጣቸው ቃል ኪዳን ዛሬም ተአምራትን እያከናወኑ እንደሆነ የመስተጋድላውያን ሚቱ ይተርካል፡፡ በመሆኑም በመኤኒት ችግር የሚፈጠረው፣ መከራ የሚመጣው በራሳቸው ተግባር እንደሆነ እና ከችግሩም መውጫው ከአምላክ ጋር ቅርበት ባላቸው እና በተመረጡ ኮሞሩቶች እና ኘራዮች አማካይነት ይቅርታን መለመን ነው፡፡*

*በያርጣ አካባቢ የወባን እልቂት ያስቀረላቸው የወባ ንጉሡ ኮሞሩት ቻሪ ነው፡፡ ቻሪ ከአምላክ በተሰጠው ኃይል የአካባቢውን ጭቃ፣ ከምራቁ ጋር በመደባለቅ በመቀባት እንዲድኑ አድርጓል፡፡ የዝንጀሮ ንጉሡም በተመሳሳይ ከችግር አድኗቸዋል፡፡*

---

*[14] እናታቸውን እና ዘመዶቻቸውን እንዳገኙ ገልጸዋል*

*[15] በክርስትና እምነት ጸሎት ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነ እንዲሁ በምድር ይሁን የሚለው እሳቤ የዚሁ ተነጻጻሪ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮት በምድር ላይ የተሠራው የሰማዩ ግልባጭ ወይም ምሳሌ እንደሆነ የትርጓሜ መምህራን ያብራራሉ፡፡*

በሌላ መልኩ እንደ ጥጋቡ ያሉ የባህል መስተጋድላውያን ነባሩ ባሕል ይከበር በማለት መጤ ያሉትን ሀሳብ ተጋፍተው ብዙዎቹ እንዲከተሏቸው ስማቸውን እና ሥራቸውን እንዲያወሩት አድርገዋል፡፡ በሚጥል በሽታ የተያዘ ልጇን አንቄ አልገድልም፣ ለገዳዮችም አልሰጥም ብላ ልጇን ይዛ የጠፋች እናት ታሪክም ይሁን በገዛ አባቷ የሞትን ጽዋ እንድትጎነጭ የታዘዘባት ሞናይ የአልሞት ባይ ተጋዳይ በመሆን መሸነፍን አሸንፈው፣ ሞትን ተገዳድረው ሕይወታውን አስቀጥለዋል፡፡

የመኤኒት ብሔረሰብ የመስተጋድላውያን ሚት የአምላክ ኃይል የተሰጣቸውን እና የባሕል መስተጋድላውያኑን ታሪክ ለሌላው የመግለጥ ፋይዳው ከፍተኛ ነው፡ ፡ በዚህም ብሔረሰቡ በሚቶቹ የተገነባ የማንነት ውቅር እንዲኖረው አበርክቷቸው እና ፋይዳቸው የጎላ ነው፡፡ በአጠቃላይ የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት፣ ለብሔረሰቡ አባላት የዓለምንና የሰውን አፈጣጠር በመግለጥ፣ ስለ ፈጠራቸው አምላክ ማንነትና ከሰው ጋር ስላለው ግንኙነት፣ እያንዳንዱ ሰው ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ሕይወት እንዴትነት፣ የልዕለ ተፈጥሮ እርዳታና ኃይል ስላላቸው ሰዎች ሥራና ተጋድሎ በመግለጥ ምስቅልቅሉን ዓለም ሥርዓት የማስያዝ ፋይዳ እየሰጣቸው ነው፡፡

## 8.2 የማጠናከር እና የመትከል ፋይዳ

ሚቶች ለአንድ ማኅበረሰብ ከሚያበረክቷቸው ልዩ ልዩ ፋይዳዎች ውስጥ አንደኛው የማጠናከር እና የመትከል ፋይዳ ነው፡፡ ኅብረተሰቡ የኔ ናቸው ብሎ የተቀበላቸው፣ የሚጠብቃቸው እና የሚያዘልቃቸው ልዩ ልዩ ባሕሎች፣ ልማዶች፣ ወጎች እና እሴቶች አሉት፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶችም ከዚሁ አንጻር በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር ማኅበረሰባዊ መዋቅርን የመገንባት ፋይዳ፣ የሥልጣን ክፍፍል እንዲኖር የማድረግ ፋይዳ፣ የስልጣን ሽኩቻን የማስወገድ ፋይዳ፣ የተለያዩ የኅብተረሰብ ክፍሎችን አንድ የማድረግ ፋይዳ፣ ማኅበራዊ ትስስርን የማጥበቅ ፋይዳ፣ የደን እና የእንስሳት ሀብትን መጨመር ፋይዳ፣ እምነቶችን፣ አመለካከቶችን፣ እሴቶችን፣ የማረጋገጥ፣ የማሳደግ እና የማጠንከር ፋይዳ ቀርበዋል፡፡

### ማኅበረሰባዊ መዋቅርን የመገንባት ፋይዳ

በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ አምላክ ቱማ አስቀድሞ የፈጠረው ናያሞን ሦስት ልጆች ወልዷል፡፡ አምላክ ቱማም ለፈጠራቸው ለናያሞን ሦስት ልጆች የሰጣቸው ጥበብና ኃይል ከእነሱ ተንስቶ ትውልድ ሁሉ እምነቱን፣ ባህሉን እና ታሪኩን እየተቀባበለው ኖሯል፡፡ ከአምላክ ቱማ በተቸራቸው በዚያ ጥበባቸው ተአምራትን እየሠሩ ኖረዋል፡፡ አባት ሲሞት ለልጅ ልጅ እየተወራረሰ እና እየበዙ፣ በጎሳ እየተከፋፈሉ ዛሬ ላይ ደርሰዋል፡፡ ይህም ቀስ በቀስ መዋቅራዊ ቅርጽ እየያዘ ዘልቋል፡፡

በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ ያሉ የዝናብ ንግሥት፣ የወባ እና የዝንጀሮ ንጉሦች በመዋቅር ደረጃ ከተርታው ወይም ከማኅበረሰቡ የተለዩ ናቸው፡፡

የዝንጀሮ ንጉሡ ከአያታቸው ጀምሮ ንግሥናውን በቤተሰብ እንደሚያውቁት ጠቅሰዋል፡፡ አባታቸው ሲሞት እሳቸው ተተክተዋል፡፡ የኲታ ዘር የዝንጀሮዎች ንጉሥ እንደሆነም ይታመናል፡፡ የወባ ንጉሡም የቻሪ የወባ ንጉሥነትም ይሁን አምላክነት የሚመነጨው፣ በዘር መሆኑን ነው፡፡ የሴላ ኮራይ ዘር በመሆናቸው ከሌሎቹ ዘሮች ተለይቶ እነሱ የወባ ንጉሥነት ስልጣን እንዳላቸው ይታመናል፡፡ በተመሳሳይም ሌማው ጃና ዝናብ ማዝነብ ለእነሱ ከአምላክ ቱማ የተሰጣቸው እና የዝናብ አማልዕክት እንደሆኑ፣ ዝናብ የእነሱ ታዛዥ እንደሆነ ያምናሉ፡፡

ሁሉም የልዕለ ተፈጥሮ እገዛ እንዳላቸው የሚያምኑት አካላት ከበታቻቸው “ኮኮ” የተሰኘ አገልጋይና ረዳት አላቸው፡፡ ማንኛውንም ሥራ ሲሠሩ “ኮኮ” የተባለ ረዳት ጋር በመሆን ነው፡፡ ይሄም አንዱ መዋቅራዊ መለያቸው ነው፡፡ ብሔረሰቡ በጎሳ መሪዎች የተዋቀረ ሲሆን በየአንዳንዱ ጎሳ ወሰጥ ባላባቶች አሉ፡፡ አንዳንዶቹ የጎሳ መሪዎች ደግሞ ዝናብ አዝናቢዎች ናቸው፡፡ በማኅበረሰቡ ዘንድ የተከበሩ ሆነው የሚታዩ ከተራው ሰው ከፍ ብለው የሚከበሩ መሆናቸው የመዋቅራዊ ሥርዓቱ አንዱ መገለጫ ነው፡፡

ከባንጃ ዘር የሚመዘዙት አዝናቢዎች በዘመናት ርቀት ወስጥም የቅድመ አያቶቻቸውን ክህሎት ይዘው ዛሬ ድረስ አሉ፡፡ የወባ ንጉሡ ቻሪ ኮሞሮት ነው፡፡ ኮሞሮት የጎሳ መሪ ነው፡፡ አብዛኞቹ አዝናቢዎችም ኮሞርቶች ናቸው፡፡ አንድ

ኮሞሮት ሲሞት የበኩር ልጁ ይተካል ይሄም መዋቅራዊ ሂደት እንዳለው የሚገልጽ ነው፡፡ ኮሞሮት ሲሞት ከልጆቹ ውስጥ አምላክ ቱማ ለወደደው ስልጣኑ ይተላለፋል፡፡ ይህ በሚቶቹ የተገነባ መዋቅር ተጠብቆ እንዲዘልቅ ማኅበረሰቡ ይፈልጋል፡፡ ምክንያቱም የመዋቅሩ መኖር በእነሱ እና በተራው ህዝብ መሐል ሊኖር ስለሚችለው መስተጋብር አንድ ማሳያ ነው፡፡ ማኅበረሰቡ ለነዚህ ባለ ተአምራትና ገድለኞች ሲያከብራቸው ነው የኖረው፡፡ የሚገባቸውን ክብር ካጓደለ ደግሞ ራሳቸው ጭምር ማኅበረሰቡ የሚቀጣበትን መንገድ ያመቻቻሉ፡፡ ይህ በተራው ሕዝብ እና በተፈጥሮና ፍጡራን ላይ ኃይል እንዳላቸው የሚታመኑት ሰዎች በሕዝቡ ተከብረው መኖር እንደሚፈልጉ ማኅበረሰቡም ይረዳል፡፡

የመኤኒት ብሔረሰብ የዳግም ውልደት ሚት በብሔረሰቡ አባላት መካከል ማኅበራዊ መዋቅርን ለመገንባት ፣ የተገነባውንም ለማጥበቅ እና ለማጽናት ሰፊ ተግባራት አከናውኗል፡፡ በብሔረሰብ የዳግም ውልደት ሚት እሳቤ አንድ የብሔረሰቡ አባል በጊዜ ሞት ወቅት የሚደረግለት የተለያየ ነው፡፡ የቀብር ሥርዓቱ እንደሚቹ እድሜ እና ማኅበረሰባዊ ሚናም የተለያየ ነው፡፡ ህጻናት ሲሞቱ፣ በእድሜ የከበሩ፣ የወለዱ እና የከበዱ ሰዎች ሲሞቱ እና የሃይማኖት መሪዎች እና ኮምሩቶች ወይም የጎሳ መሪዎች ሲሞቱ የሚከናወነው የቀብር ሥርዓት የተለያየ ማኅበረሰባዊ መዋርን የጠበቀ ነው፡፡

መዋቅሩ በእድሜ፣ በማኅበረሰባዊ ሚና፣ በሃይማኖታዊ አመራር እና በጎሳ ኃላፊነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ወልዶ እና ከብዶ ብዙ ወግ ማዕረግ ያየ ሰው ሲሞት የሚቀጠቀጡለት ከብቶች ብዛት በጊዜ ቀብሩም ይሁን ከሞት በኋላ በሚጠብቀው ሕይወት ላይ የራሱ የሆነ አሻራ አለው፡፡ ወልዶ እና ከብዶ የመኖሩ ምስጢር በርካታ ከብቶች ተቀጥቅጠውለት ከሞት በኋላ የሚጀምረው ሕይወቱ የተቃና እንዲሆን ያደርገዋል ተብሎ በመታመኑ ነው፡፡ በዳግም ሕይወቱ ወቅት የሚገለገልባቸው አሉት፡፡ ልረስ ቢል ለእርሻ፣ ላርባቸው ቢል ለርቢው፤ እጁ ረጅም እንዲሆን እና የሐብት መጠኑ በአካለ ሥጋ፣ ገሀዳዊን ዓለም እንዲመስልለት በማድረግ የብሔረሰቡ አባላት መካከል የሚታየውን ማኅበረሰባዊ መዋቅር እንዲጠበቅ ያደርገዋል፡፡

በአንጻሩ የሃይማኖት እና የጎሳ መሪዎች በቅድመ ሞት፣ በጊዜ ሞት እና ከሞት በኋላ በሚደረግላቸው ሥርዓት ከተራው ሰው የተለየ የማንነታቸው ነጸብራቅ ነው፡

፡ ይሄም በተለይም ባላባት እና የጎሳ መሪዎች ቀደም ባለው ጊዜ ረዳቶቻቸው እና የሚወዷቸውን ቁሳቁሶች ጭምር ይዘው እንዲቀበሩ እስከማድረግ ድረስ ማኅበረሰባዊ መዋቅሩ እንዲገነባ አድርጓል፡፡

ታላላቅ የሃይማኖት መሪዎች፣ ባላባቶች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ በገሀዱ ዓለም የሚኖረው ቤተ - ዘመድ ከሦስት ወራት በኋላ በመቃብሩ ላይ ዋርካ ተክሎ አካባቢውን ለቅቆ የሚሄደውም የዳግም ውልደት እና ሕይወት ጅማሬ ሚቶች የሚፈጥሩት ማኅበረሰባዊ መዋቅር ውጤትም ይመስላል፡፡

**የሥልጣን ክፍፍል እንዲኖር የማድረግ ፋይዳ፣**

በሰው ልጆች የጋራ ኑሮ ውስጥ አንዱ የጠብ እና የግጭት ምክንያት የሥልጣን ጉዳይ ነው፡፡ ስልጣን አንዱን የበላይ እና አዛዥ አንዱን ደግሞ የበታች እና ታዛዥ የሚያደርግ ነው፡፡ የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህሪ ደግሞ መከበርን፣ መመረጥን እና መሻልን አጥብቆ የሚመኝ ነው፡፡

ሥልጣን ጉዳይ እንኳን በአንድ ማኅበረሰብ አባላት ውስጥ ቀርቶ፣ በአንድ የቤተሰብ አባላት መካከል ጠብን የሚቀሰቅስ፣ ግጭትን የሚጭር እና እስከ መገዳደል የሚያደርስ ነው፡፡

በአይሁድ እና  በክርስትና ኃይማኖት አስተምህሮ ውስጥ የመጀመሪያው ጸብ ብቅ ያለው በስልጣን ጉዳይ ነው፡፡  እግዚአብሔር ራሱ የፈጠረው፣ የመላዕክት ሁሉ አለቃ የሆነው ዲያብሎስ ያለው ሥልጣን አልበቃ ብሎት በፈጠረው ላይ መፈንቅለ ሥልጣን ለማካሄድ በመሞከሩ ተዋርዶ እንደተለየ ይተርካል፡፡ በእርሱም ምትክ ከአፈር ተቦክቶ የተፈጠረው አዳም እና ከግራ ጎኑ ተፈልቅቃ የተገኘችው ሔዋንም ስህተት የገቡት “እንደ እግዚአብሔር ለመሆን” በመመኘት ትዕዛዝን በመጣሳቸው እንደሆነ ተጽፏል፡፡ የሁለቱም የሥልጣን ግባቸው አንድ ቢሆንም ፅንሰታቸው ግን ይለያያል፡፡ ዲያብሎሰ ከራሱ ሕሊና ፍላጎቱን እንዳነቃው ሲተረክ፣ አዳም በዲያብሎስ ግፊት እንደነበረ መተርጉማን ያስረዳሉ፡ ፡ ዞሮ ዞሮ ፈጣሪ ሁለቱንም የሥልጣን ጥመኞች እንደቀጣቸው የአይሁድ እና የክርስትናው ሐተታ ተፈጥሯዊ ሚት ያስረዳል፡፡

በዚሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ኦሪታዊ ትረካ ውስጥ ዮሴፍን ወንድሞቹ ለባርነት አሳልፈው የሸጡት በስልጣን እና በመመረጥ ከእነሱ እንደሚሻል የገባቸው ግዜ ነው፡፡ ዮሴፍ በህልሙ እሱም ወንድሞቹም ነዶ ይዘው ማየቱን እና ይበልጡንም የእነሱ ነዶ ለእሱ ነዶ መስገዱን በነገራቸው ግዜ ቅናት ገባቸው፡፡ የዮሴፍ በስልጣን፣ በክብር መላቅና መመረጥ አስከፋቸው እንጅ አላስደሰታቸውም፡፡ በመሆኑም በገዛ ወንድሞቹ ለመሸጥ እንደበቃ ኦሪታዊ ትረካው ይገልጻል፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ አፈጣጠር ሚት ግን የሥልጣን ሽኩቻ እንዳይፈጠር የሥልጣን ክፍፍል በማድረግ የላቀ ፋይዳ ለማኅበረሰቡ ሰጥቷል፡፡ አስቀድሞ የመኤኒቶችን ሰማይ የዘረጋላቸው፣ የመጀመሪያውንም አባታቸውን በምድር ላይ የፈጠረው አምላክ ቱማ ለናያሞን ሦስት ልጆች ልዩ ልዩ መክሊትን መስጠቱ አንዱ በአንዱ ሥራ ጣልቃ እንዳይገባ፣ አንዱ የአንዱ ተቀናቃኝ እንዳይሆን አግዟል፡፡ የባንጃ አዝናቢነት ከቦሹ የእንስሳት አለቅነት በእጅጉ ይለያል፣ እንዲሁም የኮሊ በዕፅዋት ላይ ኃይልን መላበስ የሥልጣን ክፍሉ የተለያየ እና ይበልጡንም አንዱ የአንዱን ሕልውና የሚፈልግበት እንዲሆን አድርጎታል፡፡ የኙራዩ ሥልጣን ከኮሞሮቱ መለየቱ፣ የኮሞሮቱ ከኮኮው ከፍ ማለቱ የብሔረሰቡ ሚት የሥልጣን ክፍፍሉን ዘላቂ እና በልዩነት ውስጥ የሚያስፈልግ አንድነት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

**የሥልጣን ሽኩቻን የማስወገድ ፋይዳ፣**

የሥልጣን ሽኩቻ፣ ሥልጣኑ እንደሚገባቸው በሚያምኑ ወገኖች መካከል የሚፈጠር ግጭት ነው፡፡ የፍላጎቱ ግጭት አድጎ ስነ ልቡናዊ ገደቡንም ጥሶ ወደ አካላዊ ግጭትነት ይሻገራል፡፡ በግለሰቦች መካከል የሚፈጠረው የሥልጣን ሽኩቻ ወደ ቡድናዊነት ከዚያም ከፍ ብሎ የሚሄድበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡

በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ የጎሳ መሪ በጎሳ መሪ ፣ ኮሞሩት በኮሞሩት ሲተካ፣ የአዝናቢ ልጅ የአባቱን ሥልጣኑን ሲወርስ ወይም በእንስሳት፣ በአራዊት እና በነፍሳት ላይ ሥልጣን ያለው በተከታዩ ሲተካ ጠብ፣ ግጭት እና የይገበኛል ጥያቄዎች እንዳይነሱ የብሔረሰቡ ሚቶች ዓይነተኛ ፋይዳ አበርክተዋል፡፡ ሥልጣኑን፣ ጥበቡን እና የልዕለ ተፈጥሮ አጋዥነትን የያዘው ሰው ሲያልፍ ወራሽ የሚሆነው የበኩር ልጅ ነው፡፡ ይሄው ሥርዓት ከእሱ በታች ያሉት ወንድም እህቶቹ ሥልጣኑንም ሆነ ጥበባቱን በመመኘት የሚፈጥሩት ችግር አይኖርም፡፡

በዘመናት ሂደት ውስጥ የተደነገገ ሥርዓት በመሆኑ በሁሉም ቦታዎች የጸና ነው፡ ፡ እንዲህ ዓይነቱ በኩራትን ወራሽ የማድረግ ሥርዓት በበርካታ ባሕሎች እና ሚቶች ይገኛል፡፡ በመኤኒቶችም አንድ ከፍተኛ ክብርና ቦታ ያለው ሰው በሞት ሲለይ፣ ቦታውን ለመያዝ እና ሥልጣኑ ለመረከብ ከፍተኛ ችግር እንዳይፈጠር፣ ተተኪዎች ወይም ወራሾች ተሽለው ለመገኘት፣ የየራሳቸውን ጎራ መሥርተው በልዩነት ሲፋተጉ እንዳይቆዩ፣ አንዱ አንዱን አስወግዶ ሥልጣኑን እና ክብሩን ለመቆናጠጥ እስከ ከፍተኛ ደም መፋሰስ የሚደርስ ግጭት ውስጥ እንዳይገቡ በማድረግ ፋይዳው የጎላ ነው፡፡

የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ለበኩር ልጆች መንገዱን በመጥረግ እና በማመቻቸት ሊመጣ የሚችለው ችግር እንዲወገድ አድርጓል፡፡ አዝናቢዋ ሌማው ጃና ሥልጣኑን ከእናታቸው ሲረከቡ መሥፈርቱ በኩር መሆናቸው ነው፡፡ የዝንጀሮ ንጉሡም ሆኑ የወባ ንጉሡ የበኩር ልጅ መሆናቸው ለሥልጣን አብቅቷቸዋል፡፡ የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤትና አጋዥነት በእነሱ ላይ ሆኗል፡፡ በብሔረሰቡ በሥልጣን ፍለጋና መሻት ጠብና ግጭት ሰላም እንዳይጠፋ፣ የቅሬታ እና የበታችነት ስሜቶች እንዳይፈጠሩ፣ ካሉም ጎልተው እንዳይያጡ የሚቶች ሚና የጎላ ነው፡፡

## የተለያዩ የኅብተረሰብ ክፍሎችን አንድ የማድረግ ፋይዳ

ሚቶች የተለያዩ የኅብረሰብ ክፍሎችን አንድ የማድረግ ባህሪይ እንዳላቸው ሁሉ በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ ያሉ ሚቶችም የተለያዩ የኅብረሰብ ክፍሎችን አንድ የማድረግ ሚና እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ የዝናብ ንግሥቷ ሌማው ጃና ተአምራታቸውን በሕዝብ ፊት እና በቀን አከናውነው ሲያሳዩ በሥፍራው የተገኙት በእድሜ፣ በጾታ፣ በትምህርት፣ ወዘተ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በጉዳዩ ላይ አንድ ዓይነት አቋም እንዲይዙ አድርጓቸዋል፡፡ በተመሳሳይም የዝንጀሮ ንጉሡ አቶ ሴላ በአካባቢያቸው ሕዝብ ላይ የዘመተውን የዝንጀሮ መንጋ እንዳይመጣ በማድረጋቸው ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በሚታቸው ዙሪያ አንድ ዓይነት አቋም እንዲኖራቸው አድርገዋል፡፡

ማኅበረሰቡ ችግር ሲያጋጥመው የአምላክ ቱማ ፀጋ ወዳላቸው በመሄድ አቤት እንደሚል፣ እነሱም ችግሩን መርምረው ባላቸው ኃይል እና ስጦታ ማስወገድ

እንደሚችሉ የሚያምን ማኅበረሰብ እንዲፈጠር ለማድረግ ችለዋል፡፡ ይህ በሚቶቹ እሳቤ ላይ አንድ የሆነው የማኅበረሰብ ክፍል፣ በእድሜ፣ በጾታ፣ በሥራ ዘርፍ ወዘተ የተለያየ ነው፡፡ የዝናብ ንግሥቷ ሌማው ጃና ዝናብ የማውረድ አቅም ስላላቸው፣ እሳቸውን ለማምጣት እና እንዲያዘንቡ ለማግባባት የተውጣጣው የማኅበረሰብ ክፍል ልዩ ልዩ ነው፡፡ በተመሳሳይም የዝንጀሮ መንጋ ባስቸገረበት ጊዜ ወደ ዝንጀሮው ንጉሥ የሄደው የማኅበረሰብ ክፍልም ይሁን በወባ በተጠቃ ጊዜ ድኅነትን እንዲሰጣቸው ወደ ወባ ንጉሡ ቻሪ ሄዱት በኅሳ የተለያዩ በእድሜ እና በሥራቸው ማኅበረሰቡ የሚያከብራቸውና ለአማላጅነት ጭምር የሚበቁ የማኅበረሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ እነዚህን ሰዎች ስናስብ በሚቱ ማኅበረሰቡ በአንድ ሀሳብ ላይ መስማማታቸውን የሚያሳይ ይሆናል፡፡

የፎክሎር ዘውግ በርካታ መሆን፣ የፎክሎርን ተግባርም ዘርፈ ብዙ እንዲሆን ማድረጉ አይቀሬ ነው፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ የዳግም ውልደት ሚት የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን አንድ የማድረግ ተግባርን በማከናወን ፋይዳው የጎላ ነው፡ ፡ የብሔረሰቡ አባላት በተለያዩ ጎሳዎች የተከፋፈሉ ቢሆንም ስለሞት እና ከሞት በኋላ ስላለው የብሔረሰቡ አባላት እጣ ፋንታ የጋራ የሆነ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡

በሁሉም ወረዳዎች ውስጥ የሚኖረው የመኤኒት ብሔረሰብ፤ በቅድመ ሞት፣ በጊዜ ሞት እና ከሞት በኋላ በሚደረገው ተግባር ተመሳሳይ ሥርዓትን ለዘመናት ሲጠብቅ ኖራል፡፡ አንድ የብሔረሰቡ አባል ለሞት በቀረበ ጊዜ ለማይቀረው ጉዞ ማዘጋጀት፣ ወተት በመጋት ስንቁን እንዲይዝ ማድረግና፣ በሞተ ጊዜ በቆዳ መጠቅለል ከሞተበት ጎጆም አዲስ በር ሠርቶ አስከሬኑን ማውጣት፣፣ በዚያው በግቢው ውስጥ ፊቱን ወደ ምሥራቅ አድርጎ መቅበር፣ በሞቱ እለትም ከብቶችን መቀጥቀጥ፣ በመቃብሩ ላይ ጎጆ ሠርቶ ለሦስት ወራት አስከሬኑን መጠበቅ፣ በዚያው የጊዜ ገደብ ውስጥም ከበሉት እና ከጠጡት እየቆነጠሩ ለሟች መንፈስ ማቃመስ እና ጉዞው የተሳካ እንዲሆን ማገዝ በሁሉም የብሔረሰቡ ጎሳዎች የሚተገበር ሥርዓት ነው፡፡ ይሄም የጋራ አመለካከት፣ የጋራ ታሪክ እና የጋራ ባሕል በመፍጠር አንድ የሚያደርግ ተግባር ይታይበታል፡፡

### ማኅበራዊ ትስስርን የማጥበቅ ፋይዳ

ሚቶች ማኅበረሰባዊ መዋቅርን እንደሚገነቡ ሁሉ ማኅበረሰባዊ ትስስርንም ለመፍጠር ይረዳሉ፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ ከ60 በላይ በሆኑ ጎሳዎች የተከፋፈለ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአንደኛው ጎሳ መኖር ለአንደኛው እንደዋስትና እንዲሆን ሚቶቹ የራሳቸውን አበርክቶ አድርገዋል፡፡ የዝናብ አዝናቢዋ የወደጀደራይታ ጎሳ፣ የዝንጀሮው ንጉሥ ኩታ ጎሳ እና የወባ ንጉሡም የሴላ ኮራይ ጎሳ አባላት ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ማኅበረሰቡ በሰፈረባቸው አካባቢዎች ውስጥ የተለያዩ ጎሳዎች ቢኖሩም የአንዱን ሥራ አንደኛው አለመሥራቱ የአንደኛው ሕልውና ለሌላው አስፈላጊ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ እንደ ለቅሶ እና ሰርግ ዓይነት የማኅበራዊ ሕይወት መስተጋብሮች ማኅበረሰብን እርስ በርሱ የሚያቀራርቡ እና የሚያዛምዱ ናቸው፡፡ ሞት ቀጠሮ የሌለው እና ድንገትም የሚመጣ ክስተት በመሆኑ የሟች ወገኖች ሁሌም ተዘጋጅተው ሞትን ሊጠብቁ አይችሉም፡፡ ይሁን እና እንዲህ ድንገት የሚከሰቱ አደጋዎች ሲመጡ የሟች ወገኖች ሟቹንም በክብር ለመሸኘትና ለቀስተኛውን በወጉ ለማስተናገድ ይቸገራሉ፡፡ አንዳንድ የኢትዮጵያ ክፍል ማኅበረሰቦችም "ሞት ገመና ገላጭ ነው" የሚል አባባል አላቸው፡፡ ጉዳዩ ሞት ያለዝግጅት ዱብ ብሎ ስለሚመጣ፣ ሁኔታውን ተቆጣጥሮ ሂደቱን ለማከናወን አስቸጋሪ መሆኑ ነው፡፡ በተለይም የሟች ዘመድ አዝማድና እሱን በወጉ ለመሸኘት እንዲሁም ቋሚዎቹን ለማጽናናት ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡትን የለቅሶው ተካፋዮች ለመሸኘት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በብዙ ቦታዎች እንደየ ባሕሉ የተለያየ ሥም የሚሰጥባቸው እንዲህ ዓይነቱን ማኅበራዊ ክስተቶች በመተጋገዝ የሚታለፍባቸው እንደ እድር ዓይነት ተቋማት ይገኛሉ፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ ሚትም መኤኒቶች በእንዲህ ዓይነቱ ክፉ ቀን እንዲተጋገዙ፣ እንዲረዳዱ እና ማኅበራዊ ትስስራቸው እንዲጠነክር አስችሏቸዋል፡፡ ለሟች የሚቀጠቀጡት እና የሚታረዱት ከብቶች አንደኛው ፋይዳቸው ለቀብር ከሩቅም ከቅርብም ለተሰበሰበው ሰው በምግብነት መዋል ነው፡፡ የሀዘኑ ተካፋይ የሆነ ሰው ሳይቸገር ምግብ በልቶ ወደ መጣበት እንዲመለስ ያግዛል፡፡ የመኤኒት መልክአ ምድር አቀማመጥ ወጣገባነት እና የማኅበረሰቡም አሠፋፈር የተራራቀ መሆን ለቀብር የሚመጣው ሰው ረጅም መንገድን እንዲጓዝ ያደርገዋል፡፡ በዚያ ላይ የመጓጓዣ ሁኔታው አስቸጋሪ እና በአብዛኛው በእግር የሚደረግ በመሆኑ የሰው ድካም ተደራራቢ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ለደከመው ሰው እረፍት እና

ለጥንካሬውም ምግብ ማግኘቱ በጎ ጎን አለው፡፡ የሚች ወገኖችም ብቻቸውን ይሄንን ክስተት እንዳይጋፈጡት እንዲረዳዱ፣ እና ችግርን በጋራ እንዲያሳልፉ የማድረግ ፋይዳው የጎላ ነው፡፡

## የደን እና የእንስሳት ሀብትን መጨመር ፋይዳ

የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶች ለማኀበረሰቡ ከሰጡት ፋይዳዎች አንዱ የተፈጥሮ ሀብት እንዳይራቆት ማድረጉ ነው፡፡ መኤኒቶች አንድ ሰው ከሞተ በኋላ በቀበሩበት ቦታ ላይ አንድ ዛፍ የመትከል ልማድ አላቸው፡፡ ይሄውም ሚቱ የሰጣቸው ልምድ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው በሕይወት ዘመኑ በተለያዩ አጋጣሚዎች ከተከላቸው ዛፎች ውጪ በሞቱ ጊዜ ዘመዶቹ በስሙ የሚተክሉት ዛፍ መኖሩ ለአካባቢው የደን ሽፋን አንድ በጎ ፋይዳ ነው፡፡ በዚህኛው ዓለም ያላቸውን የእድሜ ገደብ አጠናቅቀው ወደ ሞኡ ሲሄዱ ለኖሩባት ምድር አንድ ዛፍ መትከላቸው በዕድሜ እና በጤና ቆይተው የሞቱ መኤኒቶች የሚደረግላቸው ክብር ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው የብሔረሰቡ ሚት ለደን ጥበቃው የሰጠው ፋይዳ ሞኡ አካባቢ ያሉ ልዩ ልዩ ዕፅዋት እንዲቆረጡ አለመፈቀዱ ነው፡፡ እንደ ብሔረሰቡ ሚት ሥፍራው የሁለተኛው ሕይወታቸው ምዕራፍ መኖሪያ እና ከሞት በኋላ ያለው ሕይወታቸው የሚቀጥልበት በመሆኑ ተከብሮ እና ዕፅዋቱም ሳይነኩ እንዲኖር በማድረግ ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ ሞኡ አካባቢ እግሩ ያደረሰው የገሀዱ ዓለም ኗሪ አንዲት ቅጠል እንዳይበጥስ፣ ከበጠሰም እዚያው ቦታ ጥሎ እንዲሄድ የሚያስገድድ ሚት መኖሩ ዕፀዋት እንዳይነኩ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

የመኤኒት ብሔረሰብ ከቤት እንስሳት ጋርም የጠበቀ ቁርኝት አለው፡፡ የብሔረሰቡ የአፈጣጠር ሚት እንደሚያስረዳው እንስሳት እና መኤኒቶች ሕብረት የፈጠሩት አስቀድሞ በዘፍጥረት ዘመናቸው ነው፡፡ የብሔረሰቡ መሥራች የአብራክ ፍሬ ከሆኑት ልጆች ውስጥ አንዱ በእንስሳት ላይ ሥልጣን የተሰጠው ኮሊ ነው፡፡ እንስሳትን ለምግብነት ከማዋል ባሻገር በእነሱ ላይ የተለየ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ከዚሁ የአፈጣጠር ሚት ጋር ተያይዞ በዘለቀው የብሔረሰቡ እምነት ከብቶች ዛሬም ድረስ ጥብቅ ቁርኝት አላቸው፡፡ በተለይ ከቤት እንስሳት ውስጥ የቀንድ ከብቶች እንዲሁም በግና ፍየሎች፣ በአካላቸው፣ በሥጋቸው እና በደማቸው ጭምር ከፍተኛ ፋይዳ ያለው በረከት እየሰጡ ነው፡፡

ለአብዛኛው መኤኒት የማኅበራዊ ሕይወቱ ማከናወኛ የቤት እንስሳት እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ብሔረሰቡ አርብቶአደር ብሔረሰብ በመሆኑ የኢኮኖሚ ሀብቱ ከተመሠረተባቸው ዋና ዋና መሠረቶች አንዱ የእንስሳት እርባታ ነው፡፡ በግብርና ላይ ከተመሠረተው ሕይወቱ ጋር ሲተሳሰር የከብቶቹን አስፈላጊነት ያጎላዋል፡፡ ይህ የብሔረሰቡ ኢኮኖሚያዊ መዋቅር ነው፡፡ ከዚህ ላይ የሚጨመረው የማኅበራዊ ሕይወቱ መስተጋብር ከእንስሳት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ አንድ ወንድ ለአቅመ አዳም ደርሶ ሚስት ማግባት በፈለገ ጊዜ ለሴቷ በጥሎሽ የሚሰጣቸው ከብቶች ከሰባት ማነስ አይኖርባቸውም፡፡ ከዚያ ሊጨምሩ የሚችሉ ሲሆን የመጨረሻ ጣርያም አልተበጀም፡፡ አቅም ያለው እና የሐብቱን ብዛት ማሳየት የፈለገ ቁጥራቸውን ሊጨምር ይችላል፡፡ ወደ ቆላው አካባቢ ደግሞ የጥሎሽ ከብቶች እስከ ሰላሳና አርባ ይደርሳል፡፡ ይህ ጉዳይ ደግሞ አንድ ወንድ እስከ አምስት ሚስቶችን ማግባት እንደሚችል በሚፈቅደው ነባር ልማድ ላይ ሲደመር ለጥሎሽ የሚሰጡትን ከብቶች ቁጥር በእጅጉ ይጨምረዋል፡ ፡

በሌላ ዐውድም አንድ ወንድ የራሱ ካልሆነች ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ቢፈጽም እና ድርጊቱንም እንደፈጸመ ከተረጋገጠ፣ ለሴቷ ባል ከሚወሰንብት የገንዘብ ስጦታ በተጨማሪ አንድ በሬ ወይም ላም ይከሳል፡፡ አንድ በማኅበረሰቡ የተከበረ፣ የወለደ እና የከበደ ሰው ሲሞትም የሚቀጠቀጥለት ከብት ቁጥር ብዙ ነው፡፡ በተለይም የወለዳቸው ሴት ልጆቹ ያገቡ ከሆኑ በልጆቹ መዳር የሚደርሰው የከብት ብዛት መጨመር ብቻ ሳይሆን በሞተም ጊዜ የሚቀጠቀጥለት ከብት ቁጥር ይበዛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በመኤኒት ብሔረሰብ ባሕላዊ የፍትህ ሥርዓት፣ የሰው መግደል እርቅ በሆነው “አሻ ሥርዓት” ላይ የገዳይ ቤተሰቦች ለሟች ቤተሰቦች በካሳነት የሚሰጡት አንዲት ልጃገረድ እና ሰባት ከብቶችን ነው፡፡ ከእነዚህ ሰባት ከብቶች ውስጥ ሁለቱ ቀደም ብለው የሚሰጡ ሲሆኑ፣ የጦር መመለሻ እና የመቅበሪያ ከብት ናቸው፡፡ ሟችም የሚቀበረው በዚሁ በተሰጠ ከብት ቆዳ ተጠቅልሎ ነው፡፡ አሁን አሁን እና በተለይም ለከተማ ቅርብ በሆኑት የደጋው የመኤኒቶች ክፍል በልጃገረዷ ፋንታ ተጨማሪ ሰባት ከብቶች እንዲሰጡ እና እርቁ በአሥራ ዐራት ከብቶች እንዲያልቅ የማድረግ ሙከራዎች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ በአብዛኛው እና

በቆላማው አካባቢ ግን የልጃገረዲቱ መሰጠት እንደቀጠለ ነው፡፡ የእርቁ ዕለትም የእርቁን መስመር ለማየት እና ዕርቁ በሁለቱም ወገን በትክክል መፈጸሙን በዕለቱ ከሚታረደው በሬ አንጀት ውስጥ የሚያነብቡ አይጨለቆዎች የተሰኙ አንጀት አንባቢዎች አሉ፡፡ በዚህም የከብቶች አንጀትም ለእርቅ ማጽኛ ፋይዳ ይውላል፡፡ በመጨረሻም ለዕርቁ የሚሰበሰቡት የሁለቱም ወገኖች በጠቅላላ በጦር ተወግቶ የሚገደልን በግ ደም ተራምደው ያልፋሉ፡፡ የሚች ወንድም እና ገዳይ በሽማግሌዎች ፊት ከአንድ ሜትር ባልበለጠ ርቀት ላይ ተንበርክከው፣ ዓይን ለዓይን እየተያዩ የበግ አንጀት እየበሉ እንዲቀራረቡ ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም የበጉን እና የከብቱን ስጋ ከሚገነፋ የበቆሎ ገንፎ ጋር በመደባለቅ እርቁን ያጸናሉ፡፡

ከላይ ለማሳየት እንደተመለከተው የከብቶች መኖር ከእርሻ ሥራ እና ከምግብነት ባሻገር ለብሔረሰቡ የሚሰጡት ጥቅም ብዙ ነው፡፡ በመሆኑም በመኤኒት ብሔረሰብ የእንስሳት አስፈላጊነት ከፍ ያለ ነው፡፡ መኤኒቶችም ማኅበረሰባዊ አኗኗራቸው የከብቶች አጠቃቀም ፍላጎታቸውን ከፍ የሚያደርገው ቢሆንም የሚጠየቀውንም ለማሟላት ከብቶችን ማርባት አስፈላጊ የኑሮ ፍልስፍናቸው ነው፡፡ በሞት ግዜ በርካታ ወይፈን እና ጥጆች ተቀጥቅጠው ይገደላሉ፣ ይታረዳሉ፡፡ ለሃጢያት ማስተሰርያ እና በውርስ ጋብቻ ጊዜ ሴቷን በደም ለማጠብ በግና ፍየሎችም ይታረዳሉ፡፡ በግድያ እርቅ ጊዜ በአንጀታቸው እርቅ ያጸናሉ ከዚህ አንጻር የመኤኒት ሚቶች መኤኒቶች እና እንስሳት የጠበቀ ቁርኝት እንዲኖራቸው አድርገዋል፡፡

በአጠቃላይ ከቀንድ ከብቶች ጋር ያስተሳሰሯቸውም ይሁን፣ ለሚች ሰው ዋርካ መትከል እና ከሞኡ ቅጠል አለመበጠስን የሚያዙት ሚቶች የእንስሳት ሐብትን ለመጨመር እንዲሁም የደን ሀብትን በማስጠበቅ ረገድ ፋይዳቸው የጎላ ነው፡፡

## እምነቶችን፣ አመለካከቶችን፣ እሴቶችን፣ የማረጋገጥ፣ የማሳደግ እና የማጠንከር ፋይዳ

ሚቶች በአንድ ማኅበረሰብ ያለፈ ታሪክ ውስጥ እንደመመሥረታቸው በመኤኒት ብሔረሰብ ዘንድም ስለ ዝናብ ንጉሦችና ንግሥቶች በቃል ሲነገር ለመጣው ሚት አንድ ማሳያ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ሚቶች ባለፈና ተደርጓል በተባሉ

ትርክቶች ላይ ያተኮሩ ቢሆኑም በየቀኑም የሚከወኑ ጭምር ናቸው፡፡ የዝናብ ንግሥቷ፣ የኮላይዋ ወ/ሮ ሌማው ጃና የቀደመውን በብሔረሰቡ ዘንድ ስለ አዝናቢዎች የነበረውን እምነት፣ አመለካከት እና እሴት በተግባር እንዲረጋገጥ፣ እንዲያድግ እና እንዲጠናከር አድርገዋል፡፡ በተመሳሳይም የዝንጀሮ ንጉሡ እና የወባ ንጉሡ በብሔረሰቡ ዘንድ ያለው የሚት እሳቤ ከዘመን ዘመን እየተሸጋገረ ለመገኘቱ፣ ሚትም ያለፈ ጊዜ ትርክት ብቻ ሳይሆን የአሁንም ዘመን የማንነት መገለጫ መሆኑን የማሳያ ሁነኛ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

ሌማው ጃና የዝናብ አዝናቢ ዘር መሆናቸው፣ ዝናብ ማዝነብ የሚያስችል አቅምና ኃይል ወይም ልዩ ተሰጥኦና ጥበብ እንዳላቸው አስመስክረዋል፡፡ ሌማው የሚቱን ቀጣይነት እና ተአማኒነት ለማረጋገጥ ችለዋል፡፡ ዝናብ ማዝነብ ከአምላክ ቱማ ከመጀመሪያው ዝርያቸው ከባንጃ ጀምሮ ለእነሱ ዘር የተሰጠ መሆኑን አስመስክረዋል፡፡ ዝናብን ባዘነቡበት ወቅት በኮላይ ቀበሌ እና አካባቢው ያሉት ሁሉ ተአምራቱን ቆመው ያዩ በመሆናቸው የኖረውና ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው እሴት እንዲጠናከር እንደ አዲስም እንዲነገር እድል ሰጥቷል፡፡

የሚት ትረካ በአማኙ ዘንድ የታመነ እና እውነትነት ያለው ነው፡፡ የዝናብ አዝናቢዋ ሌማው ጃና ዝናብን የማዘዝ የልዕለ ተፈጥሮ ኃይል መኖርን በሥፍራው ተገኝተው ያዩት ደግሞ የበለጠ ሚቱ በዚህ ዘመን ውስጥ በገሃድ በመፈጸሙም የአመለካከቱ እና የእሳቤው ማጠንከሪያ መንገድም ሆኗል፡፡ የወባ ንጉሡ ቻሪም ብሔረሰቡ፤ በቆየውና በጸናው የሚት አመለካከቱ ላይ እርግጠኛነት እንዲሰማው፣ እንዲጠብቀው፣ እንዲያጠነክረው አድርጓል፡፡ በተመሳሳይ የዝንጀሮ ንጉሡ የሠሩት ሥራ እምነቶችን፣ አመለካከቶችን፣ እሴቶችን፣ በማረጋገጥ፣ በማሳደግ እና በማጠንከር ረገድ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑን ማሳያ ነው፡፡

የመኤኒት ብሔረሰብ ድግመ ውልደትና ድግመ ጅማሬ ሚት በማኅበረሰቡ ዘንድ ከሞት በኋላ የሚቀጥለው የዳግም ሕይወት እሰቤ አምላክ ቱማ ለብሔረሰቡ አባላት ከልሎና አዘጋጅቶ ባዘጋጀላቸው ሞኡ እንደሆነ የሚተርከውን ሚት አረጋግጠላቸዋል፡፡ አምላክ ቱማ ለብሔረሰቡ አባላት ያዘጋጀው ቦታ በተለምዶ ‹‹ቆላ›› እንደሚባል ብዙዎቹ ያምናሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ሞኡ እዚሁ ምድር ላይ የሚገኝ በጸጥታው እና በግርማው የሚያስፈራ፣ በዕፅዋት የተሞላ ሸንጠ ረጅም የሆነ ተራራ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ሞኡ በጉራ ፈርዳ አካባቢ መገኘቱ እንዲሁም

መኤኒቶች የሚቾችን ፊት ወደ ሞኡ አቅጣጫ አድርገው መቅበራቸው የሚቱ ውጤት እና የማኅበራዊ ፍልስፍናቸው ማሳያ ነው፡፡

የጉራ ፈርዳ ወረዳው ኗሪ አቶ ማዮኒ ደግሞ ከዚያ ‹‹ቆላ›› ወይም ‹‹ሞኡ›› ከተባለው ቦታ ደርሰው እንደመጡ መናገራቸው፣ በቦታው ውለውና አድረው ያዩትን በዚህ በገሀዳዊው ዓለም ለሚኖረው የማኅበረሰብ ክፍል መግለጻቸው የማኅበረሰብን የቆየ እምነት፣ አመለካከት እና እሴት በማረጋገጥ ትልቅ ሚና እንዳለው መገመት ይቻላል፡፡ አንድ የመኤኒት ብሔረሰብ አባል ከገሀዳዊው ዓለም በሥጋ ሞት ተለይቶ ወደ አዲሱ ዓለም እና ከሞት በኋላ ወዳለው የሕይወት ምዕራፍ እንደሚሸጋገር ሲታመን ለረጅም ጉዞው የሚሆነው ስንቅ በማኅበረሰቡ እንዲዘጋጅ መደረጉ ማኅበረሰቡ ለዘመናት ጠብቆ ያቆየው አንዱ የባሕል እሴቱ ነው፡፡

ሚች ከጊዜ ሞት በኋላ በቀብሩ ሥነ- ሥርዓት ላይ ወንድ ልጆቹ፣ የሴት ልጆቹ ባሎች እና ወንድሞቹ ከብት የሚቀጠቅጡለት በዳግም ሕይወቱ ላይ በጎ ተጽዕኖ ለማሳረፍ እና ሚቹ በአዲሱ ሕይወቱ የሐብት ችግር እንዳይገጥመው በከብቶቹ እየተጠቀመ በዳግም ሕይወቱን የተሳካ እንዲያደርግ በሚል እምነት ነው፡፡ ይህ የጋራ እና የማኅበረሰቡ እምነት የብሔረሰቡን አባላት አምላክ ቱማ በምድር ላይ እንዲበዙ ካደረጋቸው ዘመን ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ ለትውልዱ ሲተላለፍ ከዛሬው የደረሰ ነው፡፡ ይህ አመለካከት ጠንካራ የባሕል እሴት ሆኖ አሁንም ማኅበረሰቡ እየተጠቀመበት፣ እየጠበቀው፣ እያሳደገው እና እያጠናከረው ያለ ተግባር ነው፡፡ በስነ- ሰብዕ ተመራማሪዎች እሳቤ ፎክሎር የቡድን ሕላዌ ማጠንከሪያ፣ እንዲያም ብሎ ማጽኛና እንደሆነ የሚገለጸው ለዚህም ነው፡፡

በመኤኒት ብሔረሰብ ከሞት በኋላ ላለው ሕይወት ቅድመ ሞት፣ በሞት ጊዜም ሆነ ከሞት በኋላ የሚከናወኑት ተግባራት የብሔረሰቡ የጸና ባሕል እንደሆነ ቀጥሏል፡፡ ለዚህም ይመስላል ባህል ተጠብቆ እንዲኖር ፎክሎር ዓይነተኛ ሚና የመጫወት ተግባር ያለው፡ የመኤኒት ብሔረሰብ ከሞት በኋላ ያለ የዳግም ሕይወት ጅማሬ እሳቤ የማኅበረሰቡን እምነት፣ አመለካከት እንዲሁም እሴትን የማረጋገጥ፣ የማሳደግ እና የማጠናከር ተግባር እየሰጠ ይገኛል፡፡

## 8.3 የማምለጥ ፋይዳ

የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶች ለብሔረሰቡ አባላት ከሚሰጧቸው በርካታ ፋይዳዎች ውስጥ ከዚህ በታች ሁለት ፋይዳዎች ማለትም፤ እውነታን በመሸሽ እና ዘለዓለማዊ ጥያቄዎችን በመመለስ ረገድ ያላቸው ፋይዳ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

### እውነታን ለመሸሽ

በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ፣ ማኅበረሰቡ አምኖ የተቀበላቸው እና ተጠብቀው እንዲቆዩ፣ እንዲፀኑ እና እንዲዘልቁ የሚያደርጋቸው የራሱ እሴቶች አሉ፡፡ እነዚህ ነባር ልማድና እሴቶች አንዳንዴ በአዳዲስና በሞጋች እሳቤዎች ሊፈተኑ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ማኅበረሰቡ አጥብቆና አጥልቆ ስለሚይዛቸው ውጤታቸው ለጊዜውም አይታይም፡፡ በእንደዚህ ዓይነቱ ውስጥ ነባሩን ልማድ የሚሞግትና የሚፈትን አስተሳሰብ ሲነሳ አንዳንዴ የማኅበረሰቡ አባላት በሚቶቹ አማካይነት ከዚያ ፈተናና ተግዳሮት ይሸሻሉ፣ ያመልጣሉ፡፡ አንድ የማኅበረሰቡ አባል ከሱ ቀድመው በተከሰቱ መስተጋድላውያን ታሪክ ውስጥ ራሱን ከዋኝ አድርጎ በሀሳብ እና በምናብ ይጓዛል፡፡ ማኅበረሰቡ ያቆማቸውን አጥሮች እየተሻገረ፣ ቋሚና ዘላቂ የሚመስሉ ሕጎችን እየሻረ፣ ራሱን ከልዕለ ተፈጥሮ አንዳች እርዳታና ኃይል እንደተቀበለ በማስመሰል በምናብ ይሻገራል፡፡ የሚት ታሪኮቹን በመተረክ አይደረሴ የሚመስሉ ቦታዎች ላይ ይደርሳል፣ አይነኬ የሆኑ ጉዳዮችን ይነካል፣ ዋጋ የሚያስከፍሉ ተግዳሮቶችን ይገዳደራል፡፡ ምክንያቱም አፍ አድርጎ የሚናገረው ገድለኞቹን፣ እግር አድርጎ የሚጓዘው መስተጋድላውያኑን እና ሚቶችን ነው፡፡ በሚቶቹ አማካይነት ከተጠያቂነት ያመልጣል፡፡

በሌላም መልኩ የሰው ልጅ ለዘለዓለማዊው ጥያዌዎቹ እና ለሚፈጠሩበት ወይም ተፈጥረው ለሚያገኛቸው እንከኖች፣ ችግሮች፣ ክስተቶች ሁሉ ሚት ባለቤት ስለሚሰጥለት ከአታካችና ከዘወትራዊ ጥያዌው ያመልጣል፡፡ ራሱም ይጠይቅ ከሌላ አካልም ይጠየቅ ያቆመው ሚት መልሱን በመስጠት እንዲያመልጥ ያደርገዋል፡፡ ለማጠቃለል ያህል የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት የብሔረሰቡ አባላት ሊያነሷቸው ለሚችሏቸው የማንነት፣ የየት መጣንነት፣ ከሞት በኋላ ስላለው የሕይወት እና የአጠቃላይ የሕይወት መስተጋብር ስስጋት የራሳቸው መልስ

ያዘጋጁ ናቸው፡፡ በመጠየቅ እንዳይደክም ሚቶቹ መልስ በመስጠት ማምለጫ መንገድ በመሆን ጠቅመውታል፡

## ዘለዓለማዊ ጥያቄዎችን የመመለስ ፋይዳ

የሰው ልጅ ከአቅሙ በላይ ለሆኑት ነገሮች ሁሉ ከለላ ይሻል፣ ታግሎ እንደማያሸንፋቸው ላመናቸው ችግሮቹ ሁሉ የራሱን መፍትሔ ያበጃጃል፡፡ በመሆኑም ተስፋ ቆራጭ እና በቀቢፀ ተስፋ ውስጥ የሚዳክር መሆኑን ሲረዳ፣ በጨለማው ውስጥ ብርሃን የሚያበራለት፣ ከአረንቋው እጁን ይዞ እና መንጥቆ የሚያወጣው ከእሱ የተሻለ አጋር ኃይል ይፈልጋል፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶች ለመኤኒቶች የልዕለ ተፈጥሮ እገዛ የማይለያቸው፣ አምላካቸው ማንኛውንም ችግራቸውን እንደሚፈታላቸው ያስረዳሉ፡፡ ሚቱ ማኅበረሰቡ ደህንነት እንዲሰማው በማድረግ ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ የመኤኒት ማኅበረሰብ በድርቅ የሚመታው፣ ዝናብ የሚጠፋበት፣ በወባ የሚያልቀው ወይም ሌላ አደጋ የሚደርስበት አምላክ ቱማን ሲያስቀይም መሆኑን ሚቶቹ ይተርካሉ፡፡ ስለዚህ ሚቶቹ ለሚነሳው ጥያቄ የራሳቸውን መልስ ይሰጣሉ፡፡ ጥያቄውን ከነመልሱ ያቀርባሉ፡፡ አምላክ ቱማ በኮሞሩቶች እና በኘራዮች ይታረቃል፡፣ የተነሳ በሽታም ይሁን የመጣ ችግር በዚሁ መልኩ ይወገዳል፡፡ በመሆኑም ማኅበረሰቡ አታካች ጥያቄዎች ውስጥ አይገባም፡፡ ሚቶቹ ራሱን አውቆና መፍትሄውን ተገንዝቦ እንዲኖር በማድረግ ከጥያቄና ከመብሰልሰል እንዲወጣ ያግዙታል፡፡ ለምሣሌ በሲዳማ ብሔረሰብ እምነት ሞት ወደ ዓለም የመጣው በቅሎ አምላክ ማጋኖን በመራገጧ ነው [16]፡፡ ለመኤኒቶችም ጥፋት የሚመጣው አምላክ ቱማን በማስቀየም ነው፡፡ የመጡት ጥፋቶች ሁሉ በሚቱ ትረካ ባለቤት ስለተበጀላቸው አዕምሮውን ያሳርፋል፣ ሲጠየቅም መልስ ይሰጣል፡፡

ችግሮች ሲከሰቱባቸው በቅርበት ወደሚያገኟቸው የልዕለ ተፈጥሮ ኃይል ወደተሰጣቸው አካላት በመቅረብና ሽማግሌ በመላክ ችግሮቻቸውን እንዲያስወግዱላቸው ይማጸናሉ፡፡ ዝናብ በታጣበት የኮላይ ምድር አዝናቢዋ ሌማው ጃና፣ ወባ የያርጣና አካባቢውን ሕዝቡን በጨረሰ ጊዜ የወባው ንጉሥ

[16] *በአንዳንድ ማኅበረሰቦች ክፍሎች እምነት፣ በቅሎ የማትወልደው፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ጥላ እንደሆነ ሲነገር በሌላ ታሪክ ደግሞ ሰማይን እረግጣ እንደሆነ ይተረካል፡፡*

ቻሪ፣ የዝንጀሮ መንጋ የጎማ እና አካባቢውን አዝመራ ሊያወድም ባሰፈሰፈ ወቅት የዝንጀሮ ንጉሡ መፍትሄ ሰጥተዋቸዋል፡፡ መኤኒቶች በዘመናት ጉዟቸው እና በትውልድ ሽግግራቸው ሁሉ፣ ለችግር የሚደርሱላቸውን በመማጸን የልዕለ ተፈጥሮ ጥበቃ እንዳላቸው እያረጋገጡ ኖረዋል፡፡ ከብሔረሰቡ የአፈጣጠር ሚት እንደምንረዳው፣ ጥንትም ይሁን ዛሬ መኤኒቶች የልዕለ ተፈጥሮ ጥበቃ እና እገዛ በቅርበት እንዳላቸው እንዲያምኑ በማድረግ ሚቶቹ ዘለዓለማዊ ጥያቄዎቻቸውን ለመመለስ በመቻል ፋይዳቸው ከፍተኛ ነው፡፡

እውነታ በርካታ መገለጫ ቢኖረውም፣ እምነት የየራሱ መመዘኛ ቢያስፈልገውም በአንድ ሁኔታ ላይ ግን መስማማት ይቻላል፡፡ በተፈጥሮ ለሚከሰቱ ነባራዊ ሁኔታዎች፣ መከሰታቸውን ብቻ አንድ እውነታና አንድ ሀቅ ቆጥሮ የተከሰቱበት ምክንያትና ሰበብ ላይ ግን የተለያየ ግንዛቤ ሊኖር እንደሚችል መግባባት ይቻላል፡፡ ጅብ ካሉት የኋላ እግሮች የአንደኛው ማጠር በየትኛም ዘመን እና በየትኛም አካባቢ ባሉ የጅብ ዝርያዎች ላይ  የሚታይ እውነታ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ በአራት እግር ከሚሄዱ እንስሳትና አራዊት ሁሉ ጅብን ለየት ያለ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በዚህ እሳቤ የጅብ አንደኛው እግሩ ስለምን እንዳጠረ የሰው ልጅ ዘመናቱን ሁሉ እየጠየቀ ቢኖር የሚያገኘው ተጨባጭ እና ሳይንሳዊ መልስ አይኖርም፡፡ ነገር ግን በሚት እሳቤ የጅብ የኋላ እግሩ ለምን እንዳጠረ እንደየ ማኅበረሰቡ ታሪክና ባሕል እሴት መልስ ይሰጣል፡፡ ይሄም ከሰርክ እና ከዘለዓለማዊ ጥያቄዎች ማኅበረሰቡ እዲያመልጥ እና መልስ እንዲሆነው ይረዳዋል፡፡

ፎክሎራዊ ጉዳይ መተንተን ያለበት ፎክሎራዊ ጉዳዮች በሚገኙበት የመከወኛ ቦታ፤ በከዋኙ ማኅበረሰብ ባሕል፣ ድርጊቱ በሚከወንበት የድርጊት ጊዜ ውስጥ በመወሰን እንደሆነ የሚገለጸውም ለዚህ ነው፡፡ እንደ ብሔረሰቡ አባላት እምነት ከሞት በኋላ የለው እጣ ፈንታ አንደ ክርስትና፣ አይሁድ እና እስልምና ሃይማኖቶች አስተምህሮዎች አዲስ ዓለም፣ አዲስ የመኖሪያ ወይም ቅጣትን የመቀበያ ቦታ የላቸውም፡፡ ሁሉም ሰው እዚሁ ምድር ላይ ተከልሎ በተሰጠው ‹‹ሞኡ›› በተሰኘው ቦታ ላይ በነባራዊው ዓለም ይኖሩ እንደነበሩት ሆነው ይኖራሉ፡፡ ከብት አርቢው ከብት ያረባል፣ አራሽ ገበሬው ያርሳል፣ ነጋዴውም ይነግዳል፡፡ በመኤኒት ብሔረሰብ የዳግም ውልደት እና የዳግም ሕይወት ጅማሬ

እሳቤ ብዙም ውስብስብ አይመስልም፡፡ የማይዳሰስ እና የማይጨበጥ ዓይነት አይደለም፡፡ ገነትም ይሁኑ ገሐነመ - እሳት ለሕሊና የራቁ እና ወደፊትም የሚገለጡ ናቸው፡፡ እነሱ ከመገለጣቸውም በፊት አሁን እንዳሉ የሚታመኑት ገነት/ጀነት/ እና ሲያል ማለፍ አለባቸው፡፡ የቀዳሚዎቹን እና የኋለኞቹን አንድነት እና ልዩነት፣ ጊዚያዊነት እና ዘለዓለማዊነት ማመስጠርን ያጠይቃል፡፡ ምስላቸውን ለመሳል እና ለአዕምሮ ለማቅረብ እጅግ ረቀቅ እና ጠለቅ ያሉ ምሳሌዎችንና ትኅሜዎችን ይፈልጋል፡፡ ለአዕምሮም ሆነ ለልቡና የመቅረብ እድላቸው በእምነትና በመንፈስ ካልተቃኘ ቀላል አይሆንም፡፡ በመኤኒት ብሔረሰብ ግን ‹‹ሞኡ›› በጥያቄዎቹን ቀለል አድርጎ ይመልሳል፡፡ የብሔረሰቡ አባላት ቀብር የሚችን ፊት ወደ ምሥራቅ የመሆኑ ምስጢር የ‹‹ሞኡ›› በምሥራቅ የምድር ገጽ መገኘትን ያመሰጥራል፡፡ ሚች ወደዚያው ተጓዥ በመሆኑ ሲነሳ መንገድ እንዳይስትም የሚጠቅመው ይመስላል፡፡

በመኤኒት ብሔረሰብ የዳግም ውልደት እና የዳግም ሕይወት ጅማሬ ሚት የማኅበረሰቡ አባላት ከሞት በኋላ ምን እንሆናለን፣ ወዴት እንሄዳለን ለሚለው ዘለዓለማዊ ጥያቄ መልስ በመስጠት ለማኅበረሰቡ የረፍት ቦታ ፈጥሮላቸዋል፡፡

በተጨማሪም ለመኤኒት ብሔረሰብ ዲዚ፣ ሽኮ፣ ቤሩ፣ ዚልማሞ፣ ሱርማ እና ቤንች የተሰኙ ብሔረሰቦች አጎራባቾቹ ናቸው፡፡ ከእነዚህ አጎራባቾቹ ብሔረሰቦች ተለይቶ፣ በስም፣ በኃይማኖት፣ በቋንቋ እና በባሕል በራሱ ማንነት የቆመ ነው፡፡ የዚህን ልዩነቱ ከየት መጣነት፣ የብሔረሰቡ የአፈጣጠር ሚት መልስ በመስጠት ፋይዳው ትልቅ ነው፡፡ ለምሳሌ የብሔረሰቡ መነሻ አካባቢ ተብሎ በሚታመነው የደቡብ ኦሞ አካባቢ ካሉት ሕዝቦች ውስጥ የሐመር ብሔረሰብ አምላክ ቦርጆ ነው፡፡ ሰማይና ምድርን እንዲሁም ሐመሮችን የፈጠረው እሱ ነው፡፡ መኤኒቶች ደግሞ እንደፈጠራቸው የሚያምኑት አምላክ ቱማ ነው፡፡ በመልክአ ምድር ብዙም ባልተራራቁ ሕዝቦች መሐል እንዲህ ዓይነቱ የአፈጣጠር ሚት ልዩነት በብዙ ቦታ ያለ ቢሆንም የቁም ነገር ማጠንጠኛው ሚቶቹ ያላቸው የልዕለ ተፈጥሮ ጥበቃ፣ ለሚቱ እውነታዎች መሸሻ እና ለዘለዓለማዊ ጥያቄዎች መልስ የመስጠት ፋይዳቸው ነው፡፡

## 8.4 የማስተማር ሚና

ፎክሎር የማኅበረሰቡን እሴት ማስተበቂያ ሁነኛ መንገድ ከሚሆንባቸው መልኮች አንዱ የማስተማር ሚናው ከፍ ያለ በመሆኑ ነው፡፡ አንድ ማኅበረሰብም ይሁን ከዚያ ከፍ ያለ የፎክ ቡድን የራሱ የሆኑትን መለያ እሴቶች አስጠብቆ የሚሄደው ዘላቂ እና ጠላቂ እውቀቶችን ለማኅበረሰቡ አባላት ማስተማርና ማስተላለፍ ሲችል ነው፡፡ በዚህም የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶች ማኅበረሰቡን በማስተማር ፋይዳቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ በታች የብሔረሰቡ ሚቶች ከሚሰጧቸው ልዩ ልዩ የማስተማር ፋይዳዎች ውስጥ ሃይማኖትን፣ ታሪክን፣ ባሕልን፣ የማኅበረሰቡን መልካም እሴቶች የማስተማር ፋይዳ ነው፡፡

አንድ ማኅበረሰብ የራሱ የሆኑ እና ካለፉት ትውልዶች የተቀበላቸው፣ አሁን እሱ የሚተዳደር የሚገዛባቸው፣ ወደፊትም ለትውልዱ ሊያወርሳቸው የሚጠብቃቸው ልዩ ልዩ ሃይማኖት፣ ታሪክ፣ ባሕል፣ የመልካም እሴቶች ቁቦች አሉ፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶችም የብሄረሰቡ አባላትን ስለ አፈጣጠራቸው፣ ስለዘራቸው አመጣጥ፣ ስለ ብሔረሰቡ ታሪክ፣ ስለ አምላካቸው ማንነት እና እነሱን ስለመፍጠሩ ያስተምራሉ፡፡ የመስተጋድላውያን ታሪክ ዋቢ በማድረግ እና በመጥቀስ አርአያቸውን እንዲከተሉ ያስገነዝባሉ፡፡ መኤኒቶችን አምላክ ቱማ ስለመፍጠሩ፣ ለልጅ ልጅ የሚተረፍ በረከትና ጸጋን እንደሰጠ እና ይሄም በኮሞሮቶቻቸው እና በኘራዮቻቸው እንደሚገለጽ ያስረምራሉ፡፡

የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶች ለብሔረሰቡ አባላት ስለ ይቅርታ በማስተማር ከፍተኛ ፋይዳ ይሰጣሉ፡፡ እንደ ብሔረሰቡ አባላት እምነት ማንኛውም እነሱን የሚያጋጥሟቸው ችግሮች መነሻቸው ሁለት ነው፡፡ አንደኛው ሕዝቡ በአምላክ ቱማ የተለየ ፀጋ የተሰጣቸውን ሰዎች ሲያስከፉ፣ ሁለተኛው ደግሞ ፈጣሪያቸውን ቱማን ሲያስቀይሙ እና ሲበድሉ ነው፡፡ በእነዚህ መንገዶች የተሠሩ ስህተቶች በብሔረሰቡ አባላት ላይ ጉዳት ሲያስከትሉ፣ የብሔረሰቡ አባላት ጉዳቱ የደረሰባቸው በጥፋታቸው እንደሆነ ያምናሉ፡፡ አምላካቸውንም ይሁን እርሱ ፀጋ የሰጣቸውን ሰዎች ካስቀየሙ ራሳቸውን ለይቅርታ ያዘጋጃሉ፡፡ ለዚህም ከማኅበረሰቡ ውስጥ የተከበሩ፣ በንግግራቸው የሚደመጡ፣ በተላኩበት ጉዳይ ተቀባይነት የሚኖራቸው ሰዎች በመላክ ይቅርታን ይጠይቃሉ፡፡ በመሆኑም

ብሔረሰቡ ይቅርታ መጠየቅን እሴቱ አድርጎት ይታያል፡፡ የዚህ መሠረቱ ደግሞ የብሔረሰቡ ሚት ነው፡፡

በብሔረሰቡ አንዲት ሴት የራሷ ካልሆነ ወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ብትፈጽም፣ ከድርጊቱ በኋላ ራሷ ያደረገችውን ሥራ ለባሏ ትናገራለች፡፡ ደብቃ ብትቆይ በስውር የሠራችውን በግልጽ የሚያየው አምላክ ቱማ ከበድ ያለ ቅጣት በእሷ፣ በልጆቿ፣ በዘመዶቿ እንዲሁም በሀብት በንብረቷ ላይ ስለሚመጣ የሆነውን ሳትደብቅ ትናገራለች፡፡ ከሴቷ ጋርም ድርጊቱን የፈጠረው ወንድ ሴቷ ድርጊቱን እንደማትደብቅ ስለሚያውቅ ለተሠራው ስህተት ወደ ሽማግሌ ሄዶ ይቅርታ በመጠየቅ፣ እንዲያማልዱት፣ የበደለውን ሰው ለመካስ ይዘጋጃል፡፡ በዚህ ሒደት ውስጥ በዳይ እና ተበዳይ በሽማግሌ ፊት ቀርበው በዳይ ተበዳይን ይቅርታ ይጠይቃል፡፡ ከዚህም በላይ አስታራቂ ሽማግሌዎች የሚወስኑበትን ገንዘብ እና አንድ ከብት በካሳ መልክ ይሰጣል፡፡ ሴቷም ለዚሁ ድርጊት ማመሳከሪያ በሚሰዋው በግ ወይም ፍየል ደም ታጥባ ትነጻለች፡፡ ከዚህ የይቅርታ እና የዕርቅ ክንውን በኋላ ባል ሚስቱን ይዞ ወደቤቱ ይሄዳል፡፡ በደም ታጥባለች እና ያለፈ ኃጢያቷም ዳግም አይነሳም፡፡ አጥፊውም ይቅርታ ጠይቆ፣ በደም አጥቦ ክሷልና ሁለቱ ወንዶች በመንገድ፣ በገበያም ሆነ በሌላ ማኅበራዊ ዐውድ ቢገናኙ የተፈጸመውን ድርጊት አንስተው አይወቃቀሱም፣ በጠብም አይፈላለጉም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ እሴት የዳበረውም በሚቶቹ አማካይነት በመሆኑ የሚቶቹ ፋይዳ ብሔረሰቡ ለቆመባቸው እሴቶች  መሠረት መሆኑን ጭምር የሚገለጥ ነው፡፡ በዚህም የማኅበረሰቡ አባላት በድሎም ሆነ ተበድሎ ይቅር ማለት እንደሚቻል ያውቃሉ፡፡

የሰው ልጅ በእለት ከእለት የሕይወት መስተጋብሩ እንኳን ከሰው ጋር ከራሱ ጋር የሚጣላና የሚጋጭ ፍጡር በመሆኑ፣ በሰዎች መካከል በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠረው ጸብ ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የመኤኒት ሚት ይሄንን ተፈጥሯዊ ጸብ በማብረድ የይቅርታ መንፈስን በማስፈን የሚሰጡት ፋይዳ ሁሉንም የሚያስተምር ነው፡፡ በተለይም ህጻናት እና አዳጊዎች እንዲህ ዓይነቱን መልካም እሴት ከመነሻቸው ጀምሮ እያዩት ስለሚያድጉ ሚቱ በውስጣቸው እንዲሰርጽ በማድረግ የማስተማር ሚናው የጎላ ነው፡፡ በሌላም መንገድ ከመስተጋድላውያኑ በሚወስዱት አርአያነት ራሳቸውን ያስተምራሉ፣ ያጠነክራሉ፣

፡ መስተጋድላውያኑ እንደተጋፈጡት ችግርን መጋፈጥና ማለፍን ይማራሉ፡፡ የያርጣ ቀበሌዋ ታዳጊ ሞናይ የወሰደችው የአልሞት ባይ ተጋዳይነት ለብዙዎች ምሣሌ ሆኗል፡፡ ራሷን ከአዞ አፍ አትርፋ፣ አባቷ ካቀረበላት የስቅላት ሞት ተርፋ፣ የአባቷን ጠማርና በነባር ሚት አዳሪነት አለሳልሳና አሳምና፣ ለዚህም ተባባሪ አድርጋ ሕይወቷን ማስቀጠሏ ለሌሎች አስተማሪነቱ የጎላ ነው፡፡ በባህል መስተጋድላውያን ሚት ትረካ ብዙዎቹ ልጆቻቸውን ለሞት አለመስጠትን ተምረዋል፡፡ አዳጊዎችም አንዳች የማምለጫ ቀዳዳ እንዳለም እንዲረዱ አድርጓቸዋል፡፡ ይሄም ሚቱ ማኅበረሰቡን በማስተማር ረገድ ያለው ፋይዳ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሕይወት በዚህ ምድር ብቻ እንደማያበቃ፣ ይልቁንም የዚህ ገሀድ ዓለም ነጸብራቀ የሆነ ዓለም መኖሩን ሚቱ ያስተምራል፡፡ በዚህ ገሀዳዊ ዓለም ሀብት አፍርቶ መኖር ለቀጣይም ሕይወት እንደዋስትና መሆኑን በማሳየት ማኅበረሰቡን በማስተማር ዋጋው ከፍ ያለ ነው፡፡

## 8.5 የመግታትና የመቆጣጠር ሚና

የአንድ ማኅበረሰብ ሚቶች ለማኅበረሰቡ ከሚሰጡት ፋይዳ አንደኛው የመግታት እና የመቆጣጠር ሚና ነው፡፡ ሚቶቹ ማኅበረሰቡ መሠረት አድርጎ የቆመባቸው ልዩ ልዩ እሴቶቹ ተጠብቀው እና ተከብረው እንዲዘልቁ ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በሚቶቹ አማካይነት ችግሮች እንዳይፈጠሩ ለመግታት ሲያገለግል፣ ከተፈጠሩም ለመቆጣጠር እና የማስወገድ ሚናን ይጫወታል፡፡ እንደመኤኒት ብሔረሰብ እምነት የሚጥል በሽታ የአምላክ ቁጣ ነው፡፡ በዚህ በሽታ የተያዘ ሰው እንደ እርጉም ስለሚቆጠር እጣ ፋንታው፣ ዕድል ተርታው መወገድ ነው፡፡ በሽታው ተላላፊ ነው ተብሎም ስለሚታሰብ በሽተኛውን መንካት መልሶ በበሽታው መለከፍ ተደርጎ ስለሚወሰድ ራሳቸውን ያርቃሉ፡፡ ነባሩ ልማድና እምነት ብዙዎቹ ላይ ተጽዕኖው ከፍተኛ ነው፡፡ ሞናይ በበሽታው መያዟ እጣ ፈንታዋ መሪር እንዲሆን አድርጓል፡፡ ሚቱ እጣ ፈንታዋን ደንግጎታል፣ መገደልና መወገድ የተጻፈላት ነው፡፡ ወላጅ አባቷም ያንን ማስፈጸም ግዴታው ነው፡፡ ያ ካልሆነ በማኅበረሰቡ የመገለል ዕጣውን ሚቱ ወስኖታል፡፡ ለዚህም ነው አባት ልጁን ታላቅ ወንዝ ዳርቻ ወስዶ በእንጨት ገፍቶ የጣላት፣ ሚቱ ያን እንዲያደርግ ይቆጣጠረዋልና፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ታላላቅ የሆኑ ወንጀሎች እንደ መግደል፣ የራስ ካልሆነች ሴት ጋር ወሲብ መፈጸም፣ ስርቆሽ

ወዘተ… እንዳይከሰቱ የመግታትና የመቆጣጠር ፋይዳም አለው፡፡ እነዚህ ለብሔረሰቡ አባላት የመኖርና የሕልውና አደጋ የሆኑ ተግባራት ከተፈጸሙም በቶሎ ለመግታትና ለመቆጣጠር የሚቶቹ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ አጥፊ እንዳይኖር፣ ጥፋትም ከተፈጸመ ለመቆጣጠር ከፍተኛ ጠቀሜታ እየሰጡ ነው፡፡

እውነትን መናገር የመኤኒት ብሔረሰብ ዋና እሴቶች ከሆኑት ውስጥ አንዱ ነው፡ ፡ መኤኒቶች ጥፋት አጥፍተው እንዳይዋሹ፣ በጥፋታቸው የሚመጣውን ቅጣት ተቀብለው ሕይወታቸውን በእርቅና በካሳ እንዲቀጥሉ ሚቱ ይቆጣጠራል፡፡ ከመረጃና ማስረጃ ርቀው፣ በድብቅ የተሠሩ ወንጀሎች እንዲጋለጡ የሚያደርግን ሥርዓት ሚቱ በመዘርጋቱ እውነት በብሔረሰቡ አባላት ዘንድ ዋጋዋ ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡ አልፎ አልፎ የሚከሰቱ መካካዶችን እና ስውር ጥፋቶችንም የማስወገድ ሚናው ከፍተኛ ነው፡፡ በኮሞሮቶች እና በኘራዮች ፊት መዋሸት የሚያስከትለው ጣጣ ከፍተኛነት በብሔረሰቡ አባላት ዘንድ ስለሚታወቅ ከአምላክ ቱማ በተሰጠ ስልጣን የኮሞሮቶች እና የኘራዮች እጅን በሀሰት መምታትና መማል እንዳይኖር ሚቱ ጥልቅ እና ጥብቅ ሥርዓት በማበጀቱ እንዲህ ዓይነቶችንም ችግሮች በመግታትና በመቆጣጠር የብሔረሰቡ እሴቶች ቀጣይነት እንዲኖራቸው የሚቱ ፋይዳ ከፍ ያለ ነው፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የመኤኒት ብሔረሰብ የሚት ዓይነቶችን ለይቶ መግለጽ እና የሚቶቹን ፋይዳ መርምሮ ውጤቱን ማሳየት ዐቢይ ዓላማ አድርጎ የተነሣና ጥናት ነው፡፡ በብሔረሰቡ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና የሚት ዓይነቶች ለይቶ ተንትኗል፡፡ በሚቶቹ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ ትዕምርቶችም ፈክሯል፣ የብሔረሰቡ አባላት ለሚቶቹ ያላቸውን አመለካከት እና የሚቶችን ማኀበረሰባዊ ፋይዳ በዝርዝር አሳይቷል፡፡

ጥናቱ የመኤኒት ብሔረሰብ የሚት ዓይነቶችን ለይቶ የገለጸ ሲሆን፣ በውጤቱም በብሔረሰቡ ውስጥ የሚገኙ የሚት ዓይነቶች የአፈጣጠር ሚት፣ መንፈሳዊ ሚት፣ የመስተጋድላውያን ሚት እና የድግም ውልደት ሚት መሆናቸውን አሳይቷል፡፡ የብሔረሰቡ የአፈጣጠር ሚት ለብሔረሰቡ አባላት ከየት እንደመጡ እና የሚኖሩበትን ዓለም ማን እንዳስገኘው መልስ በመስጠት ብሔረሰባዊ እፎይታ ሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም መንፈሳዊ ሚቱ የፈጠራቸው አምላክ ቱማ መሆኑንና ከመፍጠር ባሻገር በምድር ላይ ሲኖሩ ሊገለገሉበት የሚችሉበትን ጥበብ እንደሰጣቸው ያስረዳል፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ አምላክ ቱማ ለሰዎች ቅርብ የነበረ ቢሆንም አሁን በኘራዮች እና በኮሞሮቶች አማካይነት ምሕረትና ቅጣትን እየላከ እንደሚያኖራቸው ይገልጣል፡፡ የብሔረሰቡ የመስተጋድላውያን ሚት በተጋድሏቸው የማኀበረሰቡን ችግር በመፍታት እና የራሳቸውንም የገድል ጥሪ በመቀበል በተጋድሏቸው ስለ ፀኑ የባሕል መስተጋድላውያን በመተረክ ሌሎች እንዲማሩና አርአያነታቸውን እንዲከተሉ አስችሏል፡፡ በየዳግም ውልደት ሚታቸው መኤኒቶች "ከሞት በኋላ ወዴት እንሄዳለን፣ ምን እንሆናለን?" ለሚሉ ጥያቄዎቻቸው መልስ ሰጥተዋቸዋል፡፡ መኤኒቶች ከሞት በኋላ ሕይወትን የሚቀጥሉበት ምድር ላይ የሚገኝ ሞኡ የተሰኘ ስፍራ እንዳላቸው እንዲያውቁ እና የጊዜ እሳቤያቸውም ቀጥተኛ መሆኑን ጥናቱ ገልጿዋል፡፡

ጥናቱ በሁለተኛ ደረጃ በብሔረተሰቡ ሚት ውስጥ ያሉ ትዕምርቶችን ፍካሬ አሳይቷል፡፡ የብሔረሰቡን ሚቶች ለመረዳት፣ ተናጠላዊ ባህሪያቸውንና መልዕክታቸውን ለመመርመር በሚቶቹ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ ትዕምርቶች ተፈክረዋል፡፡ የትዕምርቶቹ ፍካሬዎች በትንተናው ውስጥ የተገለጹ ሲሆን፣ በሚቶቹ ውስጥ የሚገኙ ትዕምርቶች ፍካሬ ብሔረሰቡ ለሚቶቹ ያለውን አመለካከት ለመረዳትና ሚቶቹም የሚሰጡት ፋይዳ ለማወቅ አግዟል፡፡

አንድ መኤኒት ሲሞት ወተት እንዲጠጣ ይደረጋል፡፡ የዚህ ትዕምርት ፍካሬ ሟች የሩቅ ተጓዥ በመሆኑ፣ የጥንት አባትና እናቶቹ ወደሚኖሩበት ቦታ (ሞኡ) ስለሚጓዝ አስቀድሞ ስንቅ እንዲይዝ ነው፡፡ ምክንያቱም ሟች በጉዞው ርሀብና ጥም እንዳያሸንፈው ለማገዝ ነው፡፡ እንደዚሁ የመኤኒት ሰው ሲሞት ፊቱን ወደ ሞኡ አቅጣጫ ተደርጎ ይቀበራል፡፡ የዚህም ትዕምርት ፍካሬ ሰውዬው ከሞት በኋላ በአዲስ መልክ ሕይወቱን ወደሚቀጥልበት ወደ ሞኡ ለሚያደርገው ጉዞ የአቅጣጫ ችግር እንዳያጋጥመው እና እንደተነሳ እንዲጓዝ በማሰብ ነው፡፡ በብሔረሰቡ የሚገኙ ዝናብ አዝናቢዎች በማኅበረሰቡ ተከፍተው ዝናብ እንዳይዘንብ ካደረጉ በኋላ ሰውነታቸውን ቀዝቃዛ ውኃ እንዳይነካው ይጠነቀቃሉ፡፡ የዚህ ትዕምርትም ፍካሬ የእነሱን ገላ ቀዝቃዛ ውኃ ከነካው የሞቀው ሰማይ ቀዝቅዞ፣ ደመና ይመጣል በሚል እምነት ነው፡፡ ዝናብንም ለማዝነብ ሲፈልጉ ከሚያደርጉት ሥራ አንዱ ሰውነታቸውን በዶሮ ደም ተቀብተው መልሰው በቀዝቃዛ ውኃ ወይም ብዙውን ጊዜ በወንዝ ውኃ መታጠብ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኮላይ ቀበሌ ኗሪ የሆኑት የዝናብ ንግሥቷ ወ/ሮ ሌላው ጃና ዝናብ ያዘነቡት በጥቁር ዶሮ ደም ሰውነታቸውን ከተቀቡ እና ከታጠቡ በኋላ ነው፡፡ የዚህ በጥቁር ደም የመታጠብ ትዕምርት ፍካሬ፣ የዶሮው መጥቆር ማኅበረሰቡ የተሠራው የክፉ ሥራ ምሳሌ ሲሆን፣ ደሙን በሰውነታቸው ላይ መቀባታቸው የማኅበረሰቡን ችግር እሳቸው መቀበላቸውን ሲያጠይቅ እንደገና መታጠባቸው ደግሞ ከችግር፣ ከበደል የመንጻት ምልክት መሆኑን ጥናቱ አብራርቷል፡፡

ጥናቱ ካሳያቸው ውጤቶች ውስጥ በሦስተኛው ማኅበረሰቡ ለሚቶቹ ያለውን አመለካከት ማሳየት ነው፡፡ በመሆኑም የመኤኒት ብሔረሰብ የማንነት መገለጫው ለሆኑት ሚቶቹ ክብር እና ተገዥነት እንዳለው ሚቶቹን እንደሚጠብቅ፣

እንደሚያጸና እና እንደሚያስተላልፋቸው አሳይቷል፡፡ ብሔረሰቡ ከፍተኛ መንፈሳዊ እና ዓለማዊ ሥልጣን ያላቸውን፣ ከአምላክ ረድኤትና በረከት እንደተቀበሉ የሚያምናቸው ሰዎች እንደሚያከብር እንዲሁም ለችግሩ ደራሽ እንደሆኑ እንደሚያምን ይገልጻል፡፡ ቃላቸውን ይሰማል ቁጣቸውን፣ ተግሳጻቸውንና እርግማናቸውን ይፈራል፡፡ በመሆኑም በፊታቸው ሲቀርብ በአክብሮት ሲሆን እነሱን መዋሸት እና እጃቸውንም በውሸት በመሀላ መምታት ከፍተኛ እርግማን እንደሚያመጣበት ያምናል፡፡ የተፈጥሮም ይሁን ሰው ሰራሽ ችግር ሲያጋጥመው ወደ እነሱ ፈጥኖ በመሄድ መፍትሔ እንዲፈልጉለት ይጠይቃል፡፡ መፍትሔ ሲሰጡትም ያመሰግናል፡፡ የኮላይ ቀበሌ ሕዝብ ዝናብ ሲያጣ ወደ ወ/ሮ ሌማው፣ የያርጣ ቀበሌ ኗሪዎች የወባ ወረርሽኝ ሲፈጃቸው ወደ ኮሞሮት ቻሪ፣ የጨበራና አካባቢው ሰው የዝንጀሮ መንጋ ሰብሉን ሲያወድምበት ወደ የዝንጀሮ ንጉሥ አቶ ሴላ በመሄድ መፍትሔ እንዳገኙ ጥናቱ ተንትኖ አሳይቷል፡፡

ብሔረሰቡ የሚጥል በሽታ እርግማን ነው ብሎ ስለሚያምን ሕጻናትን አንቆ እስከመግደል ወይም አርቆ እስከመጣል በመድረስ ለሚቶቹ ታማኝ ይሆናል፡፡ የያርጣ ቀበሌ ኗሪ የሆኑት ወ/ሮ ኮራይ እና ወጣቷ መስተጋድል ሞናይ ማኅበረሰቡ የሚያምንበትን ሕግ በመቃወማቸው ሊደርስባቸው የሚችለውን ሞት ተጋፍጠው አካባቢያቸውን ለቅቀው እስከመሰደድ መድረሳቸውን ጥናቱ ያሳያል፡፡

ጥናቱ የመኤኒት ብሔረሰብ ሚቶች ለማኅበረሰቡ እየሰጡ ያሉትን ልዩ ልዩ ፋይዳዎችን በዝርዝር አብራርቷል፡፡ ከእዚህም ውስጥ የመግለጥ ፋይዳው አንደኛው ነው፡፡ ሚቶቹ የዓለምንና የሰውን አፈጣጠር (ምስቅልቅሉን ዓለም ሥርዓት የማስያዝ)፣ የአምላክ ቱማን ማንነት እና ከሰው ጋር ስላለው ግንኙነት፣ ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ሕይወት እንዴትነት፣ የልዕለ ተፈጥሮ እርዳታና ኃይል ስላላቸው ሰዎች እንዲሁም ስለባሕል መስተጋድላውያን ሥራና ተግባር የመግለጥ ፋይዳዎችን ተተንትነዋል፡፡ የብሔረሰሰቡ ሚቶች ለብሔረሰቡ አባላት ከሰጧቸው ፋይዳዎች ውስጥ የማጠናከር እና የመትከል ፋይዳ ሌላው ነው፡፡ በዚህም ሚቶቹ፤ ማኅበረሰባዊ መዋቅርን የመገንባት፣ የሥልጣን ክፍፍል እንዲኖር የማድረግ፣ የሥልጣን ሽኩቻን የማስወገድ፣ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን

አንድ የማድረግ፣ ማኅበራዊ ትስስርን የማጥበቅ፣ የደን እና የእንስሳት ሀብትን የመጨመር፣ እምነቶችን፣ አመለካከቶችን፣ እሴቶችን፣ የማረጋገጥ፣ የማሳደግ እና የማጠንከር ፋይዳዎች መስጠታቸው በጥናቱ ተብራርቷል፡፡

ሌላው የብሔረሰቡ ሚቶች ፋይዳ ከሆኑት ውስጥ የማምለጥ ፋይዳ ነው፡፡ የብሔረሰቡ አባላት በተፈጥሮም ይሁን በድንገት ለሚከሰቱባቸው እንደ የዝናብ ማጣት፣ ወረርሽኝ፣ ርሀብ እና መሰል አጠቃላይ ችግሮች ምክንያትን በመፈለግ፣ ጥያቄዎችን እያነሱ፣ እየተሟገቱ አይኖሩም፡፡ ምላሽ ፍለጋ ከመባተል ይልቅ ችግሮቹ ሊፈጠሩ የሚችሉባቸውን አጠቃላይ መነሾዎች ያስቀምጣሉ፡፡ ጉዳዩን ከፈጣሪ እና ከፈጣሪ ጋር የቀረበ ትስስር ወዳላቸው ኀራዮች እና ኮሞሮቾች በማስጠጋት እነሱ ከጥያቄውም ሆነ ከተጠያቂነት ይሸሻሉ፡፡ በመሆኑም ሚቶቹ የሰርክ ጥያቄዎችን በመመለስ ማኅበረሰቡ ከጥያቄው እንዲያመልጥ በማስቻል ፋይዳ እንዳላቸው በጥናቱ ታይቷል፡፡

ማስተማር ሌላው የሚቶቹ ፋይዳ እንደሆነ ጥናቱ ይገልጻል፡፡ ብሔረሰቡ ሚቶቹን ለዘመናት የጠበቃቸው የማንነት መገለጫዎቹ፣ ታሪኮቹ፣ ባሕሎቹ እና ልዩ ልዩ እሴቶቹ ተጠብቀው እንዲኖሩ፣ በቀጣይም ለትውልዱ እንዲሸጋገሩ በማድረግ ለብሔረሰቡ አባላት የማስተማር ሚናቸው የጎላ እንደሆነ በጥናቱ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

በመጨረሻም የብሔረሰቡ ሚቶች የመግታትና የመቆጣጠር ፋይዳ እንዳላቸውም ጥናቱ ያሳየ ሲሆን፣ ብሔረሰቡ በሚቶቹ አማካይነት ግለሰቦችንም ይሁን ቡድኖች በባሕሉ፣ በእምነቱ፣ በእሴቶቹ እና በልማዶቹ ሥር እንዲኖሩ የመቆጣጠር፣ የተጣሱ ሕጎችን የማስከበር እና እንዳይፈጠሩም የመግታት ሚና ለማኅበረሰቡ እየሰጡ እንደሆነ አብራርቷል፡፡

ይህ የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት መጠናቱ ብሔረሰቡን ማዕከል አድርገው ለሚወጡ ልዩ ልዩ የልማት እና የባሕል ፖሊሲዎች እንዲሁም በብሔረሰቡ ላይ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ አካላት እንደ ግብአት በመሆን ያገለግላል፡፡ ከዚህ አንጻር የብሔረሰቡ ሚቶች እንዲጠበቁ፣ ማኅበረሰባዊ ፋይዳቸውም የበለጠ

እንዲጎላ፣ አንዳንዶቹ ልማዶች ደግሞ እንዲሻሻሉ ከዚህ በታች ያሉት የይሁንታ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

1. እንደ ሌማው ጃና ዓይነት ዝናብን የማዝነብ ኃይል ከፈጣሪ የተሰጣቸውን መስተጋድላውያን፣ የተሻለ እውቅና በመስጠት ኃይላቸውን እና ጥበባቸውን ለማኅበረሰባዊ እድገትና ስልጣኔ እንዲያበቁት ማበረታታት ቢቻል፡፡
2. እንደ የዝንጀሮ እና የወባ ንጉሦችን ዓይነት የልዕለ ተፈጥሮ እገዛ እንዳላቸው ማኅበረሰቡ የሚያምናቸው ሰዎች፣ ማኅበረሰቡን ከልዩ ልዩ በሽታዎች የሚጠብቁ እና የሕዝቡ ሰላም ተከብሮ እንዲኖር የሚያደርጉ በመሆናቸው የሚጫወቱት ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም የመንግሥት አካላት ለሥራቸው እውቅና በመስጠት ድጋፍ ቢያደርግላቸው፡፡
3. የባሕል ሃይማኖት መሪዎቹና ኮሞሮቶች ማስረጃ የሌላቸውን ወንጀሎች በማውጣት ረገድ ያላቸው ማኅበረሰባዊ ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ ከመንግሥት አካላት በተለይም ከዘመናዊው የፍትሕ ሥርዓት ጋር ትስስር እንዲያደርጉ እና መዋቅራዊ በሆነ መንገድ እንዲሠሩ ቢደረግ፡፡
4. እንደ የሚጥል ዓይነት በሽታዎች በማኅበረሰቡ ዘንድ በስፋት የሚከሰቱ ናቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ በሽታ በብሔረሰቡ ዘንድ በስፋት የሚከሰትበት ሰበብ ምን እንደሆነ ሳይንሳዊ ጥናት ቢደረግበት እና መፍትሔ የሚሆን ነገር እንዲመጣ ትኩረት ቢሰጥበት፡፡
5. የሚጥል በሽታ በማኅበረሰቡ ዘንድ የአምላክ ቁጣ እንደሆነ እና ተላላፊ በሽታም እንደሆነ ይታመናል፡፡ በዚህም ምክንያት በርካታ ህጻናትና ታዳጊዎች ሲገደሉ እና ሲጣሉ ኖረዋል፡፡ ይኸንን አስተሳሰብ ለማስቀረት እና በሽታው ተላላፊ አለመሆኑንም ለማስረዳት ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ይሁን እንጂ ሥር የሰደደ እና የኖረ እምነት በመሆኑና ከከተማ በራቁ የቆላ አካባቢዎችም በስፋት ችግሩ ስለሚታይ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በተሻለ እና በተደራጀ መልኩ ድጋፍ ቢያደርጉ፡፡

# ማረጋገጫ

ይህ የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ የሚለው ጥናት የእኔ መሆኑንና በጥናቱ ውስጥ የጠቀስኳቸውን መረጃዎች በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

**ስም** ---------------------------------------------

**ፊርማ** -------------------------------------------

# የተጠቀሱ ምንጮች


ሕይወት አበሩ፣ "የለቅሶ ሥርዓት በመኤኒት ብሔረሰብ"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለማስተርስ ዲግሪ ሟሟያነት የቀረበ፣ 2004፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ፣ 19 62 ዓ.ም ዕትም፡፡

ስንታየሁ አባተና ብርሃኑ አድማስ፣ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/በሰ/ት/ ቤቶች ማደራጃ መምሪያ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 1996ዓ.ም.

ባይለየኝ ጣሰው፣ *የአኙዋ ተረቶች*፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1995 ዓ.ም.

ቤታና ሆጤሶ፣ *የሲዳማ ሕዝብና ባሕሉ፤* አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም.

ቴዎድሮስ ገብሬ፣ *በይነ-ዲስፒሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ፤* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ አዲስ አበባ፣ ፪ሺ.ህ፬

አንዱዓለም አባተ፣ "ባህላዊ የግጭት አፈታት በመኤኒት ብሔረሰብ"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ሟሟያነት የቀረበ፣ 2004፡፡

ኪዳነወልድ ክፍሌ፣ *መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ፤ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፡* አርቲስትቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948 ዓ.ም.

ዳንኤል አለባቸው፣ "ጋብቻ ትውፊት በመኤኒት ብሔረሰብ"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ሟሟያነት የቀረበ፣ 1984፡፡

ፈቃደ አዘዘ፤ የሰነቃል መምሪያ፣ አዲስአበባ፤ ኢተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም፣ 1991፡፡

Abbink, Jon. “The Deconstructions of Tribe: Ethnicity and Politics in South Western Ethiopia.” *Journal of Ethiopian Studies.* Vol. 24,1991. pp.1-21.

______. “An Ethno-Historical Perspective on Me’en Territorial (Southwest Ethiopia).” *Anthropos.* Vol. 87, No.4/6,1992. pp.351-364.

______. “The Final Rite: Burial Among the Me’en of South-West Ethiopia.” *Proceedings of First International Conference of Ethiopian Studies, April 11-2,1990*. Eds. Pankhurst, Richard, Ahmed Zekaria and Taddese Beyene. Addis Ababa: IES, 1990. pp.65-75.

______. “The Me’en as Historical Transformation of the ‘Surma’: Preliminary Notes on Society and Culture.” *Proceeding of Ninth International Conference of Ethiopian Studies.* Vol. I. Section II: East Africa.Moscow: Nauka Publishers,1986, pp.177-207.

______. *The Me’en of South-western Kafa: Material Culture on Ethiopian Shifting — cultivator*, Addis Ababa: Addis Ababa University Press, 1992.

______. “Me’en Ritual, Medicinal and Other Plants: A Contribution to Southwest Ethiopian Ethno-Botany.” *Journal of Ethiopian Studies*. Vol. 26, No. 2,1993. pp. 1-21.

_______. “Ritual and Environment: The Mosit Ceremony of the Ethiopian Me’en People.” *Journal of Religion in Africa.* Volume 25, No.2,1995. pp.163-190.

________. “Tribal Formation on the Ethiopian Fringe: Toward a History of the ‘Tishana’.”, *Northeast African Studies*. Vol.12, No. 1, 1990. pp.21-43.

Aweke Hamzaye, “Mosaic Culture and Peoples of South Nation’s Nationalities and Peoples, Regional State. Hawassa:” Africa printing PLc, 2007.

Bascom, William R. “Four Functions of Folklore”. *The Journal of American Folklore.* 1954.

________. “THE FORMS OF FOLKLORE: PROSE NARRATIVES”, *The Journal of American Folklore,* Vol. 78, No. 307 (Jan. - Mar., 1965), pp. 3-201354, 9600 Garsington Road, Oxford OX4 2DQ, UK.

Bayleyegn Tasew, “Anyuaa Oral Prose Narratives Ethnic Generes and Social Funcitions”, Master‘s Thesis, University, Departement of Foreign Language and Litereature, Addis Ababa. 1999.

Brian Richardson, “Recent Concepts of Narrative and the Narratives of Narrative Theory”, Volume 34, No, 2, University of Maryland, 2000.

Brown, Timothy J. “Deconstructing the Dialectical Tensions in The Horse Whisperer: How Myths Represent Competing Cultural Values”,

*The Journal of Popular Culture,* Vol. 38, No. 2, Blackwell Publishing, USA, 2004.

Bryant, Megan E. *Oh My Gods!, A Look-It-Up Guide to the Gods of Mythology (Mythlopedia)*, Scholastic Inc. 2009.

Campbell, Joseph. *THE HERO WITH A THOUSAND FACES,* Prince ton University Press, 2004.

Dorson, M. Richard. "Current Folklore Theories", Journal Of Current Anthropology,1963.

Finnegan, Ruth. *Oral literature in Africa*. London and New York: Routledge, 1970.

______ *Oral Tradition and Verbal Art, A Guide to Research Practices,* New York; Routledge Publishing Company, 1992.

Frye, Northrop. ''Myth as a Matrix of Literature.'', The Georgia Review Vol. 38, No,3, pp. 465- 476. 1984.

Goldstein, Kenneth S. A *Guide For Field Workers in Folklore*, Folklore Associates, INC. Hatboro, Pennsylvania, USA. 1964.

Hailu Megersa. "A History of Me'en People E,C.1898-1991", A Thesis Submitted to Graduate Programme of In Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Master of Arts in History, Bahir dar University, June, 2012.

http://anthropology.ua.edu/cultures/cultures.php?culture = Functionalism

Jones M, Jaja. *Myths in African concept of reality*, Institute of Foundation Studies, Rivers State University of Science and Technology, Nigeria, January, 2012.

Kit Kittelstad, *Types of Mythology*, M.A. Education, Your Dictionary, 2013,

Leeming, David A. *Mythology the Voiage of the Hero 3rd ed*, New York: Oxford University Press, 1998.

______ *Creation Myths of the World An Encyclopedia 2nd ed.* California: Greenwood Publication Group, 2010.

______ *Myth: a Biography of Belief,* New York: Oxford University Press, 2002.

Mac, Donald A. *Field work, Collecting Oral Literature*, In Richard Dorson (Ed.), The University of Chicago Press, London, 197.

Malinowski, Bronislaw, "Argonauts of the Western Pacific", In *Anthropological Theory: An Introductory History,* Jon R. McGee and Richard L. Warms, eds. Pp. 154-170. New York, 2012.

Muller, F. Max. *Natural Religion*, Longmans Green and Co. 1907.

Paul, Cobley. *Narratology*, The Johns Hopkins University Press, 2005.

Philip, Neil, *Myths and Legends Explained*, DK Publishing, New York, 2007.

Porth, Eric, Kimberley Neutzling, and Jessica Edwards. “Functionalism.” University of Alabama: Department of Anthropology. Last modified 2009. Web12,Feb. 2012.

Radcliffe, Brown, A.R, “On Joking Relationships”, In *Anthropological Theory:* An Introductory History, Jon R. McGee and Richard L. Warms, eds. pp. 170-181, New York, 2012.

Segal, Robert *(2004).* Myth in Religion, University of Aberdeen*.* Elsevier Ltd, UK. 2015.

Zerihun Doda, “The Ethino-history Me’enit Ethinic Group, South Nation’s Nationalities and Peoples, Regional Government”, Institute of Language, Culture and History Study, Department of History and Heritages, 2008.

# አባሪዎች

## 1. በመኤኒት ብሔረሰብ ለተመረጡ መረጃ ሰጪዎች፣ ስለ መኤኒት ብሔረሰብ የአፈጣጠር ሚት የቀረቡ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

### መግቢያ

ከሁሉ አስቀድሜ "የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ" በሚል ርዕስ ለምሠራው የዶክትሬት ዲግሪ ሚሚያ ጥናት፤ ቃለ መጠይቅ እንዳደርግልዎ ፈቅደው፣ ውድ ጊዜዎትም ስለሰጡኝ በእኔና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስም ከልብ አመሠግናለሁ፡፡

1. ስምን ማን ይባላል?
2. እድሜዎ ስንት ነው?
3. ሥራዎ ምንድነው? በምን ይተዳደራሉ?
4. የሚኖሩበት አካባቢ ማን ይባላል?
5. መኤኒቶችን ማን ነው የፈጠረው?
6. የመኤኒቶች አምላክ (ቱማ) መኤኒቶችን እንዴት ነው የፈጠረው?
7. ቱማ መኤኒቶችን ከምንድን ነው የፈጠረው?
8. ቱማ መኤኒቶችን መቼ ነው የፈጠረው?
9. ቱማ መኤኒቶችን ለምንድነው ነው የፈጠረው?
10. ቱማ መኤኒቶችን የት ነው የፈጠረው?
11. ቱማ መጀመሪያ የፈጠረው ማንን ነው?
12. መኤኒት ማለት ምን ማለት ነው?
13. ዓለምን የፈጠረው ማን ነው?
14. ሰማይን ምድርን የፈጠረው ማን ነው?

## 2. በመኤኒት ብሔረሰብ ለተመረጡ መረጃ ሰጪዎች፣ ስለ መኤኒት ብሔረሰብ የሃይማኖት ሚት የቀረቡ ጥያቄዎች

**መግቢያ**

ከሁሉ አስቀደሜ "የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ" በሚል ርዕስ ለምሠራው የዶክትሬት ዲግሪ ሟሟያ ጥናት፤ ቃለ መጠይቅ እንዳደርግልዎ ፈቅደው፣ ውድ ጊዜዎትም ስለሰጡኝ በእኔና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስም ከልብ አመሠግናለሁ፡፡

1. ስምዎ ማን ይባላል?
2. እድሜዎ ስንት ነው?
3. ሥራዎ ምንድነው? በምን ይተዳደራሉ?
4. የሚኖሩበት አካባቢ ማን ይባላል?
5. መኤኒቶችን ማን ነው የፈጠረው?
6. የመኤኒቶች አምላክ ማን ነው?
7. የመኤኒቶች አምላክ ከመኤኒቶች ጋር የሚገናኘው እንዴት ነው?
8. የመኤኒቶች አምላክ ከመኤኒቶች ጋር የሚገናኘው መቼ መቼ ነው?
9. መኤኒቶች አምላክ አምላክ መኖሩን የሚያውቁት እንዴት ነው?
10. በመኤኒቶች እና በአምላካችሁ መካከል ያሉ ቅዱሳኖች አሉ ወይ ነው?
11. መኤኒቶች እና በአምላክ መካከል ያለው ግንኙነት ዱሮና አሁን እንዴት ነው?
12. በመኤኒቶች እና በአምላክ መካከል ጥንት እና አሁን ግንኙነት ሲደረግ ልዩነት ካለው ልዩነቱ እንዴት መጣ?
13. በመኤኒቶች እና በአምላክ መካከል ጥንት እና አሁን ግንኙነት ሲደረግ ልዩነት ካለው ልዩነቱ በምን ምክንያት መጣ?
14. በመኤኒቶች እና በአምላክ መካከል ጥንት እና አሁን ግንኙነት ሲደረግ ልዩነት ካለው ልዩነቱ መቼ መጣ?
15. አምላክ ለመኤኒቶች የሰጣቸው የተለየ ሥልጣን ወይም ኃይል አለ ወይ?
16. የመኤኒቶች አምላክ ለመኤኒቶች የሰጣቸው የተለየ ሥልጣን ወይም ኃይል ካለ ያ ኃይል ወይም ጥበብ ምንድ ነው?

## 3. በመኤኒት ብሔረሰብ ለተመረጡ መረጃ ሰጪዎች፣ ስለ መኤኒት ብሔረሰብ የመስተጋድላውያን ሚት የቀረቡ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

**መግቢያ**

ከሁሉ አማስቀድሜ "የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ" በሚል ርዕስ ለምሠራው የዶክትሬት ዲግሪ ሚሚያ ጥናት፤ ቃለ መጠይቅ እንዳደርግልዎ ፈቅደው፣ ውድ ጊዜዎትን ስለሰጡኝ በእኔና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስም ከልብ አመሠግናለሁ፡፡

1. ስምዎ ማን ይባላል?
2. እድሜዎ ስንት ነው?
3. ሥራዎ ምንድነው? በምን ይተዳደራሉ?
4. የሚኖሩበት አካባቢ ማን ይባላል?
5. መኤኒቶችን ማን ነው የፈጠረው?
6. በመኤኒቶች ብሔረሰብ ውስጥ የተለየ ጥበብና ኃይል ከአምላክ የተሰጣቸው ሰዎች አሉ ወይ?
7. ኮሞሩት ማለት ምን ማለት ነው?
8. ኮሞሩትነት የሚገኘው እንዴት ነው?
9. ኮሞሩት የተለየ አኗኗር አለው?
10. ኮሞሩትነት የተለየ ሥልጣን አለው?
11. የተለየ ሥልጣን ካለው ምንድነው?
12. ኮሞሮቶች ሥራቸውን የሚያከናውኑት ብቻቸውን ነው ወይስ ረዳቶች አሏቸው? ካሏቸው ምን በመሥራት ያግዟቸዋል?
13. እርስዎ ከኮሞሮት በጋር ተገናኝተው ያውቃሉ? ካወቁ በምን አጋጣሚ
14. ኮሞሮቶች ተአምር ሲሠሩ ወይ የሆነ ለሕዝቡ ጠቃሚ ነገር ሲያከናውኑ አይተዋል?
15. ኮሞሮቶች ተአምር ሲሠሩ ወይ የሆነ ለሕዝቡ ጠቃሚ ነገር ሲያከናውኑ ሰምተዋል?

16.ከሰሙ ምንድነው የሰሙት?

17.አንድ ሰው ለኮሞሮቶች አልገዛም ቢል ምን ያጋጥመዋል?

18.ዝናብ የማውረድ ሥልጣን የመጣው ከየት ነው?

19.ዝናብ አውራጆች ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው?

20.ዝናብ አውራጆች ሥልጣኑን እንዴት ያገኙታል?

21.ስለዝናብ አውራጆች የሰሙት ወይም ያዩት አለ? ካለ ምን ታሪክ ሰሙ?

22.ኘራይ ማለት ምን ማለት ነው?

23.ኘራይነት የሚገኘው እንዴት ነው?

24.ኘራይ የተለየ አኗኗር አለው?

25.ኘራይ የተለየ ሥልጣን አለው?

26. የተለየ ሥልጣን ካለው ምንድነው?

27.ኘራይዮች ሥራቸውን የሚያከናውኑት ብቻቸውን ነው ወይስ ረዳቶች አሏቸው? ካሏቸው ምን በመሥራት ያግዟቸዋል?

28.እርስዎ ከኘራይ ቢጋር ተገናኝተው ያውቃሉ? ካወቁ በምን አጋጣሚ

29.ኘራዮች ተአምር ሲሠሩ ወይ የሆነ ለሕዝቡ ጠቃሚ ነገር ሲያከናውኑ አይተዋል?

30.ኘራዮች ተአምር ሲሠሩ ወይ የሆነ ለሕዝቡ ጠቃሚ ነገር ሲያከናውኑ ሰምተዋል?

31.ከሰሙ ምንድነው የሰሙት?

32.አንድ ሰው ለኘራዮች አልገዛም ቢል ምን ያጋጥመዋል

33.የኘራነት ሥልጣን የመጣው ከየት ነው?

34.ኘራዮች ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው?

35.ኘራዮችሥልጣኑን እንዴት ያገኙታል?

36.ኘራዮች የሰሙት ወይም ያዩት አለ? ካለ ምን ታሪክ ሰሙ?

## 4. በመኤኒት ብሔረሰብ ለተመረጡ መረጃ ሰጪዎች፣ ስለ መኤኒት ብሔረሰብ የዳግም ውልደት ሚት የቀረቡ ጥያቄዎች

*መግቢያ*

ከሁሉ በማስቀደሜ "የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ" በሚል ርዕስ ለምሠራው የዶክትሬት ዲግሪ ሟሟያ ጥናት፤ ቃለ መጠይቅ እንዳደርግልዎ ፈቅደው፣ ውድ ጊዜዎትን ስለሰጡኝ በእኔና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስም ከልብ አመሠግናለሁ፡፡

1. ስምዎ ማን ይባላል?
2. እድሜዎ ስንት ነው?
3. ሥራዎ ምንድነው? በምን ይተዳደራሉ?
4. የሚኖሩበት አካባቢ ማን ይባላል?
5. መኤኒቶች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ወዴት ይሄዳሉ?
6. በመኤኒት ነባር እምነት ከሞት በኋላ ሕይወት አለ?
7. ሕይወት ካለ እንዴት ያለ ነው?
8. መኤኒቶች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ወደ ሞኡ ይሄዳሉ ይባላል ሞኡ የት ነው?
9. መኤኒቶች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ የሚቀበሩት ፊታቸው ወደ ምሥራቅ ተደርጎ ነው ለምንድነው?
10. መኤኒቶች ከዚህ ዓለም በሞት ሊለዩ አስከሬናቸው ከቤት ሲወጣ አዲስ በር የሚቀደደው/ የሚዘጋጀው ለምንድነው?
11. መኤኒቶች ከዚህ ዓለም በሞት እንደሚለዩ ሲገመት ታማሚውን ወደ አዲስ ጎጆ የሚወስዱት እና ከሌሎቹ የሚለዩት ለምንድነው?
12. በመኤኒቶች አንድ ሰው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ወተት በጉሮሮው የሚጨምሩት ለምንድነው?
13. ሞኡ የተባለው ሥፍራ የት ይገኛል?
14. ሞኡ አካባቢ ሄደው፣ ሥፍራውን ኅብንተው ያውቃሉ?
15. ስለ ሞኡ የሚያውቁትን እና የሰሙትን ታሪክ ይንገሩኝ?
16. አቶ ማዮኒ ስለሚባሉት ሰው ያውቃሉ?
17. ስለ አቶ ማዮኒ የሰሙትን ወይም የሚያውቁትን ይንገሩኝ?
18. አቶ ማዮኒ በአካባቢው ሰው እንዴት ይታያሉ? ሰው ምን ይላቸዋል?

19. ሞኡ ሂዶ የመጣ ሰው ገጥሞዎት ያውቃል?
20. ከዚህ በፊት ስለ ሞኡ የተነገሩ ወይም ወደዚያ አካባቢ ሂዶ ስለመጣ ሰው የሰሙት ታሪክ አለ?
21. ሌሎች ሰዎች /ከመኤኒቶች ውጪ ያሉ/ ስለ ሞኡ ምን ይላሉ?
22. በሞኡ ያለው ሕይወት ምን ይመስላል?
23. ሰዎች ምን በሞኡ ምን ይሠራሉ? እዚያ ያለው ኑሮ እንዴት ያለነው?
24. ሞኡ ደርሶ የመጣ ሰው ያውቃሉ?
25. ካወቁ መቼና ማንን?

## 5. ለወ/ሮ ሌማው ጃና የቀረበ ቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

**መግቢያ፤**

ከሁሉ አማስቀድሜ "የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ" በሚል ርዕስ ለምሠራው የዶክትሬት ዲግሪ ሟሟያ ጥናት፤ የቃለ መጠይቅ እንዳደርግልዎ ፈቅደው፣ ውድ ጊዜዎትን ስለሰጡኝ በእኔና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስም ከልብ አመሠግናለሁ፡፡

1. ስምዎን ማን ይባላል?
2. እድሜዎ ስንት ነው?
3. ሥራዎ ምንድነው? በምን ይተዳደራሉ?
4. የሚኖሩበት አካባቢ ማን ይባላል?
5. የቤተሰብ ሁኔታዎ እንዴት ነው? ልጆች አሉዎት?
6. ለቤተሰብዎ ስንተኛ ልጅ ነዎት?
7. ዝናብ የማዝነብን ኃይል እንዴት አገኙት?
8. ዝናብ የማዝነብን ኃይል ከማን አገኙት?
9. ዝናብ የማዝነብን ኃይል መቼ አገኙት?
10. እርስዎ ዝናብ ማዝነብን መች ጀመሩ?
11. ከዚህ በፊት አዝንበው ያውቃሉ?
12. ዝናብ በምን ምክንያት ይጠፋል?
13. ዝናብ እንዳይዘንብ ማድረግ ይችላሉ?
14. ከቻሉ እንዳይዘንብ ለማድረግ ምን ያደርጋሉ?
15. ዝናብ እንዲዘንብላቸው ሰዎች ወደርስዎ ዘንድ የሚመጡት ምን ይዘውና በምን አኳኋን ነው?
16. ዝናብ ለማዝነብ የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች አሉ?
17. ካሉ ምን ምን ዓይነት ናቸው?
18. ግብአቶችን የሚጠቀሙባቸው እንዴት ነው?
19. እርስዎ ዝናብ እንዲወርድ በሚያደርጉበት ሰዓት የሚያግዙዎት ሰዎች/ረዳቶች አሉዎት?
20. ካሉ ረዳትዎ ምን በመሥራት ነው የሚያግዙዎ?

21. ከሦስት ዓመት በፊት አካባቢ እርስዎ ዝናብ አዝንበዋል ተብሏል እውነት ነው?
22. እውነት ከሆነ ዝናብ በምን ምክንያት ጠፋ?
23. ዝንብ ሲጠፋ ወደ እርስዎ ማን መጣና እንዲያዘንቡ ጠየቀዎ?
24. ከተጠየቁ በኋላሰ ምን አደረጉ?
25. የአዝናቢዎች የተለየ አኗኗር ምንድ ነው? ከማኅበረሰቡ ጋር ያለዎት ግንኙነት እንዴት ነው?
26. እርስዎ በኮላይ ቀበሌ ዝናብ ካዘነቡ በኋላ ማኅበረሰቡ ምን አደረገልዎ?
27. ዝናብ ለሕዝቡ ካዘነቡ በኋላ ከመንግሥት የተለየ ነገር ተደርጎሎታል?
28. ማኅበረሰቡ እርስዎን እንዴት ነው የሚይዎ? ይከበራሉ?
29. ማኅበረሰቡ የሚያከብርዎ ከሆነ ምን ምን በማድረግ ያከብረዎታል?
30. የማያከብርዎ ከሆነ ለምን አያከብርዎትም?

## 6. ለ"ዝንጀሮ ንጉሥ" የቀረቡ ጥያቄዎች

### መግቢያ

ከሁሉ አስቀድሜ "የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ" በሚል ርዕስ ለምሠራው የዶክትሬት ዲግሪ ሟሟያ ጥናት፤ ቃለ መጠይቅ እንዳደርግልዎ ፈቅደው፣ ውድ ጊዜዎን ስለሰጡኝ በእኔና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስም ከልብ አመሠግናለሁ፡፡

1. ስምዎ ማን ይባላል?
2. እድሜዎ ስንት ነው?
3. ሥራዎ ምንድነው? በምን ይተዳደራሉ?
4. የሚኖሩበት አካባቢ ማን ይባላል?
5. የቤተሰብ ሁኔታዎ እንዴት ነው? ልጆች አሉዎት?
6. ለቤተሰብዎ ስንተኛ ልጅ ነዎት?
7. የዝንጀሮ ንጉሥነትን የማዝነብን ኃይል እንዴት አገኙት?
8. የዝንጀሮ ንጉሥነትን ኃይል ከማን አገኙት?
9. የዝንጀሮ ንጉሥነትን ኃይል መቼ አገኙት?
10. እርስዎ የዝንጀሮ ንጉሥነትን መች ጀመሩ?
11. ከዚህ በፊት ዝንጀሮችን አዝዘው ያውቃሉ?
12. ዝንጀሮዎች በምን ምክንያት ለጥፋት ይመጣሉ?
13. ዝንጀሮን በፈለጉ ጊዜ ሰዓት ለማዘዝ ይችላሉ?
14. ከቻሉ ለማዘዝ ምን ያደርጋሉ?
15. ከዝንጀሮ ጥፋት እንዲታደጓቸው ሰዎች ወደርስዎ ዘንድ የሚመጡት ምን ይዘውና በምን አኳኋን ነው?
16. ዝንጀሮን ለማዘዝ የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች አሉ?
17. ካሉ ምን ምን ዓይነት ናቸው?
18. ግብአቶችን የሚጠቀሙባቸው እንዴት ነው?
19. እርስዎ ዝንጀሮዎችን በሚያዝዙበት ሰዓት የሚያግዙዎት ሰዎች/ረዳቶች አሉዎት?

20. ካሉ ረዳትዎ ምን በመሥራት ነው የሚያግዙዎ?
21. ከጥቂት ዓመታት በፊት አካባቢ እርስዎ ዝናብ አዝንበዋል ተብሏል አውነት ነው?
22. እውነት ከሆነ የዝንጀሮ መንጋ በምን ምክንያት መጣ?
23. የዝንጀሮ መንጋ ሲመጣ ወደ እርስዎ ማን መጣና እንዲያግዷቸው ጠየቀዎ?
24. ከተጠየቁ በኋላሰ ምን አደረጉ?
25. የዝንጀሮ ንጉሦች የተለየ አኗኗር ምንድ ነው? ከማኅበረሰቡ ጋር ያለዎት ግንኙነት እንዴት ነው?
26. እርስዎ በጨበራና አካባቢው ባሉ ቀበሌዎች የዝንጀሮን መንጋ ከመለሱ በኋላ ማኅበረሰቡ ምን አደረገለዎት?
27. የዝንጀሮን መንጋ ከመለሱ በኋላ ከመንግሥት ወይም ከአካባቢው ኃላፊዎች የተለየ ነገር ተደርጎለዎታል?
28. ማኅበረሰቡ እርስዎን እንዴት ነው የሚቀበልዎ? ይከበራሉ?
29. ማኅበረሰቡ የሚያከብርዎ ከሆነ ምን ምን በማድረግ ያከብረዎታል?
30. የማያከብርዎ ከሆነ ለምን አያከብርዎትም?

## 7. ስለ የ"ወባ ንጉሥ" ለማኅበረሰቡ አባላት የቀረቡ ጥያቄዎች

***መግቢያ***

*ከሁሉ አስቀድሜ "የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ" በሚል ርዕስ ለምሠራው የዶክትሬት ዲግሪ ሚሚያ ጥናት፤ ቃለ መጠይቅ እንዳደርግልዎ ፈቅደው፣ ውድ ጊዜዎንም ስለሰጡኝ በእኔና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስም ከልብ አመሠግናለሁ፡፡*

1. *ስምዎ ማን ይባላል?*
2. *እድሜዎ ስንት ነው?*
3. *ሥራዎ ምንድነው? በምን ይተዳደራሉ?*
4. *የሚኖሩበት አካባቢ ማን ይባላል?*
5. *የቤተሰብ ሁኔታዎ እንዴት ነው? ልጆች አሉዎት?*
6. *የወባ ንጉሥነት የሚገኘው እንዴት ነው?*
7. *የወባ ንጉሥነት ከማን  ይገኛል?*
8. *የወባ ንጉሥነት መቼ  ይገኛል?*
9. *ከዚህ በፊት ወባ ይዞዎት ያውቃል?*
10. *ካወቀ በምን ወይም በማን ዳኑ?*
11. *ያዳነዎት የወባ ንጉሡ ከሆነ ማን ይባላሉ፣ የት ነው የሚገኙት?*
12. *በአካባቢው ያሉት የወባ ንጉሥ ምን በማድረግ አዳኑዎት?*
13. *የወባው ንጉሡ ካዳኑዎት በኋላ ወባ ይዞዎት ያውቃል?*
14. *የወባ ወረርሽኝ ወይም በሽታው በዚህ አካባቢ የሚመጣው በምንድነው?*
15. *የወባ ወረርሽኝ ወይም በሽታው በዚህ አካባቢ ሲከሰት የሚደረገው ምንድነው?*
16. *ማኅበረሰቡ ለወባ ንጉሥ ያለው እምነት ምን ያህል ነው?*
17. *የወባ ንጉሥ ሕዝቡን ሲያድን ምን ምን ይጠቀማል ?*
18. *ግብአቶችን የሚጠቀሙባቸው እንዴት ነው?*
19. *የወባ ንጉሥ የሚያግዙት ሰዎች/ረዳቶች አሉት?*
20. *ካሉ ረዳቶቹ  ምን በመሥራት ነው የሚያግዙት?*

21. የወባ በሽታ በምን ምክንያት ይመጣል?
22. የወባ ንጉሦች የተለየ አኗኗር ምንድ ነው? ከማኅበረሰቡ ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዴት ነው?
23. ማኅበረሰቡ የወባ ንጉሡን እንዴት ነው የሚያየው?
24. ማኅበረሰቡ የሚያከብራቸው ከሆነ ምን ምን በማድረግ ያከብራቸዋል?
25. የማያከብር ከሆነ ለምን አያከብርም?

## 8. "ሞቼ ተነስቻለሁ" ለሚሉት ለአቶ ማዮኒ የቀረቡ ጥያቄዎች

**መግቢያ**

ከሁሉ አስቀደሜ "የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ" በሚል ርዕስ ለምሠራው የዶክትሬት ዲግሪ ሚሚያ ጥናት፤ ቃለ መጠይቅ እንዳደርግልዎ ፈቅደው፣ ውድ ጊዜዎንም ስለሰጡኝ በእኔና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስም ከልብ አመሠግናለሁ፡፡

1. ስምዎ ማን ይባላል?
2. እድሜዎ ስንት ነው?
3. ሥራዎ ምንድነው? በምን ይተዳደራሉ?
4. የሚኖሩበት አካባቢ ማን ይባላል?
5. የቤተሰብ ሁኔታዎ እንዴት ነው?
6. እርስዎ ሞተው እንደተነሱ ይነገራል እውነት ነው?
7. በምን ምክንያት ነበር "የሞቱት"?
8. ከሞቱ በኋላ ወዴት ሄዱ?
9. የሄዱበት ቦታ ምን ያህል ጊዜ ቆዩ?
10. ከሞት በኋላ የሄዱት የት ነው?
11. እዚያ የሄዱበት ቦታ የሚኖሩት ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው?
12. ከሞት በኋላ ባለው ሕይወት ውስጥ የሚኖሩት ሰዎች የሠሩት ሥራ አለ?
13. ከሞት በኋላ የሚኖሩት ሰዎች በሚኖሩበት ሥፍራ ሥራ የሚሠሩ ከሆነ ምን ምን ሥራ ሲሠሩ አዩ?
14. በዚያ ከሞት በኋላ የሚኖሩ ሰዎች ባሉበት ሥፍራ መኖሪያ ቤቶች አሉ ወይ? ካሉ ምን ዓይነት ናቸው?
15. በዚያ ከሞት በኋላ መኤኒቶች በሚኖሩበት ስፍራ ምን ዓይነት ምግብ ይበላል፣ የሚጠጣውስ ምን ዓይነት ነው?
16. ከሞት በኋላ የሚኖሩ መኤኒቶች ያሉበት ስፍራ በዚህ ዓለም ካለው በምን

    ይለያል?
17. እርስዎ በዚያ ሥፍራ በምን አኳኋን ነበሩ? ልብስ ለብሰው ነበር?
18. ወደዚህ ገሀዳዊ ዓለም በምን ምክንያ ተመለሱ?

## 9. ለኘራይ አወቀ ፎሮሾዋ የቀረቡ ጥያቄዎች

**መግቢያ**

ከሁሉ አስቀደሜ "የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ" በሚል ርዕስ ለምሠራው የዶክትሬት ዲግሪ ሚሚያ ጥናት፣ ቃለ መጠይቅ እንዳደርግልዎ ፈቅደው፣ ውድ ጊዜዎንም ስለሰጡኝ በእኔና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስም ከልብ አመሠግናለሁ፡፡

1. ስምዎ ማን ይባላል?
2. እድሜዎ ስንት ነው?
3. ሥራዎ ምንድነው? በምን ይተዳደራሉ?
4. በምን ይተዳደራሉ?
5. የሚኖሩበት አካባቢ ማን ይባላል?
6. የቤተሰብ ሁኔታዎ እንዴት ነው?
7. ኘራይነት ምንድነው?
8. ኘራይነት እንዴት ይገኛል?
9. ኘራይነትን ሲቀበሉ እንዴት ነበር?
10. በኘራይነት ምን ምን ሠርተዋል?
11. ሕዝቡ ለኘራዮች ያለው እምነት እንዴት ነው?
12. ምን ምን ዓይነት ሰዎች እርስዎ ጋ ይመጣሉ?
13. ምን ምን ጉዳዮች ይቀርባሉ?
14. ከየት አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው የሚመጡት?
15. በእርስዎ ጥሪ እንዲመጡ የተላከባቸው ሰዎች አሉ?
16. ካሉ ጥሪው እንዴት ነው የሚተላለፈው?
17. በእርስዎ ፊት ቀርቦ የተከሰሰበትን ድርጊት ቢክድ ምን ይደረጋል
18. የካዱ ሰዎችስ አሉ?
19. በእርስዎ ፊት ቀርቦ የካደ እና በኋላ የተረገመ ሰው አለ?
20. በፊት ድርጊቱን እንዳልፈጸመ ክዶ በኋላ የመጣ እና ያመነ ሰው አለ?
21. ኘራይነት ከአምላክ ቱማ የመጣ አይደለም የሚሉ ሰዎች አሉ፣ እርስዎ ለዚህ ምን ምላሽ ይሠጡኛል?

22. የመንግሥት አካላት ለእናንተ ምን ዓይነት አመለካከት አላቸው?

23. ከመንግሥት አካላትስ ጋር በትብብር ትሠራላችሁ?

24. ከሠራችሁ ምን ምን ላይ ትተባበራላችሁ?

25. እርስዎ ኅብረተሰቡን በምን መልኩ እየጠቀሙት ነው?

26. እርስዎስ ከኅብረተሰቡ ምን ይጠብቃሉ?

# 10. ለቡድን ውይይት የቀረቡ ጥቅል ጥያቄዎች

***መግቢያ***

ከሁሉ አስቀደሜ "የመኤኒት ብሔረሰብ ሚት ማኅበረሰባዊ ፋይዳ" በሚል ርዕስ ለምሠራው የዶክትሬት ዲግሪ ሚሚያ ጥናት፤ የቡድን ውይይት እንድናደርግ ፈቅዳችሁ፣ ውድ ጊዜያችሁን ለሰጣችሁኝ ተወያዮች፣ በእኔና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስም ከልብ አመሠግናለሁ፡፡

1. የዝናብ ንግሥት፣ የወባ እና የዝንጀሮ ንጉሥ የሚባሉ አሉ?
2. ካሉ ምን ምን ሠርተዋል?
3. ኀራይነት ከጥንት የመጣ ነው ወይስ በቅርብ የመጣ ነው?
4. ኮሞሮቶችና ኀራዮች ለእናንተ ምን ጥቅም ይሰጧችኋል?
5. ከሞት በኋላ ቀጣይ ሕይወት አለ? ካለ የት?
6. በእናንተ አካባቢ ለረጅም ጊዜ ዝናብ ጠፍቶ ነበር ወይ?
7. ከጠፋ በምን ምክንያት ጠፋ ብላችሁ ታምናላችሁ?
8. ዝናቡን ማን አዘነበው?
9. ዝናቡን ያዘነቡት ሴት በምን ኃይል አዘነቡት ብላችሁ ታምናላችሁ?
10. ዝናቡ ሲዘንብ እርስዎ የት ነበሩ?
11. አዝናቢዋ ለአካባቢው እና ለሕዝቡ/ ለእናንተ ምን ጥቅም ሰጧችሁ?
12. የዝናብ መጥፋት፣ የወባ በሽታ መከሰት ወይም ሌላ ጥፋት በማኅበረሰቡ/ በእናንተ ላይ የሚመጣው በምን ምክንያት ነው?
13. ጥፋቱ፣ ችግሩ እንዲወገድ ምን ይደረጋል?
14. የወባ ንጉሥ ለአካባቢው ሰው ምን አድርጓል?

## 11. ቁልፍ የመረጃ ሰጪዎች መግለጫ

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ዕድሜ | የመኖሪያ አካባቢ | የሥራ ድርሻ | ሃይማኖት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ዋየች ጃቫ | 60 | ዱማ | የሀገር ሽማግሌ (ኮሞሩት አሻ) | ኀራይ |
| 2 | አቶ ብርሃኑ ወርቁ | 53 | ዱማ | የመኤኒት ጎልድያ ወረዳ ጤና ጽ/ቤት በኋላም የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሐላፊ | ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ |
| 3 | አቶ አወቀ ፎሮሹዋ | 58 | ዱማ | ኀራይ | ኀራይ |
| 4 | ኬኒ ቀኛዝማች ጋሊ | 60 | ካንቲ | ኮሞሮት | ኀራይ |
| 5 | አቶ በድሉ ካሳ | 38 | ባቹማ | የመኤኒት ጎልድያ ወረዳ በባሕልና ቱሪዝም፣ በሴቶችና ሕጻናት፣ በመንገድ ት/ት ጽ/ቤቶች በሐላፊነት የሠሩ | ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ |
| 6 | አቶ ጥጋቡ መንገሻ | 47 | ዱማ | ገበሬ | ኀራይ |
| 7 | አቶ ቻካም ሚሮ | 68 | ኩዱም | ገበሬ | ኀራይ |
| 8 | ወ/ሮ ሌማው ጃና | 64 | ኮላይ | አዝናቢ | ኀራይ |
| 9 | አስር አለቃ ግርማ | 30 | ኮላይ | ፖሊስ | ፕሮቴስታንት |
| 10 | አቶ ገብሬ | 45 | ኮላይ | የኮላይ ቀበሌ ሊቀመንበር | ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ |
| 11 | አቶ ሻልታ ታዬ | 46 | | | ፕሮቴስታንት |
| 12 | አቶ ኮሬ … | 38 | ኮላይ | ነጋዴ | ኀራይ |
| 13 | አቶ ማዮኒ | 72 | ጉራፈርዳ | ገበሬ | ኀራይ |
| 14 | አቶ ቦኒ ሀየች | 44 | ጉራፈርዳ | የጉራ ፈርዳ ወረዳ የፀጥታ ዘርፍ ሐላፊ | ፕሮቴስታንት |
| 15 | ወ/ሮ ጊብዝኒ ሞሮች | 56 | ጉራፈርዳ | ገበሬ | ኀራይ |
| 16 | አቶ ሾልዋ… | 64 | ጉራፈርዳ | ገበሬ | ኀራይ |

## 12.አጋዥ የመረጃ ሰጪዎች መግለጫ

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ዕድሜ | የመኖሪያ አካባቢ | የሥራ ድርሻ | ሃይማኖት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ አልጋነሽ ኩትያ | 36 | ኤራ | ገበሬ | ኘራይ |
| 2 | አቶ ታዬ መስፍን | 30 | ጨበራ | ነጋዴ | ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ |
| 3 | አቶ መልኬ ኬላገ | 36 | ጉማ | የመኤኒት ጎልድያ ወረዳ አስተዳዳሪ | ፕሮቴስታንት |
| 4 | አቶ ቻካም ሚሮ | 68 | ኩዱም | ገበሬ | ኘራይ |
| 5 | አቶ ኦይቱሉዋ ፋጂዎ | 70 | ባሮ | ገበሬ | ኘራይ |
| 6 | ወ/ሮ ቦልጃ ገሲዮ | 48 | ኤራ | ገበሬ | ኘራይ |
| 7 | ወ/ሮ ኮያ ታይሲ | 50 | ወጅናሌሙ | ገበሬ | ኘራይ |
| 8 | አቶ ጳሎጋ ጎርጌ | 60 | ሀዱባ | ገበሬ | ኘራይ |
| 9 | አቶ ካንጋ ባሩኚ | 65 | ዳርጃ | ገበሬ | ኘራይ |
| 10 | አቶ ጳስጋላ ቢጎሎኚ | 72 | ቂራ | ገበሬ | ኘራይ |
| 11 | ወ/ሮ ሞናይ ጋሹ | 40 | ጀሙ | ገበሬ | ኘራይ |
| 12 | አቶ ኮርዲ ሆይሺጊን | 65 | ቡክቱ | ገበሬ | ኘራይ |
| 13 | አቶ ሹማቻኤዳ በርግዋ | 60 | ጢይጉይ | ገበሬ | ኘራይ |
| 14 | ሹማቻኤዳ ውለጌ | 72 | ጥቅምትሸት | ገበሬ | ኘራይ |
| 15 | አቶ ቢጎሎኝ በርጉዋ | 60 | ያርጣ | ገበሬ | ኘራይ |
| 16 | አቶ ቡሻይ ባሩኝ | 74 | ጉራፈርዳ | ገበሬ | ኘራይ |
| 17 | አቶ ጌልቶ ካማና | 56 | ጉራፈርዳ | ገበሬ | ኘራይ |
| 18 | አቶ ኬላጊ ቃጅዎ | 60 | ኮላይ | ገበሬ | ኘራይ |
| 19 | ወ/ሮ ትዕግሥት | 26 | ኮላይ | ነጋዴ | ፕሮቴስታንት |
| 20 | ወ/ሮ ጊብዚኒ | 42 | ኮላይ | ነጋዴ | ኘራይ |
| 21 | አቶ ቢኒያም | 34 | ሼቤንች | ነጋዴ | ኦርቶዶክስ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 22 | አቶ ጉነማሬጮ በናሻ | 60 | ያርጣ | ገበሬ | ኘራይ |
| 23 | ወ/ሮ ኦድሉ አርካሻ | 58 | ያርጣ | ገበሬ | ኘራይ |
| 24 | አቶ ማናቻ | 44 | ያርጣ | የያርጣ ቀበሌ ፖሊስ | ፕሮቴስታንት |
| 25 | ሽማው ጆኒዮ | 60 | ያርጣ | ገበሬ | ኘራይ |
| 26 | አቶ ዱጋች | 76 | ጨበራ | ገበሬ | ኘራይ |
| 27 | አቶ ወቲመጉት | 70 | ጨበራ | ገበሬ | ኘራይ |
| 28 | ወ/ሮ ኮያ | 60 | ጨበራ | ገበሬ | ኘራይ |
| 29 | ወ/ሮ ሲቡይ | 62 | ጎማ | ገበሬ | ኘራይ |
| 30 | አቶ ቡሻይ | 60 | ጉራፈርዳ | ገበሬ | ኘራይ |
| 31 | አቶ ጌልቶ ካማና | 62 | ጉራፈርዳ | ገበሬ | ኘራይ |
| 32 | አቶ ዳንኬር | 72 | ያርጣ | ገበሬ | ኘራይ |